# መጽሐፈ መዝሙር

## አንደኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 1-41

### መዝሙር 1
**ሁለቱ መንገዶች**

1 በክፉዎች ምክር የማይሄድ፣
በኀጢአተኞች መንገድ የማይቆም፣
በፌዘኞችም ወንበር የማይቀመጥ፣
ሰው ብፁዕ ነው፡፡
2 ነገር ግን ደስ የሚሰኘው *በእግዚአ
ብሔር ሕግ ነው*፤
ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያሰላስለዋል፡፡
3 እርሱም በወራጅ ውሃ ዳር እንደ
ተተከለች፣
ፍሬዋን በየወቅቱ እንደምትሰጥ፣
ቅጠሏም እንደማይጠወልግ ዛፍ ነው፤
የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል፡፡
4 ክፉዎች ግን እንዲህ አይደሉም፤
ነገር ግን ነፋስ ጠራርጎ
እንደሚወስደው፣
ገለባ ናቸው፡፡
5 ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ ፊት፣
ኀጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር
መቆም አይችሉም፤
6 *እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ
ይጠብቃልና*፤
የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች፡፡

### መዝሙር 2
**መሢሓዊ ትዕይንት**

1 ሕዝቦች ለምን ያሤራሉ?[ሀ]
ሰዎችስ ለምን ከንቱ ነገር ያውጠነጥናሉ?
2 የምድር ነገሥታት ተነሡ፤
ገዦችም *በእግዚአብሔርና* በመሢሑ[ለ]
ላይ፣
ሊመክሩ ተሰበሰቡ፤
3 "ሰንሰለታቸውን እንበጥስ፣
የእግር ብረታቸውንም አውልቀን
እንጣል" አሉ፡፡
4 በሰማይ ዙፋን ላይ የተቀመጠው
ይሥቃል፤
ጌታም ይሣለቅባቸዋል፡፡
5 ከዚያም በቍጣው ይናገራቸዋል፤
በመዓቱም ያስደነግጣቸዋል፤
6 ደግሞም፣ "እኔ ግን በተቀደሰው
ተራራዬ፣
በጽዮን ላይ የራሴን ንጉሥ ሾምሁ"
ይላል፡፡
7 *የእግዚአብሔርን ሕግ ዐውጃለሁ*፤
እርሱም እንዲህ አለኝ፤ "አንተ ልጄ ነህ፤
እኔ ዛሬ ወለድሁህ፤[ሐ]
8 ለምነኝ፤
መንግሥታትን ርስት አድርጌ፣
የምድርንም ዳርቻ ግዛት እንዲሆንህ
እሰጥሃለሁ፡፡
9 አንተም በብረት በትር ትቀጠቅጣቸዋለህ፤[መ]
እንደ ሸክላ ዕቃ ታደቃቸዋለህ፡፡"
10 ስለዚህ እናንት ነገሥታት ልብ በሉ፤
እናንት የምድር ገዦችም፣
ተጠንቀቁ፡፡
11 *እግዚአብሔርን* በፍርሀት አገልግሉት፤
ለእርሱ መራድም ደስ ያሰኛችሁ፡፡
12 እንዳይቈጣና በመንገድ እንዳትጠፉ፣
ዝቅ ብላችሁ ልጁን ሳሙት፤
ቍጣው ፈጥኖ ይነዳልና፡፡
እርሱን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ
የተባረኩ ናቸው፡፡

### መዝሙር 3
**የመከራ ተቀባዩ የጧት ጸሎት**

ዳዊት ከልጁ ከአቤሰሎም በሸሸ ጊዜ የዘመረው
መዝሙር

1 *እግዚአብሔር ሆይ*፤ ጠላቶቼ ምንኛ በዙ!
ስንቱስ በእኔ ላይ ተነሣ!
2 ብዙዎች ነፍሴን፣ "እግዚአብሔር
አይታደግሽም" አሏት፡፡ ሴላ[ሠ]
3 *እግዚአብሔር ሆይ*፤ አንተ ግን ዙሪያዬን
የምትከልል ጋሻ ነህ፤
ክብሬና፣ ራሴንም ቀና ቀና
የምታደርግ አንተ ነህ፡፡[ረ]
4 ወደ *እግዚአብሔር* ድምፄን ከፍ
አድርጌ እጮሃለሁ፤
እርሱም ከተቀደሰ ተራራው
ይመልስልኛል፡፡ ሴላ
5 እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁ፤
*እግዚአብሔር* ደግፎ ይዞኛልና
እነቃለሁ፡፡

1፥1 ዘፍ49፥6፤ ዘዳ33፥29፤ኢዮ11፥3፤ 21፥16፤ መዝ10፥2-11፤26፥4:9፤37፥38፤ 40፥4፤51፥13፤89፥15 ፤104፥35፤128፥4፤ ምሳ 1፥22፤ ኢሳ28፥14፤ሆሴ7፥5
1፥2 ዘፍ24፥63፤ መዝ 19፥7፤112፥1፤ 119፥1:16:35፤ ሕዝ 11፥20፤18፥17፤ ሮሜ7፥22
1፥3 ዘፍ39፥3፤ ዘኍ24፥6፤ኢዮ14፥9፤ መዝ46፥4፤52፥8፤65፥9፤ 92፥12:14፤128፥3፤ ኢሳ1፥30፤33፥21፤ 64፥6፤ኤር11፥16፤ 31፥9፤ሕዝ17፥5፤ 47፥12፤ዘካ4፥3
1፥4 ኢዮ13፥25፤ ኢሳ40፥24፤ኤር13፥24
1፥5 ኢዮ19፥29፤መዝ 5፥5፤26፥12፤35፥18፤ 82፥1፤89፥5፤107፥32 ፤111፥1፤149፥1
1፥6 ዘሌ26፥38፤መዝ 9፥6፤37፥18፤121፥5፤ 145፥20፤ናሆ1፥7
2፥1 መዝ21፥11፤ 83፥5፤ምሳ24፥2
2፥2 1ሳሙ9፥16፤ መዝ48፥4፤ዮሐ1፥41፤ ሐሥ4፥25-26
2፥3 2ሳሙ3፥34፤ ኢዮ36፥8
2፥4 መዝ37፥13፤ ምሳ1፥26፤ኢሳ37፥16፤ 40፥22፤66፥1
2፥5 መዝ6፥1፤21፥9 ፤27፥9፤38፥1፤79፥6፤ 90፥7፤110፥5
2፥6 ዘፀ15፥17፤ 2ነገ19፥31፤መዝ9፥11፤ 10፥16፤24፥10፤ 48፥2:11፤78፥68፤ 110፥2፤133፥3
2፥7 2ሳሙ7፥14፤ ማቴ3፥17፤4፥3፤ ሐሥ13፥33፤ዕብ1፥5፤5፥5
2፥8 ኢዮ22፥26፤ መዝ22፥27፤67፥7፤ ማቴ21፥38፤ራእ2፥26
2፥9 ዘፍ49፥10፤ ዘፀ15፥6፤ኢሳ30፥14፤ ኤር19፥10፤ራእ2፥27 ፤12፥5፤19፥15
2፥10 መዝ141፥6፤ ምሳ8፥15፤27፥11፤ አሞ2፥3
2፥11 1ዜና16፥30፤ መዝ9፥2፤35፥9፤ 103፥11፤104፥34፤ ኢሳ 61፥10
2፥12 ቍ7፤ዘዳ9፥8፤ መዝ5፥11፤34፥8፤64፥ 10፤84፥12፤ራእ6፥16
3፥1 ርዕስ 2ሳሙ15፥14
3፥2 መዝ22፥8፤ 71፥11፤ኢሳ36፥15፤37፥20
3፥3 ዘፍ15፥1፤መዝ27፥6
3፥4 ኢዮ 30፥20፤መዝ2፥6
3፥5 ዘሌ26፥6፤መዝ17፥15፤139፥18

[ሀ]1 ዕብራይስጡ እንዲሁ ሲሆን ሰብዓ ሊቃናት ግን *ይቈጣሉ* ይላል፡፡
[ለ]2 ወይም *የተቀባው*
[ሐ]7 ወይም *... አባትህ ሆንሁ*
[መ]9 ወይም *በብረት ዘንግ ትሰባብራቸዋለህ*
[ሠ]2 በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ በተደጋጋሚ የሚገኝ ሲሆን የቃሉ ትርጕም በትክክል አይታወቅም፤ የሙዚቃ ምልክት ሳይሆን አይቀርም

6በየአቅጣጫው የከበበኝን፣
አእላፍ ሕዝብ አልፈራም፡፡
7*እግዚአብሔር* ሆይ ተነሥ!
አምላኬ ሆይ፤ ታደገኝ፤
የጠላቶቼን ሁሉ መንጋጋ ትመታለህ፤
የክፉዎችንም ጥርስ ትሰባብራለህ፡፡
8ማዳን የ*እግዚአብሔር* ነው፤
በረከትህ በሕዝብህ ላይ ይሁን፡፡
ሴላ

## *መዝሙር* 4

### የሠርክ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዜም የዳዊት መዝሙር*

1የጽድቄ አምላክ ሆይ፤
በጠራሁህ ጊዜ መልስልኝ፤
ከጭንቀቴ አሳርፈኝ፤
ማረኝ፤ ጸሎቴንም ስማ፡፡
2ሰዎች ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ ክብሬን
ዝቅ[ሰ] ታደርጋላችሁ?
እስከ መቼስ ድረስ ከንቱ ነገርን
ትወዳላችሁ?
ሐሰትንስ[ሸ] ትሻላችሁ? ሴላ
3*እግዚአብሔር* ጻድቁን ለራሱ እንደ ለየ
ዕወቁ፤
*እግዚአብሔር* ወደ እርሱ በተጣራሁ
ጊዜ ይሰማኛል፡፡
4ስትቈጡ ኀጢአት አትሥሩ፤
በዐልጋችሁም ላይ ሳላችሁ፣
ልባችሁን መርምሩ፤ ጸጥም በሉ፡፡
ሴላ
5የጽድቅን መሥዋዕት አቅርቡ፤
በ*እግዚአብሔርም* ታመኑ፡፡
6ብዙዎች፣ "አንዳች በጎ ነገር ማን
ያሳየናል? ይላሉ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የፊትህ ብርሃን
በላያችን ይብራ፡፡
7ስንዴና አዲስ የወይን ጠጅ በብዛት
ባመረቱ ጊዜ ከሚያገኙት ደስታ
ይልቅ፣
አንተ ልቤን በታላቅ ሐሤት
ሞልተኸዋል፡፡
8በሰላም እተኛለሁ፤ አንቀላፋለሁም፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ያለ ሥጋት
የምታሳድረኝ አንተ ብቻ ነህና፡፡

## *መዝሙር* 5

### የጧት ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዘመር፣ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ቃሌን አድምጥ፤
መቃተቴንም ቸል አትበል፡፡
2ንጉሤና አምላኬ ሆይ፤
ወደ አንተ እጸልያለሁና፣
ድረስልኝ ብዬ ስጮህ ስማኝ፡፡
3*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በማለዳ ድምፄን
ትሰማለህ፤
በማለዳ ልመናዬን በፊትህ አቀርባለሁ፤
ፈቃድህንም በጥሞና እጠባበቃለሁ፤
4አንተ በክፋት ደስ የምትሰኝ አምላክ
አይደለህም፤
ክፉም ከአንተ ጋር አያድርም፡፡
5እብሪተኞች በፊትህ መቆም አይችሉም፤
ክፉ አድራጊዎችንም ሁሉ ጠላህ፡፡
6ሐሰት የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ፤
ደም የተጠሙትንና አታላዮችን፣
*እግዚአብሔር* ይጸየፋቸዋል፡፡
7እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት
ወደ ቤትህ እገባለሁ፤
አንተንም በመፍራት፣
ወደ ተቀደሰው መቅደስህ እሰግዳለሁ፡፡
8*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከጠላቶቼ የተነሣ፣
በጽድቅህ ምራኝ፤
መንገድህንም በፊቴ አቅናልኝ፡፡
9በንግግራቸው ውስጥ እውነት የለም፤
ልባቸው የጥፋት ጕሬ ነው፤
ጕሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው፤
በምላሳቸውም ይሸነግላሉ፡፡
10አምላክ ሆይ፤ የእጃቸውን ስጣቸው!
ተንኰላቸው መውደቂያቸው ይሁን፤
ከኀጢአታቸው ብዛት የተነሣ
አስወግዳቸው፣
በአንተ ላይ ዐምፀዋልና፡፡
11አንተን መጠጊያ የሚያደርጉ ሁሉ ግን
ደስ ይበላቸው፤
ዘላለም በደስታ ይዘምሩ፤
ስምህን የሚወዱ በአንተ ደስ እንዲላቸው፣
ተከላካይ ሁንላቸው፡፡
12*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ጻድቃንን
ትባርካቸዋለህ፤
በሞገስህም እንደ ጋሻ ትከልላቸዋለህ፡፡

## *መዝሙር* 6

### በጭንቅ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር በሸሚኒት[ቀ]*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በቍጣህ
አትገሥጸኝ፤

**3፥6** ኢዮ11፥15፤ መዝ23፥4፤27፥3፤ 118፥11
**3፥7** 2ዜና6፥41፤ ኢዮ16፥10፤29፥17፤ መዝ6፥4፤7፥1፤57፥4፤ 59፥1፤109፥21፤ 119፥153፤ምሳ30፥14፤ ኢሳ25፥9፤33፥22፤ 35፥4፤36፥15፤ 37፥20፤ኤር42፥11፤ ሰቆ3፥16፤ማቴ6፥13
**3፥8** ዘኍ6፥23፤መዝ 27፥1፤29፥11፤37፥39 ፤62፥1፤129፥8፤ኢሳ 43፥3:11፤44፥6:8፤ 45፥21፤ሆሴ13፥4፤ ዮና2፥9፤ራእ7፥10
**4፥1** ዘፍ32፥7፤ መሳ2፥15፤መዝ13፥3፤ 17፥6 ፤30፥10፤54፥2፤ 69፥16፤84፥8፤86፥7፤ 88፥2፤102፥2
**4፥2** ዘፀ16፥7፤ መሳ2፥17፤1ሳሙ4፥21፤ 2ነገ19፥26፤ኢዮ8፥22 ፤መዝ31፥6፤35፥26፤ 40፥4፤ኤር13፥25፤ 16፥9፤አሞ2፥4
**4፥3** መዝ6፥8፤ 12፥1፤30፥4፤31፥23፤ 79፥2፤ሚክ7፥2:7፤ 1ጢሞ4፥7፤2ጴጥ3፥11
**4፥4** መዝ63፥6፤ ዳን 2፥28፤ኤፌ4፥26
**4፥5** መዝ31፥6፤ 115፥9፤ምሳ3፥5፤28፥26 ፤ኢሳ26፥4፤ዮሐ14፥1
**4፥6** ዘኍ6፥25
**4፥7** ዘፍ27፥28፤ ዘዳ 28፥51፤ኢሳ9፥3፤ 35፥10፤65፥14:18፤ ሐሥ14፥17
**4፥8** ዘሌ26፥6፤ ዘኍ6፥26፤ዘዳ33፥28፤ ኢዮ11፥18፤ኤር32፥37
**5፥1** 1ነገ8፥29፤ መዝ17፥1፤38፥9፤40፥1፤ 116፥2፤ኢሳ35፥10፤ 51፥11፤ዳን9፥18
**5፥2** ኢዮ19፥7፤ 24፥12፤36፥5፤መዝ 44፥4፤68፥24፤84፥3
**5፥3** መዝ62፥1፤ 119፥81፤130፥5፤ ኢሳ28፥19፤50፥4፤ ኤር21፥12፤ ሕዝ46፥13፤ዕን2፥1፤ ሶፎ3፥5፤ሮሜ8፥19
**5፥4** መዝ1፥5፤11፥5 ፤104፥35፤ምሳ2፥22
**5፥5** 2ነገ19፥32፤ መዝ1፥5፤45፥7፤73፥3 ፤75፥4፤101፥3፤ 119፥104፤ምሳ8፥13፤ ኢሳ33፥19፤37፥33
**5፥6** ምሳ19፥22፤ዮሐ 8፥44፤ሐሥ5፥3፤ራእ21፥8
**5፥7** ዘዳ13፥4፤ 2ሳሙ12፥16፤1ነገ8፥48 ፤መዝ138፥2፤ ኤር44፥10፤ዳን6፥26
**5፥8** 1ነገ8፥36፤መዝ 23፥3፤31፥1፤71፥2፤85፥13፤89፥16፤ምሳ8፥20፤ዮሐ1፥23 **5፥9** መዝ 12፥2፤28፥3፤36፥3፤ምሳ15፥4፤ኤር5፥16፤9፥8፤ሉቃ11፥44፤ሮሜ3፥13
**5፥10** መዝ78፥40፤106፥7፤107፥11፤ሰቆ1፥5፤3፥42 **5፥11** ኢዮ 22፥19፤መዝ33፥1፤69፥36፤81፥1፤90፥14፤92፥4፥95፥1፤119፥132፤ 145፥7 **5፥12** ዘፍ15፥1፤መዝ32፥7፤112፥2 **6፥1** መዝ2፥5

[ሬ]3 ወይም *እግዚአብሔር … ወደ ላይ የምታነሣ ክብሬ ሆይ*
[ሰ]2 ወይም *ወደ ራሳችሁ* [ሸ]2 ወይም *የሐሰት አማልክት*
[ቀ]የ6 *መግቢያ* ርእስ ሲሆን በሙዚቃ ውስጥ የሚጠቀሙበት ቃል ሳይሆን አይቀርም፡፡

በመዓትህም አትቅጣኝ።
2 እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐቅመ ቢስ ነኝና
ማረኝ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ዐጥንቶቼ ተናግተ
ዋልና ፈውሰኝ።
3 ነፍሴ እጅግ ታውካለች፤
እስከ መቼ፤ አንተ እግዚአብሔር ሆይ፤
ይህ እስከ መቼ ድረስ ይሆናል?
4 እግዚአብሔር ሆይ፤ ተመለስና ሕይወቴን
ታደጋት፤
ስለ ጽኑ ፍቅርህም አድነኝ፤
5 በሞት የሚያስታውስህ የለምና፤
በሲኦልስ[ሀ] ማን ያመሰግንሃል?
6 ከመቃተቴ የተነሣ ዝያለሁ፤
ሌሊቱን ሁሉ በልቅሶ ዐልጋዬን አርሳለሁ፤
መኝታዬንም በእንባዬ አሾቃለሁ።
7 ዐይኖቼ በሐዘን ብዛት ደክመዋል፤
ከጠላቶቼም ሁሉ የተነሣ ማየት
ተስኖአቸዋል።
8 እናንተ ክፉ አድራጊዎች ሁሉ፤ ከእኔ
ራቁ፤
እግዚአብሔር የልቅሶዬን ድምፅ
ሰምቶአልና።
9 እግዚአብሔር ልመናዬን አድምጦአል፤
እግዚአብሔር ጸሎቴን ይቀበላል።
10 ጠላቶቼ ሁሉ ያፍራሉ፤ እጅግም
ይደነግጣሉ፤
በመጡበት ይመለሳሉ፤ ድንገትም
ይዋረዳሉ።

## መዝሙር 7

### በስደት ጊዜ የጻድቁ ሰው ጸሎት

*ዳዊት በብንያማዊው በኩዝ ምክንያት ለእግዚአብሔር የዘመረው መዝሙር*

1 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ አንተ
መሸሸጊያዬ ነህ፤
ከሚያሳድዱኝ ሁሉ አድነኝ፤ ታደገኝም፤
2 አለበለዚያ እንደ አንበሳ ይዘነጣጥሉኛል፤
የሚያድነኝ በሌለበትም ይቦጫጭቁኛል።
3 እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ይህን
አድርጌ ከሆነ፣
በደልም በእጄ ከተገኘ፣
4 በጎ ለዋለልኝ ክፉ መልሼ ብሆን፣
ጠላቴንም በከንቱ ዘርፌ ከሆነ፣
5 ጠላቴ አሳዶ ይያዘኝ፤
ሕይወቴን ከምድር ይቀላቅል፤
ክብሬንም ከዐፈር ይደባልቅ። ሴላ
6 እግዚአብሔር ሆይ፤ በመዓትህ ተነሥ፤
በቍጣ በተነሡብኝ ላይ ተነሥ፤
አምላኬ ሆይ፤ ንቃ፤ ትእዛዝም አስተላልፍ!
7 የሕዝቦች ጉባኤ ይክበብህ፤
አንተም ከላይ ሆነህ ግዛቸው፤
8 እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ ይፈርዳል።
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ጽድቄ
ፍረድልኝ፤
ልዑል ሆይ፤ እንደ ቅን አካሄዴ
መልስልኝ።
9 ልብንና ኵላሊትን የምትመረምር፣
ጻድቅ አምላክ ሆይ፤
የክፉዎችን ዐመፅ አጥፋ፤
ጻድቁን ግን አጽና።
10 ጋሻዬ[ተ] ልዑል አምላክ ነው፤
እርሱ ልበ ቅኖችን ያድናቸዋል።
11 እግዚአብሔር ጻድቅ ዳኛ ነው፤
ቍጣውንም በየዕለቱ የሚገልጥ አምላክ
ነው።
12 ሰው በንስሓ የማይመለስ ከሆነ ግን፣
ሰይፉን[ቸ] ይስላል፤
ቀስቱን ይገትራል።
13 የሚገድሉ ጦር ዕቃዎቹን አሰናድቶአል፤
የሚንበለበሉትን ፍላጻዎቹንም
አዘጋጅቶአል።
14 ክፋትን እያማጠ ያለ ሰው፣
ቅጥፈትን አርግዞ፣ ሐሰትን ይወልዳል።
15 ጕድጓድ ምሶ ዐፈሩን የሚያወጣ፣
ባዘጋጀው ጕድጓድ ራሱ ይገባበታል።
16 ተንኰሉ ወደ ራሱ ይመለሳል፤
ዐመፃውም በገዛ ዐናቱ ላይ ይወርዳል።
17 ስለ ጽድቁ ለእግዚአብሔር ምስጋና
አቀርባለሁ፤
የልዑል እግዚአብሔርን ስም
በመዝሙር አወድሳለሁ።

## መዝሙር 8

### የፈጣሪ ግርማ በፍጥረቱ ላይ

*ለመዘምራን አለቃ፣ በዋሽንት የሚዜም፤ የዳዊት መዝሙር*

1 እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤
ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ
ግርማዊ ነው!
ክብርህ ከሰማያት በላይ፣
ከፍ ከፍ ብሎአል።
2 ከልጆችና ጡት ከሚጠቡ ሕፃናት አፍ፣
ምስጋናን[ኀ] አዘጋጀህ፤
ከጠላትህ የተነሣ፣
ባላንጣንና ቂመኛን ጸጥ ታሰኝ ዘንድ።

[ሀ]5 ወይም *በመቃብር*
[ተ]10 ወይም *የኔ ልዑል*
[ቸ]12 ወይም *ሰው ንስሓ ካልገባ፣ እግዚአብሔር ሰይፉን …*
[ኀ]2 ወይም *ብርታትን*

**6፥2** ዘኍ12፥13፤መዝ 4፥1፤22፥14፤26፥11፤31፥10፤32፥3፤38፥3፤42፥10፤61፥2፤77፥3፤102፥3፤142፥3፤ኢሳ40፥31፤ኤር3፥12፤8፥18፤12፥15፤31፥20፤ሕዝ21፥7
**6፥3** 1ሳሙ1፥14፤1ነገ18፥21፤ኢዮ7፥11፤መዝ4፥2፤31፥7፤38፥8፤55፥4፤89፥46፤ኢሳ6፥11፤ኤር4፥14፤ዕን1፥2፤ዘካ1፥12፤ዮሐ12፥27፤ሮሜ9፥2፤2ቆሮ2፥4
**6፥4** መዝ13፥5፤25፥ 16፤31፥2:16፤69፥16፤71፥2፤77፥8፤85፥7፤86፥16፤88፥2፤102፥2፤119፥41:132፤ኢሳ54፥8:10
**6፥5** መዝ30፥9፤88፥10-12፤115፥17፤መክ9፥10፤ኢሳ38፥18
**6፥6** መሳ8፥5፤ኢዮ3፥24፤7፥3፤16፥16፤23፥2፤መዝ12፥5፤77፥3፤102፥5፤ሰቆ1፥8:11:21:22፤ሉቃ7፥38፤ሐሥ20፥19
**6፥7** ኢዮ16፥8፤መዝ 31፥9፤69፥3፤119፥82፤ኢሳ38፥14
**6፥8** መዝ5፥5፤119፥115፤139፥19፤ማቴ 7፥23
**6፥9** መዝ28፥6፤116፥1
**6፥10** 2ነገ19፥26፤መዝ40፥14
**7** ርዕስ ዕን3፥1
**7፥1** መዝ2፥12፤3፥7፤11፥1፤31፥1:15፤119፥86:157:161
**7፥2** ዘፍ49፥9፤መዝ 3፥2፤71፥11፤ራእ4፥7
**7፥3** ኢሳ59፥3
**7፥4** መዝ35፥7:19፤ምሳ24፥28
**7፥5** ዘፀ15፥9፤2ሳሙ 22፥43፤2ነገ9፥33፤ኢዮ7፥21፤ኢሳ10፥6፤ሰቆ3፥16
**7፥6** 2ዜና6፥41፤መዝ35፥23፤44፥23፤ 138፥7
**7፥7** መዝ68፥18
**7፥8** ዘፍ3፥5፤20፥5፤ዘኍ24፥16፤1ሳሙ26፥23፤1ዜና16፥33፤መዝ18፥20፤ማር5፥7
**7፥9** 1ዜና28፥9፤መዝ 26፥2፤37፥23፤40፥2፤ኤር11፥20፤ራእ2፥23
**7፥10** ኢዮ33፥3፤መዝ3፥3
**7፥11** ዘፍ18፥25፤ዘዳ 9፥8፤መዝ9፥8፤67፥4፤75፥2፤96፥13፤98፥9፤ኢሳ11፥4፤ኤር 11፥20
**7፥12** ዘዳ32፥41፤2ሳሙ22፥35፤መዝ21፥12፤ኢሳ5፥28፤13፥18፤ሕዝ 3፥19 **7፥13** መዝ11፥2፤18፥14፤64፥3 **7፥14** ኢሳ59፥4፤ያዕ1፥15
**7፥15** ኢዮ4፥8፤መዝ 35፥7:8፤40፥2፤94፥13፤ምሳ26፥27
**7፥17** ዘፍ14፥18፤ 2ዜና31፥2፤መዝ5፥8፤ሮሜ15፥11፤ዕብ2፥12
**8፥1** ዘፀ15፥11፤1ዜና16፥10፤መዝ57፥5፤8፥5፤113፥4፤148፥13፤ዕን3፥3፤ሉቃ2፥9 **8፥2** መዝ143፥12፤ማቴ21፥16

3የጣቶችህን *ሥራ*፣
ሰማያትህን ስመለከት፣
በስፍራቸው ያኖርሃቸውን፣
ጨረቃንና ከዋክብትን ሳይ፣
4በሐሳብህ ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው
ምንድን ነው?
ትጠነቀቅለትም ዘንድ የሰው ልጅ
ምንድን ነው?
5ከመላእክት በጥቂት አሳንሰኸው፤
የክብርንና የሞገስን ዘውድ
አቀዳጀኸው።
6በእጆችህ *ሥራ* ላይ ሾምኸው፤
ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት፤
7በጎችንና ላሞችን ሁሉ፣
የዱር አራዊትንም፣
8የሰማይ ወፎችንና፣
የባሕር ዓሦችን፣
በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱትንም
ሁሉ አስገዛህለት።
9*እግዚአብሔር* አምላካችን ሆይ፤
ስምህ በምድር ሁሉ ላይ ምንኛ
ግርማዊ ነው!

## መዝሙር 9[ነ]

### በክፉ ላይ ፍርድ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በሙትላቤን ቅኝት፤ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
ስለ ድንቅ *ሥራዎ*ችህም ሁሉ እናገራለሁ።
2በአንተ ደስ ይለኛል፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ፤
ልዑል ሆይ፤ ስምህን በመዝሙር
እወድሳለሁ።
3ጠላቶቼ ወደ ኋላ በተመለሱ ጊዜ፣
ተሰነካክለው ከፊትህ ይጠፋሉ፤
4ፍርዴም ጕዳዬም በአንተ እጅ ናቸውና፤
ቅን ፍርድ እየሰጠህ በዙፋንህ ላይ
ተቀምጠሃል።
5ሕዝቦችን ገሠጽህ፤ ክፉዎችንም አጠፋህ፤
ስማቸውንም እስከ ወዲያኛው
ደመሰስህ።
6ጠላቶች ለዘላለም ጠፉ፤
ከተሞቻቸውንም ገለባበጥሃቸው፤
መታሰቢያቸውም ተደምስሶአል።
7*እግዚአብሔር* ግን ለዘላለም በዙፋኑ ላይ
ነው፤
መንበሩንም ለፍርድ አጽንቶአል።
8ዓለምን በጽድቅ ይዳኛል፤
ሕዝቦችንም በፍትሕ ይገዛል።
9*እግዚአብሔር* ለተጨቈኑት ዐምባ ነው፤
በመከራም ጊዜ መጠጊያ ይሆናቸዋል።

8፥3 ዘፍ1፥16፤15፥5፤ዘፀ8፥19፤ዘዳ10፥14፤1ዜና16፥26፤ 2ዜና2፥12፤መዝ102፥25፤1ቆሮ15፥41
8፥4 1ዜና29፥14
8፥5 ዘፍ1፥26፤ መዝ 21፥5፤103፥4
8፥6 ዘፍ1፥28፤ 1ነገ 5፥3፤ኢዮ10፥3፤መዝ19፥1፤102፥25፤145፥10፤ኢሳ26፥12፤29፥23፤45፥11፤1ቆሮ15፥25:27፤ኤፌ1፥22፤ዕብ1፥10፤2፥6-8
8፥7 ዘፍ2፥19፤ 13፥5 ፤26፥14
8፥8 ዘፍ1፥26
8፥9 ቍ1
9፥1 ዘዳ4፥34፤ መዝ 86፥12፤111፥1፤119፥2:10:145፤138፥1
9፥2 2ዜና31፥2፤ ኢዮ22፥19፤መዝ14፥7፤31፥7፤70፥4፤92፥1፤97፥8፤126፥3፤ ምሳ23፥15፤ኢሳ25፥9፤ ኤር30፥19፤ ኢል2፥21፤ሶፎ3፥14፤ ማቴ5፥12፤ራእ19፥7
9፥4 1ነገ8፥45፤ ኢዮ 16፥21፤ መዝ7፥11፤11፥4፤47፥8፤67፥4፤98፥9፤ ኢሳ6፥1፤1ጴጥ2፥23
9፥5 ዘፍ20፥7፤37፥10፤ 1ዜና16፥21፤ ኢዮ 18፥17፤ መዝ59፥5፤105፥14፤ ኢሳ26፥14፤ 66፥15
9፥6 ዘዳ29፥28፤መዝ34፥16፤109፥15፤መክ9፥5፤ኢሳ14፥22፤26፥14፤ኤር2፥3፤46፥1-51:58፤ሶፎ2፥8-10
9፥7 1ዜና16፥31፤ መዝ11፥4፤47፥8፤93፥2፤ኢሳ6፥1፤66፥1፤ራእ19፥6
9፥8 ቍ4፤መዝ7፥11፤11፥7፤45፥6፤72፥2
9፥9 ዘዳ33፥27፤ 2ሳሙ22፥3፤ መዝ10፥18፤32፥7፤74፥21፤121፥7
9፥10 ዘፍ28፥15፤ ዘዳ4፥31፤መዝ22፥1፤37፥25፤70፥4፤71፥11፤91፥14፤ኢሳ49፥14፤ ኤር15፥18፤ዕብ13፥5
9፥11 መዝ2፥6፤7፥17፤18፥49፤44፥11፤57፥9፤105፥1፤106፥27፤ኢሳ24፥13፤ሕዝ20፥23፤1ጢሞ3፥16
9፥12 ቍ18፤2ሳሙ4፥11፤መዝ10፥17፤22፥24፤72፥4፤ኢሳ49፥13
9፥13 ዘኍ10፥9፤ኢዮ17፥16፤መዝ3፥7፤6፥2፤18፥3፤41፥4፤51፥1፤86፥3፡16፤119፥132፤ማቴ16፥18

10ስምህን የሚያውቁ ይታመኑብሃል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሚሹህን
አትተዋቸውምና።
11በጽዮን ለሚኖር ለ*እግዚአብሔር* ዘምሩ፤
*ሥራ*ውንም በሕዝቦች መካከል
በግልጽ አውሩ፤
12ደም ተበቃዩ ዐስቦአቸዋልና፤
የጭቍኖችንም ጩኸት አልዘነጋም።
13*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጠላቶቼ
የሚያደርሱብኝን መከራ
ተመልከት፤
አይተህም ራራልኝ፤ ከሞት ደጆም
አንሥተህ መልሰኝ፤
14ይህን ስታደርግልኝ፣ በጽዮን ሴት ልጅ
ደጆች፣
ምስጋናህን ዐውጃለሁ፤
በማዳንህም ሐሤት አደርጋለሁ።
15አሕዛብ በቈፈሩት ጕድጓድ ገቡ፤
እግራቸውም ራሳቸው በሰወር
ባስቀመጡት ወጥመድ ተያዘ።
16*እግዚአብሔር* በትክክለኛ ፍርዱ የታወቀ
ነው፤
ክፉዎችም በእጃቸው *ሥራ* ተጠመዱ።
ሒጋዮን[ኘ] ሴላ
17ክፉዎች ተመልሰው ወደ ሲኦል[ኣ]
ይወርዳሉ፤
እግዚአብሔርን የሚዘነጉ ሕዝቦችም ሁሉ
እንደዚሁ።
18ችግረኞች ግን መቼም ቢሆን
አይረሱም፤
የድኾችም ተስፋ ለዘላለም መና ሆኖ
አይቀርም።
19*እግዚአብሔር* ሆይ ተነሥ፤ ሰውም
አያይል፤
አሕዛብም በፊትህ ይፈረድባቸው።
20*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ድንጋጤ
አምጣባቸው፤
ሕዝቦች ሰው ከመሆን እንደማያልፉ
ይወቁ። ሴላ

9፥14 2ነገ19፥21፤መዝ13፥5፤35፥9፤50፥23፤51፥12:15፤ኢሳ1፥8፤10፥32፤37፥22፤62፥11፤ኤር4፥31፤6፥2፤ሰቆ1፥6፤ሚክ1፥13፤ሶፎ3፥14፤ዘካ2፥10፤ማቴ21፥5፤ዮሐ12፥15፤1ጴጥ2፥9 9፥15 ኢዮ4፥8፤መዝ35፥7:8፤57፥6 9፥16 ምሳ5፥22 9፥17 ዘኍ16፥30፤ኢዮ8፥13፤ምሳ5፥5 9፥18 ቍ12፤መዝ25፥3፤39፥7፤71፥5፤74፥19፤ምሳ23፥18፤ኤር14፥8 9፥19 2ዜና14፥11፤መዝ3፥7፤110፥6፤ኢሳ2፥4፤ኢል3፥12 9፥20 ዘፍ35፥5፤መዝ31፥13፤62፥9፤ኢሳ13፥8፤31፥3፤ሕ28፥2፤ሉቃ21፥26

[ነ]ምዕ9 መዝ9 እና 10 በመጀመሪያው የጥንት ቅጅ ላይ አንጓዎቹ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምሩ እንዲሁም ጅማሬው ወይም መጨረሻው ትርጕም አዘል የሆነ አንድ ወጥ ግጥም ነበር፤ በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ሁለቱም አንድ መዝሙር ናቸው።
[ኘ]16 ወይም *በተመሥጦ ማሰብ*
[ኣ]17 ወይም *መቃብር*

## መዝሙር 10[ከ]
## ፍትሕ ለማግኘት የቀረበ ልመና

1*እግዚአብሔር ሆይ፤ ለምን እንዲህ ርቀህ ቆምህ?*
*በመከራ ጊዜስ ለምን ድምፅህን አጠፋህ?*
2ክፉዎች የተጨነቀውን በእብሪት ያሳድዳሉ፤
በወጠኑት ተንኰል ይጠመዱ።
3ክፉ ሰው በልቡ ምኞት ይኵራራል፤
ስግብግቡን ይባርካል፤ እግዚአብሔርንም ይዳፈራል።
4ክፉ ሰው ከትዕቢቱ የተነሣ እግዚአብሔርን አይፈልግም፤
በሐሳቡም ሁሉ አምላክ የለም፤
5መንገዱ ዘወትር የተሳካ ነው፤
ዕቡይ፣ ከሕግህም የራቀ ነው።
በመሆኑም በጠላቶቹ ላይ ያፌዛል።
6በልቡም፣ "ከስፍራዬ የሚነቀንቀኝ የለም፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም መከራ አያገኘኝም" ይላል።
7አፉ መርገምን፣ ቅጥፈትንና ግፍን የተሞላ ነው፤
ሽንገላና ክፋት ከምላሱ ሥር ይገኛሉ።
8በየመንደሩ ሥርቻ ያደፍጣል፤
ንጹሓንን በሰዋራ ስፍራ ይገድላል።
ዐይኖቹንም በምስኪኖች ላይ ያነጣጥራል።
9በደኑ ውስጥ እንዳለ አንበሳ በስውር ያደባል፤
ረዳት የሌለውን ለመያዝ ያሸምቃል፤
ድኻውንም አፈፍ አድርጎ በወጥመዱ ይጐትታል።
10ምስኪኑም ይደቃል፤ ዐንገቱን ይደፋል፤
ያልታደለውም በክንዱ ሥር ይወድቃል።
11በልቡም፣ "እግዚአብሔር ረስቶአል፤
ፊቱን ሸፍኖአል፤ ፈጽሞም አያይም" ይላል።

12*እግዚአብሔር ሆይ ተነሥ፤ አምላክ ሆይ፤ ክንድህን አንሣ፤*
*ረዳት የሌላቸውንም አትርሳ።*
13ክፉ ሰው በእግዚአብሔር ላይ ለምን ክፉ ይናገራል?
በልቡስ፣ "ስለ ሥራዬ አይጠይቀኝም" ለምን ይላል?
14አንተ ግን መከራንና ሐዘንን ታያለህ፤
በእጅህም ዋጋ ለመክፈል ትመለከታለህ፤
ምስኪኑም ራሱን በአንተ ላይ ይጥላል፤
ለድኻ ዐደግም ረዳቱ አንተ ነህ።
15የክፉውንና የበደለኛውን ክንድ ስበር፤
የእጁንም ስጠው፤
ምንም እስከማይገኝ ድረስ።
16*እግዚአብሔር* ከዘላለም እስከ ዘላለም ንጉሥ ነው፤
ሕዝቦችም ከምድሩ ይጠፋሉ።
17*እግዚአብሔር ሆይ፤ የተገፉትን ምኞት ትሰማለህ፤*
*ልባቸውን ታበረታለህ፤ጆሮህንም ወደ እነርሱ ጣል ታደርጋለህ፤*
18ከዐፈር የተፈጠረ ሰው ከእንግዲህ እንዳያስጨንቃቸው፣
*አንተ ለድኻ ዐደጉና ለተገፋው ትሟገታለህ።*

## መዝሙር 11
## የጻድቃን ትምክሕት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር።*

1*በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤*
*ታዲያ ነፍሴን፣ "እንደ ወፍ ወደ ተራራ ብረሪ"*
*ለምን ትሏታላችሁ?*
2*ደግሞም ለምን እንዲህ ትሉኛላችሁ?*
"ክፉዎች፣ እነሆ፣ ቀስታቸውን ገትረዋል፤
ቅን ልብ ያላቸውን በጨለማ ለመንደፍ፣
ፍላጻቸውን በአውታሩ ላይ ደግነዋል።
3*መሠረቱ ከተናደ፣*
*ጻድቅ ምን ማድረግ ይችላል?"*[ኸ]
4*እግዚአብሔር* በተቀደሰ *መቅደሱ* አለ፤
*የእግዚአብሔር* ዙፋን በሰማይ ነው።
ዐይኖቹ ሰዎችን *ይመለከታሉ፤*
ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን *ይመረምራሉ።*
5*እግዚአብሔር ጻድቁንና ኀጥኡን ይመረምራል፤*[ወ]
*ዐመፃን የሚወዱትን ግን፣*
*ነፍሱ ትጠላቸዋለች።*
6እርሱ በክፉዎች ላይ የእሳት ፍምና ዲን ያዘንባል፤
*የጽዋቸውም ዕጣ ፈንታ፣*
*የሚለበልብ ዐውሎ ነፋስ ነው።*
7*እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና፤*
*የጽድቅ ሥራም ይወዳል፤*
*ቅኖችም ፊቱን ያያሉ።*

## መዝሙር 12
## ከክፉ ዓለም ለመዳን የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በስምንተኛው ቅኝት የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር።*

1*እግዚአብሔር ሆይ፤ ደግ ሰው የለምና*

[ከ]*ምዕ10 መዝ9 እና 10 በመጀመሪያው የጥንት ቅጅ ላይ አንጓዎች ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምሩ እንዲሁም ጅማሬው ወይም መጨረሻው ትርጒም ዐዘል የሆነ አንድ ወጥ ግጥም ነበር በሰብዓ ሊቃናት ውስጥ ሁለቱ አንድ መዝሙር ናቸው።*
[ኸ]3 ወይም ***ጻድቁ ምን እያደረገ ነው?***
[ወ]5 ወይም ***ጻድቁ እግዚአብሔር ኀጥኡን ይመረምራል***

10፥1 መዝ13፥1፤ 22፥1:11፤35፥22፤ 38፥21፤71፥12
10፥2 ቆላ9፤ ኢዮ20፥19
10፥3 ኢዮ1፥5፤ መዝ 49፥6፤94፥4፤ ኤር48፥30
10፥4 መዝ36፥1
10፥5 መዝ18፥27፤ 101፥5፤ምሳ6፥17፤ ኢሳ13፥11፤ኤር48፥29
10፥6 ራእ18፥7
10፥7 ኢዮ20፥12፤ መዝ73፥8፤119፥134፤ መክ4፥1፤ኢሳ30፥12 ፤ሮሜ3፥14
10፥8 መዝ37፥32፤ 59፥3፤71፥10፤ ምሳ1፥11፤ኤር5፥26፤ ሆሴ6፥9፤ሚክ7፥2
10፥9 ቆላ2፤ ኢዮ 18፥8
10፥10 ኢዮ9፥17
10፥11 ኢዮ22፥13: 14፤መዝ42፥9፤77፥9
10፥12 መዝ3፥7፤ 9፥12፤17፥7፤20፥6፤ 106፥26፤ኢሳ26፥11 ፤ሚክ5፥9
10፥13 ቆላ3፤ ኢዮ 31፥14
10፥14 ቆላ7፤ ዘዳ 33፥29፤ መዝ22፥11፤37፥5
10፥15 ኢዮ31፥22
10፥16 ዘፀ15፥18 ፤ዘዳ8፥20
10፥17 ዘፀ22፥23፤ መዝ9፥12
10፥18 ዘዳ24፥17፤ መዝ9፥9፤146፥9
11፥1 ዘፍ14፥10፤ መዝ7፥1፤50፥11
11፥2 2ሳሙ22፥35 ፤ኢዮ33፥3፤መዝ7፥10: 13፤10፥8፤58፥7
11፥3 መዝ18፥15፤ 82፥5፤ኢሳ24፥18
11፥4 1ነገ8፥48፤ 2ዜና6፥18፤መዝ9፥7፤ 18፥6፤27፥4፤33፥18፤ 66፥7፤ምሳ15፥3፤ ዮና2፥7፤ሚክ1፥2፤ ዕን2፥20፤ማቴ5፥34፤ 23፥22፤ራእ4፥2
11፥5 ዘዳ7፥13፤ኢዮ 23፥10፤28፥28፤መዝ 5፥5፤45፥7፤ኢሳ1፥14
11፥6 ዘፍ19፥24፤ 41፥6፤ኢዮ1፥19፤ ራእ 9፥17
11፥7 2ዜና12፥6፤ ዕዝ9፥15፤ኢዮ1፥1፤ መዝ9፥8፤17፥15፤ 33፥5፤99፥4፤ 140፥13፤ኢሳ28፥17፤ 30፥18፤56፥1፤61፥8፤ ኤር9፥24፤ሉቃ23፥50፤ 2ጢሞ4፥8
12፥1 ኢሳ57፥1፤ ሚክ7፥2

አንተው ድረስልኝ!
ከሰዎችም መካከል አንድ ታማኝ
አይገኝም።
2እርስ በርሳቸው ውሸት ይነጋገራሉ፤
በሽንገላ ከንፈርና በሁለት ልብ
ይናገራሉ፤
3ሽንጋዩን ከንፈር ሁሉ፣
ነገር የምታበዛውንም ምላስ እግዚ
አብሔር ያጥፋ!
4እነዚህም፣ "በአንደበታችን እንረታለን፤
ከንፈራችን የእኛ ነው፤[0] ጌታችንስ
ማነው?"
የሚሉ ናቸው።

5እግዚአብሔር፣ "ስለ ድኾች መከራ፣
ስለ ችግረኞችም ጩኸት፣
አሁን እነሣለሁ፤
በናፈቁትም ሰላም አኖራቸዋለሁ"
ይላል።
6የእግዚአብሔር ቃል የጠራ ቃል ነው፤
ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ፣
በምድር ላይ በከውር እንደ ተፈተነ
ብር ነው።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ትጠብቀናለህ፤
ከዚህም ትውልድ ለዘላለም
ትከልለናለህ።
8በሰዎች ዘንድ ክፋት ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ፣
ዐመፀኞች በየአቅጣጫው በዛቻ
ይዞራሉ።

## መዝሙር 13
### በአምላኩ የታመነ ሰው አቤቱታ
*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር።*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ መቼ ድረስ
ለዘላለሙ ትረሳኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ የምትሰውረው እስከ
መቼ ድረስ ነው?
2ከሐሳቤ ጋር የምሟገተው፣
ልቤም ቀኑን ሙሉ የሚያዝነው እስከ
መቼ ነው?
ጠላቴስ በእኔ ላይ የሚያይለው እስከ
መቼ ድረስ ነው?

3እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ተመልከት፤
ስማኝም፤
የሞት እንቅልፍ እንዳልተኛ ዐይኖቼን
አብራ፤
4በዚህም ጠላቴ፣ "አሸነፍሁት" እንዳይል፣
ባላጋራዎቼም በውድቀቴ ደስ
እንዳይላቸው ርዳኝ።

5እኔ ግን በጸናች ፍቅርህ እታመናለሁ፤
ልቤም በማዳንህ ደስ ይለዋል።
6ቸርነቱ በዝቶልኛልና፣
ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ።

12፥2 መዝ5፥6፡9፤ 34፥13፤141፥3፤ምሳ 6፥19፤12፥17፤13፥3፤ ኢሳ32፥7፤ሮሜ16፥18
12፥3 መዝ73፥9፤ ምሳ26፥28፤28፥23፤ ዳን7፥8፤ያዕ3፥5፤ ራእ 13፥5
12፥4 ምሳ18፥21፤ ያዕ3፥6
12፥5 መዝ3፥7፤6፥6 ፤34፥6፤35፥10፤44፥24 ፤62፥10፤72፥14፤73፥8 ፤መክ4፥1፤5፥8፤ኢሳ 3፥15፤5፥7፤30፥12፤ 59፥13፤ሐሥ7፥34
12፥6 2ሳሙ22፥31 ፤ኢዮ23፥10፤28፥1፤መዝ 18፥30፤119፥140፤ ኢሳ48፥10፤ዘካ13፥9
12፥7 መዝ16፥1፤27፥5 ፤37፥28፤ዮሐ17፥12
12፥8 መዝ55፥10-11
13፥1 ዘዳ31፥17፤ መዝ6፥3፤22፥24፤ 42፥9፤ኢሳ8፥17፤ 54፥9፤ ሰቆ5፥20
13፥2 መዝ42፥4፤ 55፥2፤94፥3፤139፥23 ፤ኢሳ33፥18፤ዳን7፥28
13፥3 ዕዝ9፥8፤መዝ 4፥1፤9፥12፤25፥18፤ 31፥7፤35፥23፤59፥4፤ 76፥5፤80፥14፤90፥5፤ 107፥41፤119፥50፡15 3፤ኤር51፥39
13፥4 1ነገ19፥2፤መዝ 25፥2፤38፥16፤118፥13
13፥5 ኢዮ33፥26፤ መዝ6፥4፤9፥14፤ ኢሳ 25፥9፤33፥2
13፥6 ዘፀ15፥1፤ መዝ 7፥17
14፥1 መዝ10፥4
14፥2 ዕዝ6፥21፤ኢዮ 41፥34፤መዝ85፥11፤9 2፥6፤102፥19፤ሰቆ3፥50
14፥3 1ሳሙ8፥3፤ 1ነገ8፥46፤መዝ143፥2 ፤መክ7፥20፤ሮሜ3፥1 0-12፤1ጢሞ 5፥15፤2ጴጥ2፥7
14፥4 መዝ27፥2፤ 79፥6፤82፥5፤ኢሳ64፥7 ፤65፥1፤ኤር4፥22፤ 10፥25፤ሆሴ7፥7፤ ሚክ3፥3
14፥6 2ሳሙ22፥3
14፥7 ዘዳ30፥3፤ መዝ 2፥6፤ኤር48፥47
15፥1 ዘፀ15፥17፤ 25፥8፤29፥46፤2ዜና 22፥19፤መዝ20፥2፤ 23፥6፤27፥4፤61፥4፤ 78፥69፤150፥1
15፥2 ዘፍ6፥9፤መዝ 18፥32፤ምሳ16፥13፤ ኢሳ45፥19፤ኤር7፥28 ፤9፥5፤ዘካ8፥3፡16፤ሮሜ 9፥1፤ኤፌ1፥4፤4፥25፤ 1ተሰ3፥13፤ቲቶ1፥6
15፥3 ዘሌ19፥16
15፥4 ዘዳ23፥21፤

## መዝሙር 14
### አምላክ የለሽ ሰዎች
14፥1-7 ተጓ ምብ-መዝ53፥1-6

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር።*

1ሞኝ[ʺ] በልቡ፣
"እግዚአብሔር የለም" ይላል።
ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም
ጸያፍ ነው፤
በጎ ነገር የሚሠራ አንድም የለም።
2የሚያስተውል፣ እግዚአብሔርን የሚፈልግ
መኖሩን ለማየት፣
እግዚአብሔር ከሰማይ
ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ።
3ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤
በአንድ ላይም ብልሹ ሆነዋል፤
አንድ እንኳ፣
መልካም የሚያደርግ የለም።
4የእግዚአብሔርን ስም የማይጠሩት፣
ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉት፣
ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ዕውቀት
የላቸውምን?
5ባሉበት ድንጋጤ ውጦአቸዋል፤
እግዚአብሔር በጻድቃን መካከል
ይገኛልና።
6እናንተ የድኾችን ዕቅድ ለማፋለስ
ትሻላችሁ፤
እግዚአብሔር ግን መጠጊያቸው ነው።
7ምነው እስራኤልን የሚያድን ከጽዮን
በወጣ!
እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ
በሚመልስበት ጊዜ፣
ያዕቆብ ደስ ይበለው፤ እስራኤልም
ሐሤት ያድርግ።

## መዝሙር 15
### የእግዚአብሔር ቤተኛ
*የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በድንኳንህ ውስጥ
ማን ያድራል?
በተቀደሰው ኰረብታህስ ማን መኖር
ይችላል?

2አካሄዱ ንጹሕ የሆነ፣
ጽድቅን የሚያደርግ፤
ከልቡ እውነትን የሚናገር፤
3በምላሱ የማይሸነግል፤
በባልንጀራው ላይ ክፉ የማይሠራ፤
ወዳጁን የማያማ፤
4ነውረኛ በፊቱ የተናቀ፤

[0]4 ወይም *ከንፈራችን ማረሻ ምላጫችን ነው*
[ʺ]1 በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ *ሞኝ* ወይም *ተላላ* ተብለው የተ ተረጐሙት የዕብራይስጥ ቃላት ግብረ ገባዊ ንቅዘ ትን የሚያመለክቱ ናቸው።

*እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ግን*
*የሚያከብር*፤
ዋጋ የሚያስከፍለውም ቢሆን፣
*ቃለ መሐላውን የሚጠብቅ*፤
5ገንዘቡን በዐራጣ የማያበድር፣
በንጹሓን ላይ ጉቦ የማይቀበል፤

እነዚህን የሚያደርግ፣
ከቶ አይናወጥም።

## *መዝሙር* 16

**እግዚአብሔር ርስቴ**

የዳዊት ቅኔ

1አምላክ ሆይ፤ መጠጊያዬ ነህና፣
በከለላህ ሰውረኝ።

2*እግዚአብሔርን*፣ “አንተ ጌታዬ ነህ፤
ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም”
አልሁት።
3በምድር ያሉ ቅዱሳን፣
*ሙሉ ደስታ የማገኝባቸው ክቡራን*
*ናቸው*።[ሠ]
4ሌሎችን አማልክት የሚከተሉ፣
*ሐዘናቸው ይበዛል*፤
እኔ ግን የደም ቍርባናቸውን አላፈስም፤
ስማቸውንም በአፌ አልጠራም፤

5*እግዚአብሔር የርስት ድርሻዬና ጽዋዬ*
*ነው*፤
*ዕጣዬም በእጅህ ናት*።
6*መካለያ ገመድ ባማረ ስፍራ*
*ተጥሎልኛል*፤
በርግጥም የተዋበች ርስት አግኝቻለሁ።

7*የሚመክረኝን እግዚአብሔርን* እባርካለሁ፤
በሌሊት እንኳ ልቤ ቀናውን
*ያመላክተኛል*።
8*እግዚአብሔርን* ሁልጊዜ በፊቴ
አድርጌአለሁ፤
እርሱ በቀኜ ስላለ አልናወጥም።
9ስለዚህ ልቤ ደስ አለው፤ ነፍሴም
ሐሤት አደረገች፤
*ሥጋዬም ያለ ሥጋት ዐርፎ*
ይቀመጣል፤
10በሲኦል[ረ] ውስጥ አትተወኝምና፤
ቅዱስህም[ሰ] መበስበስን እንዲያይ
አታደርግም።
11*የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ*፤[ሸ]
በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣
በቀኝህም የዘላለም ፍሥሓ አለ።

## *መዝሙር* 17

**የንጹሕ ሰው አቤቱታ**

የዳዊት ጸሎት

1*እግዚአብሔር ሆይ*፤ በቅንነት የቀረበውን
አቤቱታዬን ስማ፤
ጩኸቴንም አድምጥ፤
ከአታላይ ከንፈር ያልወጣውን፣
ጸሎቴን አድምጥ።
2ጽድቄ ከአንተ ዘንድ ይምጣ፤
ዐይኖችህም ፍትሕን ይዩ።

3ልቤን መረመርኸው፣ በሌሊት ጠጋ
ብለህ ፈተንኸኝ፤
ፈተሽኸኝ አንዳች አላገኘህብኝም፤
አንደበቴም ዕላፊ አልሄደም።
4ከሰዎች ተግባር፣
በከንፈርህ ቃል፣
ከዐመፀኞች መንገድ፣
ራሴን ጠብቄአለሁ።
5*አረማመዴ በመንገድህ ጸንቶአል*፤
እግሮቼም አልተንሸራተቱም።

6አምላክ ሆይ፤ ስለምትመልስልኝ አንተን
እጣራለሁ፤
ጆሮህን ወደ እኔ ጣል አድርገህ
ጸሎቴን ስማ።
7ከጠላቶቻቸው መተገኛ ያደረጉህን፣
በቀኝ እጅህ የምትታደግ ሆይ፤
ጽኑ ፍቅርህን ድንቅ አድርገህ ግለጥ።
8እንደ ዐይንህ ብሌን ጠብቀኝ፤
በክንፎችህም ጥላ ሰውረኝ፤
9ከሚያስጨንቁኝ ከክፉዎች፣
ከሚከብቡኝ አደገኛ ባላንጣዎቼ
ጋርደኝ።

10ደንዳና ልባቸውን ደፈኑት፤
በአፋቸውም ትዕቢት ይናገራሉ።
11አሳደው ደረሱብኝ፤ ከበቡኝም፤
*መሬት ላይ ሊዘርሩኝም አፈጠጡብኝ*።
12እነርሱ ለንጥቂያ እንደሚጓጓ አንበሳ፣
በስውርም እንደሚያደባ ደቦል አንበሳ
ናቸው።

13*እግዚአብሔር ሆይ*፤ ተነሥተህ
ግጠማቸውና ጣላቸው፤
በሰይፍህም ከክፉዎች ታደገኝ።
14*እግዚአብሔር ሆይ*፤ እንዲህ ካሉት
ሰዎች በክንድህ አድነኝ፤
ዕድል ፈንታቸው ይህችው ሕይወት
ብቻ ከሆነች፣ ከዚህ ዓለም ሰዎች
ታደገኝ።

ኢሱ9፥18፤
ኢዮ19፥9፤ማቴ5፥33፤
ሐሥ28፥10
**15፥5** ዘፀ18፥21፤
22፥25፤1ሳሙ8፥3፤
ኢዮ29፥18፤
መዝ 21፥7፤112፥6፤
ሐሥ 2፥25፤24፥26፤
ዕብ12፥28፤2ጴጥ1፥10
**16፥1** መዝ2፥12፤
12፥7
**16፥2** መዝ31፥14፤
73፥25፤118፥28፤140፥6
**16፥3** ዘዳ33፥3፤
መዝ 30፥4፤85፥8፤
101፥6፤ዳን7፥18፤
ሐሥ9፥13፤ሮሜ1፥7
**16፥4** ዘፀ18፥11፤
20፥3፤23፥13፤
ዘዳ8፥19፤31፥20፤
መዝ32፥10፤ምሳ23፥29
**16፥5** ዘሌ2፥2፤
ኢዮ31፥2፤መዝ23፥5፤
75፥8፤116፥13፤
ኢሳ51፥17፤ሰቆ4፥21፤
ሕዝ23፥32-34፤ዕን2፥16
**16፥6** ዘዳ19፥14፤
ኢዮ22፥26፤መዝ
104፥9፤ምሳ8፥29፤
ኤር5፥22
**16፥7** ኢዮ35፥10፤መዝ
42፥8፤73፥24፤77፥6፤
ምሳ15፥22፤ኢሳ11፥2
**16፥8** 1ነገ2፥19፤
1ዜና6፥39፤
መዝ15፥5፤73፥23
**16፥9** ዘዳ33፥28፤
መዝ4፥7፤13፥5፤
28፥7፤30፥11
**16፥10** ዘኍ16፥30
፤2ነገ19፥22፤ኢዮ
17፥14፤መዝ30፥3፤31፥17፤
86፥13፤ሆሴ13፥14፤
ሐሥ2፥31፤13፥35
**16፥11** መዝ21፥6፤
80፥17፤139፥24፤ማቴ
7፥14፤ሐሥ2፥25-28
**17፥1** መዝ5፥1፡2፤
30፥10፤39፥12፤64፥1
፤80፥1፤140፥6፤142፥6፤
143፥1፤ኢሳ29፥13
**17፥2** መዝ24፥5፤
26፥1፤99፥4፤ኢሳ46፥
13፤50፥8-9፤54፥17
**17፥3** ኢዮ7፥18፤
23፥10፤መዝ39፥1፤13
9፥1፤ኤር12፥3፤50፥20
**17፥5** ዘዳ32፥35፤
ኢዮ23፥11፤
መዝ 44፥18፤73፥2፤
119፥133፤121፥3
**17፥6** መዝ4፥1፤
86፥ 7፤116፥2
**17፥7** መዝ2፥12፤
10፥12፤31፥21፤
69፥13፤106፥45፤
107፥43፤117፥2
**17፥8** ዘኍ6፥24፤
ዘዳ32፥10፤ሩት2፥12
፤መዝ27፥5፤31፥20፤
32፥7፤36፥7፤63፥7፤
ምሳ7፥2፤ኢሳ34፥15
**17፥9** መዝ109፥3
**17፥10** 1ሳሙ2፥3፤መዝ73፥7፤119፥70፤ኢሳ6፥10
**17፥11** መዝ 88፥17 **17፥12** ዘፍ49፥9፤መዝ7፥2፤
ኤር5፥6፤12፥8፤ሰቆ3፥10 **17፥13** ዘኍ10፥35፤ መዝ35፥8፤
55፥23፤73፥18 **17፥14** መዝ 49፥17፤ኢሳ2፥7፤ 57፥17፤
ሉቃ16፥8፡25

[ሠ]3 ወይም *በምድሪቱ ላሉ አረማውያን፣ ካህናትና ደስ ለተሰኙባቸው መኳንንት ሁሉ ይህን እላለሁ*
[ረ]10 ወይም *በመቃብር*
[ሰ]10 ወይም *በአንተ የታመነውን*
[ሸ]11 ወይም *ታሳውቀኛለህ*

ከመዝገብህ ሆዳቸውን ሞላህ፤
ልጆቻቸውም ተትረፍርፎላቸዋል፤
ለልጆቻቸውም ሀብት ያከማቻሉ፡፡
15እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤
ስነቃም ክብርህን አይቼ እረካለሁ፡፡

## *መዝሙር* 18

**የድል *መዝሙር***

18 ርእስ-50 ተጓ ምብ-2ሳሙ22፥1-51

*ለመዘምራን አለቃ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝሙር፤ ይህም እግዚአብሔር ከሳዖልና ከጠላቶቹ ሁሉ እጅ በታደገው ጊዜ፣ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል የዘመረው ነው፦*

1ጕልበቴ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
እወድሃለሁ፡፡

2*እግዚአብሔር* ዐለቴ፣ መጠጊያዬና
ታዳጊዬ ነው፤
አምላኬ የምሸሸግበት ዐለቴ፤
እርሱ ጋሻዬ፣ የደንነቴ ቀንድና[ገ]
ዐምባዬ ነው፡፡
3ምስጋና የሚገባውን *እግዚአብሔርን*
እጠራለሁ፤
ከጠላቶቼም እድናለሁ፡፡

4የሞት ገመድ አነቀኝ፤
የጥፋት ጐርፍም አጥለቀለቀኝ፡፡
5የሲኦል[ጠ] ገመድ ተጠመጠመብኝ፤
የሞት ወጥመድም ተጋረጠብኝ፡፡
6በተጨነቅሁ ጊዜ *እግዚአብሔርን*
ጠራሁት፤
እንዲረዳኝም ወደ አምላኬ ጮኽሁ፤
እርሱም ከመቅደሱ ድምፄን ሰማ፤
ጩኸቴም ከፊቱ ደረሰ፤ ወደ ጆሮውም
ገባ፡፡

7ምድር ተንቀጠቀጠች፤ ተናወጠችም፤
የተራሮችም መሠረት ተናጋ፤
ጌታ ተቈጥቶአልና ተንቀጠቀጡ፡፡
8ከአፍንጫው ጢስ ወጣ፤
የሚባላ እሳት ከአፉ፤
የፍም ነበልባል ከእርሱ ፈለቀ፡፡
9ሰማያትን ሰንጥቆ ወረደ፤
ከእግሩም በታች ጥቍር ደመና ነበረ፡፡
10በኪሩቤል ላይ ተቀምጦ በረረ፤
በነፋስም ክንፍ መጠቀ፡፡
11ጨለማን መሰወሪያው፣ በዙሪያውም
አጐበሩ አደረገው፤
በዝናብ አዘል ጥቍር ደመናም ተሸፈነ፡፡
12በፊቱ ካለው ብርሃን የተነሣ፣
ደመናት፣ የበረዶ ድንጋይና መብረቅ
ወጡ፡፡
13*እግዚአብሔር* ከሰማያት አንጐደጐደ፤
ልዑልም ድምፁን አስተጋባ፡፡[ጨ]
14ፍላጻውን አስፈንጥሮ በተናቸው፤
መብረቅ አዥጐድጕዶ አሳደዳቸው፡፡
15*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከተግሣጽህ የተነሣ፣
ከአፍንጫህም እስትንፋስ የተነሣ፣
የባሕር ወለል ተገለጠ፤
የዓለምም መሠረት ራቍቱን ቀረ፡፡

16ከላይ እጁን ወደ ታች ዘርግቶ ያዘኝ፤
ከብዙ ጥልቅ ውሃም አወጣኝ፤
17ከኀያላን ጠላቶቼ አዳነኝ፤
ከእኔ ከሚበረቱ ባላንጣዎቼም ታደገኝ፡፡
18እነርሱ በመከራዬ ቀን መጡብኝ፤
*እግዚአብሔር* ግን ድጋፍ ሆነኝ፡፡
19ወደ ሰፊ ስፍራ አወጣኝ፤
ደስ ተሰኝቶብኛልና አዳነኝ፡፡

20*እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መለሰልኝ፤
እንደ እጄ ንጽሕናም ከፍሎኛል፤
21*የእግዚአብሔርን* መንገድ ጠብቄአለሁና፤
አምላኬንም በመተው ክፉ አላደረግሁም፡፡
22ሕጎቹ ሁሉ በፊቴ ናቸው፤
ሥርዐቱን ከፊቴ አላራቅሁም፡፡
23በፊቱ ነቀፋ አልነበረብኝም፤
ራሴንም ከኀጢአት ጠብቄአለሁ፡፡
24*እግዚአብሔር* እንደ ጽድቄ መጠን፣
በፊቱም እንደ እጄም ንጽሕና
ከፍሎኛል፡፡

25ከታማኙ ጋር ታማኝ ትሆናለህ፤
እንከን ከሌለበት ጋር ያለ እንከን
ትሆናለህ፤
26ከንጹሑ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ፤
ለጠማማው አንተ ትጠምበታለህ፡፡
27አንተ ትሑታንን ታድናለህ፤
ትዕቢተኛውን ዐይን ግን ታዋርዳለህ፡፡
28*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ መብራቴን
ታበራለህ፤
አምላኬ ሆይ፤ ጨለማዬን ብርሃን
ታደርገዋለህ፡፡
29በአንተ ጕልበት በሰራዊት ላይ
እረማመዳለሁ፤[ጸ]
በአምላኬም ኀይል ቅጥር እዘላለሁ፡፡

**17፥15** ዘኍ12፥8፤ መዝ3፥5፤ማቴ5፥8፤ 1ዮሐ3፥2
**18፥1** ዘፀ15፥2፤ዘዳ 33፥29፤1ሳሙ2፥10፤ መዝ22፥19፤28፥7፤ 59፥9፤81፥1፤ኢሳ12፥2፤ 49፥5፤ኤር16፥19
**18፥2** ዘፍ15፥1፤ዘፀ 33፥22፤1ሳሙ2፥1፤ መዝ2፥12፤9፥9፤28፥7 ፥8፤31፥2፥3፤40፥17፤ 84፥9፤94፥22፤ 119፥114፤144፥2፤ ኢሳ17፥10፤ ኤር16፥19፤ሉቃ1፥69
**18፥3** 1ዜና16፥25 ፤መዝ9፥13
**18፥4** መዝ93፥4፤ 116፥3፤124፥4፤ ኢሳ 5፥30፤17፥12፤ ኤር6፥23፤51፥42፥ 55፤ሕዝ 43፥2
**18፥5** ምሳ13፥14
**18፥6** ዘዳ4፥30፤ ኢዮ16፥18፤መዝ30፥2፤ 66፥19፤99፥6፤102፥2፤ 116፥1፤120፥1
**18፥7** መሳ5፥4፥5፤ ኢዮ9፥5፤መዝ97፥4 ፤ኢሳ5፥25፤64፥3፤ኤር 10፥10
**18፥8** ዘፀ15፥7፤ 19፥18፤ኢዮ41፥20፥ 21፤መዝ50፥3፤97፥3፤ ምሳ25፥22፤ዳን7፥10፤ ሮሜ12፥20
**18፥9** ዘፍ11፥5፤ ዘፀ20፥21፤ዘዳ33፥26፤ መዝ57፥3፤104፥3
**18፥10** ዘፍ3፥24፤ ዘዳ33፥26፤መዝ 104፥3፤ሕዝ10፥18
**18፥11** ዘፀ19፥9፤ ዘዳ4፥11፤ኢዮ22፥14፤ ኢሳ4፥5፤ኤር43፥10
**18፥12** ኢሱ10፥11፤ ኢዮ36፥30፤ መዝ 104፥2
**18፥13** ዘፀ9፥23፤ 1ሳሙ2፥10
**18፥14** ዘዳ32፥23፤ መሳ4፥15፤ኢዮ36፥30፤ ራእ4፥5
**18፥15** ዘፀ15፥8፤ መዝ 11፥3፤76፥6፤ 104፥7፤106፥9፤ ኢሳ 50፥2
**18፥16** ዘፀ15፥5፤ መዝ 69፥2፤ ምሳ18፥4፤20፥5
**18፥17** ቍ48፤ምሳ 18፥26፤መዝ38፥19፤ 59፥1፤143፥9
**18፥18** መዝ20፥2፤ ምሳ1፥27፤16፥4፤ ኢሳ3፥1፤ኤር17፥17፤ 40፥2፤አብ1፥13
**18፥19** ዘኍ14፥8፤ መዝ31፥8
**18፥20** ሩት2፥12 ፤1ሳሙ26፥23፤2ዜና 15፥7፤ኢዮ22፥30 ፤መዝ24፥4፤1ቆሮ3፥8 **18፥21** 2ዜና34፥33፤መዝ37፥34፤119፥2፥ 102፤ምሳ8፥32፤23፥26 **18፥22** መዝ119፥30 **18፥23** ዘፍ6፥9 **18፥24** 1ሳሙ26፥23 **18፥25** መዝ25፥10፤31፥23፤37፥28፤ 40፥11፤50፥5፤89፥24፤146፥6፤ምሳ2፥8 **18፥26** ምሳ3፥34፤15፥26፤ ማቴ5፥8፤10፥16፤ሉቃ16፥8፤ፊል1፥10፤1ጢሞ5፥22፤ቲቶ 1፥15፤ 1ዮሐ3፥3 **18፥27** 2ዜና33፥23፤ኢዮ41፥34፤መዝ10፥5፤ምሳ3፥33-34፤ማቴ23፥12 **18፥28** 1ነገ11፥36፤ኢዮ29፥3፤መዝ97፥11፤ 112፥4፤132፥17፤ ዮሐ1፥5፤ ሐሥ26፥18፤ 2ቆሮ4፥6፤2ጴጥ1፥19 **18፥29** ቍ32፥39፤ኢሳ45፥5፤ዕብ11፥34

[ገ]2 *ቀንድ* በዚህ ቦታ ብርታትን ያመለክታል
[ጠ]5 ወይም *የመቃብር*
[ጨ]13 *አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሰብዓ ሊቃናት* (በተጨማሪ 2ሳሙ22፥14 *ይመ*) *እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች ግን* ... *አስተጋባ፤ በድንጋይ ዝናብ በድንገተኛ መብረቅ መካከል* የሚለውን *ይጨምራሉ፡፡*
[ጸ]29 ወይም ... *በመሰናክል ውስጥ መሮጥ እችላለሁ*

[30]የአምላክ *መንገድ ፍጹም ነው*፤
*የእግዚአብሔር ቃል* የነጠረ ነው፡፡
*መጠጊያ ለሚያደርጉት ሁሉ*፣
እርሱ ጋሻ ነው፡፡
[31]*ከእግዚአብሔር* በቀር ማን አምላክ አለ?
ከአምላካችንስ በቀር ዐምባ ማን ነው?
[32]*ኀይልን የሚያስታጥቀኝ*፣
*መንገዴንም የሚያቃና* እግዚአብሔር
ነው፡፡
[33]እርሱ እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች
ያደርጋል፤
በከፍታዎችም ላይ ያቆመኛል፡፡
[34]እጆቼን ለጦርነት ያሠለጥናቸዋል፤
ክንዴም የናስ ቀስት መገተር ይችላል፡፡
[35]የድል ጋሻ ሰጥተኸኛል፤
ቀኝ እጅህም ደግፋ ይዛኛለች፤
ዝቅ ብለህም ከፍ አደረግኸኝ፡፡
[36]ከሥሬ ያለውን ስፍራ ለአረማመዴ
አሰፋህልኝ፤
እግሬም አልተንሸራተተም፡፡

[37]ጠላቶቼን አሳድጄ ያዝኋቸው፤
እስኪጠፉም ወደ ኋላዬ
አልተመለስሁም፡፡
[38]እንዳያንሰራሩ አድርጌ አደቀቅኋቸው፤
ከእግሬም ሥር ወደቁ፡፡
[39]አንተ ለጦርነት ኀይልን አስታጠቅኸኝ፤
ባላንጦቼ እግሬ ላይ እንዲደፉ
አደረግህ፡፡
[40]ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው እንዲሸሹ አደረግህ፤
እኔም የሚጠሉኝን አጠፋኋቸው፡፡
[41]ለርዳታ ጮኹ፤ የሚያስጥላቸው ግን
አላገኙም፤
ወደ *እግዚአብሔር* ጮኹ፤ እርሱም
አልመለሰላቸውም፡፡
[42]ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ
አደቀቅኋቸው፤
እንደ መንገድ ላይ ጭቃም አውጥቼ
ጣልኋቸው፡፡

[43]ከሕዝብ ግርግር አወጣኸኝ፤
የሕዝቦች መሪ አድርገህ አስቀመጥኸኝ፤
የማላውቀውም ሕዝብ ተገዛልኝ፡፡
[44]ትእዛዜን እንደ ሰሙ ይታዘዙልኛል፤
ባዕዳንም በፊቴ አንገት ደፉ፡፡
[45]ባዕዳን በፍርሃት ተዋጡ፤
ከምሽጋቸውም እየተንቀጠቀጡ ወጡ፡፡

[46]*እግዚአብሔር* ሕያው ነው! ዐምባዬ
ይባረክ፤
ያዳነኝ አምላክ ከፍ ከፍ ይበል፡፡
[47]እርሱ በቀሌን የሚመልስልኝ፣
ሕዝቦችንም የሚያስገዛልኝ አምላክ ነው፤
[48]ከጠላቶቼም የሚታደገኝ እርሱ ነው፡፡
አንተ ከባላንጦቼ በላይ ከፍ ከፍ
አደረግኸኝ፤
ከጨካኞች አዳንኸኝ፡፡
[49]*እግዚአብሔር ሆይ*፤ ስለዚህ በአሕዛብ
መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም በመዝሙር እወድሳለሁ፡፡
[50]እርሱ ላንገሠው ታላላቅ ድሎችን
ይሰጣል፤
ጽኑ ፍቅሩንም ለቀባው፣
ለዳዊትና ለዘሩ ለዘላለም ይገልጣል፡፡

## *መዝሙር* 19

### እግዚአብሔር የጽድቅ ፀሓይ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፤
የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ
ያውጃሉ፡፡
[2]ቀን ለሌላው ቀን ይናገራል፤
ሌሊትም ለሌሊት ዕውቀትን
ይገልጣል፤
[3]ንግግር የለም፤ ቃል የለም፤
ድምፃቸው በጆሮ የሚሰማ አይደለም፡፡[a]
[4]ያም ሆኖ ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፣
ቃላቸውም[b] እስከ ዓለም ዳርቻ
ይወጣል፡፡

እርሱ በሰማያት ለፀሓይ ድንኳን
ተክሎአል፤
[5]ፀሓይም ከእልፍኙ እንደሚወጣ ሙሽራ
ይወጣል፤
ወደ ግቡም እንደሚሮጥ ብርቱ ሰው
ደስ ይለዋል፡፡
[6]መውጫው ከሰማያት ዳርቻ ነው፤
ዑደቱም እስከ ሌላኛው ዳርቻ ነው፤
ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም፡፡

[7]*የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው*፤
*ነፍስንም መልሶ ያለመልማል*፤
*የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ ነው*፤
*አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል*፡፡
[8]*የእግዚአብሔር ሕግጋት ትክክል ናቸው*፤
ልብን ደስ ያሰኛሉ፡፡
*የእግዚአብሔር* ትእዛዝ ብሩህ ነው፤
ዐይንን ያበራል፡፡
[9]*እግዚአብሔርን መፍራት* ንጹሕ ነው፤
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡
*የእግዚአብሔር* ፍርድ የታመነ፣
ሁለንተናው*ም* ጻድቅ ነው፤

18፥30 ዘዳ32፥4፤ መዝ2፥12፤3፥3፤ 12፥6 ፤ምሳ30፥5
18፥31 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ4፥35፤32፥39፤መዝ 35፥10፤86፥8፤89፥6፤ ኢሳ44፥6፥8፤45፥5፡ 6፡14፡18፡21፤46፥9
18፥32 ቍ29፤ መዝ 15፥2፤19፥13፤ ዕብ 10፥14፤ 1ጴጥ5፥10፤ያዕ3፥2
18፥33 ዘዳ32፥13፤ መዝ42፥1፤ምሳ5፥19፤ ኢሳ35፥6፤ዕን3፥19
18፥34 መዝ144፥1
18፥35 መዝ3፥5፤ 37፥5፡17፤41፥3፤51፥12 ፤54፥4፤55፥22፤119፥116 ፤ኢሳ41፥4፡10፡ 13፤43፥2፤46፥4
18፥36 ኢዮ18፥7 ፤መዝ31፥8፤66፥9
18፥37 ዘሌ26፥7
18፥38 መዝ36፥12 ፤47፥3፤68፥21፤ 110፥6፤140፥10፤ ኢሳ 26፥14
18፥39 ቍ32፡47፤ መዝ47፥3፤144፥2፤ ኢሳ 45፥5፡24
18፥40 ቍ37፤ ኢሱ 7፥12
18፥41 1ሳሙ8፥18 ፤14፥37፤2ነገ14፥26፤ መዝ50፥22፤ኤር11፥11
18፥42 ዘዳ9፥21፤ ኢሳ2፥22
18፥43 2ሳሙ8፥1-14፤ኢሳ55፥5
18፥44 መዝ54፥3 ፤144፥7፡11፤ኢሳ25፥5
18፥45 1ሳሙ17፥32 ፤መዝ9፥9፤ኢሳ66፥2፤ ሆሴ3፥5፤11፥10፤ ሚክ7፥17፤2ቆሮ4፥1፤ ዕብ 12፥3
18፥46 ቍ31፤ ዘፀ33፥22፤ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ14፥39፤1ዜና 16፥35፤መዝ21፥13፤ 35፥27፤40፥16፤108፥5 ፤ ሉቃ1፥47፤2ቆሮ13፥4
18፥47 ቍ39፤ ዘፍ 4፥24፤መሳ4፥23
18፥48 ቍ17፤ መዝ 7፥10፤37፥40፤ 140፥1፤ዳን3፥17
18፥49 መዝ7፥17፤ 9፥2፡11፤101፥1፤108፥1 ፤146፥2፤ሮሜ15፥9
18፥50 2ሳሙ23፥1 ፤መዝ89፥4፤144፥10
19፥1 ዘፍ1፥8፤ መዝ4፥2፤8፥1፡6፤50፥6 ፤89፥5፤97፥6፤103፥22፤ 148፥3፤ኢሳ6፥3፤ 40፥22፤ሮሜ1፥19
19፥2 መዝ74፥16
19፥4 መሳ5፥31፤ ኢዮ36፥29፤መዝ 104፥2፤ሮሜ10፥18
19፥5 1ሳሙ17፥4፤ኢዮ36፥29፤ኢል2፥16 19፥6 ዘዳ30፥4፤ መዝ113፥3፤መክ1፥5 19፥7 ዘዳ4፥6፤መዝ1፥2፤23፥3፤93፥5፤ 111፥7፤119፥130፡138፡142፡144፤ያዕ1፥25 19፥8 ዕዝ9፥8፤ መዝ33፥4፤38፥10፤119፥14፡128 19፥9 መዝ34፥11፤111፥10፤ 119፥138፤ምሳ1፥7፤መክ12፥13፤ኢሳ33፥6

[a]3 ወይም *የሚናገሩት የላቸውም፤ ቃላት የለም፤ ከእርሱ ምንም ድምፅ አይሰማም*
[b]4 ሰብዓ ሊቃናት የሩምና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ ዕብራይስጡ ግን ድንበራቸው ይላል፡፡

10ከወርቅ ይልቅ የከበረ፣
እጅግ ከጠራ ወርቅም የተሻለ ነው፤
ከማር ይልቅ ይጣፍጣል፤
ከማር ወለላም ይበልጥ ይጥማል።
11ደግሞም አገልጋይህ በእርሱ ጥንቃቄ
ያደርጋል፤
እርሱንም መጠበቅ ወሮታ አለው።

12ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላል?
ከተሰወረ በደል አንጻኝ።
13ባሪያህን ከድፍረት ኀጢአት ጠብቅ፤
እንዳይሠለጥንብኝም ርዳኝ፤
ያን ጊዜ ያለ እንከን እሆናለሁ፤
ከታላቅ በደልም እነጻለሁ።

14መጠጊያዬና አዳኜ እግዚአብሔር ሆይ፤
የአፌ ቃልና የልቤ ሐሳብ፣
በፊትህ ያማረ ይሁን።

## መዝሙር 20

### ጸሎት ለንጉሡ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር በጭንቅ ቀን ይስማህ፤
የያዕቆብም አምላክ ስም ይጠብቅህ።
2ከመቅደሱ ረድኤት ይላክልህ፤
ከጽዮንም ደግፎ ይያዝህ።
3ቍርባንህን ሁሉ ያስብልህ፤
የሚቃጠል መሥዋዕትህን ይቀበልልህ።
4የልብህን መሻት ይስጥህ፤
ዕቅድህን ሁሉ ያከናውንልህ።
5በአንተ ድል ደስ ይበለን፤
በአምላካችን ስም አርማችንን ከፍ
እናደርጋለን፤
እግዚአብሔር የለመንኸውን ሁሉ
ይፈጽምልህ።

6እግዚአብሔር፣ የቀባውን እንደሚያድን
አሁን ዐወቅሁ፤
የማዳን ኀይል ባለው ቀኝ እጁ፣
ከተቀደሰው ሰማይ ይመልስለታል።
7እነዚህ በሰረገላ፣ እነዚያ በፈረስ
ይመካሉ፤
እኛ ግን ትምክህታችን የአምላካችን
የእግዚአብሔር ስም ነው።
8እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ፤
እኛ ግን ተነሣን፤ ጸንተንም ቆምን።

9እግዚአብሔር ሆይ፤ ንጉሥን አድን፤
እኛም በጠራንህ ቀን ስማን።[ፊ]

## መዝሙር 21

### ምስጋና ስለ ንጉሡ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ንጉሥ በኀይልህ
ደስ ይለዋል፤
በምትሰጠውም ድል እጅግ ሐሤት
ያደርጋል።
2የልቡን መሻት ሰጠኸው፤
የከንፈሮቹንም ልመና አልከለከልኸውም። ሴላ

3መልካም በረከት ይዘህ በመንገዱ ላይ
ጠብቀኸው፤
የንጹሕ ወርቅ ዘውድም በራሱ ላይ
ደፋህለት።
4ሕይወትን ለመነህ፤
ረዥም ዘመናትንም እስከ ዘላለም
ሰጠኸው።
5ባቀዳጀኸው ድል ክብሩ ታላቅ ሆነ፤
ክብርንና ሞገስን አጐናጸፍኸው።

6ዘላለማዊ በረከትን ሰጠኸው፤
ከአንተ ዘንድ በሚገኝ ፍስሓም ደስ
አሰኘኸው፤
7ንጉሡ በእግዚአብሔር ተማምኖአልና፤
ከልዑልም ጽኑ ፍቅር የተነሣ፣
ከቆመበት አይናወጥም።

8እጅህ ጠላቶችህን ሁሉ ታገኛቸዋለች፤
ቀኝ እጅህም የሚጠሉህን ፈልጋ
ትይዛለች።
9በምትገለጥበት ጊዜ፣
እሳት እንደሚንቀለቀልበት ምድጃ
ታደርጋቸዋለህ፤
እግዚአብሔር በመዓቱ እንዳልነበሩ
ያደርጋቸዋል፤
እሳቱም ሙጥጥ አድርጋ ትበላቸዋለች።
10ዘራቸውን ከምድር፣
ዘር ማንዘራቸውንም ከሰው ልጆች
መካከል ታጠፋለህ።
11ክፉት ቢያስቡብህ፣
ተንኰል ቢወጥኑብህም አይሳካላቸውም፤
12በመጡበት ትመልሳቸዋለህና፤
ቀስትህንም በፊታቸው ላይ ታነጣጥራለህ።

13እግዚአብሔር ሆይ፤ በብርታትህ ከፍ
ከፍ በል፤
ኀይልህን እናወድሳለን፤ እንዘምራለንም።

## መዝሙር 22

### የጻድቅ ሰው መከራና ተስፋ

ለመዘምራን አለቃ፤ በ"ንጋት አጋዘን" ዜማ የሚዜም፤
የዳዊት መዝሙር

1አምላኬ፣ አምላኬ ለምን ተውኸኝ?
እኔን ከማዳን፣
ከመቃተቴም ቃል ለምን ራቅህ?
2አምላኬ ሆይ፤ በቀን ወደ አንተ
አጮኻለሁ፤

19፥10 2ሳሙ·14፥27፤ ኢዮ22፥24፤ መዝ 119፥72፡103፤ ምሳ8፥10፤ ማሕ4፥11፤ሕዝ3፥3
19፥12 መዝ51፥2፤ 90፥8፤መክ12፥14
19፥13 ዘፍ6፥9፤ ዘኍ15፥30፤መዝ 18፥32፤119፥133
19፥14 ዘዐ6፥6፤ ኢዮ 19፥25፤ መዝ18፥31፤104፥34
20፥1 ዘፀ3፥6፤መዝ 4፥1፤46፥7፡11፤59፥1፤ 69፥29፤91፥14
20፥2 ዘኍ3፥28፤ መዝ2፥6፤18፥18፤ 30፥10፤33፥20፤ 37፥40፤40፥17፤54፥4፤ 118፥7፤128፥5፤ 134፥3፤135፥21
20፥3 ዘዳ33፥11፤ ሐሥ10፥4
20፥4 መዝ21፥2 ፤37፥4፤140፥8፤145፥ 16፡19፤ምሳ16፥3፤ ኢሳ26፥8፤ሕዝ24፥25፤ ዳን11፥17፤ሮሜ10፥1
20፥5 ዘኍ1፥52፤ 1ሳሙ·1፥17፤ኢዮ3፥7 ፤መዝ60፥4፤ኢሳ5፥26 ፤ 11፥10፡12፤13፥2፤ 30፥17፤49፥22፤ 62፥10፤ኤር50፥2፤ 51፥12፡27
20፥6 2ሳሙ·23፥1 ፤ኢዮ40፥14፤ መዝ28፥8፤ዕን3፥13
20፥7 ዘዳ17፥16፤ 2ነገ19፥23፤2ዜና 32፥8፤መዝ33፥17፤ 147፥10፤ምሳ21፥31፤ ኢሳ 31፥1፤36፥8፡9
20፥8 ኢዮ11፥15፤ መዝ27፥2፤37፥23፤ ምሳ10፥25፤ኢሳ7፥9፤ 40፥30፤ኤር46፥6፤ 50፥32፤ሚክ7፥8
20፥9 መዝ17፥6
21፥1 1ሳሙ·2፥10 ፤2ሳሙ·22፥51
21፥2 መዝ20፥4
21፥3 2ሳሙ·12፥30 ፤ዘካ6፥11፤ራእ14፥14
21፥4 መዝ10፥16፤ 45፥17፤48፥14፤133፥3
21፥5 ቍ1፤መዝ8፥5 ፤18፥50፤44፥4፤45፥3፤ 93፥1፤96፥6፤104፥1
21፥6 1ዜና17፥27 ፤መዝ43፥4፤126፥3
21፥7 ዘፍ14፥18፤ 2ነገ18፥5፤መዝ6፥4፤ 15፥5፤55፥22
21፥8 ኢሳ10፥10
21፥9 ዘዳ32፥22፤ መዝ50፥3፤ኤር15፥14
21፥10 ዘዳ28፥18
21፥11 ኢዮ10፥3፤ መዝ2፥1፤10፥2፤ 26፥10፤37፥7
21፥12 ዘፀ23፥27 21፥13 መዝ18፥1፡46 22፥1 ኢዮ3፥24፤ 6፥15፤መዝ9፥10፤10፥1፤ማቴ27፥46፤ማር15፥34 22፥2 ኢዮ19፥7፤ መዝ42፥3፤88፥1

[ፊ]9 ወይም አድን! ንጉሥ ሆይ፤ ስማን

አንተ ግን አልመለስህልኝም፤
በሌሊት እንኳ አላረፍሁም።
3 አንተ ግን ቅዱሱ ነጋሢ፤[ፐ]
የእስራኤልም ምስጋና ነህ።
4 አባቶቻችን በአንተ ታመኑ፤
ተማመኑብህ፤ አንተም ታደግሃቸው።
5 ወደ አንተ ጮኹ፤ ዳኑም፤
በአንተም ታመኑ፤ አላፈሩም።
6 እኔ ግን ትል እንጂ ሰው አይደለሁም፤
ሰው ያላገጠብኝ፣ ሕዝብም የናቀኝ
ነኝ።
7 የሚያዩኝ ሁሉ ይሣለቁብኛል፤
ራሳቸውንም እየነቀነቁ እንዲህ እያሉ
ይዘልፉኛል፤
8 "*በእግዚአብሔር ተማምኖአል*፤
እንግዲህ እርሱ ያድነው፤
ደስ የተሰኘበትን፣
እስቲ ይታደገው።"
9 አንተ ግን ከማሕፀን አወጣኸኝ፤
በእናቴም ጡት ሳለሁ፣
መታመኛ ሆንኸኝ።
10 ከማሕፀን ስወጣም በአንተ ላይ ተጣልሁ፤
ከእናቴ ሆድ ጀምሮም አንተ አምላኬ
ነህ።
11 መከራ እየተቃረበ ነውና፣
የሚረዳኝም የለምና፣
ከእኔ አትራቅ።
12 ብዙ ኰርማዎች ከበቡኝ፤
ኀይለኛ የባሳን በሬዎችም ዙሪያዬን
ቆሙ።
13 እንደሚነጥቅና እንደሚያገሣ አንበሳ፣
አፋቸውን ከፈቱብኝ።
14 እንደ ውሃ ፈሰስሁ፤
ዐጥንቶቼም ሁሉ ከመጋጠሚያቸው
ወለቁ፤
ልቤ እንደ ሰም ሆነ፤
በውስጤም ቀለጠ።
15 ጕልበቴ እንደ ገል ደረቀ፤
ምላሴ ከላንቃዬ ጋር ተጣበቀ፤
ወደ ሞት ዐፈርም አወረድኸኝ።[ሀ]
16 ውሾች ከበቡኝ፤
የክፉዎች ሸንጎ በዙሪያዬ ተሰልፎአል፤
እጆቼንና እግሮቼንም ቸነከሩኝ።[ለ]
17 ዐጥንቶቼን ሁሉ አንድ በአንድ
መቍጠር እችላለሁ፤
እነርሱም አፍጥጠው ይመለከቱኛል።
18 ልብሶቼን ተከፋፈሉ፤
በእጀ ጠባቤም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።
19 አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤ ከእኔ
አትራቅ፤
አጋዤ ሆይ፤ እኔን ለመርዳት ፍጠን።
20 ነፍሴን ከሰይፍ ታደጋት፤
ውድ ሕይወቴንም ከውሾች ጡጫ
አድናት።
21 ከአንበሶች አፍ አድነኝ፤
ከአውራሪስ ቀንድም ታደገኝ።[ሐ]
22 ስምህን ለወንድሞቼ እናገራለሁ፤
በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ።
23 እናንተ እግዚአብሔርን የምትፈሩ፤
አወድሱት፤
እናንተ የያዕቆብ ዘር ሁላችሁ፤ አክብሩት፤
የእስራኤልም ዘር ሁላችሁ፤ እርሱን
ፍሩት።
24 እርሱ የተጨነቀውን ሰው ጭንቀት፣
አልናቀም፤ ቸልም አላለምና፤
ፊቱንም ከእርሱ አልሰወረም፤
ነገር ግን ድረስልኝ ብሎ ሲጮኽ ሰማው።
25 በታላቅ ጉባኤ የማቀርበው ምስጋናዬ
ከአንተ የመጣ ነው፤
እርሱን በሚፈሩት[መ] ፊት ስእለቴን
እፈጽማለሁ።
26 ምስኪኖች በልተው ይጠግባሉ፤
እግዚአብሔርን የሚሹትም
ያመሰግኑታል፤
ልባችሁም ለዘላለም ሕያው ይሁን!
27 የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስታውሳሉ፤
ወደ እግዚአብሔርም ይመለሳሉ፤
የሕዝቦች ነገዶች ሁሉ፣
በፊቱ ይሰግዳሉ።
28 መንግሥት የእግዚአብሔር ናትና፤
ሕዝቦችንም የሚገዛ እርሱ ነው።
29 የምድር ከበርቴዎች ይበላሉ፤
ይሰግዱለታልም፤
ነፍሱን በሕይወት ማቆየት
የማይችለው፣ ወደ ዐፈር፣
ተመላሽ የሆነው ሁሉ በፊቱ
ይንበረከካል።
30 የኋለኛው ትውልድ ያገለግለዋል፤
ለመጪው ትውልድ ስለ ጌታ
ይነገረዋል።

22፥3 ዘፀ15፥2፤2ነገ19፥22፤መዝ71፥22፤148፥14፤ማር1፥24
22፥4 መዝ78፥53፤107፥6
22፥5 1ዜና5፥20፤2ዜና13፥18፤መዝ25፥3፤31፥17፤71፥1፤ኢሳ 8፥17፤25፥9፤26፥3፤30፥18፤49፥23፤ሮሜ9፥33
22፥6 2ሳሙ12፥14፤ኢዮ4፥19፤መዝ31፥11፤64፥8፤69፥19፤109፥25፤119፥141፤ኢሳ49፥7፤53፥3፤60፥14፤ሚል2፥9፤ማቴ16፥21
22፥7 ኢዮ17፥2፤መዝ35፥16፤69፥12፤74፥18፤ማቴ27፥39፡41፡44፤ማር15፥29፡31፡32፤ሉቃ23፥36፡39
22፥8 2ሳሙ22፥20፤መዝ3፥2፤ 91፥14፤ማቴ3፥17፤27፥43
22፥9 ኢዮ10፥18፤መዝ71፥6፤78፥7፤ናሆ1፥7
22፥10 መዝ71፥6፤ኢሳ46፥3፤49፥1
22፥11 ቍ19፤2ነገ14፥26፤መዝ10፥1፡14፤ኢሳ41፥28
22፥12 ዘዳ32፥14፤መዝ17፥9፤27፥6፤49፥5፤68፥30፤109፥3፤140፥9፤ኢሳ2፥13፤ሕዝ 27፥6፤39፥18፤አሞ4፥1
22፥13 ቍ24፤ዘፍ49፥9፤ሰቆ3፥46፤ሕዝ22፥25፤ሶፎ3፥3
22፥14 ኢሱ7፥5፤ኢዮ23፥16፤መዝ6፥2፤68፥2፤97፥5፤መዝ107፥26፤ዳን5፥6፤ሚክ1፥4
22፥15 ኢዮ7፥21፤መዝ104፥29፤137፥6፤ኢሳ45፥9፤ሰቆ4፥4፤ሕዝ3፥26፤ዮሐ19፥28
22፥16 ኢሳ51፥9፤53፥5፤ዘካ12፥10፤ዮሐ20፥25፤ፊል3፥2
22፥17 መዝ25፥2፤30፥1፤35፥19፤38፥16፤ሰቆ2፥17፤ሚክ7፥8፤ሉቃ23፥35
22፥18 ዘሌ16፥8፤ማቴ27፥35፤ማር9፥12፤15፥24፤ሉቃ23፥34፤ዮሐ19፥24
22፥19 ቍ11፤መዝ 18፥1፤38፥22፤40፥13፤70፥5፤141፥1
22፥20 ኢዮ5፥20፤መዝ35፥17፤37፥14፤ፊል3፥2
22፥21 ቍ12፡13፤ዘኍ23፥22፤ኢዮ4፥10
22፥22 መዝ26፥12፤35፥18፤40፥9፡10፤68፥26፤ዕብ2፥12
22፥23 ዘዳ14፥23፤መዝ33፥2፡8፤50፥15፤66፥8፤86፥12፤103፥1፤106፥1፤113፥1፤117፥1፤135፥19፤ኢሳ24፥15፤25፥3፤29፥23፤60፥9፤ኤር3፥17 22፥24 ኢዮ24፥12፤36፥5፤መዝ9፥12፤13፥1፤27፥9፤69፥17፤102፥2፡17፤143፥7፤ዕብ5፥7 22፥25 ዘኍ30፥2፤መዝ26፥12፤35፥18፤40፥9፤82፥1 22፥26 መዝ40፥16፤107፥9
22፥27 መዝ2፥8፤86፥9፤102፥22፤ዳን7፥27፤ሚክ4፥1
22፥28 መዝ47፥7፤ዘካ14፥9 22፥29 መዝ45፥12፤89፥48፤95፥6፤96፥9፤99፥5፤ኢሳ26፥19፤27፥13፤49፥7፤66፥23፤ዘካ14፥16
22፥30 መዝ102፥18፤ኢሳ53፥10፤54፥3፤61፥9፤66፥22

[ፐ]3 ወይም *አንተ ግን ቅዱስ ነህ፤ በእስራኤል ምሥጋና ላይ በዙፋን ተቀምጠሃል*
[ሀ]15 ወይም *... ዐፈር ውስጥ ተኛኹኝ*
[ለ]16 አንዳንድ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች፣ ሰብዓ ሊቃናትና ሱርስት እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኞዎቹ የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆች *እንደ አንበሳ*፣ ይላሉ።
[ሐ]21 ወይም *ሰምተኸኛል*
[መ]25 ዕብራይስጡ *እኔ በሚፈሩኝ* ይላል።

31ገና ላልተወለደ ሕዝብ፣
ጽድቁን ይነግራሉ፤
እርሱ ይህን አድርጎአልና።

## መዝሙር 23

### መልካሙ እረኛ

*የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* እረኛዬ ነው፤
አንዳች አይጐድልብኝም።
2በለመለመ መስክ ያሳርፈኛል፤
በዕረፍት ውሃ ዘንድ ይመራኛል፤
3ነፍሴንም ይመልሳታል።
ስለ ስሙም፣
በጽድቅ መንገድ ይመራኛል።
4በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ፤[ሠ]
ብሄድ እንኳ፣
አንተ ከእኔ ጋር ስለ ሆንህ፣
ክፉን አልፈራም፤
በትርህና ምርኵዝህ፣
እነርሱ ያጽናኑኛል።
5ጠላቶቼ እያዩ፣
በፊቴ ማዕድ አዘጋጀህልኝ፤
ራሴን በዘይት ቀባህ፤
ጽዋዬም ሞልቶ ይፈስሳል።
6በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
በጎነትና ምሕረት በእርግጥ
ይከተሉኛል፤
እኔም *በእግዚአብሔር* ቤት፣
ለዘላለም እኖራለሁ።

## መዝሙር 24

### ወደ መቅደስ መግቢያ ጸሎት

*የዳዊት መዝሙር*

1ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣
ዓለምና በውስጧ የሚኖር ሁሉ *የእግዚ
አብሔር* ነው፤
2እርሱ በባሕሮች ላይ መሥርቶአታልና፤
በውሆችም ላይ አጽንቶአታል።
3ወደ *እግዚአብሔር* ተራራ ማን ሊወጣ
ይችላል?
በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል?
4ንጹሕ እጅና ቅን ልብ ያለው፤
ነፍሱን ለሐሰት ነገር የማያስገዛ፤
በውሸት የማይምል፤[ረ]
5እርሱ በረከትን *ከእግዚአብሔር* ዘንድ፣
ምሕረትንም ከአዳኝ አምላኩ ይቀበላል።
6እርሱን የሚፈልግ ትውልድ እንዲህ
ነው፤
የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ፊትህን[ሰ] የሚፈልግ
እንዲህ ያለ ነው። ሴላ
7እናንተ ደጆች፤ ቀና በሉ፤
እናንተ የዘላለም በሮች፤
የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ!
8ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?
*እግዚአብሔር* ነው ብርቱና ኀያል፤
*እግዚአብሔር* ነው በውጊያ ኀያል።
9እናንተ ደጆች፤ ቀና በሉ፤
እናንተ የዘላለም በሮች፤
የክብር ንጉሥ እንዲገባ ብድግ በሉ!
10ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?
የሰራዊት *አምላክ*፣
እርሱ የክብር ንጉሥ ነው። ሴላ

## መዝሙር 25[ሸ]

### በአደጋ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

*የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ነፍሴን ወደ አንተ
አነሣለሁ፤
2አምላኬ ሆይ፣ በአንተ እታመናለሁ፤
እባክህ አታሳፍረኝ፤
ጠላቶቼም አይዘባነኑብኝ።
3አንተን ተስፋ የሚያደርጉ፣
ከቶ አያፍሩም፤
ነገር ግን እንዲያው ያለ ምክንያት፣
ተንኰለኞች የሆኑ ያፍራሉ።
4*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አካሄድህን
እንዳውቅ አድርገኝ፤
መንገድህንም አስተምረኝ።
5አንተ አዳኜ፣ አምላኬም ነህና፣
በእውነትህ ምራኝ፤ አስተምረኝም፤
ቀኑን ሙሉ አንተን ተስፋ
አድርጌአለሁ።
6*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህንና
ፍቅርህን አስብ፤
እነዚህ ከጥንት የነበሩ ናቸውና።
7የልጅነቴን ኀጢአት፣
መተላለፌንም አታስብብኝ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ
ብዛት፣
እንደ ምሕረትህም መጠን ዐስበኝ።
8*እግዚአብሔር* መልካምና ቅን ነው፤
ስለዚህ ኀጢአተኞችን በመንገድ
ይመራቸዋል።
9ዝቅ ያሉትን በፍትሕ ይመራቸዋል፤
ለትሑታንም መንገዱን
ያስተምራቸዋል።

**22፥31** መዝ5፥8፤ 40፥9፥71፥18፥78፥6፤ 102፥18፤ሉቃ18፥31፤ 24፥44
**23፥1** ዘፍ48፥15፤ መዝ28፥9፥34፥9፥10፤ 84፥11፥107፥9፤ ዮሐ10፥11፤ፊል4፥19
**23፥2** መዝ36፥8፤ 46፥4፤ራእ7፥17
**23፥3** መዝ5፥8፤ 19፥7፥25፥9፥11፤ 31፥3፥73፥24፥79፥9፤ 106፥8፥109፥21፤ 143፥11፤ኢሳ42፥16
**23፥4** ኢዮ3፥5፤ መዝ3፥6፥16፥8፥27፥1፤ 107፥14፤ኢሳ43፥2
**23፥5** ኢዮ36፥16፤ መዝ16፥5፥45፥7፤ 92፥10፤ሉቃ7፥46
**23፥6** ነህ9፥25
**24፥1** ዘፀ9፥29፤ኢዮ 41፥11፤1ቆሮ10፥26
**24፥2** ዘፍ1፥6፤ መዝ104፥3፤2ጴጥ3፥5
**24፥3** መዝ2፥6፤ 15፥1፥65፥4
**24፥4** 2ሳሙ22፥21 ፤መዝ51፥10፥73፥1፤ ሕዝ18፥15፤ማቴ5፥8
**24፥5** ዘዳ11፥26፤ መዝ17፥2
**24፥6** መዝ27፥8፤ 105፥4፥119፥58፤ ሆሴ5፥15
**24፥7** መዝ29፥3፤ 44፥4፥74፥12፥118፥19፥ 20፤ኢሳ26፥2፥60፥11፥ 18፤62፥10፤ዘካ9፥9፤ ማቴ21፥5፤ ሐሥ7፥2፤1ቆሮ2፥8
**24፥8** ዘፀ15፥3፥6፤ ዘዳ4፥34፤1ዜና29፥11 ፤መዝ89፥13፤ኤር 50፥34፤ኤፌ6፥10
**24፥10** 1ሳሙ1፥11
**25፥1** መዝ86፥4፤ 143፥8
**25፥2** መዝ31፥6፤ 143፥8
**25፥3** መዝ22፥5፤ ኢሳ24፥16፥29፥22፤ ዕን1፥13፤ሶፎ3፥4፤ 2ጢሞ3፥4
**25፥4** ኢዮ34፥32
**25፥5** ቀኦ3፤መዝ 24፥5፥31፥3፥33፥20፤ 39፥7፥42፥5፥43፥3፤ 71፥5፥130፥7፤ 131፥3፤ዮሐ16፥13
**25፥6** መዝ5፥7፤ 98፥3፤ኢሳ63፥7፥15፤ ኤር31፥20፤ሆሴ11፥8
**25፥7** ዘፀ23፥21፤ 1ዜና16፥34፤ኢዮ 13፥26፤መዝ6፥4፥34፥ 8፥51፥1፥69፥16፥73፥ 1፥107፥17፥109፥26፤ 119፥124፤ኢሳ54፥4 ፤ኤር3፥25፥31፥19፤ 32፥30፤ሕዝ16፥22፥60 ፤23፥3፤2ጢሞ2፥22
**25፥8** መዝ32፥8፤92፥15፤ኢሳ26፥7፤ 28፥26
**25፥9** ቀኦ4፤መዝ23፥3፤27፥11

[ሠ]4 ወይም *እጅግ ጨለማ በሆነው ሸለቆ ውስጥ*
[ረ]4 ወይም *በሐሰትም ያልማለ*
[ሰ]6 ሁለት የዕብራይስጥ የጥንት ቅጆችና ሱርስት (እንዲሁም ሰብዓ ሊቃናት ይመ) እንዲሁ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ የዕብራይ ስጥ የጥንት ቅጆች ግን *ያዕቆብ፤ ፊትህን* ..
[ሸ]25 ይህ መዝሙር እያንዳንዱ ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀምር፣ ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጉም የሚሰጥ ግጥም ነው።

10 ኪዳኑንና ሥርዐቱን ለሚጠብቁ፣
*የእግዚአብሔር* መንገድ ሁሉ ቸርነትና
እውነት ናቸው።
11 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ኀጢአቴ ታላቅ
ነውና፣
ስለ ስምህ ይቅር በልልኝ።
12 *እግዚአብሔርን* የሚፈራ ሰው ማን ነው?
በተመረጠለት መንገድ ያስተምረዋል።
13 ዘመኑን በተድላ ደስታ ያሳልፋል፤
ዘሩም ምድርን ይወርሳል።
14 *እግዚአብሔር* ምስጢሩን ከሚፈሩት
ወዳጆቹ አይሰውርም፤
ኪዳኑንም ይገልጥላቸዋል።
15 ዐይኖቼ ሁልጊዜ ወደ *እግዚአብሔር*
ናቸው፤
እግሮቼን ከወጥመድ የሚያላቅቃቸው
እርሱ ነውና።

16 እኔ ብቸኛና የተጨነቅሁ እንደ መሆኔ፣
ወደ እኔ ተመለስ፤ ምሕረትም
አድርግልኝ።
17 የልቤ መከራ በዝቶአል፤
ከጭንቀቴ ገላግለኝ።
18 ጭንቀቴንና መከራዬን ተመልከት፤
ኀጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ።
19 ጠላቶቼ እንዴት እንደ በዙ ተመልከት፤
እንዴት አምርረው እንደሚጠሉኝ
እይ።
20 ነፍሴን ጠብቃት፤ ታደገኝም፤
መጠጊያዬ ነህና አታሳፍረኝ።
21 አንተን ተስፋ አድርጌአለሁና፣
ታማኝነትና ቅንነት ይጠብቁኝ።

22 አምላክ ሆይ፤ እስራኤልን፣
ከመከራው ሁሉ አድነው።

## መዝሙር 26

### የንጹሕ ሰው ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ያለ ነቀፋ እንደ
መሆኔ፣
አንተው ፍረድልኝ።
ወዲያ ወዲህ ሳልልም፣
*በእግዚአብሔር* ታምኛለሁ።
2 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፈትነኝ፤
መርምረኝም፤
ልቤንና ውስጤን መርምር፤
3 ምሕረትህ ከፊቴ አልተለየምና፣
በእውነትህም ተመላለስሁ።
4 ከማይረቡ ጋር አልተቀመጥሁም፤
ከግብዞችም ጋር አልተባበርሁም።
5 የክፉዎችን ማኅበር ተጸየፍሁ፤
ከዐመፀኞችም ጋር አልቀመጥም።
6 እጆቼን በየዋህነት እታጠባለሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መሠዊያህንም
እዞራለሁ፤
7 የምስጋናን ድምፅ አሰማ ዘንድ፣
ታምራትህንም አወራ ዘንድ ነው።
8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ የምትኖርበትን
ቤት፣
የክብርህን ማደሪያ ቦታ ወደድሁ።

9 ነፍሴን ከኀጢአተኞች ጋር፣
ሕይወቴንም ከደም አፍሳሾች ጋር
አታስወግዳት።
10 በእነርሱ እጅ የተንኰል ዕቅድ አለ፤
ቀኝ እጃቸውም ጒቦን ያጋብሳል።
11 እኔ ግን በተአማኒ ሕይወት እጓዛለሁ፤
አድነኝ፤ ምሕረትንም አድርግልኝ።

12 እግሮቼ በደልዳላ ስፍራ ቆመዋል፤
በታላቅ ጉባኤ መካከልም *እግዚአ
ብሔርን* እባርከዋለሁ።

## መዝሙር 27

### ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ሰው ድፍረት

የዳዊት መዝሙር

1 *እግዚአብሔር* ብርሃኔና መድኅኔ ነው፤
የሚያስፈራኝ ማን ነው?
*እግዚአብሔር* ለሕይወቴ ዐምባዋ ነው፤
ማንን እፈራለሁ?
2 ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ፣[ቀ]
ክፉዎች ገፍተው በመጡ ጊዜ፣
ጠላቶቼና ባላጋራዎቼ በተነሡብኝ ጊዜ፣
እነርሱ ተሰነካክለው ወደቁ።
3 ሰራዊት ቢከበኝ እንኳ፣
ልቤ አይፈራም፤
ጦርነት ቢነሣብኝ እንኳ፣
ልበ ሙሉ ነኝ።

4 *እግዚአብሔርን* አንዲት ነገር
እለምነዋለሁ፤
እርሷንም እሻለሁ፤
ይኸውም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ፣
*በእግዚአብሔር* ቤት እኖር ዘንድ፣
*የእግዚአብሔርን* ክብር ውበት አይ
ዘንድ፣
በመቅደሱም ሆኜ አሰላስል ዘንድ ነው።
5 በመከራ ቀን፣
በድንኳኑ ውስጥ ይሰውረኛልና፤
በድንኳኑም ጓዳ ይሸሽገኛል፤
በዐለትም ላይ ያቆመኛል።

**25፥10** መዝ18፥25፤ 103፥18፤132፥12
**25፥11** ዘፀ9፥16፤ 32፥30፤34፥9፤ መዝ31፥3፤78፥38፤ 79፥9፤ኤር14፥7
**25፥12** ቍ8፤ ኢዮ1፥8
**25፥13** ዘኍ14፥24 ፤ዘዳ30፥15፤1ነገ3፥14 ፤ኢዮ8፥7፤ማቴ5፥5
**25፥14** ዘፍ17፥2፤ ምሳ3፥32፤ዮሐ7፥17
**25፥15** 2ዜና20፥12 ፤ኢዮ34፥30፤መዝ 119፥110፤123፥2፤ ዕብ 12፥2
**25፥16** ዘኍ6፥25፤ መዝ6፥4፤68፥6
**25፥17** 1ነገ1፥29፤ መዝ6፥3፤34፥6፥17፤ 39፥2፤40፥12፤ 54፥7፤116፥3
**25፥18** 2ሳሙ16፥12 ፤መዝ13፥3፤103፥3፤ ሮሜ12፥12
**25፥19** መዝ3፥1፤ 9፥13፤35፥19፤ 38፥19፤69፥4
**25፥20** ቍ3፤ መዝ 2፥12፤17፥13፤ 22፥21፤43፥1፤71፥2፤ 86፥2፤116፥4፤140፥1፤ 142፥6፤144፥11
**25፥21** ቍ3፤ ዘፍ20፥5፤1ነገ9፥4፤ መዝ85፥10፤ 111፥8፤ምሳ10፥9፤ ኢሳ60፥17፤ሚል2፥6
**25፥22** መዝ130፥8 ፤ሉቃ24፥21
**26፥1** 1ሳሙ24፥15 ፤2ነገ20፥3፤መዝ15፥2 ፤22፥4፤40፥4፤ ምሳ20፥7፤ኢሳ12፥2፤ 25፥9፤ኤር17፥7፤ ዳን3፥28፤ዕብ10፥23
**26፥2** ዘዳ6፥6፤መዝ 7፥9፤66፥10፤ኤር11፥ 20፤20፥12፤ሕዝ11፥5
**26፥3** 1ነገ2፥4፤ መዝ6፥4፤40፥11፤ 43፥3፤86፥11፤119፥30
**26፥4** መዝ1፥1፤ 28፥3፤ማቴ6፥2
**26፥5** መዝ139፥21
**26፥6** መዝ73፥13፤ ማቴ27፥24
**26፥7** ኢሱ3፥5፤መዝ 9፥1፤ኢሳ42፥12፤60፥6
**26፥8** ዘፀ29፥43፤ 2ዜና7፥1፤መዝ96፥6፤ 122፥6፤ኢሳ66፥10
**26፥9** መዝ5፥6፤ 28፥3፤55፥23፤ 139፥19፤ምሳ29፥10
**26፥10** ኢዮ36፥18፤ መዝ21፥11፤ ኢሳ1፥23፤ሕዝ22፥12
**26፥11** መዝ31፥5፤ 69፥18፤119፥134፤ ቲቶ2፥14

**26፥12** መዝ22፥25፤27፥11፤40፥2፤143፥10፤ኢሳ26፥7፤40፥3-4 ፤45፥13፤ዘካ4፥7፤ሉቃ6፥17 **27፥1** ዘፀ15፥2፤2ሳሙ22፥29፤ኢዮ 13፥15፤መዝ3፥8፤9፥9፤56፥4፡11፤118፥6 **27፥2** መዝ9፥3፤20፥8 ፤37፥24፤ዳን11፥19፤ሮሜ11፥11 **27፥3** ዘፍ4፥7፤ኢዮ4፥6፤መዝ 3፥6 **27፥4** መዝ23፥6፤61፥4፤ሉቃ10፥42 **27፥5** ኢዮ38፥23፤ መዝ12፥7፤17፥8፤40፥2

[ቀ]2 ወይም *ስሜን ሊያጠፉ*

6በዚህ ጊዜ በዙሪያዬ ባሉ ጠላቶቼ ላይ፣
ራሴ ከፍ ከፍ ይላል፤
በድንኳኑም ውስጥ የእልልታ መሥዋዕት
እሠዋለሁ፤
ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፤
እዘምርለታለሁም።

7እግዚአብሔር ሆይ፤ ድምፄን ከፍ
አድርጌ ስጮኽ ስማኝ፤
ራራልኝ፤ ስማኝም።
8"ፊቴን ፈልጉ" ባልህ ጊዜ፤[ሀ]
ልቤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ፊትህን
እሻለሁ አለች።
9ፊትህን ከእኔ አትሰውር፤
ተቈጥተህ አገልጋይህን አታርቀው፤
መቼም ረዳቴ ነህና።
አዳኝ አምላኬ ሆይ፤
አትጣለኝ፤ አትተወኝም።
10አባቴና እናቴ ቢተዉኝ እንኳ፣
እግዚአብሔር ይቀበለኛል።
11እግዚአብሔር ሆይ፤ መንገድህን
አስተምረኝ፤
ስለ ጠላቶቼም፣
በቀና መንገድ ምራኝ።
12ለጠላቶቼ ፍላጎት አሳልፈህ አትስጠኝ፤
የሐሰት ምስክሮች ተነሥተውብኛልና፣
ዐመፃ የሚረጩ ናቸው።

13የእግዚአብሔርን ቸርነት፣
በሕያዋን ምድር እንደማይ፣
ሙሉ እምነቴ ነው።
14እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤
አይዞህ፣ በርታ፤
እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።

## መዝሙር 28

### ልመናና ምስጋና

*የዳዊት መዝሙር*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ዐለቴ ሆይ፤ ሰምተህ እንዳልሰማ
አትሁንብኝ፤
አንተ ዝም ካልኸኝ፤
ወደ ጕድጓድ እንደሚወርዱ እሆናለሁ።
2ለርዳታ በጮኽሁ ጊዜ፣
ወደ ቅዱስ ማደሪያህ፣
እጆቼን በዘረጋሁ ጊዜ፣
የልመናዬን ቃል ስማ።

3በልባቸው ተንኰል እያለ፣
ከባልንጀሮቻቸው ጋር በሰላም ከሚናገሩ፣
ከክፉ አድራጊዎችና፣
ከዐመፃ ሰዎች ጋር ጐትተህ
አትውሰደኝ።
4እንደ ሥራቸው፣
እንደ ክፉ ተግባራቸው ክፈላቸው፤
እንደ እጃቸው ሥራ ስጣቸው፤
አጸፋውን መልስላቸው።

5ለእግዚአብሔር ሥራ ግድ ስለሌላቸው፣
ለእጆቹም ተግባራት ስፍራ ስላልሰጡ፣
እርሱ ያፈርሳቸዋል፤
መልሶም አይገነባቸውም።

6የልመናዬን ቃል ሰምቶአልና፣
እግዚአብሔር የተባረከ ይሁን።
7እግዚአብሔር ብርታቴና ጋሻዬ ነው፤
ልቤ በእርሱ ይታመናል፤ እርሱም
ዐግዞኛል፤
ልቤ ሐሤት አደረገ፤
በዝማሬም አመሰግነዋለሁ።

8እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታታቸው
ነው፤
ለቀባውም የመዳን ዐምባ ነው።
9ሕዝብህን አድን፤ ርስትህንም ባርክ፤
እረኛ ሁናቸው፤ ለዘላለሙም ዐቅፈህ
ያዛቸው።

## መዝሙር 29

### ለማዕበሉ ጌታ የቀረበ ውዳሴ

*የዳዊት መዝሙር*

1እናንተ ኀያላን፣ ለእግዚአብሔር ስጡ፤
ክብርንና ብርታትን ለእግዚአብሔር
ስጡ።
2ለስሙ የሚገባ ክብር ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
በቅድስናው ግርማ ለእግዚአብሔር
ስገዱ።

3የእግዚአብሔር ድምፅ በውሆች ላይ
ነው፤
የክብር አምላክ አንጐደጐደ፤
እግዚአብሔር በታላላቅ ውሆች ላይ
አንጐደጐደ።

4የእግዚአብሔር ድምፅ ኀያል ነው፤
የእግዚአብሔር ድምፅ ግርማዊ ነው።
5የእግዚአብሔር ድምፅ ዝግባን ይሰብራል፤
እግዚአብሔር የሊባኖስን ዝግባ
ይሰባብራል።
6ሊባኖስን እንደ ጥጃ፣
ስርዮንንም[+] እንደ አውራሪስ ግልገል
ያዘልላል።
7የእግዚአብሔር ድምፅ
የእሳት ነበልባል ይረጫል።

27፥6 ዘፀ15፥1፤ 2ሳሙ22፥49፤ዕዝ 3፥13፤ኢዮ22፥26፤ መዝ3፥3፤18፥48፤ 22፥12፤33፥2፤50፥14፤ 54፥6፤92፥1፤107፥22 ፤116፥17፤147፥7፤ ኤፌ5፥19
27፥7 መዝ4፥1፤ 5፥3፤18፥6፤55፥17፤ 119፥149፤130፥2፤ ኢሳ 28፥23
27፥8 1ዜና16፥11
27፥9 ዘፍ49፥25፤ ዘዳ4፥31፤31፥17፤ 33፥29፤መዝ2፥5፤ 18፥46፤22፥24፤37፥28፤ 119፥8፤ኢሳ41፥17፤ 62፥12 ፤ኤር14፥9
27፥11 ዘፀ33፥13፤ ዕዝ8፥21፤መዝ5፥8፤ 72፥4፤78፥42፤ 106፥10፤ኤር21፥12
27፥12 ዘዳ19፥16፤ ማቴ26፥60፤ሐሥ6፥13 ፤1ቆሮ15፥15
27፥13 ዘፀ33፥19፤ 2ዜና6፥41፤ኢዮ28፥13 ፤መዝ23፥6፤31፥19፤ 145፥7
27፥14 ዘዳ1፥21፤ መሳ5፥21፤መዝ33፥20 ፤130፥5፡6፤ኢሳ8፥17 ፤30፥18፤ዕን2፥3፤ ሶፎ 3፥8፤ሐሥ1፥4፤ ኤፌ 6፥10
28፥1 ዘዳ1፥45፤ አስ4፥14፤ኢዮ33፥18
28፥2 ዕዝ9፥5፤ መዝ5፥7፤11፥4፤17፥1፤ 61፥1፤63፥4፤116፥1፤ 130፥2፤141፥2፤ 142፥1፤143፥1፤ ሰቆ2፥19፤1ጢሞ2፥8
28፥3 መዝ12፥2፤ 26፥4፤55፥21፤ኤር9፥8
28፥4 መዝ62፥12፤ ሰቆ3፥64፤2ጢሞ4፥14፤ ራእ18፥6፤22፥12
28፥5 ኢሳ5፥12
28፥6 ቈላ2፤ ዘፍ24፥27፤2ቆሮ1፥3፤ ኤፌ1፥3፤1ጴጥ1፥3
28፥7 ዘዳ16፥15፤ መዝ13፥5፤16፥9፤ 18፥1፤33፥3፤40፥3፤ 69፥30፤112፥7፤144፥9፤ 149፥1፤ኢሳ26፥3
28፥8 ዘፀ15፥2፤ መዝ 18፥1፤20፥6፤ 27፥1፤ዕን 3፥13
28፥9 ዘፀ34፥9፤ ዘዳ 1፥31፤32፥11፤ 1ዜና11፥2፤16፥35፤ መዝ23፥1፤78፥52፡71፤ 80፥1፤106፥47፤118፥ 25፤ኢሳ40፥11፤46፥3፤ 63፥9፤ኤር31፥10፤ ሕዝ34፥12-16፡23፡ 31፤ሚክ7፥14
29፥1 ቈላ2፤2ሳሙ 1፥19፤2ዜና16፥28፤ መዝ8፥1፤103፥20፤ ኢሳ10፥13 29፥2 1ዜና16፥29፤መዝ96፥7-9 29፥3 ዘፀ15፥10፤ 1ሳሙ2፥10፤ኢዮ37፥5፤መዝ18፥13፤24፥7፤46፥6፤68፥33፤77፥17፤ ኤር10፥13፤25፥30፤ኤል2፥11፤አሞ1፥2፤ሐሥ7፥2 29፥4 መዝ68፥33 29፥5 መሳ9፥15 29፥6 ዘኍ23፥22፤ዘዳ3፥9፤ኢዮ39፥9፤ መዝ 92፥10፤114፥4 29፥7 ሕዝ1፥14፤ራእ8፥5

[ሀ]8 ወይም *ልቤ ሆይ፤ ለአንተ "ፊቴን ..." አለ*
[+]6 አርሞንዔም የተባለው ተራራ ነው።

8የእግዚአብሔር ድምፅ ምድረ በዳውን
ያናውጣል፤
የእግዚአብሔር ድምፅ የቃዴስን
ምድረ በዳ ያናውጣል።
9የእግዚአብሔር ድምፅ ወርካዎችን
ይወዘውዛል፤[ቾ]
ጫካዎችንም ይመነጥራል፤
ሁሉም በእርሱ ቤተ መቅደስ ሆኖ
"ይክበር!" ይላል።
10እግዚአብሔር በጐርፍ ላይ ዙፋኑን
ዘርግቶ ተቀምጦአል፤[ኀ]
እግዚአብሔር በንጉሥነቱ ለዘላለም
በዙፋኑ ላይ ይቀመጣል።
11እግዚአብሔር ለሕዝቡ ብርታትን
ይሰጣል፤
እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካል።

## መዝሙር 30

### ከክፉ አደጋ የዳነ ሰው ምስጋና

ለቤተ መቅደሱ ምረቃ የተዘመረ፤ የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ከታች
አንሥተኸኛልና፣
ጠላቶቼም በላዬ እንዳይደሰቱ
አድርገሃልና፣
ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።
2እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ትረዳኝ
ዘንድ ወደ አንተ ጮኽሁ፤
አንተም ፈወስኸኝ።
3እግዚአብሔር ሆይ ነፍሴን ከሲኦል[ኀ]
አወጣሃት፤
ወደ ጉድጓድ ከመውረድም መልሰህ
ሕያው አደረግኸኝ።
4እናንተ ቅዱሳኑ፤ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ቅዱስ ስሙንም አወድሱ።
5ቍጣው ለዐጭር ጊዜ ነው፤
ቸርነቱ ግን እስከ ዕድሜ ልክ ነውና፤
ሌሊቱን በልቅሶ ቢታደርም፣
በማለዳ ደስታ ይመጣል።
6እኔም በተረጋጋሁ ጊዜ፣
"ከቶ አልናወጥም" አልሁ።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ በአንተ ሞገስ፣
ተራሮቼ[ኘ] ጸኑ፣
ፊትህን በሰወርህ ጊዜ ግን፣
ውስጤ ታወከ።
8እግዚአብሔር ሆይ፤ ወደ አንተ ተጣራሁ፤
ወደ ጌታም እንዲህ ብዬ ጮኽሁ፤
9"በእኔ ወደ ጉድጓድ መውረድ፣
በመሞቴ ምን ጥቅም ይገኛል?[ኦ]
ዐፈር ያመሰግንሃልን?
ታማኝነትህንስ ይናገራልን?
10እግዚአብሔር ሆይ፤ ስማ፤ ማረኝም፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ረዳት ሁነኝ።"
11ዋይታዬን ወደ ሽብሸባ ለወጥህልኝ፤
ማቄን አውልቀህ ፍሥሓን አለበስኸኝ፤
12እንግዲህ ነፍሴ ታመስግንህ፤ ዝምም
አትበል፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ለዘላለም
አመሰግንሃለሁ።

## መዝሙር 31

### የመከራ ጊዜ ጸሎት

31፥1-4 ተጓ ምብ-መዝ71፥1-3

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ሆይ፤ በአንተ ተተግኛለሁ፤
እንግዲህ ዕፍረት ከቶ አይድረስብኝ፤
በጽድቅህም ታደገኝ።
2ጆሮህን ወደ እኔ መልሰህ ስማኝ፤
ፈጥነህ አድነኝ፤
መጠጊያ ዐለት ሁነኝ፤
ታድነኝም ዘንድ ምሽግ ሁነኝ።
3አንተ ዐለቴና መጠጊያዬ ነህና፣
ስለ ስምህ ስትል ምራኝ፤
መንገዱንም ጠቍመኝ።
4አንተ መጠጊያዬ ነህና፣
በስውር ከተዘረጋብኝ ወጥመድ
አውጣኝ።
5መንፈሴን በእጅህ ዐደራ እሰጣለሁ፤
እግዚአብሔር የእውነት አምላክ ሆይ፤
አንተ ተቤዠኸኝ።
6ለከንቱ ጣዖታት ስፍራ የሚሰጡትን
ጠላሁ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ታመንሁ።
7በምሕረትህ ደስ እሰኛለሁ፤ ሐሤትም
አደርጋለሁ፤
መከራዬን አይተሃልና፤
የነፍሴንም ጭንቀት ዐውቀሃል።
8ለጠላት አሳልፈህ አልሰጠኸኝም፤
ነገር ግን እግሮቼን ሰፊ ቦታ ላይ
አቆምሃቸው።
9እግዚአብሔር ሆይ፤ በመከራ ውስጥ ነኝና
ማረኝ፤
ዐይኖቼ በሐዘን ደክመዋል፤
ነፍስና ሥጋዬም ዝለዋል።
10ሕይወቴ በመጨነቅ፣
ዕድሜዬም በመቃተት ዐለቀ፤
ከመከራዬ[ኸ] የተነሣ ጒልበት ከዳኝ፤
ዐጥንቴም በውስጤ ሟሟ።
11ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ፣
ለጎረቤቶቼ መዘባበቻ፣

29፥8 ዘኍ13፥26፤ 20፥1
29፥9 ዘኍ13፥32፤ መዝ26፥8፤ኢሳ2፥13፤ሕዝ27፥6፤አሞ2፥9
29፥10 ዘፍ6፥17፤ ዘፀ15፥18
29፥11 ዘሌ26፥6፤ ዘኍ6፥26፤መዝ18፥1፤ 28፥8፤68፥35
30፥1 ዘፀ15፥2፤ ኢዮ11፥8፤መዝ22፥17፤ 63፥9፤107፥26፤ ምሳ9፥18፤ኢሳ14፥15
30፥2 ዘኍ12፥13፤ መዝ5፥2፤88፥13
30፥3 መዝ16፥10፤ 28፥1፤55፥23፤56፥13፤69፥15፤86፥13፤ 143፥7፤ምሳ1፥12፤ ኢሳ38፥17፤ዮና2፥6
30፥4 ዘፀ3፥15፤ መዝ16፥3፤33፥1፤21፤ 47፥7፤68፥4፤103፥1፤ 145፥21
30፥5 2ሳሙ15፥30፤ዕዝ3፥11፤ኢዮ14፥13፤መዝ6፥6፤103፥9፤ 126፥6፤ኤር31፥16፤ 2ቆሮ 4፥17
30፥6 ኢዮ29፥18
30፥7 ዘዳ31፥17
30፥9 ኢዮ33፥18፤ መዝ6፥5፤88፥11፤ ኢሳ 38፥18
30፥10 መዝ4፥1፤ 17፥1፤20፥2
30፥11 ዘፀ15፥20፤ ዘዳ16፥15፤2ሳሙ3፥31፤አስ4፥1፤ መዝ16፥9፤35፥13
30፥12 መዝ35፥18፤ 44፥8፤52፥9፤75፥1፤118፥21፤ራእ11፥17
31፥1 መዝ5፥8፤7፥1
31፥2 ዘፀ2፥17፤ 2ሳሙ22፥3፤ መዝ6፥4፤18፥2
31፥3 መዝ18፥2፤ 23፥3
31፥4 1ሳሙ28፥9፤ኢዮ18፥10፤መዝ9፥9
31፥5 ኢሳ45፥19፤ 65፥16፤ሉቃ23፥46፤ ሐሥ7፥59
31፥6 ዘዳ32፥21፤ መዝ4፥5
31፥7 መዝ13፥3፤ 25፥17፤ሉቃ22፥44
31፥8 ዘዳ32፥30፤ 2ሳሙ22፥20
31፥9 መዝ4፥1፤ 6፥7፤63፥1
31፥10 ቆላ7፤ መዝ6፥2፥6፤22፥15፤ 25፥18፤32፥4፤ 38፥10፤73፥6
31፥11 ዘዳ30፥7፤ መዝ3፥7፤22፥6፤ 25፥19፤38፥11፤ 102፥8

[ቾ]9 ወይም *እግዚአብሔር ኢጋዘን እንድትወልድ ያደርጋል*
[ኀ]10 ወይም *ይቀመጣል* [ኀ]3 ወይም *ከመቃብር*
[ኘ]7 ወይም *ኰረብታማ የሆነች አገሬ*
[ኦ]9 ወይም *ዝም ብል … ይገኛል?*
[ኸ]10 ወይም *ከበደሌ*

ለወዳጆቼ *መሣለቂያ* ሆኛለሁ፤
*መንገድ* ላይ የሚያገኙኝም ይሸሹኛል።
12እንደ ሞተ ሰው ተረሳሁ፤
እንደ ተሰበረ የሸክላ ዕቃም
ተቈጠርሁ።
13የብዙ ሰዎችን ሹክሹክታ እሰማለሁና፤
ዙሪያው ሁሉ ሽብር አለ፤
በእኔ ላይ ባሤሩ ጊዜ፣
ሕይወቴን ለማጥፋት ዶለቱ።
14*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔ ግን በአንተ
እታመናለሁ፤
"አንተ ፅምላኬ ነህ" እልሃለሁም።
15ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው፤
ከጠላቶቼ እጅ ታደገኝ፤
ከሚያሳድዱኝም አድነኝ።
16ፊትህን በአገልጋይህ ላይ አብራ፤
በምሕረትህም አድነኝ።
17*እግዚአብሔር* ሆይ፤
ወደ አንተ እጮኻለሁና አልፈር፤
ክፉዎች ግን ይፈሩ፤
ሲኦል[ኸ] ገብተውም ጸጥ ይበሉ።
18በጻድቁ ላይ በእብሪት የሚናገሩ፣
ትዕቢትንና ንቀትን የተሞሉ፣
ዋሾ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።

19በሰዎች ልጆች ፊት፣
ለሚፈሩህ ያስቀመጥሃት፣
መጠጊያ ላደረጉህም ያዘጋጀሃት፣
በጎነትህ ምንኛ በዛች!
20ከሰዎች ሤራ፣
በማደሪያህ ውስጥ ትሸሽጋቸዋለህ፤
ከአንደበት ጭቅጭቅም፣
በድንኳንህ ውስጥ ትከልላቸዋለህ።

21በተከበበች ከተማ ውስጥ፣
የሚያስደንቅ ምሕረቱን ያሳየኝ፣
*እግዚአብሔር* ይባረክ።
22እኔ በደነገጥሁ ጊዜ፣
"ከዐይንህ ፊት ተወግጃለሁ" አልሁ፤
አንተ ግን ወደ አንተ ስጮኽ፣
የልመናዬን ቃል ሰማህ።

23እናንተ ቅዱሳኑ ሁሉ፣ *እግዚአብሔርን*
ውደዱት!
*እግዚአብሔር* ታማኞችን ይጠብቃል፤
ትዕቢተኞችን ግን ፈጽሞ
ይበቀላቸዋል።
24*እግዚአብሔርን* ተስፋ የምታደርጉ ሁሉ፤
በርቱ፤ ልባችሁም ይጽና።

## *መዝሙር* 32

### ግልጥ ኑዛዜ

የዳዊት ትምህርት

1*መተላለፉ* ይቅር የተባለለት፣
ኀጢአቱም የተሸፈነለት፣
እንዴት ቡሩክ ነው!
2*እግዚአብሔር* ኀጢአቱን የማይቈጥርበት፣
በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው፣
እርሱ ቡሩክ ነው።
3ቀኑን ሙሉ ከመቃተቴ የተነሣ፣
ዝም ባልሁ ጊዜ፣
ዐጥንቶቼ ተበላሹ፤
4በቀንና በሌሊት፣
እጅህ ከብዶብኛልችና፤
ኀይሌም የበጋ ትኵሳት እንደላሰው ነገር፣
ከውስጤ ተሟጠጠ። ሴላ
5ኀጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፤
በደሌንም አልሸሸግሁም፤
ደግሞም "መተላለፌን
ለ*እግዚአብሔር* እናዘዛለሁ" አልሁ፤
አንተም የኀጢአቴን በደል፣
ይቅር አልህ። ሴላ

6ስለዚህ ጻድቅ ሁሉ፣
በጭንቅ ጊዜ ወደ አንተ ይጸልይ፤
ኀይለኛ ጐርፍ አካባቢውን ቢያጥለ
ቀልቅም፣
እርሱ አጠገብ አይደርስም።
7አንተ መሸሸጊያዬ ነህ፤
ከመከራ ትጠብቀኛለህ፤
በድል ዝማሬም ትከበኛለህ። ሴላ

8አስተምርሃለሁ፤ በምትሄድበትም
*መንገድ* እመራሃለሁ፤
እመክርሃለሁ፤ በዐይኔም እከታተልሃለሁ።
9በልባብና በልጓም ካልተገሩ በቀር፣
ወደ አንተ እንደማይቀርቡት፣
ማስተዋል እንደሌላቸው፣
እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።
10የክፉዎች ዋይታ ብዙ ነው፤
*በእግዚአብሔር የሚታመን ግን*፣
ምሕረት ይከበዋል።

11ጻድቃን ሆይ፤ *በእግዚአብሔር* ደስ
ይበላችሁ፤ ሐሤትም አድርጉ፤
ቅን ልብ ያላችሁም ሁሉ እልል በሉ።

## *መዝሙር* 33

### ውዳሴ ለቸር አምላክ

1ጻድቃን ሆይ፤ *በእግዚአብሔር* ደስ
ይበላችሁ፤
ቅኖች ሊወድሱት ይገባቸዋል።
2*እግዚአብሔርን* በመሰንቆ አመስግኑት፤
ዐሥር አውታር ባለውም በገና ዘምሩለት።
3አዲስ *መዝሙር* ዘምሩለት፤
በገናውን ባማረ ቅኝት ደርድሩ፤
እልልም በሉ።
4*የእግዚአብሔር* ቃል እውነት ነውና፤

31፥12 *መዝ*28፥1፤ 88፥4
31፥13 ዘፍ37፥18፤ ዘሌ19፥16፤ኢዮ18፥11፤*መዝ*41፥7፤50፥20፤56፥6፤71፥10፤83፥3፤ ኢሳ13፥8፤ኤር6፥25፤20፥3፡10፤46፥5፤49፥5 ፤ሰቆ2፥22 ማቴ12፥14
31፥14 *መዝ*4፥5
31፥15 ኢዮ14፥5
31፥16 ዘኍ6፥25፤ *መዝ*6፥4
31፥17 1ሳሙ2፥9፤ *መዝ*22፥5፤94፥17፤ 115፥17
31፥18 1ሳሙ2፥3፤ *መዝ*120፥2፤ምሳ10፥18፤26፥24፤ይሁ1፥15
31፥19 *መዝ*2፥12፤ 23፥5፤27፥13፤ ሮሜ11፥22
31፥20 ዘፍ37፥18፤ *መዝ*17፥8፤55፥8
31፥21 1ሳሙ23፥7፤*መዝ*17፥7፤28፥6
31፥22 ኢዮ6፥9፤ 17፥1፤*መዝ*6፥9፤37፥9፤66፥19፤88፥5፤ 116፥1፡11፤145፥19፤ ኢሳ 38፥12
31፥23 ዘዳ32፥41፤ *መዝ*4፥3፤18፥25፤94፥2፤ራእ2፥10
31፥24 *መዝ*27፥14
32፥1 *መዝ*85፥2፤103፥3
32፥2 ዮሐ1፥47፤ሮሜ4፥7-8፤ ራእ 14፥5
32፥3 ኢዮ3፥24፤ 31፥34፤*መዝ*6፥6፤ 31፥10
32፥4 1ሳሙ5፥6፤ ኢዮ9፥34፤*መዝ*22፥15፤38፥2፤39፥10
32፥5 ዘሌ26፥40፤ አዮ31፥33፤ *መዝ*103፥12፤ ምሳ28፥13፤1ዮሐ1፥9
32፥6 ዘፀ15፥10፤ *መዝ*69፥1፡13፤ ኢሳ 43፥2፤55፥6
32፥7 *መሳ*5፥1፤ 9፥35፤*መዝ*9፥9
32፥8 *መዝ*25፥8፤ 33፥18፤34፥11
32፥9 ኢዮ30፥11፤ 39፥10፤ያዕ3፥3
32፥10 *መዝ*4፥5፤ ምሳ16፥20፤ሮሜ2፥9
32፥11 *መዝ*64፥10
33፥1 *መዝ*5፥11፤ 11፥7፤101፥1፤147፥1
33፥2 ዘፍ4፥21፤ *መዝ*92፥3፤144፥9፤ 1ቆሮ14፥7፤ራእ5፥8
33፥3 ኢዮ3፥7፤*መዝ* 35፥27፤40፥3፤47፥1፤ ኢሳ42፥10፤ራእ5፥9
33፥4 *መዝ*18፥25፤

[ኸ]17 ወይም *መቃብር*

የሚሠራውም ሁሉ የታመነ ነው።
5 እርሱ ጽድቅንና ፍትሕን ይወዳል፤
ምድርም በምሕረቱ የተሞላች ናት።

6 በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተሠሩ፤
በአፉም እስትንፋስ የከዋክብት
ሰራዊት።
7 የባሕርን ውሃ በአንድ ዕቃ ይሰበስባል፤[ሠ]
ቀላዩንም በአንድ ስፍራ ያከማቻል።
8 ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፤
በዓለም የሚኖር ሕዝብ ሁሉ በፊቱ
ይንቀጥቀጥ።
9 እርሱ ተናግሮአልና ሆኑ፤
አዞአልና ጸኑም።
10 እግዚአብሔር የሕዝቦችን ምክክር
ከንቱ ያደርጋል፤
የሕዝብንም ዕቅድ ያጨናግፋል።
11 የእግዚአብሔር ሐሳብ ግን ለዘላለም
ይጸናል፤
የልቡም ሐሳብ ለትውልድ ሁሉ ነው።

12 እግዚአብሔር አምላኩ የሆነው ሕዝብ፣
ለርስቱ የመረጠውም ወገን የተባረከ
ነው።
13 እግዚአብሔር ከሰማይ ይመለከታል፤
የሰውንም ልጆች ሁሉ ያያል፤
14 ከማደሪያው ቦታ ሆኖ፣
በምድር ወደሚኖሩት ሁሉ
ይመለከታል፤
15 እርሱ የሁሉን ልብ የሠራ፣
የሚያደርጉትን ሁሉ የሚያስተውል
ነው።
16 ንጉሥ በሰራዊቱ ታላቅነት አይድንም፤
ጀግናም በኀይሉ ብርታት
አያመልጥም።
17 በፈረስ ድል አደርጋለሁ ማለት ከንቱ
ተስፋ ነው፤
በብርቱ ጒልበቱም ማንንም አያድንም።
18 እነሆ፤ የእግዚአብሔር ዐይኖች በሚፈሩት
ላይ ናቸው፤
ምሕረቱንም በሚጠባበቁት ላይ
አትኵረዋል።
19 በዚህም ነፍሳቸውን ከሞት ያድናል፤
በራብ ዘመንም በሕይወት
ያኖራቸዋል።

20 ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ
ታደርጋለች፤
እርሱ ረዳታችንና መጠጊያችን
ነው።
21 ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋል፤
በቅዱስ ስሙ ታምነናልና።
22 እግዚአብሔር ሆይ፤ ተስፋ ባደረግንህ፣
በእኛ ላይ ምሕረትህ ትሁን።

19፥8፤25፥10፤119፥1
42፤ራእ19፥9፤22፥6
33፥5 መዝ6፥4፤
11፥7
33፥6 ዘፍ1፥3፥16
፤ዘፀ8፥19፤2ዜና2፥12
፤ዕብ11፥3
33፥7 ዘፍ1፥10፤
ኢሱ 3፥16
33፥8 ዘዳ6፥13፤
4፥23፤መዝ2፥11፤49፥1
፤ኢሳ18፥3፤ሚክ1፥2
33፥9 መዝ148፥5
33፥10 ኢዮ5፥12፤
መዝ2፥1፤ኢሳ44፥25
33፥11 ዘኍ23፥19፤
ኤር51፥12፥29
33፥12 ዘፀ8፥22፤
34፥9፤ዘዳ7፥6፤
መዝ4፥3፥65፥4፤
84፥4፤144፥15
33፥13 ኢዮ28፥24
፤መዝ11፥4፤14፥2፤
53፥2፤102፥19፤
ዕብ4፥13
33፥14 ዘሌ15፥31፤
1ነገ8፥39
33፥15 ኢዮ10፥4፥8
፤መዝ119፥73፤
ኤር32፥19
33፥16 1ሳሙ14፥6
33፥17 መዝ20፥7
33፥18 ዘፀ3፥16፤
መዝ6፥4፤11፥4፤
1ጴጥ3፥12
33፥19 ኢዮ5፥20፤
መዝ56፥13፤
ሐሥ 12፥11
33፥20 መዝ27፥14
33፥21 1ሳሙ2፥1፤
መዝ30፥4፤99፥3፤
ኢል2፥23
33፥22 መዝ6፥4
34 ርዕስ 1ሳሙ
21፥13
34፥1 መዝ71፥6፤
ኤፌ5፥20፤1ተሰ5፥18
34፥2 መዝ44፥8፤
69፥32፤107፥42፤
119፥74፤ኤር9፥24፤
1ቆሮ1፥31
34፥3 ዘፀ15፥2፤
መዝ 63፥3፥86፥12፤
ዳን4፥37፤ዮሐ17፥1፤
ሮሜ15፥6
34፥4 ቍ 17፤
ዘፀ32፥11፤
መዝ18፥43፤22፥4፤
56፥13፤77፥2፤86፥13
34፥5 ዘፀ34፥29፤
መዝ25፥3፤44፥15፤
69፥7፤83፥16
34፥6 መዝ25፥17
34፥7 ዘፍ32፥1፤
መዝ22፥4፤37፥40፤
41፥1፤ 97፥10፤
ኢሳ31፥5፤ዳን3፥28፤
ማቴ18፥10፤ሐሥ12፥11
34፥8 መዝ2፥12፤
ዕብ6፥5፤1ጴጥ2፥3
34፥9 ዘዳ6፥13፤
መዝ23፥1፤ራእ14፥7

## መዝሙር 34[ፀ]

### የእግዚአብሔር ፍትሕ ውዳሴ

እንደ እብድ ሆኖ አቤሜሌክ ፊት በመቅረቡ ተባሮ
በወጣ ጊዜ የዘመረው፤ የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፤
ምስጋናውም ዘወትር ከአፌ አይለይም።
2 ነፍሴ በእግዚአብሔር ተመካች፤
ትሑታንም ይህን ሰምተው ሐሤት
ያደርጋሉ።
3 ኑና ከእኔ ጋር እግዚአብሔርን አክብሩት፤
ስሙንም በአንድነት ከፍ ከፍ
እናድርግ።

4 እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤ እርሱም
መለሰልኝ፤
ከፍርሀቴም ሁሉ አዳነኝ።
5 ወደ እርሱ የሚመለከቱ ያበራሉ፤
ፊታቸውም ከቶ አያፍርም።
6 ይህ ችግረኛ ጮኸ፤ እግዚአብሔርም
ሰማው፤
ከመከራውም ሁሉ አዳነው።
7 እግዚአብሔርን በሚፈሩት ዙሪያ
የእግዚአብሔር መልአክ ይሰፍራል፤
ያድናቸዋልም።

8 እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ
እዩ፤
እርሱን መጠጊያ የሚያደርግ ምንኛ
ቡሩክ ነው!
9 እናንተ ቅዱሳኑ፤ እግዚአብሔርን ፍሩት፤
እርሱን የሚፈሩት አንዳች አያጡምና።
10 አንበሶች ሊያጡ፣ ሊራቡም ይችላሉ፤
እግዚአብሔርን የሚሹ ግን መልካም
ነገር አይጐድልባቸውም።
11 ልጆቼ ሆይ፣ ኑ፤ ስሙኝ፤
እግዚአብሔርን መፍራት
አስተምራችኋለሁ።
12 ሕይወትን የሚወድ፣
በጎውንም ያይ ዘንድ ዕድሜን የሚመኝ
ማን ነው?
13 አንደበትህን ከክፉ ነገር ከልክል፤
ከንፈርህንም ከሽንገላ ጠብቅ።

14 ከክፉ ሽሽ፤ መልካሙንም አድርግ፤
ሰላምን ፈልጋት፤ ተከተላትም።

15 የእግዚአብሔር ዐይኖች ወደ ጻድቃን
ናቸው፤

34፥10 መዝ23፥1 34፥11 መዝ19፥9፤32፥8፤66፥16
34፥12 መክ3፥13 34፥13 መዝ12፥2፤39፥1፤141፥3፤
ምሳ13፥3፤21፥23፤ያዕ1፥26፤1ጴጥ2፥22 34፥14 መዝ37፥27
፤ኢሳ1፥17፤ሮሜ14፥19፤3ዮሐ1፥11 34፥15 ኢዮ23፥10፤
36፥7፤መዝ33፥18፤ሚል3፥16፤ዮሐ9፥31

[ሠ] 7 ወይም የባሕርን ውሃ ይሰበስባል
[ፀ] 34 እያንዳንዱ የዚህ መዝሙር ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆሄያት የሚጀመር ሲሆን ጅማሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጒም የሚሰጥ ግጥም ነው።

ጆሮዎቹም ለጩኸታቸው ክፍት
ናቸው።
16 መታሰቢያቸውን ከምድር ለማጥፋት፣
የእግዚአብሔር ፊት በክፉ አድራጊዎች
ላይ ነው።

17 ጻድቃን ሲጮኹ፣ እግዚአብሔር
ይሰማቸዋል፤
ከመከራቸውም ሁሉ ያድናቸዋል።
18 እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ
ነው፤
መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።

19 የጻድቅ መከራው ብዙ ነው፤
እግዚአብሔር ግን ከሁሉም ያድነዋል።
20 ዐጥንቶቹን ሁሉ ይጠብቃል፤
ከእነርሱም አንድ አይሰበርም።

21 ኀጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል፤
ጻድቃንን የሚጠሉ ይፈረድባቸዋል።
22 እግዚአብሔር የባሪያዎቹን ነፍስ
ይቤዣል፤
እርሱንም መጠጊያ ያደረገ
አይፈረድበትም።

## መዝሙር 35

### የተጨቈነ ሰው ጸሎት

የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ የሚታገሉኝን
ታገላቸው፤
የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው።
2 ትልቁንና ትንሹን ጋሻ ያዝ፤
እኔንም ለመርዳት ተነሥ።
3 በሚያሳድዱኝ ላይ፣
ጦርና ጭሬ ምዘዝ፤[ʺ]
ነፍሴንም፣ "የማድንሽ እኔ ነኝ" በላት።

4 ሕይወቴን የሚፈልጓት፣
ይቅለሉ፣ ይዋረዱ፤
እኔን ለማጥፋት የሚያሤሩ፣
ዐፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።

5 በነፋስ ፊት እንዳለ እብቅ ይሁኑ፤
የእግዚአብሔር መልአክ ያሳዳቸው።
6 መንገዳቸው ጨለማና ድጥ ይሁን፤
የእግዚአብሔር መልአክ ያባራቸው።
7 ያለ ምክንያት ወጥመዳቸውን በስውር
አስቀምጠውብኛልና፤
ያለ ምክንያት ለነፍሴ ጕድጓድ
ቈፍረውላታል።
8 ያልታሰበ ጥፋት ይምጣባቸው፤
የሰወሩት ወጥመድ ይያዛቸው፤
ይጠፉም ዘንድ ወደ ጕድጓዱ
ይውደቁ።
9 ነፍሴም በእግዚአብሔር ደስ ይላታል፤
በማዳኑም ሐሤት ታደርጋለች።

34፥16 ዘፀ17፥14፤ ዘሌ17፥10፤መዝ9፥6፤ ኤር23፥30፤ 1ጴጥ3፥10-12
34፥17 መዝ145፥19
34፥18 ዘዳ4፥7፤ መዝ51፥17፤109፥16፤ 119፥151፤145፥18፤ 147፥3፤ኢሳ50፥8፤ 61፥1
34፥19 ቍ17፤ኢዮ 5፥19፤መዝ25፥17፤ 2ጢሞ3፥11
34፥20 ዮሐ19፥36
34፥21 መዝ7፥9፤ 9፥16፤11፥5፤37፥20፤ 73፥27፤94፥23፤106፥ 43፤112፥10፤140፥11 ፤ምሳ14፥32፤24፥16
34፥22 ዘፀ6፥6፤ 15፥13፤መዝ2፥12፤ ሉቃ1፥68፤ራእ14፥3
35፥1 ዘፀ14፥14፤ 1ሳሙ24፥15
35፥2 ዘፍ50፥24፤ ኢዮ17፥3፤መዝ3፥3፡7
35፥3 ዘኍ25፥7፤ ኢሱ8፥18፤መዝ27፥1
35፥4 መዝ25፥3፤ 38፥12፤40፥14፤69፥6 ፡19፤70፥2፤83፥17፤ 129፥5፤ኢሳ45፥16፤ ኤር4፥30፤ሚል2፥9
35፥5 ኢዮ13፥25፤ መዝ1፥4፤34፥7
35፥7 ኢዮ9፥31፤ 18፥8፤መዝ7፥4፡15፤ 55፥23
35፥8 መዝ7፥15፤ ኢሳ47፥11፤1ተሰ5፥3
35፥9 መዝ2፥11፤ 9፥14፤13፥5፤27፥1፤ ሉቃ1፥47
35፥10 ዘፀ9፥14፤ መዝ12፥5፤18፥17፡31 ፤37፥14፤74፥21፤86፥1 ፤109፥16፤113፥5፤ 140፥12፤ኢሳ41፥17
35፥11 ዘፀ23፥1፤ ማቴ26፥60
35፥12 መዝ38፥20 ፤109፥5፤ምሳ17፥13 ፤ኤር18፥20
35፥13 2ሳሙ3፥31 ፤1ነገ20፥31፤ኢዮ 30፥25፤መዝ30፥11፤ 69፥10፡11፤109፥24
35፥14 መዝ38፥6፤ 42፥9፤43፥2
35፥15 ኢዮ16፥10፤ 31፥29
35፥16 ኢዮ16፥9፤ መዝ22፥7፤ማር9፥18፤ 10፥34፤ሐሥ7፥54
35፥17 መዝ6፥3፤ 22፥20፤22፥21፤ 57፥4፤58፥6
35፥18 መዝ22፥22 ፡25፤42፥4፤109፥30
35፥19 ቍ7፤መዝ 9፥13፤38፥19፤69፥4፤ ምሳ6፥13፤10፥10፤ ዮሐ15፥25
35፥20 መዝ38፥12፤55፥21፤ኤር9፥8፤ ሚክ6፥12
35፥21 ኢዮ16፥10፤መዝ40፥15፤70፥3፤ ሕዝ25፥3
35፥22 ዘፀ3፥7፤መዝ10፥1፡14

10 የሥራ አካላቴ እንዲህ ይልሃል፤
"እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ አንተ
ማን አለ?
ድኻውን ከእርሱ ከሚበረቱ፣
ችግረኛውንና ምስኪኑን ከቀማኞች
ታድናለህ"።

11 ጨካኝ ምስክሮች ተነሡ፤
ስለማላውቀውም ነገር ጠየቁኝ።
12 በበጎ ፈንታ ክፉ መለሱልኝ፤
ነፍሴንም ብቸኛ አደረጓት።
13 እኔ ግን እነርሱ በታመሙ ጊዜ
ማቅ ለበስሁ፤
ነፍሴንም በጾም አደከምኋት፤
ጸሎቴም መልስ አጥቶ ወደ ጕያዬ
ተመለሰ።

14 ለወዳጄ ወይም ለወንድሜ እንደ
ማደርግ፣
እየተንቈራጠጥሁ አለቀስሁ፤
ለእናቴም እንደማለቅስ፣
በሐዘን ዐንገቴን ደፋሁ።
15 እነርሱ ግን እኔ ስሰናከል በእልልታ
ተሰበሰቡ፤
ግፈኞች በድንገት ተሰበሰቡብኝ፤
ያለ ዕረፍትም ቦጫጨቁኝ።
16 እንደ ምናምንቴዎች አፌዙብኝ፤[ꟸ]
ጥርሳቸውንም አፋጩብኝ።
17 ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ ዝም ብለህ
ታያለህ?
ነፍሴን ከክፉ ሥራቸው፣
ብርቅ ሕይወቴን ከአንበሶች ታደጋት።
18 በታላቅ ጉባኤ መካከል አመሰግንሃለሁ፤
ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበትም
አወድስሃለሁ።

19 ከምድር ተነሥተው ጠላቶቼ የሆኑት፣
በላዬ ደስ አይበላቸው፤
እንዲያው የሚጠሉኝ፣
በዐይናቸው አይጣቀሱብኝ።
20 የሰላም ንግግር ከአፋቸው አይወጣም፤
ዳሩ ግን በምድሪቱ በጸጥታ በሚኖሩት
ላይ፣
ነገር ይሸርባሉ።
21 አፋቸውን አስፍተው ከፈቱብኝ፤
"ዕሠይ! ዕሠይ! በዐይናችን አየነው" አሉ።

22 እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህን አይተሃልና
ዝም አትበል፤
ጌታ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ።

[ʺ]3 ወይም … መንገድ ዝጋ
[ꟸ]16 ሰብዓ ሊቃናት እንዲሁ ሲሆን በዕብራይስጥ ግን ምናምንቴ ፌዘኞች ማለት ሊሆን ይችላል።

23ጽምባኬ፣ ጌታዬ፤ ለእኔ ለመሟገት ተነሥ!
ልትከራከርልኝም ተንቀሳቀስ።
24እግዚአብሔር ጽምባኬ ሆይ፤ በጽድቅህ
ፍረድልኝ፤
በእኔም ላይ ደስ አይበላቸው።
25በልባቸው፣ “ዕሠይ! ያሰብነው ተሳካ!
ዋጥ አደረግነውም” አይበሉ።
26በጭንቀቴ ደስ የሚላቸው፣
ይፈሩ፤ ግራም ይጋቡ፤
በእኔ ላይ ራሳቸውን ከፍ ከፍ
የሚያደርጉ፣
ዕፍረትንና ውርደትን ይከናነቡ።
27ፍትሕ ማግኘቴን የሚወዱ፣
እልል ይበሉ፤ ሐሤትም ያድርጉ፤
ዘወትርም፣ “የባርያው ሰላም ደስ
የሚለው፣
እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ይበል!” ይበሉ።
28አንደበቴ ጽድቅህን፣
ምስጋናህንም ቀኑን ሙሉ ይናገራል።

## መዝሙር 36

### የኀጥኡ ክፋት፣ የእግዚአብሔር በጎነት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝሙር*

1ክፉውን ሰው፣
በደል በልቡ ታናግረዋለች፤[የ]
እግዚአብሔርን መፍራት፣
በፊቱ የለም፤
2በደሉ ግልጽ ወጥቶ እንዳይጠላ፣
ራሱን በራሱ እጅግ ይሸነግላልና።
3ከአንደበቱ የሚወጣው የክፋትና የተን
ኰል ቃል ነው፤
ማስተዋልንና በጎ ማድረግን ትቶአል።
4በመኝታው ላይ ክፋትን ያውጠነጥናል፤
ራሱን በጎ ባልሆነ መንገድ ይመራል፤
ክፋትንም አያርቅም።

5*እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ እስከ
ሰማያት ይደርሳል፤
ታማኝነትህም እስከ ጠፈር
ይመጥቃል።*
6ጽድቅህ እንደ ታላላቅ ተራሮች፣
ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ነው፤
*እግዚአብሔር ሆይ፤* አንተ ሰውንም
እንስሳንም ታድናለህ።
7ጽምባክ ሆይ፤ ምሕረትህ እንዴት ክቡር
ነው!
የሰዎች ልጆች ሁሉ፣
በክንፎችህ ጥላ ሥር መጠጊያ ያገኛሉ።
8ከቤትህ ሲሳይ ይመገባሉ፤
ከበረከትህም ወንዝ ይጠጣሉ።
9የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና፤
በብርሃንህም ብርሃንን እናያለን።
10ለሚያውቁህ ምሕረትህ፣
ልባቸውም ለቀና ጽድቅህ ዘወትር
አይቋረጥባቸው።
11የትዕቢተኛ እግር በላዬ አይምጣ፤
የክፉውም ሰው እጅ አያሳደኝ።
12ክፉ አድራጊዎች እንዴት እንደ ወደቁና
እንደ ተጋደሙ፣
ቀ*ልቀ*ልም እንደ ተወረወሩና
መነሣት እንደማይችሉ ተመልከት!

## መዝሙር 37[ዶ]

### የጻድቁና የክፉው ዕጣ ፈንታ

*የዳዊት መዝሙር*

1ዐመፀኞችን በማየት አትሸበር፤
በክፉ አድራጊዎችም አትቅና፤
2እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፤
እንደ ለምለም ቅጠልም ይጠወልጋሉ።

3*በእግዚአብሔር ታመን፤ መልካምንም
አድርግ፤*
በምድሪቱ ተቀመጥ፤ ዘና ብለህ ተሰማራ።
4*በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፤*
የልብህንም መሻት ይሰጥሃል።
5*መንገድህን ለእግዚአብሔር* ዐደራ ስጥ፤
በእርሱ *ታመን፤* እርሱም
ያከናውንልሃል፤
6ጽድቅህን እንደ ብርሃን፣
ያንተን ፍትሕ እንደ ቀትር ፀሓይ
ያበራዋል።
7*በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል፤
በትዕግሥትም ተጠባበቀው፤
መንገዱ* በተቃናለት፣
ክፋትንም በሚሸርብ ሰው ልብህ
አይሸበር።

8ከንዴት ተቈጠብ፤ ቍጣንም ተወው፤
ወደ እኵይ ተግባር እንዳይመራህ
አትከፋ።
9ክፉ ሰዎች ይጠፋሉና፤
*እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን*
ምድርን ይወርሳሉ።

10ለአፍታ እንጂ፣ ክፉ ሰው አይዘልቅም፤
ስፍራውንም ብታስስ አታገኘውም።

35፥23 1ሳሙ24፥15፤መዝ7፥6፤17፥13፤80፥2
35፥24 መዝ22፥17
35፥25 ቍ21፤መዝ124፥3፤ምሳ1፥12፤ሰቆ2፥16
35፥26 ኢዮ8፥22፤19፥5፤መዝ4፥1፤22፥17፤38፥16፤109፥29፤ሚክ7፥10
35፥26 ኢዮ8፥22፤19፥5፤መዝ4፥1፤22፥17፤38፥16፤109፥29፤ሚክ7፥10
35፥27 ኢዮ17፥3፤መዝ9፥4፤20፥5፤33፥3፤መዝ147፥11፤149፥4
35፥28 መዝ5፥8፤51፥14፤71፥15፡24፤72፥15
36፥1 ኢዮ21፥6፤23፥15፤ኤር2፥19፤36፥16፡24፤ሮሜ3፥18
36፥2 ዘዳ29፥19
36፥3 ኢዮ5፥13፤መዝ5፥6፡9፤10፥7፤43፥1፤94፥8፤144፥8፡11፤ኢሳ44፥20፤ኤር4፥22፤13፥23፤አሞ3፥10
36፥4 መዝ52፥3፤ምሳ4፥16፤ኢሳ65፥2፤ሮሜ12፥9
36፥5 መዝ57፥10፤71፥19፤89፥1፡2፤103፥11፤108፥4፤119፥90
36፥6 ዘፍ1፥2፤7፥11፤ነህ9፥6፤መዝ5፥8፤68፥15፤104፥14፤145፥16
36፥7 ሩት2፥12፤መዝ6፥4፤17፥8፤57፥1፤91፥4
36፥8 ኢዮ20፥17፤መዝ23፥2፤63፥5፤65፥4፤ኢሳ25፥6፤ኤር31፥12፡14፤ራእ22፥1
36፥9 መዝ4፥6፤27፥1፤76፥4፤87፥7፤104፥2፤ምሳ10፥11፤16፥22፤ኢሳ2፥5፤9፥2፤60፥1፡19፤ኤር2፥13፤ዮሐ1፥4፤1ጴጥ2፥9
36፥10 መዝ7፥10፤11፥2፤94፥15፤125፥4፤ኤር9፥24፤22፥16፤31፥3
36፥11 መዝ71፥4፤140፥4
36፥12 መዝ18፥38
37፥1 መዝ73፥3፤ምሳ3፥31፤23፥17-18፤24፥19
37፥2 ቍ38፤2ነገ19፥26፤ኢዮ14፥2፤መዝ90፥6፤92፥7፤102፥4፤ኢሳ40፥7፤ያዕ1፥10
37፥3 ዘዳ30፥20፤ሕዝ34፥14፤ዮሐ10፥9
37፥4 ኢዮ7፥6፤27፥10፤መዝ21፥2፤145፥19፤ማቴ6፥33

37፥5 መዝ4፥5 37፥6 ኢዮ11፥17፤መዝ18፥24፤103፥17፤112፥3 37፥7 ቍ1፤ዘፀ14፥14፤መዝ21፥11፤26፥10፤27፥14፤40፥1፤119፥150፤130፥5፤ኢሳ38፥13፤41፥1፤ኤር12፥1፤ዕን3፥16፤ኤር12፥1፤ዕን3፥16፤ሮሜ8፥25 37፥8 ቍ1፤ኤፌ4፥31፤ቈላ3፥8 37፥9 ቍ22፤መዝ25፥13፤31፥22፤101፥8፤ 118፥10፤ምሳ2፥22፤ኢሳ25፥9፤26፥8፤40፥31፤49፥8፡23፤51፥5፤57፥13፤ማቴ5፥5 37፥10 ኢዮ7፥10፤ሕዝ27፥36

[የ]1 ወይም ... *ኀጢአት ከኀጥእ ይመነጫል*
[ዶ]ም37 የዚህ መዝሙር እያንዳንዱ ጥቅስ ተከታታይ ፊደላት ባሉት የዕብራይስጥ ሆህያት የሚጀምር ሲሆን ጅማ ሬው ወይም ጅማሬውና መጨረሻው ትርጕም የሚ ሰጥ ግጥም ነው።

11ገሮች ግን ምድርን ይወርሳሉ፤
በታላቅ ሰላምም ሐሤት ያደርጋሉ።
12ክፉዎች በጻድቃን ላይ ያሤራሉ፤
ጥርሳቸውንም ያፏጩባቸዋል።
13እግዚአብሔር ግን ይሥቅባቸዋል፤
ቀናቸው እንደ ደረሰ ያውቃልና።
14ድኾችንና ችግረኞችን ለመጣል፣
አካሄዳቸው ቀና የሆነውንም
ለመግደል፣
ክፉዎች ሰይፋቸውን መዘዙ፤
ቀስታቸውንም ገተሩ።
15ሰይፋቸው የገዛ ልባቸውን ይወጋል፤
ቀስታቸውም ይሰበራል።
16የጻድቅ ጥቂት ሀብት፣
ከክፉዎች ብዙ ጥሪት ይበልጣል።
17የክፉዎች ክንድ ይሰበራልና፤
ጻድቃንን ግን *እግዚአብሔር* ደግፎ
ይይዛቸዋል።
18*እግዚአብሔር* የንጹሐንን የሕይወት
ዘመን ያውቃል፤
ርስታቸውም ለዘላለም ይኖራል።
19በክፉ ጊዜ ዕንገት አይደፉም፤
በራብ ዘመንም ይጠግባሉ።
20ክፉዎች ግን ይጠፋሉ፤
የ*እግዚአብሔር* ጠላቶች እንደ መስክ
ውበት ይሆናሉ፤
ይጠፋሉ፤ እንደ ጢስም ተነው ይጠፋሉ።
21ኀጢአተኛ ይበደራል፤ መልሶም
አይከፍልም፤
ጻድቅ ግን ይቸራል።
22*እግዚአብሔር* የባረካቸው ምድርን
ይወርሳሉ፤
እርሱ የሚረግማቸው ግን ይጠፋሉ።
23የሰው አካሄድ በ*እግዚአብሔር* ይጸናል፤
በመንገዱ ደስ ይለዋል።
24ቢሰናከልም አይወድቅም፤
*እግዚአብሔር* በእጁ ደግፎ ይይዘዋልና።
25ጐልማሳ ነበርሁ፤ አሁን አርጅቻለሁ፤
ነገር ግን ጻድቅ ሲጣል፣
ዘሩም እንጀራ ሲለምን አላየሁም።
26ሁልጊዜ ቸር ነው፤ ያበድራልም፤
ልጆቹም የተባረኩ ይሆናሉ።
27ከክፉ ራቅ፤ መልካሙንም አድርግ፤
ለዘላለምም ትኖራለህ።
28*እግዚአብሔር* ፍትሕን ይወዳልና፤
ታማኞቹንም አይጥልም፤
ለዘላለምም ይጠብቃቸዋል፤
የኀጢአተኛው ዘር ግን ይጠፋል።
29ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ፤
በእርሷም ለዘላለም ይኖራሉ።
30የጻድቅ አፍ ጥበብን ይናገራል፤
አንደበቱም ፍትሐዊ ነገር ያወራል።
31የአምላኩ ሕግ በልቡ አለ፤
አካሄዱም አይወላገድም።
32ክፉዎች ጻድቁን ይከታተሉታል፤
ሊገድሉትም ይሻሉ።
33*እግዚአብሔር* ግን በእጃቸው
አይጥለውም፤
ፍርድ ፊት ሲቀርብም አሳልፎ
አይሰጠውም።
34*እግዚአብሔርን* ደጅ ጥና፤
መንገዱንም ጠብቅ፤
ምድሪቱን ትወርስ ዘንድ ከፍ ከፍ
ያደርግሃል፤
ክፉዎችም ሲጠፉ ታያለህ።
35ክፉና ጨካኙን ሰው፣
እንደ ሊባኖስ ዝግባ ለምልሞ አየሁት፤
36ዳግመኛ በዚያ ሳልፍ፣ እነሆ፣ በቦታው
አልነበረም፤
ብፈልገውም አልተገኘም።
37ንጹሐንን ልብ በል፤ ቅኑንም አስተውል፤
የሰላም ሰው ተስፋ አለውና።[ጀ]
38ኀጢአተኞች ግን በአንድነት ይጠፋሉ፤
የክፉዎችም ዘር[ገ] ይወገዳል።
39የጻድቃን ድነት ከ*እግዚአብሔር* ዘንድ
ነው፤
በመከራ ጊዜም መጠጊያቸው እርሱ
ነው።
40*እግዚአብሔር* ይረዳቸዋል፤
ይታደጋቸዋልም፤
ከክፉዎች እጅ ነጥቆ ያወጣቸዋል፤
እርሱን መጠጊያ አድርገዋልና
ያድናቸዋል።

## *መዝሙር* 38

## የጭንቅ ሰዓት ጸሎት

*የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ በቍጣህ አትገሥጸኝ፤
በመዓትህም አትቅጣኝ።
2ፍላጻዎችህ ወግተውኛልና፤
እጅህም ተጭናኛለች።
3ከቍጣህ የተነሣ ሰውነቴ ጤና አጥቶአል፤
ከኀጢአቴም የተነሣ ዐጥንቶቼ ሰላም
የላቸውም።
4በደሌ ውጦኛል፤
እንደ ከባድ ሸክምም ተጭኖኛል።

**37፥11** ዘሌ26፥6፤ ዘኍ6፥26፤14፥24፤ ማቴ5፥5
**37፥12** ኢዮ16፥9፤ መዝ2፥1፤31፥12፤ 35፥16፤112፥10
**37፥13** 1ሳሙ26፥10፤ ሕዝ12፥23
**37፥14** መዝ11፥2፤ 22፥20፤35፥10
**37፥15** 1ሳሙ2፥4፤ መዝ9፥16፤46፥9፤ ኤር49፥35
**37፥16** ምሳ15፥16፤ 16፥8
**37፥17** ኢዮ38፥15፤ መዝ10፥15፤41፥12፤ 140፥12፤145፥14፤ 146፥7
**37፥18** ቍ27፡29፤ ኢዮ23፥10፤ መዝ 44፥21
**37፥20** መዝ34፥21 ፤68፥2፤102፥3፤ ኢሳ 51፥6
**37፥21** ዘሌ25፥35፤ መዝ112፥5
**37፥22** ቍ9፤ ኢዮ 5፥3
**37፥23** ዘኍ14፥8፤ ኢዮ11፥15፤መዝ 7፥9፤66፥9፤147፥11
**37፥24** 2ዜና9፥8፤ መዝ 13፥4፤27፥2፤ 38፥17፤41፥12፤55፥22 ፤119፥165፤145፥14፤ ምሳ3፥23፤10፥9
**37፥25** ቍ28፤ ዘፍ51፥1፤መዝ111፥5፤ 145፥15፤ማር10፥46፤ ዕብ 13፥5
**37፥26** ዘሌ25፥35፤ ዘዳ28፥4፤መዝ112፥2
**37፥27** ዘኍ24፥21 ፤መዝ34፥14፤ 3ዮሐ1፥11
**37፥28** ዘፍ17፥14፤ ዘዳ7፥6፤32፥26፤ መዝ18፥25፤97፥10፤ ምሳ2፥22
**37፥29** ቍ9፤ ምሳ2፥21፤ኢሳ34፥17
**37፥30** መዝ49፥3፤ ምሳ10፥13
**37፥31** ዘዳ6፥6፤ 32፥35፤ኢዮ22፥22
**37፥32** መዝ10፥8፤ 11፥5
**37፥33** ኢዮ32፥3፤ መዝ34፥22፤79፥11፤ 2ጴጥ2፥9
**37፥34** ቍ9፤ መዝ18፥21፤ 27፥14፤52፥6
**37፥35** ኢዮ5፥3
**37፥36** ቍ10፤ ምሳ12፥7፤ኢሳ41፥12፤ ዳን 11፥9
**37፥37** ቍ18፤ ዘፍ6፥9፤መዝ11፥7፤ 18፥25 ፤ኢሳ57፥1-2
**37፥38** ቍ2፡9፤መዝ 1፥1፤73፥19 **37፥39** መዝ3፥8፤9፥9 **37፥40** 1ዜና5፥20፤መዝ 2፥12፤18፥48፤20፥2፤34፥7 **38፥1** መዝ6፥1 **38፥2** ኢዮ6፥4 **38፥3** ኢዮ33፥19፤ምሳ3፥8፤ኢሳ4፥22፤66፥14 **38፥4** ዘኍ11፥14፤ ዕዝ9፥6፤መዝ40፥12፤65፥3፤ሉቃ11፥46

[ጀ]37 ወይም *ዘር ይወጣለታል* [ገ]38 ወይም *ትውልድ*

5 ከንዝህላልነቴ የተነሣ፣
ቍስሌ ሸተተ፤ መገለም፤
6 ዐንገቴን ደፋሁ፤ ጐበጥሁም፤
ቀኑንም ሙሉ በትካዜ ተመላለስሁ::
7 ወገቤ እንደ እሳት ነዶአል፤
ሰውነቴም ጤና የለውም::
8 እጅግ ዝያለሁ፤ ፈጽሞም ደቅቄአለሁ፤
ከልቤም መታወክ የተነሣ እጮኻለሁ::

9 ጌታ ሆይ፤ ምኞቴ ሁሉ በፊትህ
ግልጽ ነው፤
ጭንቀቴም ከአንተ የተሰወረ አይደለም::
10 ልቤ በኀይል ይመታል፤ ጕልበት
ከድቶኛል፤
የዐይኔም ብርሃን ጠፍቶአል::
11 ከቍስሌ የተነሣ ወዳጆቼም
ባልንጀሮቼም ሸሹኝ፤
ጎረቤቶቼም ርቀው ቆሙ::
12 ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ ወጥመድ
ዘረጉብኝ፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ ሊያጠፉኝ ዛቱ፤
ቀኑንም ሙሉ ተንኰል ይሸርባሉ::

13 እኔ ግን እንደማይሰማ ደንቈሮ፣
አፉንም መክፈት እንደማይችል ዲዳ
ሆንሁ::
14 በእርግጥም ጆሮው እንደማይሰማ፣
አንደበቱም መልስ መስጠት
እንደማይችል ሰው ሆንሁ::
15 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በተስፋ
እጠብቅሃለሁ፤
ጌታ አምላኬ ሆይ፤ አንተ መልስ
ትሰጠኛለህ::
16 እኔ፣ "ጠላቶቼ በእኔ ላይ ደስ
አይበላቸው፤
እግሬም ሲንሸራተት፣ በላዬ
አይኵራሩብኝ" ብያለሁና::

17 ልወድቅ ተቃርቤአለሁ፤
ከሥቃዬም ከቶ አልተላቀቅሁም::
18 በደሌን እናዘዛለሁ፤
ኀጢአቴም አውካኛለች::
19 ብርቱዎች ጠላቶቼ ብዙ ናቸው፤
ያለ ምክንያት የሚጠሉኝም ስፍር
ቍጥር የላቸውም::
20 መልካሙን ስለ ተከተልሁ፣
በበጎ ፈንታ ክፉ የሚመልሱልኝ
ጠሉኝ::

21 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አትተወኝ፤
አምላኬ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ::
22 ጌታዬ መድኀኔ ሆይ፤
እኔን ለመርዳት ፍጠን::

38፥5 ቍ11፤ ኢዮ19፥17፤መዝ69፥5፤ 147፥3፤ምሳ5፥23፤12፥ 23፤13፥16፤መክ10፥3
38፥6 መዝ35፥14፤ 57፥6፤145፥14፤146፥8
38፥7 ቍ3፤ ኢዮ 14፥22
38፥8 መዝ6፥3፡6፤ 22፥1፤34፥18፤ ምሳ5፥11፤17፥22
38፥9 ኢዮ3፥24፤ መዝ119፥20፤143፥7
38፥10 ኢዮ37፥1፤ መዝ6፥7፤19፥8፤ 31፥10፤88፥9
38፥11 ቍ5
38፥12 መዝ31፥4፤ 35፥4፡20፤41፥5፤ 140፥5፤141፥9
38፥13 መዝ115፥6 ፤135፥17፤ኢሳ43፥8፤ ማር7፥37
38፥15 መዝ17፥6፤ 27፥14
38፥16 ዘዳ32፥35፤ መዝ22፥17
38፥17 ቍ7፤ ኢዮ6፥10፤መዝ37፥24
38፥18 ዘሌ26፥40
38፥19 መዝ18፥17 ፤25፥19፤35፥19
38፥20 ዘፍ44፥4፤ መዝ54፥5፤59፥10፤ 119፥23፤1ዮሐ3፥12
38፥21 መዝ10፥1፤ 22፥11፤27፥9፤35፥22 ፤71፥12፡18፤119፥8
38፥22 1ዜና16፥35 ፤መዝ22፥19፤40፥13
39፥1 1ነገ2፥4፤ ኢዮ 1፥22፤6፥24፤ መዝ34፥13፤119፥9፡ 59፤ምሳ20፥11፤ ያዕ1፥26፤3፥2
39፥2 ቍ9፤ኢዮ 31፥34፤መዝ6፥3፤ 25፥17፤31፥10፤77፥4
39፥3 መዝ1፥2፤48፥9 ፤77፥12፤119፥15፤ ኤር5፥14፤20፥9፤ 23፥29፤ሉቃ24፥32
39፥4 ዘፍ47፥9፤ ኢዮ7፥7፤14፥2፡5
39፥5 ኢዮ7፥7፤ 10፥20፤መዝ62፥9፤ 89፥45፤102፥23
39፥6 ኢዮ8፥9፤27፥17 ፤መዝ102፥11፤127፥2 ፤መክ6፥12፤ሉቃ12፥20 ፤ያዕ1፥11፤4፥14
39፥7 መዝ9፥18፤ 25፥5
39፥8 ዘዳ28፥37፤ መዝ6፥4፤32፥1፤51፥1 ፡14፤69፥7፤79፥4፤ ኢሳ 43፥28፤53፥5፡ 8፡10፤ዳን9፥16
39፥9 ቍ2፤ መዝ38፥13፤ኢሳ38፥15
39፥10 ዘፀ9፥3 ፤2ዜና21፥14

## መዝሙር 39
### ታላቅ እግዚአብሔር - ታናሽ ሰው

*ለመዘምራን አለቃ፣ ለኤዶታም፤ የዳዊት መዝሙር*

1 እኔ፣ "በአንደበቴ እንዳልበድል፣
መንገዴን እጠብቃለሁ፤
ክፉዎችም በእኔ ዘንድ እስካሉ ድረስ፣
ልጓም በአፌ አስገባለሁ" አልሁ::
2 እንደ ዲዳ ዝም አልሁ፤
ለበጎ ነገር እንኳ አፌን ዘጋሁ፤
ሆኖም ጭንቀቴ ባሰ::
3 ልቤ በውስጤ ጋለ፤
በማሰላስልበትም ጊዜ እሳቱ ነደደ፤
ከዚያም በአንደበቴ እንዲህ ተናገርሁ፤

4 "*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሕይወቴን ፍጻሜ፣
የዘመኔንም ቍጥር አስታውቀኝ፤
አላፊ ጠፊ መሆኑንም ልረዳ::
5 እነሆ፤ ዘመኔን በስንዝር ለክተህ
አስቀመጥህ፤
ዕድሜዬም በፊትህ እንደ ኢምንት
ነው፤
በእርግጥ የሰው ሁሉ ሕይወት ተን
ነው:: ሴላ
6 ሰው የጥላ ውልብታ ነው፤
በከንቱም ይታወካል፤
ለማን እንደሚሆን ሳያውቅ ሀብት
ንብረት ያከማቻል::

7 "ጌታ ሆይ፤ አሁንስ ወደ ማን ልመልከት?
ተስፋዬ በአንተ ላይ ነው::
8 ከኀጢአቴ ሁሉ አድነኝ፤
የሰነፎች መሣለቂያ አታድርገኝ::
9 ይህን ያደረግህ አንተ ነህና፣
ዝም እላለሁ፤ አፌንም አልከፍትም::
10 ክንድህን አንሣልኝ፤
ከእጅህ ምት የተነሣ ደክሜአለሁና::
11 ሰዎችን ስለ ኀጢአታቸው ለመቅጣት
ትገሥጻቸዋለህ፤
ሀብታቸውንም ብል እንደ በላው
ታደርጋለህ፤
በእርግጥ ሰው ሁሉ ተን ብቻ ነው::
ሴላ
12 "*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ጩኸቴን አድምጥ፤
ልቅሶዬንም ቸል አትበል፤
በአንተ ፊት እኔ መጻተኛ ነኝና፤
እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝ::
13 ላለመመለስ ከመሰናበቴ በፊት፣
ዳግመኛ ደስ ይለኝ ዘንድ ዐይንህን
ከላዬ አንሣ::

ሕዝ7፥9፤24፥16 39፥11 ዘዳ28፥20፤ኢዮ7፥7፤13፥28፤መዝ90፥7፤ 94፥10፤ኢሳ26፥16፤51፥8፤66፥15፤ሕዝ5፥15፤ሉቃ12፥33፤ያዕ5፥2፤ 2ጴጥ2፥16 39፥12 ዘፍ23፥4፤47፥9፤ዘሌ25፥23፤ዘዳ1፥45፤2ነገ 20፥5፤1ዜና29፥15፤መዝ17፥1፤ዕብ11፥13 39፥13 ኢዮ10፥21

## *መዝሙር* 40
## የምስጋናና የርዳታ ልመና ጸሎት

40፥13-17 ተጓ ምብ-መዝ70፥1-5

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1*እግዚአብሔርን* ደጅ ጠናሁት፤
እርሱም ዘንበል አለልኝ፤ ጩኸቴንም ሰማ።
2ከሚውጥ ጕድጓድ፣
ከሚያዘቅጥ ማጥ አወጣኝ፤
እግሮቼን በዐለት ላይ አቆመ፤
አካሄዴንም አጸና።
3ለአምላካችን የሚሆን ውዳሴ፣
አዲስ ዝማሬን በአፌ ላይ አኖረ፤
ብዙዎች ያያሉ፤ ይፈራሉም፤
*በእግዚአብሔር* ይታመናሉ።

4*እግዚአብሔርን* መታመኛው ያደረገ፣
ወደ ትዕቢተኞች የማይመለከት፣
የሐሰት አማልክትን[ጠ] ወደሚከተሉት
የማያይ፣
ሰው ብፁዕ ነው።
5*እግዚአብሔር* አምላኬ ሆይ፤
አንተ ያደረግኸው ድንቅ ነገር ብዙ ነው፤
ለእኛ ያቀድኸውን፣
ሊዘረዝርልህ የሚችል ማንም የለም፤
ላውራው ልናገረው ብል፣
ስፍር ቍጥር አይኖረውም።

6መሥዋዕትንና ቍርባንን አልፈለግህም፤
ጆሮቼን ግን ከፈትህ፤[ጨ]
የሚቃጠል መሥዋዕትን፣
የኀጢአትንም መሥዋዕት አልሻህም።
7እኔም እንዲህ አልሁ፤ "እነሆ፤
መጥቻለሁ፤
ስለ እኔ በመጽሐፍ ተጽፎአል፤
8አምላኬ ሆይ፤ ፈቃድህን ላደርግ እሻለሁ፤
ሕግህም በልቤ ውስጥ አለ።"
9በታላቅ ጉባኤ ውስጥ ጽድቅን አበሥርሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ
እንደምታውቀው፣
ከንፈሮቼን አልገጠምሁም።
10ጽድቅህን በልቤ አልሸሸግሁም፤
ታማኝነትህንና ማዳንህን እናገራለሁ፤
ምሕረትህንና እውነትህን፣
ከታላቅ ጉባኤ አልደበቅሁም።

11*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህን
አትንፈገኝ፤
ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር
ይጠብቁኝ፤
12ስፍር ቍጥር የሌለው ክፋት ከቦኛልና፤
የኀጢአቴ ብዛት ስለ ያዘኝ ማየት
ተስኖኛል፤
ከራሴ ጠጕር ይልቅ በዝቶአል፤
ልቤም ከድቶኛል።

13*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ታድነኝ ዘንድ
ፈቃድህ ይሁን፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔን ለመርዳት
ፍጠን።
14ነፍሴን ለመንጠቅ የሚፈልጉ፣
ይፈሩ፤ ይዋረዱም፤
ጕዳቴንም የሚሹ፣
ተዋርደው በመጡበት ይመለሱ።
15በእኔ ላይ፣ "እሰይ! እሰይ!" የሚሉ፣
በራሳቸው እፍረት ይደንግጡ።
16አንተን የሚፈልጉ ሁሉ ግን፣
ሐሤት ያድርጉ፤ በአንተም ደስ
ይበላቸው፤
ዘወትር የአንተን ማዳን የሚወዱ፣
"*እግዚአብሔር* ከፍ ከፍ ይበል"
ይበሉ።

17እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝ፤
ጌታ ግን ያስብልኛል።
አንተ ረዳቴና አዳኜ ነህ፤
አምላኬ ሆይ፤ አትዘግይ።

## *መዝሙር* 41
## የሕመምተኛና የብቸኛ ሰው ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1ለድኾች የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው፤
እርሱንም *እግዚአብሔር* በክፉ ቀን
ይታደገዋል።
2*እግዚአብሔር* ይጠብቀዋል፤ በሕይወትም
ያኖረዋል፤
በምድርም ላይ ይባርከዋል፤
ለጠላቶቹም ምኞትም አሳልፎ
አይሰጠውም።
3ታሞ ባለበት ዐልጋ ላይ *እግዚአብሔር*
ይንከባከበዋል፤
በበሽታውም ጊዜ መኝታውን
ያነጥፍለታል።

4እኔም፣ "*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረት
አድርግልኝ፤
አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት"
አልሁ።
5ጠላቶቼ በክፋት በመናገር፣
"የሚሞተው መቼ ነው? ስሙስ
የሚደመሰሰው ምን ቀን ነው?"
ይላሉ።
6ሊጠይቀኝ የሚመጣ ቢኖር፣
በልቡ ስድብ እያጠራቀመ፣ ከዐንገት
በላይ ይናገራል፤

40፥1 መዝ6፥9፤ 31፥22፤34፥15፤37፥7፤116፥1፤145፥19
40፥2 ኢዮ9፥31፤ 30፥19፤መዝ7፥15፤ 27፥5፤31፥8፤69፥14
40፥3 ዘፀ14፥31፤ መዝ 28፥7፤52፥6፤ 64፥9፤96፥1፤ራእ5፥9
40፥4 ዘዳ31፥20፤ መዝ4፥2፤26፥1፤34፥8፤84፥12፤101፥5፤138፥6፤ምሳ3፥34፤16፥5፤ ኢሳ65፥5፤1ጴጥ5፥5
40፥5 ዘዳ4፥34፤ መዝ 71፥15፤75፥1፤ 105፥5፤136፥4፤ 139፥17፡18
40፥6 ዘፀ21፥6፤ 1ሳሙ 15፥22፤ መዝ50፥8፤ 51፥16፤ኢሳ1፥11፤ ኤር6፥20፤ ሆሴ6፥6፤አሞ5፥22
40፥7 ኢዮ19፥23፤ ኤር36፥2፤45፥1፤ ሕዝ 2፥9፤ዘካ5፥1
40፥8 ዘዳ6፥6፤ ኢዮ 22፥22፤ ማቴ26፥39፤ ሮሜ7፥22፤ ዕብ10፥5-7
40፥9 ኢሱ22፥22፤ መዝ22፥25፡31
40፥10 መዝ22፥22፤89፥1
40፥11 መዝ26፥3፤ 61፥7፤ምሳ20፥28፤ ዘካ1፥12
40፥12 መዝ25፥17፤38፥4፤65፥3፤ 69፥4፤73፥26
40፥13 መዝ22፥19፤38፥22
40፥14 1ሳሙ20፥1፤አስ9፥2፤ መዝ35፥4፡26
40፥15 መዝ35፥21
40፥16 ዘዳ4፥29፤ 1ዜና28፥9፤መዝ9፥2፡ 10፤35፥27፤119፥2
40፥17 መዝ18፥2፤ 20፥2፤86፥1፤109፥22፤119፥60፤144፥3
41፥1 ዘዳ14፥29፤ ኢዮ24፥4፤25፥17
41፥2 ዘዳ6፥24፤ ዕዝ 9፥9፤መዝ12፥5፤ 32፥7፤37፥22፤71፥20፤ 119፥88፡159፤ 138፥7፤143፥11
41፥3 2ሳሙ13፥5፤2ነገ1፥4፤መዝ6፥6
41፥4 ዘዳ32፥39፤6፥2፤9፥13፤51፥4
41፥5 መዝ38፥12
41፥6 ዘሌ19፥16፤ መዝ12፥2፤101፥7፤ ምሳ26፥24፤ማቴ5፥11

[ጠ]4 ወይም *ሐሰትን ወደሚከተሉት* ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ጨ]6 ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *አካልን ግን አዘጋጀህልኝ* ይላል።

ወጥቶም ወሬ ይነዛል።
7ጠላቶቼ ሁሉ ግንባር ፈጥረው
ይንሾካሾኩብኛል፤
እንዲህ እያሉም፣
የከፋ ነገር በላዬ ያውጠነጥናሉ፤
8“ክፉ ደዌ ይዞታል፤
ከእንግዲህም ከተኛበት አይነሣም።”
9እንጀራዬን ተካፍሎኝ የበላ፣
የምተማመንበትም የቅርብ ወዳጄ፣
በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።

10*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ግን ምሕረት
አድርግልኝ፤
የእጃቸውን እንድከፍላቸው አስነሣኝ።
11ጠላቴ በላዬ ድል አላገኘምና፣
እንደ ወደድኸኝ በዚህ ዐወቅሁ።
12ስለ ቅንነቴ ደግፈህ ይዘኸኛል፤
በፊትህም ለዘላለም ታኖረኛለህ።

13የእስራኤል አምላክ *እግዚአብሔር*፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም የተባረከ ይሁን፤
አሜን፤ አሜን።

## ሁለተኛ መጽሐፍ
## ከ*መዝሙር* 42-72

### *መዝሙር* 42[ጸ]
### በስደት ላይ ያለ ሌዋዊ ልቅሶ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት።*

1ዋላ የምንጭ ውሃ እንደምትናፍቅ፣
አምላክ ሆይ፤ ነፍሴም እንዲሁ አንተን
ትናፍቃለች።
2ነፍሴ አምላክን፣ ሕያው አምላክን
ተጠማች፤
መቼ ደርሼ ነው የአምላክን ፊት
የማየው?
3ሰዎች ቀኑን ሙሉ፣
“አምላክህ የት አለ?” ባሉኝ ቍጥር፣
እንባዬ ቀንና ሌሊት፣
ምግብ ሆነኝ።
4ነፍሴ በውስጤ እየፈሰሰች፣
እነዚህን ነገሮች አስታወስሁኝ፤
ታላቅ ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ቤት እየመራሁ፣
በእልልታና በምስጋና መዝሙር፣
በዓል በሚያከብር በአእላፍ ሕዝብ
መካከል፣
እንዴት ከሕዝቡ ጋር እሄድ እንደ
ነበር ትዝ አለኝ።
5ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤
አዳኜና 6አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።
ነፍሴ በውስጤ ተክዛለች፤
ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር፣
በአርሞንኤም ከፍታ፣
በሚዛር ተራራ አስብሃለሁ።
7በፏፏቴህ ማስገምገም፣
አንዱ ጥልቅ ሌላውን ጥልቅ ይጣራል፤
ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ፣
ሙሉ በሙሉ አጥለቀለቀኝ።

8*እግዚአብሔር* ምሕረቱን በቀን ያዝዛል፤
ዝማሬውም በሌሊት በእኔ ዘንድ አለ፤
ይህም ለሕይወቴ አምላክ የማቀርበው
ጸሎት ነው።

9እግዚአብሔር ዐለቴን፣
“ለምን ረሳኸኝ?
ጠላትስ እያስጨነቀኝ፣
ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?” እለዋለሁ።
10ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ፣
“አምላክህ የት አለ?” እያሉ፣
በነገር ጠዘጠዙኝ፣
ዐጥንቴም ደቀቀ።

11ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፣
አዳኜና አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።

### *መዝሙር* 43[ጸ]
### በስደት ላይ ያለ ሌዋዊ ልቅሶ

1አምላክ ሆይ፤ ፍረድልኝ፤
ከጽድቅ ከራቀ ሕዝብ ጋር ተሟገትልኝ፤
ከአታላዮችና ከክፉዎች ሰዎችም አድነኝ።
2አምላክ ሆይ፤ አንተ ብርታቴ ነህና፣
ለምን ተውኸኝ?
ጠላትስ እያስጨነቀኝ፣
ለምን በሐዘን እመላለሳለሁ?
3ብርሃንህንና እውነትህን ላክ፤
እነርሱ ይምሩኝ፤
ወደ ተቀደሰው ተራራህ፣
ወደ ማደሪያህ ያድርሱኝ።

4እኔም ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ አቀናለሁ፤
ፍጹም ደስታዬ ወደ ሆነው አምላክ
እሄዳለሁ፤
እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፣
በበገና አመሰግንሃለሁ።

5ነፍሴ ሆይ፤ ለምን ትተክዢያለሽ?
ለምንስ በውስጤ ትታወኪያለሽ?
ተስፋሽን በአምላክ ላይ አድርጊ፤
አዳኜና አምላኬን፣
ገና አመሰግነዋለሁና።

[ጸ]ም42 በብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች መዝ 42 እና 43 አንድ *መዝሙር* ነው።
[ጸ]43 በብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች መዝ 42 እና 43 አንድ *መዝሙር* ነው።

41፥7 መዝ71፥10
41፥8 2ነገ1፥4
41፥9 ዘኍ30፥2፤ 2ሳሙ15፥12፤ ኢዮ19፥14፡19፤ መዝ55፥20፤89፥34፤ ማቴ26፥23፤ ሉቃ22፥21፤ዮሐ13፥18
41፥10 ቍ4፤ 2ሳሙ3፥39፤ መዝ3፥3፤9፥13
41፥11 ዘኍ14፥8፤ መዝ25፥2
41፥12 ኢዮ4፥7፤ መዝ 18፥35፤21፥6፤ 25፥21፤37፥17፤ 61፥7፤63፥8
41፥13 ዘፍ24፥27፤ መዝ72፥18፡19፤ 89፥52፤106፥48
42፥1 ዘዳ10፥7ኢዮ 19፥27፤መዝ18፥33፤ 119፥131፤ኢል1፥20
42፥2 ኢሱ3፥10፤ 1ሳሙ14፥39፤መዝ43፥4 ፤63፥1፤84፥7፤143፥6፤ ማቴ16፥16፤ሮሜ9፥26
42፥3 ቍ10፤ ኢዮ3፥24፤ መዝ79፥10፤115፥2፤ ኢል2፥17፤ሚክ7፥10
42፥4 ኢሱ6፥5፤ 1ሳሙ1፥15፤ዕዝ3፥13 ፤መዝ35፥18፤55፥14 ፤95፥2፤100፥4፤109፥30 ፤122፥1፤147፥7፤ኢሳ 2፥2፤30፥29፤ዮና2፥9
42፥5 ኢዮ20፥2፤ መዝ 9፥1፤18፥46፤ 25፥5፤38፥6፤71፥14፤ 77፥3፤ሰቆ3፥20፤ ማቴ26፥38
42፥6 ቍ11፤ዘፍ 13፥10፤ዘኍ13፥29፤ ዘዳ3፥8፤4፥48፤መዝ 43፥5፤63፥6፤77፥11
42፥7 ዘፍ1፥2፤7፥11 ፤መዝ69፥2፤ዮና2፥3
42፥8 መዝ16፥7፤ 57፥3፤77፥6፤133፥3፤ መክ5፥18፤8፥15
42፥9 ኢዮ20፥19፤ መዝ9፥13፤10፥11፤ 18፥31፤35፥14፤ 43፥2፤106፥42
42፥10 ቍ3፤ ዘዳ32፥27፤መዝ6፥2፤ 44፥16፤89፥51፤ 102፥8፤119፥42
42፥11 ቍ5፤መዝ43፥5
43፥1 መሳ6፥31፤ መዝ25፥20፤36፥3፤ 109፥2
43፥2 መዝ35፥14፤ 42፥9፤44፥9፤74፥1፤ 88፥14፤89፥38
43፥3 2ሳሙ15፥25 ፤መዝ2፥6፤25፥5፤ 26፥3፤27፥1
43፥4 ዘፍ 4፥21፤ መዝ16፥3፤21፥6፤ 26፥6፤42፥2፤84፥3
43፥5 መዝ 42፥6

## *መዝሙር* 44

### ብሔራዊ ሰቆቃ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት።*[θ]

1አምላክ ሆይ፤ በጆሮአችን ሰምተናል፤
አባቶቻችን በቀድሞ ዘመን፣
እነርሱ በነበሩበት ዘመን፣
ያደረግኸውን ነግረውናል።
2ሕዝቦችን በእጅህ አሳደህ አወጣሃቸው፤
አባቶቻችንን ግን ተከልሃቸው፤
ሕዝቦችን አደቀቅህ፤
አባቶቻችንን ግን ነጻ አወጣሃቸው።
3ምድሪቱን የወረሱት በሰይፋቸው
አልነበረም፤
ድልንም የተጐናጸፉት በክንዳቸው
አይደለም፤
አንተ ወደሃቸዋልና ቀኝ እጅህ፣
ክንድህና የፊትህ ብርሃን ይህን
አደረገ።

4እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ንጉሤ ነህ፤[ፊ]
ያዕቆብም ድል እንዲያደርግ የወሰንህ
አንተ ነህ።
5በአንተ ጠላቶቻችን በመጡበት እንዲ
መለሱ እናደርጋለን፤
በስምህም ባላጋራዎቻችንን ከእግራችን
በታች እንረግጣለን።
6በቀስቴ አልተማመንም፤
ሰይፌም አያስጥለኝም።
7አንተ ግን በጠላቶቻችን ላይ ድልን
ትሰጠናለህ፤
ባላንጣዎቻችንንም ታሳፍራለህ።

8ዘወትር በእግዚአብሔር እንመካለን፤
ስምህንም ለዘላለም እንወድሳለን። ሴላ

9አሁን ግን እነሆ ትተኸናል፤
አሳፍረኸናልም፤
ከሰራዊታችንም ጋር አትወጣም።
10ከጠላት ፊት እንድናፈገፍግ አደረግኸን፤
ባላንጣዎቻችንም ዘረፉን።
11እንደሚታረዱ በጎች አደረግኸን፤
በሕዝቦችም መካከል በተንኸን።
12ሕዝብህን በርካሽ ዋጋ ሸጥኸው፤
ከሽያጩም ያገኘኸው ትርፍ የለም።
13ለጎረቤቶቻችን ስድብ፣
በዙሪያችን ላሉትም መሣቂያና መዘበቻ
አደረግኸን።
14በሕዝቦች ዘንድ መተረቻ፣
በሰዎች መካከል በንቀት ራስ
መነቅነቂያ አደረግኸን።
15ውርደቴ ቀኑን ሙሉ በፊቴ ነው፤
ፊቴም ዕፍረትን ተከናንቦአል።
16ይህም ከሚዘልፍና ከሚያላግጥ ሰው
ድምፅ የተነሣ፣
ከጠላትና ከተበቃይ ሁኔታ የተነሣ
ነው።

17አንተን ሳንረሳ፣
ለኪዳንህም ታማኝነታችንን ሳናጓድል፣
ይህ ሁሉ ደረሰብን።
18ልባችን ወደ ኋላ አላለም፤
እግራችንም ከመንገድህ አልወጣም።
19አንተ ግን ተኵላዎች በሚውሉበት ቦታ
ሰባብረህ ጣልኸን፤
በሞት ጥላም ሸፈንኸን።

20የአምላካችንን ስም ረስተን፣
እጃችንንም ወደ ባዕድ አምላክ ዘርግተን
ቢሆን ኖሮ፣
21እግዚአብሔር ይህን ማወቅ ይሳነዋልን?
እርሱ ልብ የሰወረውን የሚረዳ ነውና።
22ይሁን እንጂ ቀኑን ሙሉ ስለ አንተ
ሞትን እንጋፈጣለን፤
እንደሚታረዱ በጎችም ተቈጥረናል።

23ጌታ ሆይ፤ ንቃ! ለምንስ ትተኛለህ?
ተነሥ፤ ለዘላለምም አትጣለን።
24ፊትህን ለምን ትሰውራለህ?
መከራችንንና መጠቃታችንን ለምን
ትረሳለህ?

25ነፍሳችን ዐፈር ውስጥ ሰጥማለች፤
ሆዳችንም ከምድር ጋር ተጣብቆአል።
26ተነሥና እርዳን!
ስለ ምሕረትህ ስትል ተቤዠን።

## *መዝሙር* 45

### የንጉሣዊ ሰርግ መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ "በጽጌረዳ" ዜማ፤ የቆሬ ልጆች ትምህርት፤ የፍቅር መዝሙር*[T]

1ልቤ መልካም ሐሳብ አፈለቀ፤
የተቀኘሁትን ቅኔ ለንጉሥ አሰማለሁ፤
አንደበቴም እንደ ባለ ሙያ ጸሓፊ
ብርዕ ነው።

2አንተ ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ውብ ነህ፤
ከንፈሮችህም የጸጋ ቃል ያፈልቃሉ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ባርኮሃል።
3ኃያል ሆይ፤ ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ፤
ግርማ ሞገስንም ተላበስ።

44፥1 ዘዳ32፥7፤ መሳ6፥13፤2ሳሙ7፥22፤ 1ዜና17፥20፤ኢዮ 37፥23፤ኤር26፥11 44፥2 ዘፀ15፥17፤ ኢሱ3፥10፤መሳ4፥23፤ 2ዜና14፥13፤ መዝ80፥9፤ኢሳ60፥21፤ ኤር32፥23፤ሐሥ7፥45 44፥3 ዘፀ15፥16፤ ዘዳ4፥37፤ኢሱ24፥12፤ መዝ77፥15፤78፥54፤ 79፥11፤89፥10፥15፤ 98፥1፤ኢሳ40፥10፤ 52፥10፤63፥5 44፥4 መዝ5፥2፤ 21፥5፤24፥7 44፥5 ኢሱ23፥5፤ መዝ60፥12፤108፥13 44፥6 ዘፍ48፥22፤ ሆሴ1፥7 44፥7 ዘዳ20፥4፤ ኢዮ 8፥22 44፥8 መዝ30፥12፤ 34፥2፤52፥1፤1ቆሮ 1፥31፤2ቆሮ10፥17 44፥9 ዘዳ8፥3፤ 31፥17፤ኢሱ7፥12፤ መዝ43፥2፤107፥39፤ 108፥11፤ኢሳ5፥15 44፥10 ዘሌ26፥17 ፤መሳ2፥14 44፥11 ቍ22፤ ዘሌ 26፥33፤ መዝ9፥11፤ኤር12፥3፤ ሕዝ6፥8፤ዘካ2፥6 44፥12 ዘዳ32፥30፤ ኢሳ50፥1፤52፥3፤ ኤር 15፥13 44፥13 ዘዳ28፥37፤ 2ዜና29፥8፤መዝ79፥4 ፤80፥6፤89፥41፤ ኢሳ30፥3፤ኤር25፥9፤ 42፥18፤44፥8፤ ሕዝ23፥32፤ሚክ2፥6 44፥14 1ነገ9፥7፤ 2ነገ19፥21 44፥15 ዘፍ30፥23፤ 2ዜና32፥21፤ መዝ34፥5፤35፥26 44፥16 1ሳሙ18፥25፤ መዝ10፥13፤42፥10፤ 55፥3፤74፥10፤ ኤር11፥19፤ሮሜ12፥19 44፥17 ዘዳ6፥12፤ 32፥18፤መዝ119፥16፤ 61፥153፥176፤ምሳ3፥1 44፥18 መዝ119፥ 51፥157 44፥19 2ዜና14፥13 ፤ኢዮ3፥5፤30፥29፤ መዝ51፥8፤ኢሳ34፥13 44፥20 ዘፀ20፥3፤ ዘዳ32፥18፤መሳ3፥7፤ ኢሳ43፥12፤ኤር5፥19 44፥21 1ሳሙ16፥7 ፤1ነገ8፥39፤ምሳ15፥11፤ ኤር12፥3፤17፥10 44፥22 ቍ11፤ ኢሳ53፥7፤ኤር11፥19፤ 12፥3፤ሮሜ8፥36 44፥23 መዝ7፥6፤ 59፥5፤74፥1፤77፥7፤78፥65 44፥24 ዘዳ26፥7፤32፥20፤መዝ13፥1፤ ሰቆ5፥20 44፥25 መዝ119፥25 44፥26 ዘኍ10፥35፤መዝ6፥4፤ 12፥5፤26፥11፤102፥13 45 ርዕስ ማሕ1፥1 45፥2 መዝ21፥6፤ ሉቃ4፥22 45፥3 ዘዳ32፥41፤2ሳሙ1፥19፤ኢዮ40፥10፤መዝ21፥5፤ 149፥6፤ራእ1፥16

[θ]44ርእስ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ፊ]4 የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም የሱርስቱ ቅጅ *ንጉሤ ነህ፤ አምላኬም ነህ* ይላሉ፤ ዕብራይስጡ ደግሞ፣ *ንጉሤ እግዚአብሔር ሆይ፤* ይላል።
[T]45ርእስ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

4ስለ እውነት፣ ስለ ትሕትና ስለ ጽድቅ፣
ሞገስን ተጐናጽፈህ በድል አድራጊነት
ገሥግሥ፤
ቀኝ እጅህም ድንቅ ተግባር ታሳይ።
5የሾሉ ፍላጻዎችህ በንጉሥ ጠላቶች ልብ
ይሰካሉ፤
ሕዝቦችም ከእግርህ በታች ይወድቃሉ።
6አምላክ ሆይ፤ ዙፋንህ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ይኖራል፤
የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር
ናት።
7ጽድቅን ወደድህ፤ ዐመፃን ጠላህ፤
ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክህ፣
ከጓደኞችህ ይልቅ አንተን የደስታ
ዘይት ቀባህ።
8ልብስህ ሁሉ በከርቤ፣ በአደስና በጥንጁት
መዐዛ ያውዳል፤
በዝኆን ጥርስ ከተዋበ ቤተ
መንግሥቶችም፣
የበገናና የመሰንቆ ድምፅ ደስ
ያሰኙሃል።
9ከተከበሩት ሴቶችህ መካከል የነገሥታት
ሴቶች ልጆች ይገኛሉ፤
ንግሥቲቱም በኦፊር ወርቅ አጊጣ
በቀኝህ ቆማለች።

10ልጄ ሆይ፤ አድምጪ፤ አስተውዪ፤
ጆሮሽንም አዘንብዪ፤
ሕዝብሽንና የአባትሽን ቤት እርሺ።
11ንጉሥ በውበትሽ ተማርኮአል፤
ጌታሽ ነውና አክብሪው።
12የጢሮስ ሴት ልጅ እጅ መንሻ ይዛ
ትመጣለች፤[ሀ]
ሀብታሞችም ደጅ ይጠኑሻል።

13የንጉሥ ልጅ ከላይ እስከ ታች ተሽልማ
እልፍኟ ውስጥ አለች፤
ልብሷም ወርቀ ዘቦ ነው።
14በጥልፍ ሥራ ባጌጠ ልብስ ወደ ንጉሥ
ትወሰዳለች፤
ደናግል ጓደኞቿም ተከትለዋት፣
ወደ አንተ ይመጣሉ።
15በደስታና በሐሤት ወደ ውስጥ
ይመራቸዋል፤
ወደ ንጉሡም ቤተ መንግሥት
ይገባሉ።

16ወንዶች ልጆችሽ በአባቶችሽ እግር
ይተካሉ፤
ገዦችም አድርገሽ በምድር ሁሉ
ትሾሚያቸዋለሽ።
17ስምሽን በትውልድ ሁሉ ዘንድ መታሰቢያ
አደርጋለሁ፤
ስለዚህ ሕዝቦች ከዘላለም እስከ ዘላለም
ያወድሱሃል።

45፥4 ዘጸ4፥34፤ መዝ21፥8፤65፥5፤ 66፥3፤ሶፎ2፥3፤ራእ6፥2
45፥5 ዘኍ24፥8፤ ዘዳ32፥23፤ መዝ9፥13፤92፥9
45፥6 ዘፍ21፥33፤ ሰቆ5፥19
45፥7 መዝ2፥2፤ 11፥5፤23፥5፤33፥5፤ ኢሳ45፥1፤61፥1፤ ዘካ4፥14፤ዕብ1፥8-9
45፥8 ዘፍ37፥25፤ ዘፀ30፥24፤ዘኍ24፥6፤ 1ነገ22፥39፤መዝ144፥ 9፤150፥4፤ምሳ27፥9፤ መሓ1፥3፤4፥10፤ኢሳ 38፥20፤ዮሐ19፥39
45፥9 ዘፍ10፥29፤ 1ነገ2፥19፤ መሓ6፥8፤ኢሳ62፥5
45፥10 ሩት1፥11፡ 16፤ኤር5፥1
45፥11 አስ1፥11፤ ሰቆ2፥15፤ኤፌ5፥33፤ 1ጴጥ3፥6
45፥12 ኢሱ19፥29፤ 1ነገ9፥16፤2ዜና9፥24
45፥13 ዘፀ39፥3፤ ኢሳ61፥10
45፥14 መሳ5፥30፤ አስ2፥15፤መሓ1፥3
45፥15 አስ8፥17
45፥16 1ሳሙ2፥8፤ መዝ68፥27፤113፥8
45፥17 ዘፀ3፥15፤ መዝ21፥4፤33፥11፤ 119፥90፤135፥13፤ 138፥4፤ራእ22፥5
46፥1 ዘዳ4፥30፤ መዝ9፥9፤18፥1፡6፤ 25፥17፤34፥18፤ 37፥39፤61፥3፤73፥26፤ 91፥2፡9፤142፥5፤ ኢሳ33፥16፤ ኤር16፥19፤17፥17፤ ሰቆ3፥57፤ኢል3፥16 ፤ናሆ1፥7፤ሉቃ1፥54
46፥2 ቀኍ6፤ዘፍ4፥7 ፤ዘፀ15፥8፤መዝ3፥6፤ 18፥7፤82፥5፤97፥5፤ ኢሳ13፥13፤24፥1፡19 ፡20፤54፥10፤ኤር4፥2 3፤ዳን11፥19፤አሞ8፥14 ፤9፥5፤ሚክ1፥4፤ናሆ 1፥5፤ዕን3፥6፤ራእ6፥14
46፥3 መሳ5፥5፤ ኢዮ9፥26፤መዝ93፥3፤ ኢሳ17፥13፤ኤር5፥22፤ ሕዝ1፥24፤ራእ19፥6
46፥4 ዘፍ2፥10፤ 14፥18፤2ሳሙ15፥25 ፤መዝ1፥3፤48፥1፡8፤ 87፥3፤101፥8፤ ራእ3፥12፤22፥1
46፥5 ዘዳ23፥14፤ 1ዜና5፥20፤መዝ26፥8 ፤125፥1፤ኢሳ12፥6፤ ዘካ2፥5
46፥6 ቀኍ2፤ኢዮ12፥23፤ መዝ29፥3፤68፥32፤ 74፥23፤102፥22፤ ኢሳ5፥30፤13፥4፡13፤ 17፥12፤23፥11፤33፥3

## መዝሙር 46
## እግዚአብሔር ከእኛ ጋር

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር፤ በደናግል የዜማ ስልት የሚዘመር[ለ]፣ መዝሙር።*

1አምላካችን መጠጊያችንና ኀይላችን፣
በሚደርስብን መከራ ሁሉ የቅርብ
ረዳታችን ነው።
2ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ እንኳ፣
ተራሮችም ወደ ባሕር ጥልቅ ቢሰምጡ
አንፈራም።
3ውሆች ቢያስገመግሙ፣ ዐረፋ ቢደፍቁም፣
ተራሮችም ከውሆቹ ሙላት የተነሣ
ቢንቀጠቀጡም አንደናገጥም።
ሴላ
4የእግዚአብሔርን ከተማ፣
የልዑልን የተቀደሰ ማደሪያ፣
ደስ የሚያሰኝ የወንዝ ፈሳሽ አለ።
5እግዚአብሔር በመካከሏ ነው፤ አትናወጥም፤
አምላክ በማለዳ ይረዳታል።
6ሕዝቦች በዐመፅ ተነሡ፤ መንግሥታትም
ወደቁ፤
ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰማ፤ ምድርም
ቀለጠች።
7የሰራዊት *አምላክ* ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።
ሴላ
8ኑና *የእግዚአብሔርን ሥራ*፣
ምድርንም እንዴት ባድማ እንዳደረጋት
እዩ።
9ጦርነትን ከዳር እስከ ዳር ከምድር
ያስወግዳል፤
ቀስትን ይሰብራል፤ ጦርን ያነክታል፤
ጋሻንም[ሐ] በእሳት ያቃጥላል።
10"ዕረፉ፤ እኔ አምላክ እንደ ሆንሁም
ዕወቁ፤
በሕዝቦች ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፤
በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።"
11የሰራዊት *አምላክ* ከእኛ ጋር ነው፤
የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።
ሴላ

## መዝሙር 47
## እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ንጉሥ የዓለም ጌታ

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር።*

1ሕዝቦች ሁላችሁ እጆቻችሁን

፤ሕዝ26፥18፤ማቴ4፥8 46፥7 ቀኍ11፤ዘፍ21፥22፤1ሳሙ1፥11፤ መዝ18፥2፤20፥1 46፥8 መዝ66፥5፤ኢሳ17፥9፤64፥10፤ዳን9፥26፤ ሉቃ21፥20 46፥9 መዝ37፥15፤አሳ2፥4፤9፥5፤22፥6፤ሕዝ39፥9፤ ሆሴ2፥18 46፥10 ዘዳ4፥35፤1ነገ18፥36፡39፤መዝ18፥46፤100፥3፤ ኢሳ2፥11፤37፥16፡20፤43፥11፤45፥21፤ሕዝ36፥23 46፥11 ቀኍ7፤ መዝ 20፥1

[ሀ] 12 ወይም፣ *የጢሮሳውያን ልብስ ተክህኖ ከስጦታዎቹ መካከል አለ*
[ለ] ም46 ርእስ ምናልባት የሙዚቃውን ሁኔታ ሊያሳይ ይችላል።
[ሐ] 9 ወይም *ሠረገላንም*

አጨብጭቡ፤
ድምፃችሁን ከፍ አድርጋችሁ ለእግዚ
አብሔር እልል በሉ።
2በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ የሆነው ንጉሥ፣
ልዑል *እግዚአብሔር* የሚያስፈራ ነውና።
3ሕዝቦችን ከእኛ በታች አደረገ፤
*መንግሥታትንም* ከእግራችን ሥር
አስገዛልን።

4ለሚወደው ለያዕቆብ ክብር የሆነችውን፣
ርስታችንን እርሱ መረጠልን።
5አምላክ በእልልታ፣
*እግዚአብሔር* በመለከት ድምፅ ዐረገ።
6አምላካችንን አወድሱት፤ አወድሱት፤
ንጉሣችንን አወድሱት፤ አወድሱት፤
7*እግዚአብሔር* የምድር ሁሉ ንጉሥ
ነውና፤
ምርጥ ዝማሬ[ሙ] አቅርቡለት።
8እግዚአብሔር በሕዝቦች ላይ ነግሦአል፤
እግዚአብሔር በተቀደሰ ዙፋኑ ላይ
ተቀምጦአል።
9ከአብርሃም አምላክ ሕዝብ ጋር፣
የሕዝቦች መኳንንት ተሰበሰቡ፤
የምድር ነገሥታት[ሠ] የእግዚአብሔር ናቸውና፤
እርሱም እጅግ ከፍ ከፍ ያለ ነው።

## መዝሙር 48

## የእግዚአብሔር ተራራ ጽዮን

*ዝማሬ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ታላቅ ነው፤
በአምላካችን ከተማ በተቀደሰው ተራራ
ከፍ ያለ ምስጋና ይገባዋል።
2የምድር ሁሉ ደስታ የሆነው፣
በሰሜን በኩል[ረ] በርቀት የሚታየው፣
በከፍታ ላይ አምሮ የደመቀው የጽዮን
ተራራ፣
የታላቁ ንጉሥ ከተማ ነው።
3እግዚአብሔር በአዳራሾቿ ውስጥ ሆኖ፤
ብርቱ ምሽግ እንደ ሆናት
አስመስክሮአል።

4እነሆ፤ ነገሥታት ተባብረው መጡ፤
አንድ ላይ ሆነውም ገሠገሡ።
5አይተውም ተደነቁ፤
ደንግጠውም ፈረጠጡ።
6ምጥ እንደ ያዛት ሴት፣
በዚያ ብርክ ያዛቸው።
7የምሥራቅ ነፋስ የተርሴስን መርከብ
እንደሚሰባብር፣
አንተ አብረከረክሃቸው።

8እንደ ሰማን፣
በሰራዊት *አምላክ* ከተማ፣
በአምላካችን ከተማ፣
እንዲሁ አየን፤
እግዚአብሔር ለዘላለም ያጸናታል። ሴላ
9አምላክ ሆይ፤ በቤተ መቅደስህ ውስጥ
ሆነን፣
ምሕረትህን እናስባለን።
10አምላክ ሆይ፤ ምስጋናህ እንደ ስምህ፣
እስከ ምድር ዳርቻ ይዘልቃል፤
ቀኝ እጅህም ጽድቅን የተሞላች ናት።
11ስለ ፍርድህ፣
የጽዮን ተራራ ሐሤት ታድርግ፤
የይሁዳ መንደሮችም ደስ ይበላቸው።

12በጽዮን አካባቢ ተመላለሱ፤ ዙሪያዋንም
ሂዱ፤
የጥበቃ ግንበኞቿንም ቍጠሩ፤
13ለሚቀጥለው ትውልድ ትናገሩ ዘንድ፣
መከላከያ ዕርዶቿን ልብ ብላችሁ
ተመልከቱ፤
መጠበቂያ ማማዎቿን እዩ።
14ይህ አምላክ ከዘላለም እስከ ዘላለም
አምላካችን ነውና፤
እስከ መጨረሻው የሚመራንም እርሱ
ነው።

## መዝሙር 49

## የሀብት ከንቱነት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር።*

1እናንተ ሕዝቦች ሁላችሁ፤ ይህን ስሙ፤
በዓለም የምትኖሩ ሁሉ፤ ይህን
አድምጡ።
2ዝቅተኞችና ከፍተኞች፤
ባለጠጎችና ድኾች ይህን በአንድነት
ስሙ።
3አፌ የጥበብን ቃል ይናገራል፤
የልቤም ሐሳብ ማስተዋልን ይሰጣል።
4ጆሮዬን ወደ ምሳሌ አዘነብላለሁ፤
እንቆቅልሼንም በበገና እፈታለሁ።

5የአጭበርባሪዎች ክፋት በከበበኝ ጊዜ፣
በክፉ ቀን ለምን እፈራለሁ?
6በሀብታቸው የሚመኩትን፣
በብልጽግናቸውም የሚታመኑትን
ለምን እፈራለሁ?
7የሌላውን ሕይወት መቤዠት የሚችል
ሰው፣
ወይም ለእግዚአብሔር ወጆ ሊከፍልለት
የሚችል ማንም የለም፤
8የነፍስ ቤዛ ውድ ነውና፤
በቂ ዋጋም ከቶ ሊገኝለት አይችልም፤

47፥1 2ነገ11፥12፤መዝ33፥3
47፥2 ዘፍ14፥18፤ ዘዳ7፥21፤መዝ2፥6፤48፥2፤95፥3፤ማቴ5፥35
47፥3 መዝ18፥39፡47፤ኢሳ14፥6
47፥4 መዝ2፥8፤16፥6፤78፥55፤አሞ6፥8፤8፥7፤1ጴጥ1፥4
47፥5 ዘኍ10፥2፤ 2ሳሙ6፥15፤ ኢዮ8፥21፤መዝ68፥18፤106፥5፤ኤፌ4፥8
47፥6 2ሳሙ22፥50
47፥7 1ዜና16፥7፤ ዘካ14፥9፤ቈላ3፥16
47፥8 1ነገ22፥19፤ 1ዜና16፥31፤ መዝ9፥4፤ራእ4፥9
47፥9 ኢዮ25፥2፤ መዝ46፥10፤97፥9
48፥1 ዘዳ33፥19፤ 2ሳሙ22፥4፤ 1ዜና16፥25፤መዝ2፥6፤18፥3፤46፥4፤86፥10፤87፥1፤96፥4፤99፥2፤135፥5፤147፥7፤ ኢሳ11፥9፤ 32፥16፤ ኤር10፥6፤31፥23፤ ዳን9፥16፤ሚክ4፥1፤ ዘካ8፥3
48፥2 ኢሱ13፥27፤ መዝ2፥6፤50፥2፤ ሰቆ2፥15፤ሕዝ16፥14፤ ማቴ5፥35
48፥3 ቍ13፤ መዝ 18፥2፤122፥7
48፥4 2ሳሙ10፥1-19
48፥5 ዘፀ15፥16፤ ኢሳ13፥8፤ኤር46፥5፤ ዳን5፥9
48፥6 ዘፍ3፥16፤ ኢዮ4፥14
48፥7 ዘፍ10፥4፤41፥6፤ 1ነገ10፥22፤22፥48
48፥8 ኤር23፥6፤ ዘካ8፥13፤14፥11
48፥9 መዝ6፥4፤39፥3
48፥10 ዘፀ6፥3፤ ኢሱ7፥9፤1ሳሙ2፥10፤ መዝ22፥27፤65፥5፤ 98፥3፤100፥1፤ ኢሳ 11፥12፤24፥16፤ 42፥10፤49፥6
48፥11 መዝ97፥8
48፥12 ነህ3፥1
48፥13 ቍ3፤2ሳሙ20፥15፤መዝ71፥18፤ 78፥6፤109፥13፤ኢሳ26፥1፤ሰቆ2፥8፤ዕን2፥1
48፥14 መዝ25፥5፤ 73፥24፤ምሳ6፥22፤ ኢሳ49፥10፤57፥18፤ 58፥11
49፥1 መዝ33፥8፤ 78፥1፤ኢሳ1፥2
49፥2 መዝ62፥9
49፥3 መዝ37፥30፤119፥130
49፥4 ዘኍ12፥8፤ 1ሳሙ16፥16፤ መዝ33፥2፤78፥2፤ምሳ1፥6፤ሕዝ12፥22፤16፥44፤18፥2-3፤ሉቃ4፥23
49፥5 መዝ23፥4፤27፥1 49፥6 ኢዮ22፥25፤36፥19፤መዝ10፥3፤73፥12፤ኤር48፥7 49፥8 ዘኍ35፥31፤ማቴ16፥26

[ሙ]7 ዕብራይስጡ ማስኪል ይላል፤ ይኸውም የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የሙዚቃውን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ሠ]9 ወይም *ጋሻች*
[ረ]2 *ዛፎን* የሚለው የዕብራይስጡ ቃል የተቀደሰ ተራራን ወይም የሰሜንን አቅጣጫ ሊያመለክት ይችላል።

[9]ቢቻልማ ለዘላለም በኖረ፣
መበስበስንም ባላየ ነበር።

[10]ጠቢባን ሟች መሆናቸው የሚታይ ነው፤
ቂልና ሞኝም በአንድነት ይጠፋሉ፤
ጥሪታቸውንም ለሌላው ጥለው
ይሄዳሉ።
[11]መሬቶችን በስማቸው ቢሰይሙም፣
መቃብራቸው የዘላለም ቤታቸው፣
ከትውልድ እስከ ትውልድም
መኖሪያቸው ይሆናል።

[12]ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም፤
ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን
ይመስላል።[ሰ]

[13]ይህ የተላላዎች ዕድል ፈንታ፣
የእነርሱንም አባባል ተቀብለው
ለሚከተሏቸው፣
መጨረሻ ግብ ነው። ሴላ
[14]እንደ በጎች ለሲኦል[ሸ] የተዳረጉ ናቸው፤
ሞትም እረኛቸው ይሆናል፤
ቅኖች በማለዳ ይገዟቸዋል፤
አካላቸው ከክብር ቤታቸው ርቆ፣
በሲኦል ይፈራርሳል።
[15]እግዚአብሔር ግን ነፍሴን[ቀ] ከሲኦል እጅ
ይቤዣታል፤
በርግጥም በእርሱ ዘንድ ተቀባይነት
አለኝ። ሴላ

[16]ሰው ባለጠጋ ሲሆን፣
የቤቱም ክብር ሲበዛለት አትፍራ፤
[17]በሚሞትበትም ጊዜ ይዞት የሚሄደው
አንዳች የለምና፤
ክብሩም አብሮት አይወርድም።
[18]በሕይወት ሳለ ራሱን እንደ ተባረከ
ቢቈጥርም፣
ሰዎች በበለጸግህ ጊዜ ቢያወድሱህም፣
[19]ብርሃን ከቶ ወደማያዩት፣
ወደ አባቶች ማኅበር ይቀላቀላል።

[20]ሰው በሀብቱ እንደ ተከበረ አይዘልቅም፤
ታይተው የሚጠፉ እንስሳትን
ይመስላል።

## መዝሙር 50

## በመንፈስና በእውነት ማምለክ

የአሳፍ መዝሙር

[1]ኀያሉ አምላክ፣ *እግዚአብሔር* ተናገረ፤
ከፀሓይ መውጫ እስከ ፀሓይ መግቢያ
ድረስ
ምድርን ጠራት።
[2]ፍጹም ውብ ከሆነችው ከጽዮን፣
እግዚአብሔር አበራ።
[3]አምላካችን ይመጣል፤ ዝምም አይልም፤
የሚባላ እሳት በፊቱ፣
የሚያስፈራ ዐውሎ ነፋስም በዙሪያው
አለ።
[4]በሕዝቡ ይፈርድ ዘንድ፣
በላይ ያለውን ሰማይንና ምድርን
እንዲህ ብሎ ይጠራል፤
[5]"በመሥዋዕት ከእኔ ጋር ኪዳን የገቡትን፣
ቅዱሳኔን ወደ እኔ ሰብስቧቸው።"
[6]ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ፤
እግዚአብሔር ራሱ ፈራጅ ነውና። ሴላ
[7]"ሕዝቤ ሆይ፤ ስማኝ፤ ልንገርህ፤
እስራኤል ሆይ፤ በአንተ ላይ ልመስክር፤
አምላክህ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።
[8]ስለ መሥዋዕትህ አልነቀፍሁህም፤
የሚቃጠል መሥዋዕትህማ ሁልጊዜ
በፊቴ ነው።
[9]እኔ ግን ኮርማህን ከበረት፣
ፍየሎችህንም ከጒረኖ የምፈልግ
አይደለሁም፤
[10]የዱር አራዊት ሁሉ፣
በሺ ተራራዎች ላይ ያለውም እንስሳ
የእኔ ነውና።
[11]በየተራራው ያለውን ወፍ ሁሉ
ዐውቃለሁ፤
በሜዳ የሚገኘው ተንቀሳቃሽ ፍጡር
ሁሉ የእኔ ነው።
[12]ብራብ ለአንተ አልነግርህም፤
ዓለምና በውስጧ ያለውም ሁሉ የእኔ
ነውና።
[13]ለመሆኑ፣ እኔ የኰርማ ሥጋ እበላለሁን?
የፍየልንስ ደም እጠጣለሁን?
[14]ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት
አቅርብ፤
ለልዑልም ስእለትህን ስጥ።
[15]በመከራ ጊዜ ወደ እኔ ጩህ፤
አድንሃለሁ፤ አንተም ታከብረኛለህ።"

[16]ክፉውን ግን እግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል፤

"ሕጌን ለማነብነብ፣
ኪዳኔንም በአፍህ ለመናገር ምን
መብት አለህ?
[17]ተግሣጼን ትጠላለህና፤
ቃሌንም ወደ ኋላህ ትጥላለህ።
[18]ሌባውን ስታይ አብረኸው ነጐድህ፤
ዕድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር
አደረግህ።
[19]አፍህን ለክፋት አዋልህ፤

49፥9 መዝ16፥10፤22፥29፤89፥48
49፥10 ኢዮ27፥17፤መዝ92፥6፤94፥8፤መክ2፥16፡18፡21፤ሉቃ12፥20
49፥11 ዘዳ3፥14፤መዝ106፥31፤ማር5፥3፤ሉቃ8፥27
49፥12 ቍ20፤ኢዮ14፥2፤2ጴጥ2፥12
49፥13 ሉቃ12፥20
49፥14 ዘኍ16፥30፤ኢዮ21፥13፤መዝ9፥17፤55፥15፤ኢሳ14፥2፤ኤር43፥11፤ሕዝ31፥14፤ዳን7፥18፤1ቆሮ6፥2
49፥15 ዘፍ5፥24፤መዝ56፥13፤ሆሴ13፥14
49፥17 መዝ17፥14፤1ጢሞ6፥7
49፥18 መዝ10፥6፤ሉቃ12፥19
49፥19 ዘፍ15፥15፤ኢዮ33፥30
49፥20 ቍ12፤ምሳ 16፥16
50፥1 ኢሱ22፥22፤መዝ113፥3
50፥2 ዘዳ33፥2፤መዝ2፥6፤48፥2፤ሰቆ2፥15
50፥3 ቍ21፤ዘሌ10፥2፤ኢዮ37፥9፤መዝ18፥8፤83፥15፤96፥13፤107፥25፤147፥18፤ኢሳ29፥6፤30፥28፤42፥14፤64፥12፤65፥6፤ዮና1፥4፤ናሆ1፥3
50፥4 ዘዳ4፥26፤31፥28፤ኢሳ1፥2፤ዕብ10፥30
50፥5 ዘፀ24፥7፤ዘዳ 7፥6፤2ዜና6፥11፤መዝ18፥25
50፥6 ዘፍ16፥5፤ኢዮ9፥15፤መዝ19፥1
50፥7 ዘፀ20፥2፤መዝ48፥14፤ዕብ2፥4
50፥8 2ሳሙ22፥16፤መዝ40፥6
50፥9 ዘሌ1፥5፤16፥5 ፤ዘኍ32፥16
50፥10 መዝ104፥20:24፤ኢሳ56፥9፤ሚክ5፥8
50፥11 መዝ8፥7፤80፥13፤ማቴ6፥26
50፥12 ዘፀ19፥5፤ዘዳ 10፥14፤ኢሱ3፥11፤መዝ24፥1፤1ቆሮ10፥26
50፥14 ዘኍ30፥2፤ዕዝ1፥4፤መዝ7፥8፤27፥6፤66፥13፤76፥11
50፥15 መዝ3፥7፤4፥1፤22፥23፤69፥17፤81፥7፤86፥7፤107፥6፤142፥2፤ኢሳ55፥6፤58፥9፤ዘካ13፥9፤ያዕ5፥13
50፥16 መዝ25፥10፤ኢሳ29፥13
50፥17 1ነገ14፥9፤ምሳ1፥22
50፥18 ኢዮ22፥15፤ሮሜ1፥32፤1ጢሞ5፥22 50፥19 መዝ10፥7፤36፥3፤52፥2፤101፥7

[ሰ]12 በሰብዓ ሊቃናት ትርጒምና በሱርስቱ ቅጂ ቍ12 ከቍ20 ጋር አንድ ዐይነት ነው፤ ዕብራይስጡ ግን ከዚህ ይለያል።
[ሸ]14 በዚህ እና በቍ15 ላይ ዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች ግን *መቃብር* ይላሉ።
[ቀ]15 ወይም *ሕይወቴን*

አንደበትህም ሸንገላን ጐነጐነ።
20ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው፤
የእናትህንም ልጅ ስም አጐደፍህ።
21ይህን አድርገህ ዝም አልሁ፤
እንዳንተ የሆንሁ መሰለህ።
አሁን ግን እገሥጽሃለሁ፣
ፊት ለፊትም እወቅስሃለሁ።

22"እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ፤ ይህን
ልብ በሉ፤
አለበለዚያ ብትንትናችሁን አወጣለሁ፤
የሚያድናችሁም የለም።
23የምስጋናን መሥዋዕት የሚሠዋ
ያከብረኛል፤
መንገዱንም ቀና ለሚያደርግ፣
የእግዚአብሔርን ማዳን አሳየዋለሁ።"[ሀ]

## መዝሙር 51

### የኀጢአት ኑዛዜ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ዳዊት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፤ የዳዊት መዝሙር።*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቸርነትህ መጠን፣
ምሕረት አድርግልኝ፤
እንደ ርኅራኄህም ብዛት፣
መተላለፌን ደምስስ።
2በደሌን ፈጽሞ እጠብልኝ፤
ከኀጢአቴም አንጻኝ።

3እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፤
ኀጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው።
4በውሳኔህ ትክክል፣
በምትሰጠው ፍርድም ንጹሕ ትሆን
ዘንድ፣
አንተን፣ በእርግጥ አንተን ብቻ በደልሁ፤
በፊትህም ክፉ ነገር አደረግሁ።
5ስወለድ ጀምሮ በደለኛ፣
ገና እናቴም ስትፀንሰኝ ኀጢአተኛ ነኝ።
6እነሆ፤ እውነትን ከሰው ልብ ትሻለህ፤[ለ]
ስለዚህ ጥልቅ ጥበብን በውስጤ
አስተምረኝ።[ሐ]

7በሂሶጵ እርጨኝ፤ እኔም እነጻለሁ፤
እጠበኝ፤ ከበረዶም ይልቅ ነጭ
እሆናለሁ።
8ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፤
ያደቀቅሃቸው ዐጥንቶቼም ደስ
ይበላቸው።
9ፊትህን ከኀጢአቴ መልስ፤
በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።

10አምላኬ ሆይ፤ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ፤
ቀና የሆነውንም መንፈስ በውስጤ
አድስ።
11ከፊትህ አትጣለኝ፤
ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ
አትውሰድ።

12የማዳንህን ደስታ መልስልኝ፤
በእሺታ መንፈስም ደግፈህ ያዘኝ።
13እኔም ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን
አስተምራለሁ፤
ኀጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።
14የድነቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
ደም ከማፍሰስ አድነኝ፤
አንደበቴም ስለ ጽድቅህ በእልልታ
ይዘምራል።
15ጌታ ሆይ ከንፈሮቼን ክፈት፤
አፌም ምስጋናህን ያውጃል።
16መሥዋዕትን ብትወድ ኖሮ ባቀረብሁልህ
ነበር፤
የሚቃጠል መሥዋዕትም ደስ
አያሰኝህም።
17እግዚአብሔር የሚቀበለው መሥዋዕት
የተሰበረ መንፈስ ነው፤[መ]
እግዚአብሔር ሆይ፤
አንተ የተሰበረውንና የተዋረደውን
ልብ አትንቅም።

18በበጎ ፈቃድህ ጽዮንን አበልጽጋት፤
የኢየሩሳሌምንም ቅጥሮች ሥራ።
19የጽድቅ መሥዋዕት፣ የሚቃጠል
መሥዋዕትና፣
ሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት ያን
ጊዜ ደስ ያሰኙሃል፤
ኮርማዎች በመሠዊያህ ላይ
የሚሠዉትም ያን ጊዜ ነው።

## መዝሙር 52

### የክፉዎች ዕጣ ፈንታ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ኤዶማዊው ዶይቅ ወደ ሳኦል መጥቶ፣ "ዳዊት ወደ አቢሜሌክ ቤት መጥቶአል" ብሎ በነገረው ጊዜ፤ የዳዊት[ሠ] ትምህርት*

1ኃያል ሆይ፤ በክፋት ለምን ትኵራራለህ?
አንተ በእግዚአብሔር ዐይን የተናቅህ፣
እንዴትስ ዘወትር ትታበያለህ?
2አንተ ማታለልን ሥራዬ ብለህ የያዝህ፤
አንደበትህ እንደ ሰላ ምላጭ፣
ጥፋትን ያውጠነጥናል።
3ከበጎ ነገር ይልቅ ክፋትን፣
እውነትን ከመናገር ይልቅ ሐሰትን
ወደድህ። ሴላ

**50፥20** ማቴ10፥21 **50፥21** መዝ6፥1፤18፥15፤76፥6፤85፥5፤104፥7፤ኢሳ42፥14፤50፥2፤57፥11፡16፤62፥1፤64፥12፤ **50፥22** ዘዳ32፥39፤ኢዮ8፥13፤ኢሳ17፥10፤ሚክ5፥8 **50፥23** መዝ9፥14፤85፥13፤91፥16፤98፥3፤ኢሳ52፥10 **51** ርዕስ 2ሳሙ11፥4፤12፥1 **51፥1** 2ሳሙ12፥13፤24፥14፤2ዜና6፥21፤ነህ4፥5፤9፥27፤መዝ9፥13፤25፥7፤39፥8፤86፥15፤119፥88፤ኢሳ63፥7፤ሐሥ3፥19 **51፥2** ሩት3፥3፤ምሳ20፥30፤ኢሳ4፥4፤ኤር2፥22፤13፥27፤ሕዝ36፥25፤ዘካ13፥1፤ማቴ23፥25-26፤ሐሥ 22፥16፤ዕብ9፥14፤1ዮሐ1፥9 **51፥3** ኢሳ59፥12 **51፥4** ዘፍ20፥6፤1ሳሙ15፥24፤ሉቃ15፥21፤ሮሜ3፥4 **51፥5** ዘሌ5፥2፤ኢዮ 5፥7 **51፥6** ኢዮ9፥4፤34፥32፤መዝ119፥66፤143፥10 **51፥7** ዘፀ12፥22፤ዘኍ19፥6፤ኢሳ1፥18፤4፥4፤43፥25፤44፥22፤ሕዝ36፥25፤ዘካ13፥1፤ዕብ9፥19 **51፥8** ዘፀ12፥46፤ኢሳ35፥10፤ኤር33፥11፤ኢል1፥16 **51፥9** 2ሳሙ12፥13፤ኤር16፥17፤ዘካ4፥10 **51፥10** መዝ24፥4፤78፥37፤ሕዝ18፥31፤36፥26፤ማቴ5፥8፤ሐሥ15፥9 **51፥11** ዘፍ4፥14፤ዘፀ33፥15፤መዝ27፥9፤71፥9፤106፥33፤138፥8፤ኢሳ63፥10፤ኤፌ4፥30 **51፥12** ኢዮ33፥26፤መዝ18፥35፤110፥3 **51፥13** ዘፀ33፥13፤ኢዮ33፥27፤መዝ1፥1፤ሐሥ9፥21-22 **51፥14** 2ሳሙ12፥9፤መዝ5፥8፤25፥5፤35፥28፤39፥8፤68፥20፤71፥15፤88፥1 **51፥15** ዘፀ4፥15 **51፥16** 1ሳሙ15፥22 **51፥17** ምሳ15፥8፤ሐጌ2፥14፤ማቴ11፥29 **51፥18** መዝ69፥35፤102፥16፤147፥2፤ኢሳ14፥32፤44፥26፤51፥3፤ዘካ1፥16-17 **51፥19** ዘዳ33፥19፤ መዝ66፥13፡15፤96፥8፤ኤር17፥26 **52** ርዕስ 1ሳሙ21፥7፤22፥9 **52፥1** መዝ10፥3፤44፥8፤94፥4 **52፥2** ዘኍ6፥5፤መዝ5፥9፤50፥19 **52፥3** ዘፀ10፥10፤1ሳሙ12፥25፤መዝ58፥3፤ኤር9፥5፤አሞ5፥14-15፤ዮሐ3፥20፤ራእ21፥8

[ሀ]23 ወይም *መንገዱን ለሚገነዘብ* ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ለ]6 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።
[ሐ]6 *አስተምረሀኛል* ወይም *ትፈልጋለህ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል።
[መ]17 ወይም *አምላክ ሆይ፤ የእኔ መሥዋዕት የተሰበረ*
[ሠ]ርእሱ ምናልባት የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

[4]አንተ አታላይ አንደበት ሆይ፤
ጐጂ ቃላትን ሁሉ ወደድህ!

[5]እግዚአብሔር ግን ለዘላለም
ያንኰታኵትሃል፤
ይነጥቅሃል፤ ከድንኳንህም መንጥቆ
ያወጣሃል፤
ከሕያዋንም ምድር ይነቅልሃል። ሴላ
[6]ጻድቃን ይህን ዐይተው ይፈራሉ፤
እንዲህ እያሉም ይሥቁበታል፤
[7]"እግዚአብሔርን መጠጊያ ያላደረገ፣
ነገር ግን በሀብቱ ብዛት የተመካ፣
በክፋቱም የበረታ፣
ያ ሰው እነሆ!"

[8]እኔ ግን በእግዚአብሔር ቤት፣
እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነኝ፤
ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
በእግዚአብሔር ምሕረት እታመናለሁ።
[9]ስላደረግኸው ነገር ለዘላለም አመሰግንሃለሁ፤
ስምህ መልካም ነውና ስምህን ተስፋ
አደርጋለሁ፤
በቅዱሳንም መካከል አመሰግንሃለሁ።

## መዝሙር 53

### አምላክ የለሾች

53፥1-6 ተጓ ምብ-መዝ14፥1-7

ለመዘምራን አለቃ፤ በማኸላት፤ የዳዊት ትምህርት።[ኘ]

[1]ቂል በልቡ፣
"እግዚአብሔር የለም" ይላል።
ብልሹዎች ናቸው፤ ተግባራቸውም
ጸያፍ ነው፤
በጎ ነገርን የሚያደርግ አንድ እንኳ
የለም።

[2]በማስተዋል የሚመላለስ፣
እግዚአብሔርን የሚፈልግ እንዳለ ለማየት፣
እግዚአብሔር ከሰማይ፣
ወደ ሰው ልጆች ተመለከተ።
[3]ሁሉም ወደ ሌላ ዘወር አሉ፤
በአንድነትም ተበላሹ፤
አንድ እንኳ፣
በጎ የሚያደርግ የለም።

[4]ሰው እንጀራ እንደሚበላ ሕዝቤን
የሚበሉት፣
እግዚአብሔርንም ጠርተው የማያውቁት፣
እነዚያ ክፉ አድራጊዎች ከቶ
አይማሩምን?
[5]የሚያስፈራ ነገር በሌለበት፣
በዚያ፣ በፍርሀት ተዋጡ፤
እግዚአብሔር የዘመቱብህን ሰዎች ዐጥንት
በተነ፤
እርሱ እግዚአብሔር ስለ ናቃቸው፣ አንተ
አሳፈርሃቸው።

52፥4 መዝ5፥9፤ 10፥7፤109፥2፤120፥2፡3፤ምሳ10፥31፤12፥19
52፥5 ዘዳ28፥63፤ 29፥28፤ኢዮ28፥13፤ 40፥12፤ኢሳ22፥19፤ ሕዝ17፥24
52፥6 ኢዮ22፥19
52፥7 2ሳሙ22፥3፤መዝ49፥6፤ ምሳ11፥28፤ማር10፥23
52፥8 መዝ1፥3፤ 6፥4፤13፥5፤ራእ11፥4
52፥9 ዘዳ7፥6፤ ኢዮ7፥6፤መዝ16፥3፤ 25፥3፤30፥12፤54፥6
53፥1 መዝ10፥4፤ 74፥22፤107፥17፤ ምሳ10፥23
53፥2 2ዜና15፥2፤ መዝ33፥13፤82፥5፤ ኤር4፥22፤8፥8
53፥3 ሮሜ3፥10-12
53፥5 ዘሌ26፥17፤2ነገ17፥20፤23፥14፤ ኢዮ8፥22፤መዝ141፥7፤ኤር6፥30፤8፥1፤ 14፥19፤ሰቆ5፥22፤ ሕዝ6፥5
54፥ ርዕስ1ሳሙ 23፥19፤26፥1
54፥1 1ሳሙ24፥15፤ 2ዜና20፥6፤መዝ20፥1
54፥2 መዝ4፥1፤ 5፥1፤55፥1
54፥3 1ሳሙ20፥1፤ መዝ18፥48፤36፥1፤ 86፥14፤140፥1፡4፡11
54፥4 1ዜና5፥20፤ መዝ18፥35፤20፥2
54፥5 ዘዳ32፥35፤ መዝ89፥49፤94፥23፤ ምሳ24፥12፤ኢሳ42፥3
54፥6 ዘሌ7፥12፡16፤ ዕዝ1፥4፤መዝ27፥6፤ 44፥8፤52፥9፤69፥30፤ 138፥2፤142፥7፤145፥1
54፥7 መዝ34፥6፤ 59፥10፤92፥11፤ 112፥8፤118፥7
55፥1 መዝ27፥9፤ ሰቆ3፥56
55፥2 1ሳሙ1፥15-16፤መዝ4፥1፤77፥3፤ 86፥6-7፤142፥2
55፥3 2ሳሙ16፥6-8፤መዝ17፥9፤44፥16፤ 71፥11፤143፥3
55፥4 ኢዮ18፥11፤ መዝ6፥3
55፥5 ዘዳ28፥67፤ ኢዮ4፥14፤ኢሳ21፥4፤ ኤር46፥5፤49፥5፤ ሕዝ7፥18፤2ቆሮ7፥15

[6]ምነው ለእስራኤል የሚሆን መዳን
ከጽዮን በወጣ!
እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ
በሚመልስበት ጊዜ፣
ያዕቆብ ሐሤት ያድርግ፤ እስራኤል
ደስ ይበለው።

## መዝሙር 54

### ለፍትሕ አምላክ የቀረበ አቤቱታ

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ ዜፋውያን ወደ ሳኦል መጥተው፣ "ዳዊት በእኛ ዘንድ ተደብቆአል" ባሉት ጊዜ፤ የዳዊት ትምህርት።[ኦ]

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ በስምህ አድነኝ፤
በኀይልህም ፍረድልኝ።
[2]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማልኝ፤
የአፌንም ቃል አድምጥ።

[3]ባዕዳን ተነሥተውብኛልና፤
ግፈኞች ነፍሴን ሽተዋታል፤
እግዚአብሔርንም ከምንም አልቈጠሩም።
ሴላ
[4]እነሆ፤ እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፤
ጌታም ደግፎ ይይዘኛል።

[5]የገዛ ክፋታቸው በሚያደቡብኝ ላይ
ይመለስባቸው፤
በቃልህ ታማኝ ነህና አጥፋቸው።

[6]በበጎ ፈቃድ መሥዋዕት እሠዋልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ መልካም ነውና፣
ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
[7]ከመከራ ሁሉ ታድጎኛልና፤
ዐይኔም የጠላቶቼን ውድቀት ለማየት
በቅቶአል።

## መዝሙር 55

### በስደት ጊዜ የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ የዳዊት ትምህርት[ከ]

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ልመናዬን ቸል አትበል፤
[2]ወደ እኔ ተመልከት፤ መልስልኝም።
በውስጤ ታውኬአለሁ፤
ተናውጬአለሁም፤
[3]በጠላት ድምፅ ተሸበርሁ፤
በክፉዎች ድንፋታ ደነገጥሁ፤
መከራ አምጥተውብኛልና፤
በቍጣም ተነሣሥተው ጠላት ሆነውብኛል።

[4]ልቤ በውስጤ ተጨነቀብኝ፤
የሞት ድንጋጤም በላዬ መጣ።
[5]ፍርሀትና እንቅጥቃጤ መጣብኝ፤
ሽብርም ዋጠኝ።

[ኘ]ርእሱ ምናልባት የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ኦ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ከ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።

6 እኔም እንዲህ አልሁ፤ “ምነው የርግብ
ክንፍ በኖረኝ!
በርሬ በሄድሁና ባረፍሁ ነበር፤
7 እነሆ፤ ኰብልዬ በራቅሁ፣
በምድረ በዳም በሰነበትሁ ነበር፤ ሴላ
8 ከዐውሎ ነፋስና ከውሽንፍር ሽሽቼ፣
ወደ መጠለያዬ ፈጥኜ በደረስሁ
ነበር።”
9 ጌታ ሆይ፤ ግፍንና ሁከትን በከተማዪቱ
ውስጥ አይቼአለሁና፣
ግራ አጋባቸው፤ ቋንቋቸውንም
ደበላልቅ።
10 ቀንና ሌሊት ቅጥሯ ላይ ወጥተው
ይዞሯታል፤
ተንኰልና መከራ በውስጧ አለ።
11 ጥፋት በመካከሏ ይገኛል፤
ግፍና አታላይነትም ከጎዳናዋ
አይጠፋም።
12 የሚዘልፈኝ ጠላት አይደለምና፤
ቢሆንማ ኖሮ በታገሥሁት ነበር፤
የሚጠላኝ፣ ራሱንም ቀና ቀና ያደረገብኝ
ባላንጣ አይደለም፤
ቢሆንማ ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር።
13 ነገር ግን አድራጊው አንተ ነህ፤
እኩያዬ፣ ባልንጀራዬና ወዳጄ፤
14 በእግዚአብሔርም ቤት አብረን በሕዝብ
መካከል ተመላለስን፤
ደስ የሚል ፍቅር በአንድነት ነበረን።
15 ሞት ሳይታሰብ ድንገት ይምጣባቸው፤
በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል[ሽ] ይውረዱ፤
ክፋት በመካከላቸው አድራለችና።
16 እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር እጣራለሁ፤
*እግዚአብሔርም* ያድነኛል።
17 በማታ፣ በጥዋትና በቀትር፣
እጮኻለሁ፤ እቃትታለሁም፤
እርሱም ድምፄን ይሰማል።
18 በተቃውሞ የተነሡብኝ ብዙዎች
ናቸውና፣
ከተቃጣብኝ ጦርነት፣
ነፍሴን በሰላም ይቤዠታል።
19 አካሄዳቸውን አልቀየሩምና፣
እግዚአብሔርንም አልፈሩትምና፣
ከጥንት ጀምሮ በዙፋኑ ላይ ያለ
እግዚአብሔር፣ ሴላ
ሰምቶ ያዋርዳቸዋል።
20 ባልንጀራዬ የምለው ሰው እጁን
በወዳጆቹ ላይ ሰነዘረ፤
ቃል ኪዳኑንም አፈረሰ።
21 አፉ ከቅቤ ይልቅ የለዘበ ነው፤
በልቡ ግን ጦርነት አለ፤

55፥7 1ሳሙ23፥14
55፥8 መዝ31፥20፤77፥18፤አሳ4፥6፤25፥4፤28፥2፤29፥6፤32፥2
55፥9 ዘፍ4፥17፤11፥9፤መዝ11፥5፤ኢሳ59፥6፤ኤር6፥7፤ሕዝ7፥11፤ዕን1፥3፤ሐሥ2፥4
55፥10 1ጴጥ5፥8
55፥11 መዝ5፥9፤10፥7
55፥13 2ሳሙ15፥12
55፥14 መዝ42፥4፤ሐሥ1፥16-17
55፥15 መዝ49፥14፤64፥7፤ምሳ6፥15፤ኢሳ 29፥5፤47፥9፡11፤1ተሰ5፥3
55፥17 መዝ5፥3፤88፥13፤92፥2፤141፥2፤ሐሥ3፥1፤10፥3፡9፡30
55፥19 ዘፀ15፥18፤ዘዳ33፥27፤መዝ29፥10፤36፥1፤64፥4 ፤78፥59
55፥20 መዝ7፥4፤41፥9
55፥21 መዝ12፥2፤57፥4፤59፥7፤64፥3፤ምሳ5፥3፤6፥24፤12፥18፤ራእ1፥16
55፥22 መዝ15፥5፤18፥35፤21፥7፤37፥24፤112፥6፤ማቴ6፥25-34፤1ጴጥ5፥7
55፥23 ኢዮ15፥32፤መዝ5፥6፤9፥15፤11፥1፤25፥2፤30፥3፤56፥3፤73፥18፤94፥13፤ኢሳ14፥15፤ሕዝ28፥8፤ሉቃ8፥31
56፥1 መዝ6፥2፤17፥9፤57፥1-3
56፥2 መዝ35፥1፡25፤124፥3
56፥3 መዝ55፥4-5፡23
56፥4 ቀኍ10፤መዝ 27፥1፤118፥6፤ማቴ10፥28፤ዕብ13፥6
56፥5 መዝ41፥7፤2ጴጥ3፥16
56፥6 መዝ17፥11፤59፥3፤71፥10፤94፥21፤ማር3፥6
56፥7 መዝ36፥12፤55፥23፤ምሳ19፥5፤ሕዝ17፥15፤ሮሜ2፥3፤ዕብ12፥25
56፥8 2ነገ20፥5፤ኢሳ4፥3፤ዳን7፥10፤12፥1፤ሚል3፥16
56፥9 ዘኍ14፥8፤ዘዳ31፥6፤መዝ9፥3፤102፥2፤

ቃሉ ከዘይት ይልቅ የለሰለሰ ነው፤
ይሁን እንጂ የተመዘዘ ሰይፍ ነው።
22 የከበደህን ነገር *በእግዚአብሔር* ላይ
ጣል፤
እርሱ ደግፎ ይይዝሃል፤
የጻድቁንም መናወጥ ከቶ አይፈቅድም።
23 አንተ ግን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤
ክፉዎችን ወደ ጥፋት ጒድጓድ
ታወርዳቸዋለህ፤
ደም የተጠሙ ሰዎችና አታላዮች፣
የዘመናቸውን እኩሌታ አይኖሩም።
እኔ ግን በአንተ እታመናለሁ።

## መዝሙር 56

### በእግዚአብሔር መደገፍ

*ለመዘምራን አለቃ፤ “ርግቢቱ ሩቅ ባለው ወርካ ላይ” በተባለው ቅኝት፤ ፍልስጤማውያን በጌት በያዙት ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ[ሠ]*

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ የሰዎች መረገጫ
ሆኛለሁና ማረኝ፤
ቀኑንም ሙሉ በውጊያ
አስጨንቀውኛል።
2 ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ በላዬ ቆሙ፤
በትዕቢት የሚዋጉኝ ብዙዎች
ናቸውና።
3 ፍርሀት በሚይዘኝ ጊዜ፣
እምነቴን በአንተ ላይ አደርጋለሁ።
4 ቃሉን በማመስግነው እግዚአብሔር፣
በእግዚአብሔር ታምኛለሁ፤ አልፈራም፤
ሥጋ ለባሽ ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
5 ቀኑን ሙሉ ቃሌን ያጣምሙታል፤
ዘወትርም ሊጐዱኝ ያሤራሉ።
6 ይዶልታሉ፤ ያደባሉ፤
ርምጃዬን ይከታተላሉ፤
ነፍሴንም ለማጥፋት ይሻሉ።
7 እግዚአብሔር ሆይ፤ ከቶ እንዳያመልጡ፣
ሕዝቦቹን በቍጣህ ጣላቸው።
8 ሰቆቃዬን መዝግብ፤
እንባዬን በዕቃህ አጠራቅም፤[ቦ]
ሁሉስ በመዝገብህ የተያዘ አይደለምን?
9 ወደ አንተ በተጣራሁ ቀን፣
ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ፤
በዚህም፣ እግዚአብሔር ከጐኔ መቆሙን
ዐውቃለሁ።
10 ቃሉን በማመስግነው እግዚአብሔር፣
ቃሉን በማመስግነው *በእግዚአብሔር*፣

[ሽ]15 *ዕብራይስጡ ሲኦል ይላል፤ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጆች ግን መቃብር ይላሉ።*
[ሠ]*ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።*
[ቦ]8 *እንባዬን በወይን አቍማዳህ ውስጥ ጨምር ወይም እንባዬን በመጽሐፍህ መዝገብ*

11በአምላክ *ታም*ኛለሁ፤ አልፈራም፤
*ሥጋ* ለባሽ ምን *ሊያ*ደርገኝ ይችላል?

12እግዚአብሔር ሆይ፤ የአንተ ስእለት
አለብኝ፤
የማቀርብልህም የምስጋና መሥዋዕት
ነው፤
13በሕያዋን ብርሃን፣[ዘ]
በእግዚአብሔር ፊት እመላለስ ዘንድ፣
ነፍሴን ከሞት፣[ዠ]
እግሬንም ከመሰናክል አድነሃልና።

## *መዝሙር* 57

### በጨካኝ ጠላቶች ዘንድ

57፥7-11 ተጓ ምብ-መዝ108፥1-5

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤ ከሳኦል ፊት ሸሽቶ በዋሻ በነበረበት ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ።[የ]

1ማረኝ፤ እግዚአብሔር ሆይ፤ ማረኝ፤
ነፍሴ አንተን መጠጊያ አድርጋለችና፤
በክንፎችህ ሥር እጠለላለሁ።

2ለእኔ ያሰበውን ወደሚፈጽምልኝ አምላክ፣
ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ።
3ከሰማይ ልኮ ያድነኛል፤
የረገጡኝን ያዋርዳቸዋል፤ ሴላ
እግዚአብሔር ምሕረቱንና ታማኝነቱን
ይልካል።

4ነፍሴ በአንበሶች ተከብባለች፤
በሚዘነጣጥሉ አራዊት መካከል
ወድቄአለሁ፤
እነዚህም፣ ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ፣
ምላሳቸውም የተሳለ ሰይፍ የሆኑ
ሰዎች ናቸው።

5እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰማያት በላይ
ከፍ ከፍ በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትስፋን።
6ለእግሬ ወጥመድን ዘረጉ፤
ነፍሴንም አጐበጧት፤
በመተላለፊያዬ ላይ ጒድጓድ ቈፈሩ፤
ነገር ግን ራሳቸው ገቡበት። ሴላ

7እግዚአብሔር ሆይ፤ ልቤ ጽኑ ነው፤
ልቤ ጽኑ ነው፤
እቀኛለሁ፤ አዜማለሁ።
8ነፍሴ ሆይ፤ ንቂ!
በገናና መሰንቆም ተነሡ!
እኔም በማለዳ እነሣለሁ።

9ጌታ ሆይ፤ በሕዝቦች መካከል
አመሰግንሃለሁ፤
በሰዎችም መካከል እዘምርልሃለሁ፤
10ምሕረትህ እስከ ሰማያት ከፍ ብላለችና፤
ታማኝነትህም እስከ ደመናት
ትደርሳለች።

11እግዚአብሔር ሆይ፤ ከሰማያት በላይ ከፍ
ከፍ በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትስፋን።

## *መዝሙር* 58

### የምድር ዳኞች ፈራጅ

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤ የዳዊት ቅኔ[ደ]

1ኀያላን ሆይ፤ በውኑ ጽድቅ ከአፋችሁ
ይወጣል?
የሰው ልጆች ሆይ፤ በቅን
ትፈርዳላችሁን?
2የለም፤ በልባችሁ ክፋትን ታውጠነጥናላችሁ፤
በእጃችሁም ዐመፅን በምድር ላይ
ትጐነጒናላችሁ።
3ክፉዎች በማሕፀን ሳሉ ከመንገድ የወጡ
ናቸው፤
ሲወለዱ ጀምሮ የተሳሳቱና ውሸታሞች
ናቸው።
4መርዛቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፤
አልሰማ ብላ ጆሮዋን እንደ ደፈነች
እፉኝት ናቸው፤
5ጆሮዋንም የደፈነችው የመተተኛውን
ወይም የጠቢቡን ደጋሚ ቃል
ላለመስማት ነው።
6አምላክ ሆይ፤ ጥርሳቸውን በአፋቸው
ውስጥ ስበር፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የአንበሶቹን
መንጋጋ አወላልቅ!
7ፈጥኖ እንደሚያልፍ ወራጅ ውሃ ይጥፉ፤
ቀስታቸውን ሲስቡ ፍላጻቸው ዱልዱም
ይሁን።
8ሲሄድ እንደሚቀልጥ ቀንድ አውጣ
ይሁኑ፤
ፀሓይን እንደማያይ ጭንጋፍ ይሁኑ።

9የእሾኽ እሳት ገና ድስታችሁን
ሳያሰማው፣
እርጥቡንም ደረቁንም እኩል በዐውሎ
ነፋስ ጠራርጎ ይወስዳቸዋል።[ጀ]
10ጻድቃን በቀልን ባዩ ጊዜ ደስ
ይላቸዋል፤
እግራቸውንም በግፈኞች ደም
ይታጠባሉ።
11ሰዎችም፣ "በርግጥ ለጻድቃን ብድራት
ተቀምጦላቸዋል፤
በእውነትም በምድር ላይ የሚፈርድ
አምላክ አለ" ይላሉ።

ሮሜ8፥31
56፥12 መዝ50፥14
56፥13 ኢዮ33፥30፤ መዝ30፥3፤33፥19፤ 49፥15፤86፥13፤ 107፥20፤116፥8
57 ርዕስ1ሳሙ22፥1፤24፥3፤መዝ142ርዕስ
57፥1 ሩት2፥12፤ መዝ2፥12፤9፥9፤ 34፥22፤ኢሳ26፥20፤ ማቴ 23፥37
57፥2 መዝ138፥8
57፥3 መዝ18፥9: 16፤25፥10፤40፥11፤ 56፥1፤69፥14፤115፥1፤ 142፥6፤144፥5:7
57፥4 መዝ35፥17፤ 55፥21፤ምሳ30፥14
57፥5 ቍ11፤ መዝ 108፥5
57፥6 አስ6፥13፤ መዝ7፥15፤9፥15፤ 10፥9፤31፥4፤38፥6፤ 140፥5፤145፥14፤ ምሳ28፥10፤መክ10፥8
57፥7 መዝ112፥7
57፥8 መዝ33፥2፤ 149፥3፤150፥3
57፥10 መዝ36፥5
57፥11 ቍ5፤ መዝ8፥1፤113፥4
58፥1 መዝ82፥2
58፥2 መዝ94፥20፤ ኢሳ10፥1፤ማቴ15፥19፤ሉቃ6፥38
58፥4 ዘኍ21፥6
58፥5 መዝ81፥11፤ መክ10፥11፤ኤር8፥17
58፥6 ኢዮ4፥10፤ መዝ3፥7
58፥7 ዘሌ26፥36፤ ኢዮ11፥16፤ መዝ11፥2፤57፥4፤64፥3
58፥8 ኢዮ3፥16፤ ኢሳ13፥7
58፥9 ኢዮ7፥10፤ 21፥8፤መዝ118፥12፤ መክ7፥6
58፥10 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ22፥19፤መዝ7፥9፤ 68፥23፤91፥8፤ኤር 11፥20፤ሮሜ12፥17-21
58፥11 ዘፍ15፥1፤ 18፥25፤መዝ128፥2፤ ሉቃ6፥23

[ዘ]13 ወይም *እኔን ከሞት*
[ዠ]13 ወይም *በሕያዋን ምድር*
[የ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ደ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ጀ]9 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጒም በትክክል አይታወቅም።

## መዝሙር 59

## ክፉዎችን በመቃወም የቀረበ ጸሎት

ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ ዳዊትን ለመግደል ሰዎች ቤቱን ከብበው እንዲጠብቁት ሳኦል በላካቸው ጊዜ፤ የዳዊት ቅኔ[ገ]

[1]አምላክ ሆይ፤ ከጠላቶቼ እጅ አድነኝ፤
ሊያጠቁኝ ከሚነሡብኝም ጠብቀኝ።
[2]ከክፉ አድራጊዎች ታደገኝ፤
ደም ከተጠሙ ሰዎችም አድነኝ።
[3]እነሆ በነፍሴ ላይ አድብተዋልና፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ጨካኞች ያለ
በደሌ፣ ያለ ኀጢአቴ
በላዬ ተሰብስበው ዶለቱብኝ።
[4]እነርሱ ያለ በደሌ ሊያጠቁኝ
ተዘጋጅተው መጡ፤
አንተ ግን ትረዳኝ ዘንድ ተነሥ፤
ሁኔታዬንም ተመልከት።
[5]የሰራዊት አምላክ የሆንህ፣ አንተ የእስራኤል
አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፤
ሕዝቦችን ሁሉ ለመቅጣት ተነሥ፤
በተንኰላቸው በደል የሚፈጽሙትንም
ሁሉ አትማራቸው። ሴላ

[6]እንደ ውሻ እያላዘኑ፣
በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤
በከተማዪቱም ዙሪያ ይራወጣሉ።
[7]ከአፋቸው የሚወጣውን ተመልከት፤
ሰይፍ በከንፈራቸው ላይ አለ፤
"ማን ሊሰማን ይችላል?" ይላሉና።
[8]እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን
ትሥቅባቸዋለህ፤
ሕዝቦችን ሁሉ በንቀት ታያቸዋለህ።

[9]ብርታቴ ሆይ፤ አንተን እጠብቃለሁ፤
አምላክ ሆይ፤ አንተ መጠጊያዬ ነህና።

[10]እግዚአብሔር በምሕረቱ ይገናኘኛል፤
አምላኬ የጠላቶቼን ውድቀት ያሳየኛል።
[11]ጋሻችን[ጠ] ጌታ ሆይ፤ አትግደላቸው፤
አለበለዚያ ሕዝቤ ይረሳል፤
በኀይልህ አንከራታቸው፤
ዝቅ ዝቅም አድርጋቸው።
[12]ከአፋቸው ስለሚወጣው ኀጢአት፣
ከከንፈራቸውም ስለሚሰነዘረው ቃል፣
በትዕቢታቸው ይያዙ።
ስለ ተናገሩት መርገምና ውሸት፣
[13]በቍጣ አጥፋቸው፤
ፈጽመህም አስወግዳቸው፤
በዚህም እግዚአብሔር የያዕቆብ ገዥ መሆኑ፣
እስከ ምድር ዳርቻ ይታወቃል። ሴላ

[14]እንደ ውሻ እያላዘኑ፣
በምሽት ተመልሰው ይመጣሉ፤
በከተማዪቱም ዙሪያ ይራወጣሉ።
[15]ምግብ ፍለጋ ይራወጣሉ፤
ካልጠገቡም ያላዝናሉ።
[16]እኔ ግን ስለ ኀይልህ እዘምራለሁ፤
በማለዳም ስለ ምሕረትህ እዘምራለሁ፤
አንተ መጠጊያዬ፣
በመከራም ቀን ዐምባዬ ነህና።
[17]ብርታቴ ሆይ፤ ውዳሴ አቀርብልሃለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ መጠጊያዬ፣
የምትወደኝም አምላኬ ነህና።

## መዝሙር 60

## ከሽንፈት በኋላ የቀረበ ብሔራዊ ጸሎት

60፥5-12 ተጓ ምብ-መዝ108፥6-13

ለመዘምራን አለቃ፤ "የኪዳን ጽጌረዳ"። በሚለው ቅኝት የሚዘመር፤[ጨ] በሰሜናዊ ምዕራብ መስጴጦምያና[ጰ] በማእከላዊ ሶርያ የሚኖሩትን አራማውያን[ጸ] በወጋቸው ጊዜ፣ ኢዮአብም ተመልሶ በጨው ሸለቆ አሥራ ሁለት ሺህ ኤዶማውያንን በፈጀ ጊዜ፣ ለትምህርት፤ የዳዊት ቅኔ

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ጣልኸን፤ አንኰታኰትኸን፤
ተቈጣኸንም፤ አሁን ግን መልሰህ
አብጀን።
[2]ምድሪቱን አናወጥሃት፤ ፍርክስክስ
አደረግሃት፤
ትንገዳገዳለችና ስብራቷን ጠግን።
[3]ለሕዝብህ አበሳውን አሳየኸው፤
ናላ የሚያዞር የወይን ጠጅ
እንድንጠጣም ሰጠኸን።
[4]ነገር ግን ከቀስት እንዲያመልጡ፣
ለሚፈሩህ ምልክት አቆምህላቸው።
ሴላ

[5]ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ፣
በቀኝ እጅህ ርዳን፤ መልስም ስጠን።
[6]እግዚአብሔር ከመቅደሱ እንዲህ ሲል
ተናገረ፤
"ደስ እያለኝ የሴኬምን ምድር
እሸንሽናለሁ፤
የሱኮትን ሸለቆ አከፋፍላለሁ።
[7]ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤
ኤፍሬም የራስ ቍሬ ነው፤
ይሁዳም በትረ መንግሥቴ ነው።
[8]ሞዓብ የመታጠቢያ ገንዳዬ ነው፤
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እወረውራለሁ፤
በፍልስጥኤም ላይ በድል እልል
እላለሁ።"

[9]ወደ ተመሸገው ከተማ ማን ያመጣኛል?
ማንስ ወደ ኤዶምያስ ይመራኛል?
[10]አምላክ ሆይ፤ የጣልኸን አንተ
አይደለህምን?

[ገ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ጠ]11 ወይም ልዑል ተብሎ መተርጐም ይችላል።
[ጨ]ርእሱ የሥነ ጽሑፉን ቅርጽ ወይም የመዝሙሩን ሁኔታ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።
[ጰ]ርእሱ የአራማውያን ወይም የሰሜን ምዕራብ መስጴጦምያ ነው።
[ጸ]ርእሱ በመካከለኛው ሶርያ የሚገኙት አራማውያንን የሚያመለክት ነው።

59 ርዕስ1ሳሙ19፥11
59፥1 መዝ20፥1፤143፥9
59፥2 14፥4፤26፥9፤36፥12፤53፥4፤92፥7፤94፥16፤139፥19፤ምሳ29፥10
59፥3 መዝ56፥6
59፥4 መዝ13፥3፤119፥3፤ማቴ5፥11
59፥5 9፥5፤44፥23፤69፥6፤80፥4፤84፥8፤ኢሳ10፥3፤ኤር18፥23
59፥6 ቍ14፤መዝ 22፥16
59፥7 ኢዮ22፥13፤መዝ55፥21፤94፥4፤ምሳ10፥32፤12፥23፤15፥2፥28
59፥8 መዝ2፥4፤37፥13፤ምሳ1፥26
59፥9 መዝ9፥9፤18፥1፥2፤62፥2፤71፥3
59፥11 ዘዳ4፥9፤6፥12፤መዝ3፥3፤84፥9፤89፥10፤106፥27፤144፥6፤ኢሳ33፥3
59፥12 መዝ10፥7፤64፥8፤ምሳ10፥14፤12፥13፤ኢሳ2፥12፤5፥15 ፤ሶፎ3፥11
59፥13 መዝ83፥18፤104፥35
59፥15 ኢዮ15፥23
59፥16 ዘጸ4፥30፤1ሳሙ2፥10፤2ሳሙ22፥3፤መዝ5፥3፤88፥13፤101፥1፤108፥1
59፥17 ቍ10
60 ርዕስ2ሳሙ8፥13
60፥1 2ሳሙ5፥20፤መዝ44፥9፤79፥5፤80፥3
60፥2 2ዜና7፥14፤መዝ18፥7
60፥3 መዝ71፥20፤75፥8፤ኢሳ29፥9፤51፥17፤63፥6፤ኤር25፥16፤ዘካ12፥2፤ራእ14፥10
60፥4 ኢሳ5፥26፤11፥10፥12፤18፥3
60፥5 ዘዳ33፥12፤ኢዮ40፥14
60፥6 ዘፍ12፥6፤33፥17
60፥7 ዘፍ41፥52፤49፥10፤ዘኍ34፥19፤ኢሱ13፥31
60፥8 2ሳሙ8፥1
60፥10 ኢሱ7፥12

ሕግዚሕብሔር ሆይ፤ ከሰራዊታችን ጋር
እኮ አልወጣ አልህ!
11በጠላት ላይ ድልን አቀዳጀን፤
የሰው ርዳታ ከንቱ ነውና።
12በሕግዚሕብሔር ክንደ ብርቱ እንሆናለን፤
ጠላቶቻችንን የሚረጋግጥልን እርሱ
ነውና።

## *መዝሙር* 61

### የግዞተኛ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር*

1ሕግዚሕብሔር ሆይ፤ ጩኸቴን ስማ፤
ጸሎቴንም አድምጥ።

2ልቤ በዛለ ጊዜ፣
ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጣራለሁ፤
ከእኔ ይልቅ ከፍ ወዳለው ዐለት ምራኝ።
3አንተ መጠጊያዬ፣
ከጠላትም የምተገንብህ ጽኑ ግንብ
ሆነኸኛልና።

4በድንኳንህ ለዘላለም ልኑር፤
በክንፎችህም ጥላ ልከለል። ሴላ

5ሕምላክ ሆይ፤ ስእለቴን ሰምተሃልና፤
ስምህን የሚፈሩትንም ሰዎች ርስት
ለእኔ ሰጠህ።

6የንጉሡን ዕድሜ አርዝምለት፤
ዘመኑንም እስከ ብዙ ትውልድ
ጨምርለት፤
7በሕግዚሕብሔር ፊት ለዘላለም ይንገሥ፤
ይጠብቁት ዘንድ ምሕረትህንና
ታማኝነትህን አዘጋጅለት።

8ስለዚህ ለስምህ ዘወትር ውዳሴ
አቀርባለሁ፤
ስእለቴንም በየጊዜው እፈጽማለሁ።

## *መዝሙር* 62

### ተስፋ በእግዚአብሔር ላይ ብቻ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ለኤዶታም፤ የዳዊት መዝሙር*

1ነፍሴ ዕረፍት የምታገኘው በሕግዚሕብሔር
ብቻ ነው፤
ድነቴም የሚመጣልኝ ከእርሱ ዘንድ
ነው።
2ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤
መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ ከቶም
አልናወጥም።

3ሰውን የምታጠቁት እስከ መቼ ነው?
ይህን የዘመመ ግድግዳ፣ የተንጋደደ
ዐጥር፣
ሁላችሁ ገፍታችሁ ልትጥሉት ትሻላችሁ?
4ከታላቅ ክብሩ ሊያዋርዱት፣
ይህን አንድ ነገር ወጠኑ፤
ሐሰት ባለበት ነገር ደስ ይሰኛሉ፤
በአፋቸው ይመርቃሉ፤
በልባቸው ግን ይራገማሉ። ሴላ

5ነፍሴ ሆይ፤ ዐርፈሽ ሕግዚሕብሔርን ብቻ
ጠብቂ፤
ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ነውና።
6ዐለቴና መድኀኒቴ እርሱ ብቻ ነው፤
መጠጊያዬም እርሱ ነው፤ እኔም
አልናወጥም።
7መዳኔና ክብሬ በሕግዚሕብሔር ነው፤[θ]
ብርቱ ዐለቴና መሸሸጊያዬ በሕግዚሕብሔር
ነው።
8ሰዎች ሆይ፤ ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ፤
ልባችሁን በፊቱ አፍስሱ፤
ሕግዚሕብሔር መጠጊያችን ነውና። ሴላ

9ከተናቀ ወገን መወለድ ከንቱ፣
ከከበረውም መወለዱ ሐሰት ነው።
በሚዛን ላይ ከፍ ብለው ቢታዩም፣
ሁሉም በአንድነት ከነፋስ የቀለሉ
ናቸው።
10በዝርፊያ አትታመኑ፤
በቅሚያም ተስፋ አታድርጉ፤
በዚህ ብትበለጽጉም፣
ልባችሁ ይህን አለኝታ አያድርግ።

11ሕግዚሕብሔር አንድ ነገር ተናገረ፤
እኔም ይህን ሁለት ጊዜ ሰማሁ፤
ኀይል የሕግዚሕብሔር ነው።
12ጌታ ሆይ፤ ምሕረትም የአንተ ነው፤
አንተ ለእያንዳንዱ፣
እንደ ሥራው ትከፍለዋለህ።

## *መዝሙር* 63

### እግዚአብሔርን መፈለግ

*በይሁዳ ምድረ በዳ በነበረ ጊዜ፤ የዳዊት መዝሙር*

1ሕግዚሕብሔር ሆይ፤ አንተ ሕምላኬ ነህ፤
አንተን ከልብ እሻለሁ፤
ውሃ በሌለበት፣
በደረቅና በተራቈተ ምድር፣
ነፍሴ አንተን ተጠማች፤
ሥጋዬም አንተን ናፈቀች።

2ስለዚህ በመቅደስ ውስጥ አየሁህ፤
ኀይልህንና ክብርህንም ተመለከትሁ።
3ምሕረትህ ከሕይወት ይበልጣልና፤
ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል።
4እንግዲህ፣ በሕይወቴ ዘመን አመሰግንሃለሁ፤
በአንተም ስም እጆቼን አነሣለሁ።
5ነፍሴ በቅቤና በሥብ እንደሚረካ ሰው
ትረካለች፤
አፌም በሚያዜሙ ከንፈሮች በደስታ
ያወድስሃል።

60፥11 መዝ146፥3፤ምሳ3፥5
60፥12 ኢዮ40፥12፤መዝ44፥5
61፥1 መዝ4፥1፤64፥1፤86፥6
61፥2 መዝ6፥2፤18፥2፤31፥2፤94፥22
61፥3 መዝ9፥9፤46፥1፤59፥9፤62፥7፤ምሳ18፥10
61፥4 ዘዳ32፥11፤መዝ15፥1፤ማቴ 23፥37
61፥5 ዘፀ6፥3፤ዘኁ30፥2፤ዘዳ33፥9፤ነህ1፥11፤መዝ56፥12፤102፥15፤ኢሳ59፥19፤ማቴ6፥9
61፥6 1ነገ3፥14፤መዝ21፥4
61፥7 መዝ40፥11፤41፥12፤ሉቃ22፥69፤ኤፌ1፥20፤ቈላ3፥1
61፥8 ዘፀ15፥1፤ዘኁ30፥2፤ዘዳ23፥21፤መዝ7፥17፤30፥4
62፥1 ቍ5፤መዝ 5፥3
62፥2 ዘፀ15፥2፤ኢዮ29፥18፤መዝ18፥31፤59፥9፤89፥26
62፥3 ኢሳ30፥13
62፥4 መዝ28፥3፤55፥21
62፥5 ቍ1
62፥7 መዝ61፥3
62፥8 1ሳሙ1፥15፤መዝ37፥5፤42፥4፤ኢሳ26፥4፤ማቴ26፥36-46
62፥9 ኢዮ7፥7፤መዝ49፥2፤ኢሳ40፥15
62፥10 ኢዮ31፥25፤መዝ12፥5፤ኢሳ61፥8፤ሕዝ22፥29፤ናሆ3፥1፤ማቴ19፥23-24፤1ጢሞ6፥6-10፡17
62፥11 1ዜና29፥11፤ራእ19፥1
62፥12 ኢዮ21፥31፤መዝ28፥4፤86፥5፤103፥8፤130፥7፤ማቴ16፥27፤ሮሜ2፥6፤1ቆሮ3፥ 8፤ቈላ3፥25
63፥1 መዝ42፥2፤84፥2፤143፥6
63፥2 ዘፀ16፥7፤መዝ15፥1፤27፥4፤68፥24
63፥3 መዝ36፥7፤69፥16፤106፥45፤109፥21
63፥4 መዝ28፥2፤104፥33፤146፥2፤ኢሳ 38፥20፤1ጢሞ2፥8
63፥5 መዝ36፥8፤ማቴ5፥6

[θ]6 ወይም *ልዑል እግዚአብሔር ድኅነቴና ክብሬ ነው* ተብሎ መተርጐም ይችላል።

[6]በመኝታዬ አስብሃለሁ፤
ሌሊቱንም ሁሉ ስለ አንተ
አሰላስላለሁ።
[7]አንተ ረዳቴ ነህና፣
በክንፎችህ ሥር ተጠልዬ በደስታ
እዘምራለሁ።
[8]ነፍሴ አንተን የሙጥኝ ብላለች፤
ቀኝ እጅህም ደግፋ ይዛኛለች።

[9]ነፍሴን ለማጥፋት የሚሹ ግን፣
ወደ ምድር ጥልቅ ይወርዳሉ፤
[10]ለሰይፍ አልፈው ይሰጣሉ፤
የቀበሮዎችም ምግብ ይሆናሉ።

[11]ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል፤
በእግዚአብሔርም ስም ቃል የሚገቡ ሁሉ
ይከብራሉ፤
የሐሰተኞች አንደበትም ትዘጋለች።

### መዝሙር 64

## የተሳዳቢዎች ቅጣት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

[1]አምላክ ሆይ፤ የብሶት ቃሌን ስማ፤
ሕይወቴንም ከሚያስፈራ የጠላት ዛቻ
ከልላት።
[2]ከክፉዎች አድማ ሰውረኝ፤
ከዐመፀኞችም ሸንጎ ጋርደኝ።

[3]እነርሱ ምላሳቸውን እንደ ሰይፍ ይስላሉ፤
መርዘኛ ቃላቸውንም እንደ ፍላጻ
ያነጣጥራሉ።
[4]አሸምቀው ንጹሑን ሰው ይነድፉታል፤
ድንገት ይነድፉታል፤ አይፈሩምም።
[5]ክፉ ተግባር ለማከናወን እርስ በርስ
ይመካከራሉ፤
በስውር ወጥመድ ለመዘርጋት ይነጋገራሉ፤
"ማንስ ሊያየን ይችላል?"[ፊ] ይባባላሉ።
[6]ግፍን ያውጠነጥናሉ፤
ደግሞም፣ "የረቀቀች ሤራ
አዘጋጅተናል" ይላሉ፤
አቤት! ልቡ፣ አእምሮውም እንዴት
ጥልቅ ነው!

[7]እግዚአብሔር ግን በፍላጻው ይነድፋቸዋል፤
እነርሱም ድንገት ይቈስላሉ።
[8]በገዛ ምላሳቸው ያሰናክላቸዋል፤
ጥፋትንም ያመጣባቸዋል፤
የሚያዩአቸውም ሁሉ በትዝብት
ራሳቸውን ይነቀንቃሉ።

[9]የሰው ልጆች ሁሉ ይፈራሉ፤
የእግዚአብሔርን ሥራ በይፋ ያወራሉ፤
ያደረገውንም በጥሞና ያሰላስላሉ።
[10]ጻድቅ *በእግዚአብሔር* ደስ ይበለው፤
እርሱንም መጠጊያ ያድርገው፤
ልበ ቅኖችም ሁሉ ደስ ይበላቸው።

63፥6 ዘጻ6፥4-9፤ መዝ16፥7፤119፥148፤ ማቴ14፥25
63፥7 ሩት2፥12፤ መዝ27፥9፤118፥7
63፥8 ዘኍ32፥12፤ መዝ41፥12፤ሆሴ6፥3
63፥9 መዝ40፥14፤ 55፥15፤71፥20፤ 95፥4፤139፥15
63፥10 ኤር18፥21፤ ሰቆ5፥18፤ሕዝ35፥5፤ አሞ1፥11
63፥11 ኢዮ5፥16፤ ኢሳ19፥18፤45፥23፤ 65፥16፤ሮሜ3፥19
64፥1 መዝ140፥1፤ 142፥2
64፥2 ዘፀ1፥10፤ መዝ 56፥6፤59፥2
64፥3 መዝ7፥13፤ 55፥21፤58፥7፤ ኢሳ 49፥2
64፥4 ኢዮ9፥23፤ መዝ10፥8፤11፥2፤ 55፥19
64፥5 ኢዮ22፥13፤ መዝ91፥3፤119፥110፤ 140፥5፤141፥9
64፥8 ዘዳ28፥37፤ 2ነገ19፥21፤ መዝ59፥12፤109፥25፤ ምሳ18፥7
64፥9 መዝ40፥3፤ ኤር51፥10
64፥10 ኢዮ22፥19፤ መዝ11፥1፤25፥20፤ 31፥2፤32፥11
65፥1 ዘዳ23፥21፤ መዝ2፥6፤116፥18
65፥2 መዝ86፥9፤ ኢሳ66፥23
65፥3 መዝ40፥12፤ 79፥9፤ሮሜ3፥25፤ ዕብ 9፥14
65፥4 ዘኍ16፥5፤ መዝ33፥12፤36፥8
65፥5 ዘዳ4፥34፤ መዝ 18፥46፤45፥4፤ 48፥10፤68፥19፤ 85፥4፤106፥22፤ 107፥23፤ኢሳ64፥3
65፥6 መዝ18፥1፤ 93፥1፤ኢሳ51፥9፤ አሞ 4፥13
65፥7 ዘዳ32፥41፤ መዝ2፥1፤74፥23፤ 89፥9፤93፥3-4፤ 107፥29፤139፥20፤ ኢሳ17፥12-13፤ ማቴ8፥26
65፥8 መዝ100፥2፤ 107፥22፤126፥2፤ ኢሳ 24፥16፤52፥9
65፥9 ዘፍ27፥28፤ ዘሌ26፥4፤ዘዳ32፥14፤ መዝ68፥9-10፤ 104፥14:24
65፥10 ዘዳ32፥2፤ 2ሳሙ1፥21፤ኢዮ 36፥28፤ሐሥ14፥17
65፥11 ዘዳ28፥12፤ ኢዮ36፥28፤መዝ

### መዝሙር 65

## የምስጋና መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት የምስጋና መዝሙር*

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ በጽዮን ለአንተ ውዳሴ
ይገባል፤[ፐ]
ለአንተ የተሳልነውን እንፈጽማለን።
[2]ጸሎትን የምትሰማ ሆይ፤
የሰው ልጆች ሁሉ ወደ አንተ ይመጣሉ።
[3]ኀጢአት ባጥለቀለቀን ጊዜ፣
አንተ መተላለፋችንን ይቅር አልህ።[ሀ]
[4]አንተ የመረጥኸው፣ ወደ ራስህ
ያቀረብኸው፣
በአደባባይህም ያኖርኸው ምስጉን ነው!
ከተቀደሰው መቅደስህ፣
ከቤትህም በረከት እንረካለን።

[5]እግዚአብሔር አዳኛችን ሆይ፤
በጽድቅ ድንቅ አሠራር መልስልን፤
አንተ ለምድር ዳርቻ ሁሉ፣
በርቀት ላለውም ባሕር ተስፋ ነህ።

[6]ተራሮችን በብርታትህ መሠረትህ፤
ኀይልንም ታጥቀሃል።
[7]አንተ የባሕሮችን ማስገምገም፣
የማዕበላቸውን ፉጨት፣
የሕዝቦችንም ሁከት ጸጥ ታደርጋለህ።
[8]ርቀው በምድር ዳርቻ ያሉት ከድንቅ
ሥራህ የተነሣ ይደነግጣሉ፤
የንጋትንና የምሽትን መምጫዎች፣
በደስታ እልል እንዲሉ
ታደርጋቸዋለህ።

[9]ምድርን ትጐበኛለህ፤ ታጠጣለህም፤
እጅግ ታበለጽጋታለህም።
ለሰዎች እህልን ይለግሱ ዘንድ፣
የእግዚአብሔር ወንዞች ውሃን የተሞሉ
ናቸው፤
አንተ እንዲህ እንዲሆን ወስነሃልና።[ሰ]

[10]ትልሚን በውሃ ታረሰርሳለህ፤
ቦይዋን ታስተካክላለህ፤
በካፊያ ታለሰልሳለህ፤
ቡቃያዋንም ትባርካለህ።
[11]ለዘመኑ በጎነትህን ታጐናጽፈዋለህ፤
ሠረገላህም በረከትን ተሞልቶ ይፈስሳል።
[12]የምድረ በዳው ሣር እጅግ ለመለመ፤
ኰረብቶችም ደስታን ተጐናጸፉ።
[13]ሜዳዎች መንጋ በመንጋ ሆኑ፤

104፥28፤147፥14፤ ሉቃ6፥38፤ዮሐ10፥10 65፥12 ኢዮ28፥26፤ መዝ98፥8፤ኢል2፥22 65፥13 መዝ72፥16፤98፥8፤144፥13፤ ኢሳ14፥8፤30፥23፤44፥23፤49፥13፤55፥12፤ዘካ8፥12

[ፊ]5 ወይም *ማንስ ሊያያቸው ይችላል*
[ፐ]1 በዕብራይስጡ የዚህ ቃል ትርጉም በትክክል አይታወቅም።
[ሀ]3 ወይም *አንተ ተቤዠህን*
[ሰ]9 ወይም *"አንተም ለዚህ ነው ምድርን ያዘጋጀሃት"*

ሽለቆችም በእህል ተሸፈኑ፤
እልል ይላሉ፤ ይዘምራሉም።

### መዝሙር 66

**የኅብረት ምስጋና**

*ለመዘምራን አለቃ፤ ማኅሌት፤ መዝሙር*

1ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል ይበል!
2ለስሙ ክብር ዘምሩ፤
ውዳሴውንም አድምቁ!
3እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት፤ “ሥራህ
እንዴት ግሩም ነው!
ጠላቶችህ ከኀይልህ ታላቅነት የተነሣ፣
በፊትህ ይርዳሉ።
4ምድር ሁሉ ይሰግድልሃል፤
በዝማሬ ያመሰግኑሃል፤
ለስምህም ይዘምራሉ። ሴላ
5ኑና፣ እግዚአብሔር ያደረገውን እዩ
በሰዎች መካከል ሥራው አስፈሪ ነው!
6ባሕሩን የብስ አደረገው፤
ወንዙን በእግር ተሻገሩ፤
ኑ፣ በእርሱ ደስ ይበለን።
7በኀይሉ ለዘላለም ይገዛል፤
ዐይኖቹ ሕዝቦችን ይመለከታሉ፤
እንግዲህ ዐመፀኞች ቀና ቀና አይበሉ። ሴላ
8ሕዝቦች ሆይ፤ አምላካችንን ባርኩ፤
የምስጋናውንም ድምፅ አሰሙ።
9እኛን በሕይወት የሚያኖረን፣
እግራችንንም ከመንሸራተት የሚጠብቅ
እርሱ ነው።
10አምላክ ሆይ፤ አንተ ፈተንኸን፤
እንደ ብርም አነጠርኸን።
11ወደ ወጥመድ አገባኸን፤
በጀርባችንም ሸክም ጫንህብን።
12ሰዎች በራሳችን ላይ እንዲፈነጩ
አደረግህ፤
በእሳትና በውሃ መካከል አለፍን፤
የኋላ ኋላ ግን ወደ በረከት አመጣኸን።
13የሚቃጠል መሥዋዕት ይዤ ወደ
መቅደስህ እገባለሁ፤
ስእለቴንም ለአንተ እፈጽማለሁ፤
14በመከራ ጊዜ ከአፌ የወጣ፣
በከንፈሬም የተናገርሁት ስእለት ነው።
15ፍሪዳዎችን የሚቃጠል መሥዋዕት
አድርጌ፣
አውራ በጎችንም የሚጤስ ቍርባን
አድርጌ አቀርብልሃለሁ፤
ኰርማዎችንና ፍየሎችንም እሠዋልሃለሁ። ሴላ
16እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሁሉ፤ ኑና ስሙ፤
ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ።
17በአፌ ወደ እርሱ ጮኽሁ፤
በአንደበቴም አመሰገንሁት።

66፥1 መዝ81፥1፤ 84፥8፤95፥1፤98፥4፤ 100፥1
66፥2 መዝ79፥9፤ 86፥9፤ኢሳ42፥8፡12፤ 43፥21
66፥3 ዘጸ7፥21፤ 10፥21፤2ሳሙ22፥45፤ መዝ65፥5፤106፥22፤ 111፥6፤145፥6
66፥4 መዝ7፥17፤ 22፥27፤67፥3
66፥5 ቍ3፤ መዝ 106፥22
66፥6 ዘፍ8፥1፤ ዘፀ14፥22፤ዘሌ23፥40፤ 1ቆሮ10፥1
66፥7 ዘፀ3፥16፤ 15፥18፤ዘኍ17፥10፤ መዝ11፥4፤112፥10፤ 140፥8፤145፥13
66፥8 መዝ22፥23
66፥9 ዘዳ32፥35፤ ኢዮ12፥5፤መዝ30፥3
66፥10 ዘፀ15፥25፤ ኢዮ6፥29፤28፥1፤ መዝ12፥6
66፥11 ዘፍ3፥17፤ ዘፀ1፥14፤መዝ38፥4፤ 142፥7፤146፥7፤ ኢሳ 10፥27፤ 42፥7፡22፤61፥1
66፥12 መዝ18፥19 ፤ኢሳ51፥23
66፥13 መዝ22፥25፤ 50፥14፤51፥19፤ 116፥14፤መክ5፥4፤ ዮና2፥9
66፥15 ዘሌ16፥5፤ መዝ51፥19
66፥16 መዝ34፥11 ፤71፥15፡24
66፥18 ዘዳ1፥45፤ 1ሳሙ8፥18፤ያዕ4፥3
66፥19 መዝ18፥6
66፥20 መዝ22፥24
67፥1 ዘኍ6፥24-26
67፥2 መዝ98፥2፤ ኢሳ40፥5፤52፥10፤ 62፥1፡2፤ሐሥ10፥35 ፤ቲቶ2፥11
67፥3 ቍ5
67፥4 መዝ9፥4፤ 68፥32፤96፥10-13፤ 100፥1-2
67፥6 ዘፍ8፥22፤ 12፥2፤ዘሌ26፥4፤መዝ 85፥12፤ኢሳ55፥10፤ ሕዝ34፥27፤ዘካ8፥12
67፥7 መዝ2፥8፤ 33፥8
68፥1 ዘኍ10፥35፤ መዝ12፥5፤18፥14፤ 89፥10፤92፥9፤132፥8፤ 144፥6፤ኢሳ17፥13፤ 21፥15፤33፥3
68፥2 ዘኍ10፥35፤ መዝ9፥3፤22፥14፤ 37፥20፤80፥16
68፥3 መዝ64፥10፤ 97፥12
68፥4 ቍ33፤ዘፀ

18ኀጢአትን በልቤ አስተናግጄ ቢሆን
ኖሮ፣
ጌታ ባልሰማኝ ነበር።
19አሁን ግን እግዚአብሔር በእርግጥ ሰምቶኛል፤
ጸሎቴንም አድምጦአል።
20ጸሎቴን ያልናቀ፣
ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ፣
እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው።

### መዝሙር 67

**የመከር ጊዜ መዝሙር**

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች የሚዘመር፤ የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

1እግዚአብሔር ይማረን፤ ይባርከን፤
ፊቱንም በላያችን ያብራ፤ ሴላ
2መንገድህ በምድር ላይ፣
ማዳንህም በሕዝቦች ሁሉ መካከል
ይታወቅ ዘንድ።
3እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰዎች ያመስግኑህ፤
ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ።
4ለሕዝቦች በቅን ስለምትፈርድላቸው፣
ሰዎችንም በምድር ላይ ስለምትመራ፣
ሕዝቦች ደስ ይበላቸው፤ በእልልታም
ይዘምሩ። ሴላ
5እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰዎች ያመስግኑህ፤
ሰዎች ሁሉ ምስጋና ያቅርቡልህ።
6ምድር ፍሬዋን ሰጠች፤
እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል።
7እግዚአብሔር ይባርከናል፤
የምድርም ዳርቻዎች ሁሉ እርሱን
ይፈሩታል።

### መዝሙር 68

**ብሔራዊ የድል መዝሙር**

*ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

1እግዚአብሔር ይነሣ፤ ጠላቶቹ ይበተኑ፤
የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ።
2ጢስ እንደሚበንን፣
እንዲሁ አብንናቸው።
ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፣
ክፉዎችም እንዲሁ ከእግዚአብሔር ፊት
ይጥፉ።
3ጻድቃን ግን ደስ ይበላቸው፤
በእግዚአብሔር ፊት ሐሤት ያድርጉ፤
ደስታንና ፍስሓን የተሞሉ ይሁኑ።
4ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ለስሙም ተቀኙ፤
በደመናት ላይ የሚሄደውን ከፍ
አድርጉት፤[ሐ]
ስሙ *እግዚአብሔር* በተባለው ፊት፣

[ሐ]4 ወይም *በምድረ በዳ ለሚሄደው መንገድን አዘጋጁለት።*

እጅግ ደስ ይበላችሁ።
5እግዚአብሔር በተቀደሰ ማደሪያው፣
ለድኻ አደጉ አባት፣ ለባልቴቲቱም
ተሟጋች ነው።
6እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤተ ሰብ መካከል
ያኖራል፤[መ]
እስረኞችን ነጻ አውጥቶ ያስፈነድቃል፤
ዐመፀኞች ግን ምድረ በዳ ይኖራሉ።
7እግዚአብሔር ሆይ፤ በሕዝብህ ፊት በወጣህ
ጊዜ፣
በምድረ በዳም በተጓዝህ ጊዜ፣ ሴላ
8በሲና አምላክ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣
በእስራኤል አምላክ፣ በእግዚአብሔር ፊት፣
ምድር ተንቀጠቀጠች፤
ሰማያትም ዶፍ አወረዱ።
9እግዚአብሔር ሆይ፣ በቂ ዝናብ አዘነብህ፤
ክው ብሎ የደረቀውን ርስትህን
አረሰረስህ።
10መንጋህ መኖሪያው አደረጋት፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ከበረከትህ ለድኾች
ሰጠህ።
11ጌታ እንዲህ ሲል ቃሉን አስተላለፈ፤
ትእዛዙን የሚያውጁትም ብዙ ሰራዊት
ናቸው፤
12"የሰራዊት ነገሥታት ፈጥነው ይሸሻሉ፤
በሰፈር የዋሉ ሴቶችም ምርኮን
ተካፈሉ።
13በበጎች በረት መካከል[ሠ] ብትገኙ እንኳ፣
ከብር እንደ ተሠሩ የርግብ ክንፎች፣
በቅጠልያ ወርቅ እንደ ተለበጡ ላባዎች
ናችሁ።"
14ሁሉን ቻዩ[ረ] በዚያ የነበሩትን ነገሥታት
በበተነ ጊዜ፣
በሰልሞን እንደሚወርድ በረዶ
አደረጋቸው።
15አንተ ብርቱ ተራራ፣ የባሳን ተራራ
ሆይ፤
አንተ ባለ ብዙ ጫፍ ተራራ፣ የባሳን
ተራራ፤
16እናንተ ባለ ብዙ ጫፍ ተራሮች ሆይ፤
እግዚአብሔር ሊኖርበት የመረጠውን
ተራራ፣
በርግጥ እግዚአብሔር ለዘላለም
የሚኖርበትን ተራራ ለምን በምቀኝነት
ዐይን ታያላችሁ?
17የእግዚአብሔር ሠረገላዎች እልፍ አእላፍ
ናቸው፤
ሺህ ጊዜም ሺህ ናቸው፤
ጌታ ከሲና ወደ መቅደሱ ገባ።
18ወደ ላይ ዐረግህ፤
ምርኮ አጋበስህ፤
እግዚአብሔር አምላክ ሆይ፤ አንተ[ሰ] በዚያ
ትኖር ዘንድ፣
ከዐመፀኞችም ሳይቀር፣
ከሰዎች ስጦታን ተቀበልህ።
19ሸክማችንን በየዕለቱ የሚሸከምልን፣
አዳኝ አምላካችን፣ ጌታ ይባረክ። ሴላ
20አምላካችን የሚያድን አምላክ ነው፤
ከሞት ማምለጥ የሚቻለውም በጌታ
በእግዚአብሔር ነው።
21በእርግጥ እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ፣
በኀጢአታቸውም የሚጸኑትን ሰዎች
ጠጕራም አናት ይፈነካክታል።
22ጌታ እንዲህ ይላል፤ "ከባሳን መልሼ
አመጣቸዋለሁ፤
ከባሕርም ጥልቀት አውጥቼ
አመጣቸዋለሁ፤
23እግርህ በጠላትህ ደም ውስጥ
እንዲጠልቅ፣
የውሻህም ምላስ ከጠላትህ ድርሻውን
እንዲያገኝ ነው።"
24አምላክ ሆይ፤ የክብር አካሄድህ ታየ፤
ይህም አምላኬና ንጉሤ ወደ ቤተ
መቅደሱ የሚያደርገው የክብር
አካሄድ ነው።
25መዘምራን ከፊት፣ መሣሪያ የሚጫወቱ
ከኋላ ሆነው ሲሄዱ፣
ከበሮ የሚመቱ ቈነጃጅትም
በመካከላቸው ነበሩ።
26እግዚአብሔርን በጉባኤ አመስግኑት፤
ከእስራኤል ምንጭ የተገኛችሁ እግዚ
አብሔርን አመስግኑ።
27የሚመራቸው ትንሹ ብንያም ነው፤
በዚያ በብዙ የሚቈጠሩ የይሁዳ
መሳፍንት፣
እንዲሁም የዛብሎንና የንፍታሌም
መሳፍንት ይገኛሉ።
28እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀይልህን እዘዝ፤[ሸ]
አምላክ ሆይ ቀድሞ እንዳደረግህልን
አሁንም ብርታትህን አሳየን።
29በኢየሩሳሌም ስላለው ቤተ መቅደስህ፣
ነገሥታት እጅ መንሻ ያመጡልሃል።
30በሸምበቆ መካከል ያሉትን አራዊት፣
በሕዝቡ ጥጆች መካከል ያለውንም
የኮርማ መንጋ ገሥጽ፤
ብር ይገብር ዘንድም ይንበርከክ፤

6፥3፤20፥21፤ዘዳ33፥26
፤2ሳሙ22፥50፤
መዝ7፥17፤30፥4፤
66፥2፤83፥18፤96፥2፤
100፥4፤135፥3
68፥5 ዘፀ22፥22
ዘዳ10፥18፤26፥15፤
መዝ10፥14፤ኤር25፥30
68፥6 መዝ25፥16፤
79፥11፤102፥20፤113፥9፤
146፥7፤ኢሳ35፥7
፤49፥10፤58፥11፤
61፥1፤ሉቃ4፥18
68፥7 ዘፀ13፥21፤
መዝ78፥40፤106፥14
68፥8 ዘዳ33፥2፤
2ሳሙ21፥10፤22፥8፤
መሳ5፥4:5፤መክ11፥3
68፥9 ዘዳ32፥2፤
ኢዮ36፥28፤ሕዝ34፥26
68፥10 ዘዳ28፥12፤
መዝ65፥9
68፥11 ሉቃ2፥13
68፥12 ኢሱ10፥16፤
መሳ5፥30
68፥13 ዘፍ49፥14
68፥14 መሳ9፥48፤
2ሳሙ22፥15
68፥15 ቍ22፤
ዘኍ21፥33፤መዝ36፥6፤
ኤር22፥20
68፥16 ዘዳ12፥5፤
መዝ2፥6፤132፥13:14
68፥17 2ነገ2፥11፤
ኢሳ66፥15፤ዳን7፥10፤
ዕን3፥8
68፥18 ዘኍ17፥10
መሳ5፥12፤መዝ7፥7፤
47፥5፤ኤፌ4፥8
68፥19 መዝ65፥5፤
81፥6
68፥20 1ሳሙ10፥19
፤መዝ56፥13፤
ኤር45፥5፤ሕዝ6፥8
68፥21 መዝ74፥14
፤110፥5፤ዕን3፥13
68፥22 ኢዮ36፥30፤
ማቴ18፥6
68፥23 1ነገ21፥19፤
2ነገ9፥36፤መዝ58፥10
68፥24 መዝ63፥2
68፥25 ዘፍ31፥27፤
1ዜና6፥31፤15፥16፤
2ዜና5፥12፤ኢሳ5፥12፤
ራዕ18፥22
68፥26 ዘሌ19፥2፤
መዝ22፥22፤ዕብ2፥12
68፥27 ዘኍ34፥21፤
መሳ5፥18፤
1ሳሙ9፥21
68፥28 ዘፀ9፥16፤
መዝ29፥11፤ኢሳ26፥12፤
29፥23፤45፥11፤
60፥21፤64፥8
68፥29 2ዜና9፥24፤
32፥23
68፥30 ኢዮ40፥21፤
መዝ18፥14፤22፥12፤
89፥10፤120፥7፤
140፥2፤ኢሳ27፥1፤
34፥7፤ 51፥9፤
ኤር50፥27፤ሕዝ29፥3

[መ]6 ወይም *ብቸኞችን በገዛ ምድራቸው*
[ሠ]13 ወይም *በኮርቻ ማስቀመጫዎች*
[ረ]14 ዕብራይስጡ *ሻዳይ* ይላል።
[ሰ]18 ወይም *እናንተ*
[ሸ]28 ብዙ የዕብራይስጥ ቅጆች፣ የሰብዓ ሊቃናት ትርጒምና የሱርስቱ ቅጅ *እግዚአብሔር ሆይ፤ ኀይልህን ጥራ* ይላሉ። አብዛኞቹ የዕብራይስጥ ቅጆች ግን *እግዚአብሔር ለአንተ ኀይል ይጠራልሃል* ይላሉ።

ጦርነትን የሚወዱ ሕዝቦችንም
በትናቸው።
31 መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ፤
ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር
ትዘረጋለች።

32 የምድር መንግሥታት ሆይ፤
ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤
ለጌታ ተቀኙ። ሴላ
33 ከጥንት ጀምሮ ከነበሩት ሰማያት በላይ
ለወጣው፣
በኀያል ድምፁ ለሚያስገመግመው
ዘምሩ።
34 ግርማው በእስራኤል ላይ፣
ኀይሉም ከደመናት በላይ ነው፣
እግዚአብሔርን ብርታት የአንተ ነው
በሉት።
35 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ በመቅደስህ
ድንቅ ነህ፤
የእስራኤል አምላክ ለሕዝቡ ኀይልና
ብርታትን ይሰጣል።

እግዚአብሔር ይባረክ!

## *መዝሙር* 69

### እንጕርጕሮ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በ"ጽጌረዳ" ዜማ፤ የዳዊት መዝሙር*

1 አምላክ ሆይ፤ አድነኝ፤
ውሃ እስከ ዐንገቴ ደርሶብኛልና።
2 የእግር መቆሚያ በሌለው፣
በጥልቅ ረግረግ ውስጥ ሰጥሜአለሁ፤
ወደ ጥልቅ ውሃ ገባሁ፤
ሞገዱም አሰጠመኝ።
3 በጩኸት ደከምሁ፤
ጉሮሮዬም ደረቀ፤
አምላኬን በመጠባበቅ፣
ዐይኖቼ ፈዘዙ።
4 ያለ ምክንያት የሚጠሉኝ፣
ከራሴ ጠጕር በዙ፤
ሕይወቴን ለማጥፋት የሚፈልጉ፣
በከንቱም የሚጠሉኝ ብዙዎች ሆኑ፤
ያልሰረቅሁትን ነገር፣
መልሰህ አምጣ ተባልሁ።

5 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ሞኝነቴን
ታውቃለህ፤
በደሌም ከአንተ የተሰወረ አይደለም።
6 ጌታ የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
አንተን ተስፋ የሚያደርጉ፣
በእኔ ምክንያት አይፈሩ፤
የእስራኤል አምላክ ሆይ፤
አንተን አጥብቀው የሚሹ፣
ከእኔ የተነሣ አይዋረዱ።
7 ስለ አንተ ስድብን ታግሻለሁና፤
እፍረትም ፊቴን ሸፍኖአልና።
8 ለወንድሞቼ እንደ ባዕድ፣
ለእናቴም ልጆች እንደ እንግዳ
ሆንሁባቸው።
9 የቤትህ ቅናት በላችኝ፤
የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ዐርፎአል።
10 ነፍሴን በጾም ባስመረርሁ ጊዜ፣
እነርሱ ሰደቡኝ።
11 ማቅ በለበስሁ ጊዜ፣
መተረቻ አደረጉኝ።
12 በቅጥሩ ደጅ ለሚቀመጡት
የመነጋገሪያ ርእስ፣
ለሰካራሞችም መዝፈኛ ሆንሁ።

13 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔ ግን
በወደድኸው ሰዓት፣
ወደ አንተ እጸልያለሁ፤
አምላክ ሆይ፤ በታላቅ ምሕረትህ፣
በማዳንህም እርግጠኝነት መልስልኝ።
14 ከረግረግ አውጣኝ፤
እስጥም ዘንድ አትተወኝ፤
ከጥልቅ ውሃ፣
ከእነዚያ ከሚጠሉኝ ታደገኝ።
15 ጐርፍ አያጥለቅልቀኝ፤
ጥልቅ ውሃም አይዋጠኝ፤
ጕድጓዱም ተደርምሶ አይዘጋብኝ።
16 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ በጎ
ናትና ስማኝ፤
እንደ ርኅራኄም ብዛት መለስ በልልኝ።
17 ፊትህን ከባሪያህ አትሰውር፤
ጭንቅ ውስጥ ነኝና ፈጥነህ መልስልኝ።
18 ወደ እኔ ቀርበህ ታደገኝ፤
ስለ ጠላቶቼም ተቤዠኝ።

19 የደረሰብኝን ስድብ፣ ዕፍረትና ውርደት
ታውቃለህ፤
ጠላቶቼንም አንድ በአንድ
ታውቃቸዋለህ።
20 ስድብ ልቤን ጐድቶታል፤
ተስፋዬም ተሟጦአል፤
አስተዛዛኝ ፈለግሁ፤ አላገኘሁምም፤
አጽናኝም ፈለግሁ፤ አንድም
አልነበረም።
21 ምግቤን ከሐሞት ቀላቀሉ፤
ለጥማቴም ሆምጣጤ ሰጡኝ።

22 የቀረበላቸው ማእድ ወጥመድ
ይሁንባቸው፤
ለማኅበራቸውም አሽክላ ይሁን።
23 ዐይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፤
ጀርባቸውም ዘወትር ይጕበጥ።
24 መዓትህን በላያቸው አፍስስ፤
የቍጣህም መቅሠፍት ድንገት
ይድረስባቸው።
25 ሰፈራቸው ባድማ ይሁን፤

68፥31 ኢሳ11፥11፤ 18፥1፤19፥19፤43፥3፤ 45፥14፤ሶፎ3፥10
68፥32 መዝ7፥17፤ 46፥6፤67፥4
68፥33 ዘፀ9፥23፤ ዘዳ33፥26፤መዝ29፥3፡ 4፤ኢሳ30፥30፤ 33፥3፤66፥6
68፥34 ቍ28፤ መዝ45፥3
68፥35 ዘፍ28፥17፤ ዘዳ7፥21፤መዝ28፥6፤ 29፥11፤18፥1፤66፥20 ፤ኢሳ40፥29፤41፥10፤ 50፥2፤2ቆሮ1፥3
69፥1 መዝ32፥6፤ 42፥7፤ዮና2፥5
69፥2 ኢዮ30፥19
69፥3 መዝ6፥6፤ 119፥82
69፥4 መዝ25፥19፤ 35፥19፤38፥19፤ 40፥14፤119፥95፤ ኢሳ32፥7፤ዮሐ15፥25
69፥5 መዝ38፥5፤ 44፥21
69፥7 መዝ39፥8፤ 44፥15፤ኤር15፥15
69፥8 ኢዮ19፥13-15፤ መዝ31፥11፤38፥11፤ ኢሳ53፥3፤ዮሐ7፥5
69፥9 መዝ89፥50- 51፤ዮሐ2፥17፤ ሮሜ15፥3
69፥10 መዝ35፥13
69፥11 2ሳሙ3፥31 ፤መዝ35፥13
69፥12 ዘፍ18፥1፤ 23፥10፤ኢዮ30፥9
69፥13 መዝ17፥7፤ 51፥1፤ኢሳ49፥8፤ 2ቆሮ6፥2
69፥14 ቍ2፤ መዝ 144፥7
69፥15 ዘኍ16፥33፤ መዝ28፥1፤124፥4-5
69፥16 መዝ63፥3
69፥17 መዝ22፥24፤ 50፥15፤66፥14፤ 143፥7
69፥18 መዝ49፥15
69፥19 መዝ22፥6
69፥20 ኢዮ16፥2፤ መዝ142፥4፤ኢሳ63፥5
69፥21 ዘኍ6፥3፤ ማቴ27፥34፡48፤ ማር 15፥23፡36፤ ሉቃ23፥36፤ ዮሐ19፥28-30
69፥22 1ሳሙ28፥9 ፤ኢዮ18፥10
69፥23 ሮሜ11፥9-10
69፥24 መዝ79፥6፤ ኤር10፥25
69፥25 ዘሌ26፥43፤ ማቴ23፥38፤ ሐሥ 1፥20

በድንኳኖቻቸው የሚኖር አይገኝ፤
[26]አንተ የመታኻቸውን አሳደዋልና፤
ያቈሰልኻቸውንም ሥቃያቸውን
አባብሰዋል።
[27]በበደላቸው በደል ጨምርባቸው፤
ወደ ጽድቅህም አይግቡ።
[28]ከሕይወት መጽሐፍ ይደምሰሱ፤
ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ።

[29]ነገር ግን እኔ በሥቃይና በጭንቅ ላይ
እገኛለሁ፤
አምላክ ሆይ፤ ማዳንህ ደግፎ ይያዘኝ።

[30]የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አወድሳለሁ፤
በምስጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ።
[31]ከበሬ ይልቅ፣
ቀንድና ጥፍር ካበቀለ እምቦሳም ይልቅ
ይህ *እግዚአብሔርን* ደስ ያሰኘዋል።
[32]ድኾች ይህን ያያሉ፤ ደስም ይላቸዋል፤
እናንተ እግዚአብሔርን የምትሹ ልባችሁ
ይለምልም!
[33]*እግዚአብሔር* ችግረኞችን ይሰማልና፤
በእስራት ያለውንም ሕዝቡን
አይንቅም።

[34]ሰማይና ምድር፣ ባሕርም፣
በውስጣቸውም የሚንቀሳቀስ ሁሉ
ያመስግኑት።
[35]እግዚአብሔር ጽዮንን ያድናታልና፤
የይሁዳንም ከተሞች መልሶ
ይሠራቸዋልና፤
ሕዝቡም በዚያ ይሰፍራል፤
ይወርሳታልም።
[36]የባሪያዎቹም ዘሮች ይወርሷታል፤
ስሙንም የሚወዱ በዚያ ይኖራሉ።

## *መዝሙር* 70

### የጭንቀት ጩኸት

70፥1-5 ተጓ ምብ-መዝ40፥13-17

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ*

[1]አምላክ ሆይ፤ ታድነኝ ዘንድ ዘንበል በል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔን ለመርዳት
ፍጠን።
[2]ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ፣
ይፈሩ፤ ሁከትም ይምጣባቸው፤
የእኔን መጐዳት የሚመኙ፣
በውርደት ወደ ኋላቸው ይመለሱ።
[3]በእኔ ላይ፣ "እሰይ! እሰይ!" የሚሉ፣
ተሸማቀው ወደ ኋላ ይመለሱ።
[4]ነገር ግን የሚሹህ ሁሉ፣
በአንተ ሐሤት ያድርጉ፤ ደስም
ይበላቸው፤
"ማዳንህን የሚወዱ ሁሉ ሁልጊዜ፣
እግዚአብሔር ከፍ ይበል!" ይበሉ።
[5]እኔ ግን ምስኪንና ችግረኛ ነኝ፤
አምላክ ሆይ፤ ፈጥነህ ድረስልኝ፤
ረዳቴም፣ ታዳጊዬም አንተ ነህና፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አትዘግይ።

## *መዝሙር* 71

### የሽማግሌ ጸሎት

71፥1-3 ተጓ ምብ-መዝ 31፥1-4

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተን መጠጊያ
አደረግሁ፤
ከቶም አልፈር።
[2]በጽድቅህ ታደገኝ፤ አስጥለኝም፤
ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤ አድነኝም።
[3]ምንጊዜም የምሸሸበት፣
መጠጊያ ዐለት ሁነኝ፤
አንተ ዐለቴ ምሽጌ ነህና፣
ታድነኝ ዘንድ ትእዛዝህ ይውጣ።
[4]አምላኬ ሆይ፤ ከክፉ እጅ፣
ከግፈኛና ከጨካኝ መዳፍ አውጣኝ።

[5]ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ተስፋዬ፤
ከልጅነቴም ጀምሮ መታመኛዬ ነህና።
[6]ከተወለድሁ ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ፤
ከእናቴ ማሕፀን ያወጣኸኝ አንተ ነህ፤
አንተ የዘወትር ምስጋናዬ ነህ።
[7]ብዙዎች እንደ ጉድ አዩኝ፤
አንተ ግን ጽኑ አምባዬ ነህ።
[8]ቀኑን ሙሉ ክብርህን ያወራ ዘንድ፣
አፌ በምስጋናህ ተሞልቶአል።

[9]በእርጅናዬ ዘመን አትጣለኝ፤
ጕልበቴም ባለቀበት ጊዜ አትተወኝ።
[10]ጠላቶቼ ተነጋግረውብኛልና፤
ሕይወቴን ለማጥፋት የሚሹ በአንድ
ላይ አሢረዋል፤
[11]እነርሱም፣ "እግዚአብሔር ትቶታል፤
የሚያስጥለው የለምና፣
ተከታትላችሁ ያዙት" አሉ።
[12]አምላክ ሆይ፤ ከእኔ አትራቅ፤
አምላኬ ሆይ፤ እኔን ለመርዳት ፍጠን።
[13]ባላንጣ የሆኑብኝ ይፈሩ፤ ይጥፉም፤
ሊጐዱኝ የሚፈልጉ፣
ንቀትንና ውርደትን ይከናነቡ።
[14]እኔ ግን ሁልጊዜ ተስፋ አደርጋለሁ፤
በምስጋና ላይ ምስጋና አቀርብልሃለሁ።
[15]አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣
ቀኑን ሙሉ ስለ ማዳንህ ይናገራል፤
ማቆሚያ ልኩንም አላውቅም።
[16]መጥቼ የጌታ *እግዚአብሔርን* ብርቱ
ሥራ ዐውጃለሁ፤
የአንተን ጽድቅ ብቻ እናገራለሁ።
[17]አምላክ ሆይ፤ አንተ ከልጅነቴ ጀምረህ
አስተማርኸኝ፤

**69፥26** ኢዮ19፥22፤ ዘካ1፥15
**69፥27** ነህ4፥5፤ መዝ 109፥14
**69፥28** ዘፀ32፥32-33፤ ሕዝ13፥9፤ሉቃ10፥20
**69፥29** መዝ20፥1
**69፥30** መዝ28፥7፤ 34፥3
**69፥31** መዝ50፥9-13፤51፥16
**69፥32** መዝ22፥26 ፤34፥2
**69፥33** መዝ12፥5
**69፥34** መዝ96፥11 ፤98፥7፤ኢሳ44፥23
**69፥35** ዕዝ9፥9፤ መዝ51፥18፤አብ1፥17
**69፥36** መዝ25፥13 ፤37፥29
**70፥1** መዝ22፥19 ፤71፥12
**70፥2** መዝ6፥10፤ 35፥4፡26፤71፥13፤ 109፥29፤129፥5
**70፥3** መዝ35፥21
**70፥4** መዝ9፥10፤ 31፥6-7፤32፥11፤ 35፥27፤118፥24
**70፥5** መዝ18፥2፤ 30፥10፤33፥20፤ 86፥1፤109፥22፤ 119፥60፤141፥1
**71፥1** ዘዳ23፥15፤ ሩት2፥12፤መዝ22፥5
**71፥2** 2ነገ19፥16
**71፥3** መዝ18፥2
**71፥4** ዘፍ48፥16፤ 2ነገ19፥19፤መዝ140፥4
**71፥5** ኢዮ4፥6፤መዝ 9፥18፤25፥5፤ኤር17፥7
**71፥6** ኢዮ3፥16፤ መዝ9፥1፤22፥9፡10፤3 4፥1፤52፥9፤119፥164 ፤145፥2
**71፥7** ዘዳ28፥46፤ 2ሳሙ22፥3፤መዝ61፥3፤ ኢሳ8፥18፤1ቆሮ4፥9
**71፥8** ቍ15፤ መዝ 51፥15፤63፥5፤ 96፥6፤104፥1
**71፥9** ዘዳ4፥31፤ 31፥6፤መዝ51፥11፤ 92፥14፤ኢሳ46፥4
**71፥10** ዘፀ1፥10፤ መዝ3፥7፤10፥8፤31፥13፤ 59፥3፤ምሳ1፥18፤ ማቴ12፥14
**71፥11** መዝ7፥2፤ 9፥10፤ኢሳ40፥27፤ 54፥7፤ሰቆ5፥20፤ ማቴ27፥46
**71፥12** መዝ22፥19 ፤38፥21፡22
**71፥13** ኢዮ8፥22፤ መዝ25፥3፤70፥2፤ ኤር18፥19
**71፥14** መዝ25፥3፤ 42፥5፤130፥7፤131፥3
**71፥15** ቍ8፤ መዝ51፥14፤66፥16
**71፥16** መዝ9፥1፤ 77፥12፤106፥2፤118፥15፤145፥4
**71፥17** ዘዳ4፥5፤ኢዮ 5፥9፤መዝ26፥7፤86፥10፤96፥3፤ኤር7፥13

እኔም እስከ ዛሬ ድረስ ድንቅ
ሥራህን ዐውጃለሁ።
18 አምላክ ሆይ፤ ሳረጅና ስሸብትም
አትተወኝ፤
ክንድህን ለመጭው ትውልድ፣
ኀይልህን ኋላ ለሚነሣ ሕዝብ ሁሉ፣
እስከምገልጽ ድረስ።
19 አምላክ ሆይ፤ ጽድቅህ እስከ ሰማያት
ይደርሳል፤
አንተ ታላላቅ ነገሮችን አድርገሃል፤
አምላክ ሆይ፤ እንደ አንተ ያለ ማን
ነው?
20 ብዙ መከራና ጭንቅ ብታሳየኝም፣
ሕይወቴን እንደ ገና ታድሳለህ፤
ከምድር ጥልቅም፣
እንደ ገና ታወጣኛለህ።
21 ክብሬን ትጨምራለህ፤
ተመልሰህም ታጽናናኛለህ
22 አምላኬ ሆይ፤ ስለ ታማኝነትህ፣
በበገና አመሰግንሃለሁ፤
የእስራኤል ቅዱስ ሆይ፤
በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ።
23 ዝማሬ በማቀርብልህ ጊዜ ከንፈሮቼ
በደስታ ይሞላሉ፤
አንተ የተቤዥሃትም ነፍሴ እልል
ትላለች።
24 አንደበቴ ስለ ጽድቅህ፣
ቀኑን ሙሉ ያወራል፤
የእኔን መጐዳት የሚፈልጉ፣
አፍረዋልና፤ ተዋርደዋልም።

## መዝሙር 72

### በተስፋ የሚጠባበቀው ንጉሥ

ስለ ሰሎሞን

1 እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍትህን ለንጉሥ፣
ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ ዐድል፤
2 እርሱም ሕዝብህን በጽድቅ ይዳኛል፤[ቀ]
ለተቸገሩትም በትክክል ይፈርዳል።
3 ተራሮች ብልጽግናን፣
ኰረብቶችም የጽድቅን ፍሬ ለሕዝቡ
ያመጣሉ።
4 ለተቸገረው ሕዝብ ይሟገታል፤
የድኾችን ልጆች ያድናል፤
ጨቋኙንም ያደቀዋል።
5 ፀሐይ እስካለች ድረስ፣
ጨረቃም በምትኖርበት ዘመን ሁሉ፣
ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።[በ]
6 እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ
ይወርዳል፤
እንደ ካፊያም ምድርን ያረሰርሳል።
7 በዘመኑ ጽድቅ ይሰፍናል፤
ጨረቃ ከስፍራዋ እስከምትታጣ

71፥18 ዘፀ9፥16፤ ኢዮ8፥8፤መዝ22፥30፡ 31፤78፥4፤145፥4፤ ኢሳ 46፥4፤ኢል1፥3
71፥19 መዝ35፥10 ፤36፥5፤77፥13፤89፥8፤ 126፥2፤ሉቃ1፥49
71፥20 መዝ25፥17 ፤63፥9፤80፥3፡19፤ 85፥4፤ሆሴ6፥2
71፥21 መዝ18፥35 ፤23፥4፤86፥17፤ ኢሳ 12፥1፤40፥1-2፤ 49፥13፤54፥10
71፥22 2ነገ19፥22፤ ኢዮ21፥12፤መዝ33፥2 ፤92፥3፤144፥9
71፥23 ዘፀ15፥13፤ መዝ20፥5
71፥24 ቀኍ13፤ አስ 9፥2፤መዝ35፥28
72፥1 ዘዳ1፥16፤ መዝ9፥8
72፥2 ኢሳ9፥7፤ 11፥4-5፤16፥5፤32፥1፤ 59፥17፤63፥1፤ ኤር23፥5፤33፥15
72፥4 ቀኍ13፤ መዝ 9፥12፤27፥11፤ 76፥9፤ኢሳ11፥4፤ 29፥19፤ 32፥7፤ 49፥13
72፥5 1ሳሙ13፥13 ፤መዝ33፥11
72፥6 ዘዳ32፥2
72፥7 መዝ92፥12፤ ምሳ14፥11
72፥8 ዘፀ23፥31፤ 1ነገ4፥21፤ዘካ9፥10
72፥10 ዘፍ10፥4፡7፤ 1ነገ9፥16፤2ዜና9፥24፤ አስ10፥1
72፥11 ዘፍ27፥29 ፤ዕዝ1፥2
72፥13 ኢሳ60፥10፤ ኢል2፥18፤ ሉቃ 10፥33
72፥14 1ሳሙ26፥21 ፤መዝ69፥18፤ ሕዝ13፥23፤34፥10
72፥15 ዘፍ10፥7፤ መዝ35፥28
72፥16 ዘፍ27፥28፤ ዘኍ22፥4፤መዝ4፥7፤ 92፥12፤104፥16፤ ኢሳ4፥2፤27፥6፤ 44፥4፤58፥11፤ 66፥14፤ሕዝ34፥27
72፥17 ዘፍ12፥3፤ ዘፀ3፥15፤መዝ89፥36፤ ሉቃ1፥48
72፥18 1ዜና29፥10 ፤ኢዮ5፥9፤መዝ41፥13 ፤106፥48፤ሉቃ1፥68
72፥19 ዘኍ14፥21፤ 2ሳሙ7፥26፤ መዝ41፥13
72፥20 ሩት4፥17
73፥1 መዝ24፥4፤ ማቴ5፥8

ድረስም ሰላም ይበዛል።
8 ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፣
ከታላቁም ወንዝ[ተ] እስከ ምድር ዳርቻ
ይገዛል።
9 የበረሓ ዘላኖች በፊቱ ይሰግዳሉ፤
ጠላቶቹም ዐፈር ይልሳሉ።
10 የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት፣
ግብር ያመጡለታል፤
የዐረብና የሳባ ነገሥታት፣
እጅ መንሻ ያቀርባሉ።
11 ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል፤
ሕዝቦችም ሁሉ ይገዙለታል።
12 ችግረኛው በጮኸ ጊዜ፣
ምስኪኑንና ረዳት የሌለውን ይታደገዋል።
13 ለድኾችና ለችግረኞች ይራራል፤
ምስኪኖችንም ከሞት ያድናል።
14 ሕይወታቸውን ከጭቈናና ከግፍ
ያድናል፤
ደማቸውም በእርሱ ፊት ክቡር ነው።
15 ዕድሜው ይርዘም!
ከዐረብ ወርቅ ይምጣለት፤
ዘወትር ይጸልዩለት፤
ቀኑንም ሙሉ ይባርኩት።
16 በምድሪቱ ላይ እህል ይትረፍረፍ፤
በተራሮችም ዐናት ላይ ይወዛወዝ።
ፍሬው እንደ ሊባኖስ ይንዠርገግ፤
በከተማ ያለውም እንደ ሜዳ ሣር
እጅብ ብሎ ይውጣ።
17 ስሙ ለዘላለም ጸንቶ ይኑር፤
ዝናው ፀሓይ የምትኖረውን ዘመን
ያህል ይዝለቅ፤
ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ ይባረኩ፤
ሕዝቡ ሁሉ ቡሩክ ነህ ይበለው።
18 ብቻውን ድንቅ ነገር የሚያደርግ፣
የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ።
19 ክቡር ስሙ ለዘላለም ይባረክ፤
ምድርም ሁሉ በክብሩ ይሞላ።
አሜን፤ አሜን።
20 የእሴይ ልጅ የዳዊት ጸሎት እዚህ ላይ
ተፈጸመ።

## ሦስተኛ መጽሐፍ
## ከመዝሙር 73-89

## መዝሙር 73

### የፍትሕ አሸናፊነት

የአሳፍ መዝሙር

1 እግዚአብሔር ልባቸው ንጹሕ ለሆነ፣
ለእስራኤል እንዴት ቸር ነው!

[ቀ]2 ወይም እርሱ ሕዝቡን በጽድቅ ይዳኝ
[በ]5 ወይም የተፈራ ይሆናል
[ተ]8 የኤፍራጥስ ወንዝ ነው።

[2]እኔ ግን እግሬ ሊሰናከል፣
 አዳልጦኝም ልወድቅ ጥቂት ቀረኝ።
[3]ክፉዎች ሲሳካላቸው አይቼ፣
 በዐመፀኞች ቀንቼ ነበርና።
[4]እንዳች ጣር የለባቸውም፤
 ሰውነታቸውም ጤናማና የተደላደለ
 ነው።
[5]በሰዎች የሚደርሰው ጣጣ
 አይደርስባቸውም፤
 እንደ ማንኛውም ሰው መከራ
 አያገኛቸውም።
[6]ስለዚህ ትዕቢት የዐንገት ጌጣቸው ነው፤
 ዐመፅንም እንደ ልብስ ተጐናጽፈዋል።
[7]የሰባ ዐይናቸው ይጕረጠረጣል፤[ቶ]
 ልባቸውም በከንቱ ሐሳብ ተሞልቶ
 ይፈስሳል።
[8]በፌዝና በክፋት ይናገራሉ፤
 ቀና ቀና ብለውም በዐመፅ ይዝታሉ።
[9]አፋቸውን በሰማይ ላይ ያላቅቃሉ፤
 አንደበታቸውም ምድርን ያካልላል።
[10]ስለዚህ ሕዝቡ ወደ እነርሱ ይነጐዳል፤
 ውሃቸውንም በገፍ[ኀ] ይጠጣሉ።
[11]"ለመሆኑ እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል?
 በልዑልስ ዘንድ ዕውቀት አለ?" ይላሉ።
[12]እንግዲህ፣ ክፉዎች ይህን ይመስላሉ፤
 ሁልጊዜ ግድ የለሽና ሀብት በሀብት
 ናቸው።
[13]ለካ ልቤን ንጹሕ ያደረግሁት በከንቱ
 ነው፤
 እጄንም በየዋህነት የታጠብሁት
 በከንቱ ኖሮአል!
[14]ቀኑን ሙሉ ተቀሠፍሁ፤
 ጠዋት ጠዋትም ተቀጣሁ።
[15]"እኔ እንደዚህ እናገራለሁ" ብልማ ኖሮ፣
 የልጆችህን ትውልድ በከዳሁ ነበር።
[16]ይህን ነገር ለመረዳት በሞከርሁ ጊዜ፣
 አድካሚ ተግባር መስሎ ታየኝ።
[17]ይኸውም ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስክገባ፣
 መጨረሻቸውንም እስካይ ድረስ ነበር።
[18]በእርግጥ በሚያዳልጥ ስፍራ
 አስቀመጥሃቸው፤
 ወደ ጥፋትም አወረድሃቸው።
[19]እንዴት ፈጥነው በቅጽበት ጠፉ!
 በድንጋጤ ፈጽመው ወደሙ።
[20]ሰው ከሕልሙ ሲነቃ እንደሚሆነው፣
 ጌታ ሆይ፤ አንተም በምትነሣበት ጊዜ፣
 እንደ ቅዠት ከንቱ ታደርጋቸዋለህ።
[21]ነፍሴ በተማረረች ጊዜ፣
 ልቤም በተቀሠፈ ጊዜ፣
[22]ስሜት የሌለውና አላዋቂ ሆንሁ፤
 በፊትህም እንደ እንስሳ ሆንሁ።

73፥2 ዘጸ32፥35፤ መዝ69፥2፤ኤፌ4፥27
73፥3 ኢዮ9፥24፤ 21፥7፤ምሳ3፥31፤ 23፥17፤24፥1-2፤ ኤር12፥1፤ሚል3፥15
73፥5 ቈላ12፤ ሕዝ 23፥42
73፥6 ዘፍ6፥11፤ 41፥42፤ዘሌ26፥19፤ ምሳ4፥17፤መሓ4፥9፤ ሕዝ16፥11
73፥7 መዝ17፥10
73፥8 መዝ10፥7፤ 12፥5፤17፥10፤41፥5፤ ሕዝ25፥15፤ቈላ3፥8
73፥12 ቈላ5፤ መዝ 49፥6
73፥13 ዘፍ44፥16፤ ኢዮ9፥29-31፤21፥15
73፥14 ቈላ5
73፥16 መክ8፥17
73፥17 ዘፀ15፥17፤ ኢዮ8፥13፤መዝ15፥1 ፤ፊል3፥19
73፥18 ዘጸ32፥35፤ መዝ17፥13፤35፥6
73፥19 ዘፍ19፥15፤ ዘዳ28፥20፤ምሳ24፥22 ፤ኢሳ47፥11
73፥20 ኢዮ20፥8፤ መዝ78፥65፤ምሳ12፥ 11፤28፥19፤ኢሳ29፥8
73፥22 መዝ49፥10 ፡12፡20፤92፥6፤94፥8፤ መክ3፥18፤9፥12
73፥23 ዘፍ48፥13
73፥24 1ነገ22፥5፤ መዝ48፥14
73፥25 መዝ16፥2፤ ፊል3፥8
73፥26 ዘዳ32፥9፤ መዝ18፥1፤31፥10፤ 40፥12፤84፥2
73፥27 ዘሌ6፥2፤ መዝ34፥21፤ኤር5፥1 1፤ሆሴ4፥12፤9፥1
73፥28 መዝ9፥9፤ 26፥7፤40፥5፤ሶፎ3፥2፤ ዕብ10፥22፤ያዕ4፥8
74፥1 መዝ43፥2፤ 44፥23፤79፥13፤95፥7 ፤100፥3
74፥2 ዘፀ15፥13፡16 ፤34፥9፤ዘዳ32፥7፤መዝ 2፥6፤43፥3፤68፥16፤ ኢሳ46፥13፤48፥20፤ ኢል3፥17፡21፤አብ 1፥17፤1ቆሮ 6፥20
74፥3 ኢሳ44፥26፤ 52፥9
74፥4 ዘኍ2፥2፤ ኤር4፥6፤ሰቆ2፥7
74፥5 ኤር46፥22
74፥6 1ነገ6፥18
74፥7 ዘሌ15፥31፤ 20፥3፤መዝ75፥1፤ ሐሥ21፥28
74፥8 2ነገ25፥9፤ 2ዜና36፥19፤መዝ94፥5፤ ኤር21፥10፤34፥22፤5

[23]ይህም ሆኖ ዘወትር ከአንተ ጋር
 ነኝ፤
 አንተም ቀኝ እጄን ይዘኸኛል።
[24]በምክርህ መራኸኝ፤
 ኋላም ወደ ክብር ታስገባኛለህ።
[25]በሰማይ ከአንተ በቀር ማን አለኝ?
 በምድርም ከአንተ ሌላ የምሻው
 የለኝም።
[26]ሥጋዬና ልቤ ሊደክሙ ይችላሉ፤
 እግዚአብሔር ግን የልቤ ብርታት፣
 የዘላለም ዕድል ፈንታዬ ነው።
[27]እነሆ፤ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና፤
 አንተ ታማኞች ያልሆኑልህን ሁሉ
 ታጠፋቸዋለህ።
[28]ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ
 ይሻለኛል፤
 ጌታ እግዚአብሔርን መጠጊያዬ
 አድርጌዋለሁ፤
 ስለ ሥራህም ሁሉ እናገር ዘንድ።

## መዝሙር 74

## ስለ መቅደሱ መፍረስ የቀረበ ጸሎት

የአሳፍ ትምህርት

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ ለዘላለም የጣልኸን
 ለምንድን ነው?
 በማሰማሪያህ ባሉ በጎችህስ ላይ ቍጣህ
 ለምን ነደደ?
[2]ጥንት ገንዘብህ ያደረግሃትን ጉባኤ፣
 የዋጀሃትን የርስትህን ነገድ፣
 መኖሪያህ ያደረግሃትን የጽዮን ተራራ
 አስብ።
[3]እርምጃህን ለዘላለሙ ባድማ ወደ ሆነው
 አቅና፤
 ጠላት በመቅደስህ ውስጥ ያለውን ሁሉ
 አበላሽቶአል።
[4]ጠላቶችህ በመገናኛ ስፍራህ መካከል
 ደነፉ፤
 አርማቸውንም ምልክት አድርገው
 በዚያ አቆሙ።
[5]በጫካ መካከል ዛፎችን ለመቍረጥ፣
 መጥረቢያ የሚያነሣ ሰው መሰሉ።
[6]በእደ ጥበብ ያጌጠውን ሥራ ሁሉ፣
 በመጥረቢያና በመዶሻ ሰባበሩት።
[7]መቅደስህን አቃጥለው አወደሙት፤
 የስምህንም ማደሪያ አረከሱ።
[8]በልባቸውም፣ "ፈጽሞ እንጨቍናቸዋለን"
 አሉ፤
 እግዚአብሔር በምድሪቱ ላይ
 የተመለከበትን ስፍራ ሁሉ አቃጠሉ።

[ቶ]7 የዕብራይስጡ ከዚህ ጋር ይስማማል፤ የሱርስቱና የሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ግን፣ *ከደነደነው ልባቸው በደል ይወጣል* ይላል።
[ኀ]10 በዕብራይስጡ የዚህ ሐረግ ትርጕም በትክክል አይታወቅም።

9የምናየው ምልክት የለም፤
ከእንግዲህ የሚነሣ አንድም ነቢይ
የለም፤
ይህ እስከ መቼ እንደሚቀጥል
የሚያውቅ በእኛ ዘንድ የለም።

10አምላክ ሆይ፤ ጠላት የሚያሾፈው እስከ
መቼ ነው?
ባላንጣስ ለዘላለም በስምህ ያላግጣልን?
11እጅህን ለምን ትሰበስባለህ?
ቀኝ እጅህን ለምን በብብትህ ሥር
ታቆያለህ?

12አምላክ ሆይ፤ አንተ ከጥንት ጀምሮ
ንጉሤ ነህ፤
በምድር ላይ ማዳንን አደረግህ።
13ባሕርን በኀይልህ የከፈልህ አንተ ነህ፤
የባሕሩንም አውሬ ራሶች በውሃ ውስጥ
ቀጠቀጥህ።
14የሌዋታንን ራሶች አደቀቅህ፤
ለምድረ በዳ ፍጥረታትም ምግብ
አድርገህ የሰጠሃቸው፣
15ምንጮችንና ፈሳሾችን ያፈለቅህ
አንተ ነህ፤
ሳያቋርጡ የሚፈሱትንም ወንዞች
አደረቅህ።
16ቀኑ የአንተ ነው፤ ሌሊቱም የአንተ
ነው፤
ጨረቃንና ፀሓይን አንተ
አጸናሃቸው።
17የምድርን ዳርቻ ሁሉ የወሰንህ አንተ
ነህ፤
በጋውንም ክረምቱንም አንተ ሠራህ።

18 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጠላት እንዴት
እንደሚያሾፍ፣
ከንቱ ሕዝብም ስምህን እንዴት
እንዳቃለለ አስብ።
19የርግብህን ነፍስ አሳልፈህ ለዱር
አራዊት አትስጥ፤
የችግረኞች ሕዝብህን ሕይወት
ለዘላለሙ አትርሳ።
20ኪዳንህን አስብ፤
የዐመፅ መናኸሪያ በምድሪቱ ጨለማ
ስፍራዎች ሞልተዋልና።
21የተጨቈኑት አፍረው አይመለሱ፤
ድኾችና ችግረኞች ስምህን ያመስግኑ።

22አምላክ ሆይ፤ ተነሥ፤ ለዐላማህ
ተሟገት፤
ከንቱ ሰው ቀኑን ሙሉ
እንደሚያላግጥብህ አስብ።
23የባላጋራዎችህን ድንፋታ፣
ዘወትር የሚነሣውን የጠላቶችህን
ፉከራ አትርሳ።

2፥13
74፥9 ዘፀ4፥17፤ 10፥1፤1ሳሙ3፥1
74፥10 ቍ22፤ መዝ 6፥3፤44፥16፤ 79፥5፤80፥4
74፥11 ዘፀ15፥6፤ ነህ 5፥13፤ሕዝ5፥3
74፥12 መዝ2፥6፤ 24፥7፤27፥1፤68፥24
74፥13 ዘፀ14፥21፤ ኢሳ27፥1፤51፥9፤ ሕዝ 29፥3፤32፥2
74፥14 ኢዮ3፥8፤ ኢሳ13፥21፤23፥13፤ 34፥14፤ኤር50፥39
74፥15 ዘፀ14፥29፤ 17፥6፤ዘኍ20፥11፤ ኢሱ2፥10
74፥16 ዘፍ1፥16፤ መዝ136፥7-9
74፥17 ዘፍ8፥22፤ ዘዳ32፥8፤ሐሥ17፥26
74፥18 ዘዳ32፥6
74፥19 ዘፍ8፥8፤ መዝ9፥18፤ኢሳ59፥11
74፥20 ዘፍ6፥18፤ ኢዮ34፥22
74፥21 መዝ9፥9፤ 10፥18፤35፥10፤ 103፥6፤ኢሳ58፥10
74፥22 መዝ17፥13 ፤53፥1
74፥23 ዘኍ25፥17 ፤መዝ46፥6፤65፥7፤ ኢሳ31፥4
75፥1 ኢሱ3፥5፤ መዝ44፥1፤71፥16፤ 77፥12፤105፥2፤107፥8 ፡15፤145፥5፡12፡18
75፥2 ዘፀ13፥10፤ መዝ7፥11
75፥3 1ሳሙ2፥8፤ 2ሳሙ22፥8፤ ኢሳ 24፥19
75፥4 1ሳሙ2፥3፤ መዝ5፥5፤ዘካ1፥21
75፥5 ኢዮ15፥25
75፥7 ዘፍ16፥5፤ 1ሳሙ2፥7፤ኢዮ5፥11 ፤መዝ50፥6፤58፥11፤ 147፥6፤ሕዝ21፥26፤ ዳን2፥21፤ራእ18፥8
75፥8 ምሳ23፥30 ፤ኢሳ51፥17፤ኤር 25፥15፤ዘካ12፥2
75፥9 ዘፍ24፥12፤ መዝ40፥10፤76፥6፤ 108፥1
75፥10 መዝ89፥17 ፤92፥10፤112፥9፤ 148፥14
76፥1 መዝ99፥3
76፥2 ዘፍ14፥18፤ 2ሳሙ5፥7፤መዝ2፥6፤ ዕብ7፥1
76፥3 መዝ46፥9፤ ሕዝ39፥9
76፥4 መዝ36፥9
76፥5 መሳ20፥44፤ መዝ13፥3፤ማቴ9፥24

## መዝሙር 75

### ለመለኮታዊው ዳኛ የቀረበ ዝማሬ

*ለመዘምራን አለቃ፤ "አታጥፋ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ የአሳፍ መዝሙር ማሕሌት*

1አምላክ ሆይ፤ ምስጋና እናቀርብልሃለን፤
ስምህ ቅርብ ነውና ምስጋና
እናቀርብልሃለን፤
ሰዎችም ስለ ድንቅ ሥራህ ይናገራሉ።

2አንተም እንዲህ አልህ፤ "ለይቼ
በወሰንኋት ሰዓት፣
በቅን የምፈርድ እኔ ነኝ።
3ምድርና ሕዝቦቿ ሁሉ በሚናወጡበት
ጊዜ፣
ምሰሶቿን አጽንቼ የምይዝ እኔ ነኝ።
ሴላ
4እብሪተኛውን፣ 'አትደንፋ'፤
ክፉውንም 'ቀንድህን ከፍ
አታድርግ' እለዋለሁ፤
5ቀንድህን ወደ ሰማይ አታንሣ፤
ዐንገትህንም መዝዘህ አትናገር።' "
6ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ፣
ወይም ከምድረ በዳ አይመጣምና፤
7ነገር ግን የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው፤
እርሱ አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ
ያደርጋል።
8 *በእግዚአብሔር* እጅ ጽዋ አለ፤
በሚገባ የተቀመመና ዐረፋ የሚወጣው
የወይን ጠጅ ሞልቶበታል፤
ይህን ከውስጡ ወደ ውጭ ገለበጠው፤
የምድር ዐመፀኞችም አተላው ሳይቀር
ይጨልጡታል።

9እኔ ግን ይህን ለዘላለም ዐውጃለሁ፤
ለያዕቆብም አምላክ ዝማሬ አቀርባለሁ።
10የክፉዎችን ሁሉ ቀንድ እሰብራለሁ፤
የጻድቃን ቀንድ ግን ከፍ ከፍ ይላል።

## መዝሙር 76

### ግርማው ለሚያስፈራው አምላክ የቀረበ ቅኔ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች፤ የአሳፍ መዝሙር ማሕሌት*

1እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፤
ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው።
2ድንኳኑ በሳሌም፣
ማደሪያውም በጽዮን ነው።
3በዚያም ተወርዋሪውን ፍላጻ፣
ጋሻንና ሰይፍን፣ ጦርንም ሰበረ። ሴላ

4አንተ ብርሃን ተላብሰህ ደምቀሃል፤
ግርማዊነትህም ከዘላለም ተራሮች
ይልቃል።
5ልበ ሙሉ የሆኑት ተዘርፈዋል፤
አንቀላፍተውም ተኝተዋል፤

ከጦረኞቹም መካከል፣
እጁን ማንቀሳቀስ የቻለ የለም።

6የያዕቆብ አምላክ ሆይ፤ ከተግሣጽህ
የተነሣ፣
ፈረስና ፈረሰኛው ጭልጥ ብለው
ተኝተዋል።
7መፈራት ያለብህ አንተ ብቻ ነህ፤
በተቈጣህ ጊዜ ማን በፊትህ መቆም
ይችላል?
8አንተ ፍርድን ከሰማይ አሰማህ፤
ምድርም ፈርታ ጸጥ አለች፤
9አምላክ ሆይ፤ ይህም የሆነው አንተ
የምድር ጐስቋሎችን ለማዳን፣
ለፍርድ በተነሣህ ጊዜ ነው። ሴላ
10ሰውን ብትቈጣ እንኳ ለክብርህ
ይሆናል፤
ከቍጣ የተረፉትንም ትገታቸዋለህ።ʼ

11ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር ተሳሉ፤
ስእለቱንም አግቡ፤
በእርሱ ዙሪያ ያሉ ሁሉ፣
አስፈሪ ለሆነው ለእርሱ እጅ መንሻ
ያምጡ።
12እርሱ የገዦችን መንፈስ ይሰብራል፤
በምድር ነገሥታትም ዘንድ የተፈራ
ነው።

## መዝሙር 77

### የእስራኤል ጥንተ ነገር አሰላስሎ

*ለመዘምራን አለቃ፤ ለኤዶታም፤ የአሳፍ መዝሙር*

1ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ እግዚአብሔር
ጮኽሁ፤
ይሰማኝም ዘንድ ወደ አምላክ ጮኽሁ።
2በመከራዬ ቀን እግዚአብሔርን ፈለግሁት፤
በሌሊትም ያለ ድካም እጆቼን ዘረጋሁ፤
ነፍሴም አልጽናና አለች።

3አምላክ ሆይ፤ አንተን ባሰብሁ ቍጥር
ቃተትሁ፤
ባወጣሁ ባወረድሁም መጠን
መንፈሴ ዛለች። ሴላ
4ዐይኖቼ እንዳይከደኑ ያዝሃቸው፤
መናገር እስኪሳነኝ ድረስ ታወክሁ።
5የድሮውን ዘመን አሰብሁ፤
የጥንቶቹን ዓመታት አውጠነጠንሁ።
6ዝማሬዬን በሌሊት አስታወስሁ፤
ከልቤም ጋር ተጫወትሁ፤ መንፈሴም
ተነቃቅቶ እንዲህ ሲል ጠየቀ:-

7"ለመሆኑ፣ ጌታ ለዘላለም ይጥላልን?
ከእንግዲህስ ከቶ በጎነትን አያሳይምን?
8ምሕረቱስ ለዘላለም ጠፋን?
የገባውስ ቃል እስከ ወዲያኛው ተሻረን?
9እግዚአብሔር ቸርነቱን ዘነጋ?

76፥6 ዘፀ15፥1፤ መዝ 50፥21
76፥7 1ዜና16፥25፤ዕዝ9፥15፤መዝ2፥5፤ ናሆ1፥6፤ራእ6፥17
76፥8 1ዜና16፥30፤ሕዝ38፥20
76፥9 መዝ9፥8፤ 58፥11፤72፥4፤74፥22፤82፥8፤96፥13
76፥10 ዘፀ9፥16፤ ሮሜ9፥17
76፥11 ዘሌ22፥18፤ 2ዜና32፥23፤መዝ 50፥14፤መክ5፥4-5
77፥1 1ነገ8፥52
77፥2 ዘፍ32፥7፤ 37፥35፤ዘፀ9፥29፤ 2ሳሙ 22፥7፤ ኢዮ11፥13፤መዝ6፥6፤ 22፥2፤88፥1፤118፥5፤ ማቴ2፥18
77፥3 ዘፀ2፥23፤ መዝ 6፥2፡6፤78፥35፤ ኤር45፥3
77፥4 መዝ39፥2
77፥5 ዘዳ32፥7፤ መዝ44፥1፤143፥5፤ መክ7፥10
77፥7 1ዜና28፥9፤ መዝ85፥1፤102፥13፤ 106፥4
77፥8 መዝ6፥4፤ 90፥14፤2ጴጥ3፥9
77፥9 መዝ25፥6፤ 40፥11፤51፥1፤ ኢሳ 49፥15

77፥10 ዘፀ15፥6
77፥11 ነህ9፥17
77፥12 ዘፍ24፥63፤ መዝ143፥5
77፥13 ዘፀ15፥11፤ መዝ71፥19፤86፥8
77፥14 ዘፀ3፥20፤ 34፥10
77፥15 ዘፀ6፥6
77፥16 ዘፀ14፥21፡ 28፤መዝ114፥4፤ ኢሳ50፥2፤ዕን3፥8፡10
77፥17 ዘፀ9፥23፤ ዘዳ32፥23፤መሳ5፥4፤ መዝ29፥3
77፥18 መሳ5፥4፤2 ሳሙ22፥13፤ መዝ55፥8
77፥19 ዘፀ14፥22፤ ኢዮ9፥8
77፥20 ዘፀ4፥16፤ 13፥21፤ዘኁ33፥1፤ መዝ78፥52፤ኢሳ63፥11
78፥1 ኢሳ51፥4፤ 55፥3
78፥2 መዝ49፥4፤ ማቴ13፥35
78፥3 መሳ6፥13
78፥4 ዘዳ11፥19፤ 32፥7፤ኢዮ5፥9፤ መዝ26፥7፤71፥17፡18

ወይስ ከቍጣው የተነሣ ርኅራኄውን
ነፈገ?" ሴላ።

10እኔም፣ "የልዑል ቀኝ እጅ እንደ
ተለወጠ ማሰቤ፣
ይህ ድካሜ ነው" አልሁ።
11*የእግዚአብሔርን* ሥራ አስታውሳለሁ፤
የጥንት ታምራትህን በእርግጥ
አስታውሳለሁ፤
12ሥራህን ሁሉ አሰላስላለሁ፤
ድንቅ ሥራህን ሁሉ አውጠነጥናለሁ።

13አምላክ ሆይ፤ መንገድህ ቅዱስ ነው፤
እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን
ነው?
14ታምራትን የምታደርግ አምላክ አንተ
ነህ፤
በሕዝቦችም መካከል ኀይልህን
ትገልጣለህ።
15የያዕቆብንና የዮሴፍን ልጆች፣
ሕዝብህን በክንድህ ተቤዠሃቸው። ሴላ

16አምላክ ሆይ፤ ውሆች አዩህ፤
ውሆች አንተን አይተው ተሸማቀቁ፤
ጥልቆችም ተነዋወጡ።
17ደመናት ውሃን አንጠባጠቡ፤
ሰማያት አንጐደጐዱ፤
ፍላጾችህም ዙሪያውን አብለጨለጩ።
18የነጐድጓድህ ድምፅ በዐውሎ ነፋስ ውስጥ
ተሰማ፤
መብረቅህ ዓለምን አበራው፤
ምድርም ራደች፤ ተንቀጠቀጠች።
19መንገድህ በባሕር ውስጥ ነው፤
መሄጃህም በታላቅ ውሃ ውስጥ ነው፤
ዱካህ ግን አልታወቀም።

20በሙሴና በአሮን እጅ፣
ሕዝብህን እንደ በግ መንጋ መራኸው።

## መዝሙር 78

### በእስራኤል የተገኘ ታሪክ

*የአሳፍ ትምህርት*

1ሕዝቤ ሆይ፤ ትምህርቴን ስማ፤
ጆሮህንም ወደ አንደበቴ ቃል
አዘንብል።
2አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ፤
ከጥንት በነበረ እንቈቅልሽ እናገራለሁ፤
3ይህም የሰማነውና ያወቅነው፣
አባቶቻችንም የነገሩን ነው።
4እኛም ከልጆቻቸው አንደብቀውም፤
*የእግዚአብሔርን* ምስጋና፣
ኀይሉንና ያደረገውን ድንቅ ሥራ፣
ለሚቀጥለው ትውልድ እንናገራለን።

ʼ10 *በሕዝብህ ላይ የምታወርደው ቍጣ ለክብርህ ይሆናል ወይም በቍጣውም መታሰቢያነት ራስህን ታስታጥቃለህ የሚሉ አሉ።*

[5]ለያዕቆብ ሥርዐትን መሠረተ፤
በእስራኤልም ሕግን ደነገገ፤
ልጆቻቸውንም እንዲያስተምሩ፣
አባቶቻችንን አዘዘ፡፡
[6]ይህም የሚቀጥለው ትውልድ እንዲ
ያውቅ፣
እነርሱም በተራቸው ለልጆቻቸው፣
ገና ለሚወለዱት እንዲነግሩ ነው፡፡
[7]እነርሱም በእግዚአብሔር ይታመናሉ፤
የእግዚአብሔርን ሥራ አይረሱም፤
ትእዛዞቹንም ይጠብቃሉ፡፡
[8]ነገር ግን እንደ አባቶቻቸው፣
እልከኞችና ዐመፀኞች፣
ልቡን ያላቀና፣
መንፈሱም በእግዚአብሔር የማይታመን
ትውልድ አይሆኑም፡፡

[9]የኤፍሬም ልጆች የታጠቁ ቀስተኞች
ቢሆኑም፣
በጦርነት ቀን ወደ ኋላ ተመለሱ፡፡
[10]የእግዚአብሔርን ኪዳን አልጠበቁም፤
በሕጉም መሠረት ለመሄድ እንቢ አሉ፡፡
[11]እርሱ የሠራውን ሥራ፣
ያሳያቸውንም ድንቅ ነገር ረሱ፡፡
[12]አባቶቻቸው በዐይናቸው እያዩ፣
በግብፅ አገር፣ በጣኔዎስ ምድር
ታምራት አደረገ፡፡
[13]ባሕሩን ከፍሎ አሻገራቸው፤
ውሃውንም እንደ ክምር አቆመ፡፡
[14]ቀን በደመና መራቸው፤
ሌሊቱንም ሁሉ በእሳት ብርሃን፡፡
[15]ዐለቱን በምድረ በዳ ሰነጠቀ፤
እንደ ባሕር የበዛ ውሃ
አጠጣቸው፤
[16]ምንጭ ከቋጥኝ አፈለቀ፤
ውሃን እንደ ወንዝ አወረደ፡፡

[17]እነርሱ ግን በምድረ በዳ በልዑል
ላይ በማመፅ፣
በእርሱ ላይ ኀጢአት መሥራታቸውን
ቀጠሉ፡፡
[18]እጅግ የተመኙትን ምግብ በመጠየቅ፣
እግዚአብሔርን በልባቸው ተፈታተኑት፡፡
[19]እንዲህም ብለው በእግዚአብሔር ላይ
ተናገሩ፤
"እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድ
ማሰናዳት ይችላልን?
[20]ዐለቱን ሲመታ፣ ውሃ ተንዶለዶለ፤
ጅረቶችም ጐረፉ፤
ታዲያ፣ እንጀራንም መስጠት ይችላል?
ሥጋንስ ለሕዝቡ ሊያቀርብ ይችላል?"
[21]እግዚአብሔር ይህን ሲሰማ፣ እጅግ
ተቈጣ፤
በያዕቆብም ላይ እሳት ነደደ፤
ቍጣውም በእስራኤል ላይ ተነሣ፤
[22]በእግዚአብሔር አላመኑምና፤
በእርሱም ማዳን አልታመኑም፡፡
[23]እርሱ ግን ከላይ ደመናትን አዘዘ፤
የሰማይንም ደጆች ከፈተ፤
[24]ይበሉም ዘንድ መና አዘነበላቸው፤
የሰማይንም መብል ሰጣቸው፡፡
[25]ሰዎች የመላእክትን እንጀራ በሉ፤
ጠግበው እስከሚተርፍ ድረስ ምግብ
ላከላቸው፡፡
[26]የምሥራቁን ነፋስ ከሰማይ አስነሣ፤
የደቡብንም ነፋስ በኀይሉ አመጣ፡፡
[27]ሥጋን እንደ ዐፈር፣
የሚበሩትን ወፎች እንደ ባሕር አሸዋ
አዘነበላቸው፤
[28]በሰፈራቸውም ውስጥ፣
በድንኳናቸው ዙሪያ አወረደ፡፡
[29]እነርሱም እስኪጠግቡ ድረስ በሉ፤
እጅግ የጐመጁትን ሰጥቶአቸዋልና፡፡
[30]ነገር ግን ገና ምኞታቸውን ሳያረኩ፣
ምግቡ ገና በአፋቸው ውስጥ እያለ፣
[31]የእግዚአብሔር ቍጣ በላያቸው ላይ መጣ፤
ከመካከላቸውም ብርቱ ነን ባዮችን
ገደለ፤
የእስራኤልንም አበባ ወጣቶች ቀጠፈ፡፡

[32]ይህም ሁሉ ሆኖ በበደላቸው ገፉበት፤
ድንቅ ሥራዎቹንም አላመኑም፡፡
[33]ስለዚህ ዘመናቸውን በከንቱ፣
ዕድሜአቸውንም በድንጋጤ ጨረሰ፡፡
[34]እርሱ በገደላቸው ጊዜ ፈለጉት፤
ከልባቸው በመሻትም ወደ እግዚአብሔር
ተመለሱ፡፡
[35]እግዚአብሔር ዐለታቸው፣
ልዑል አምላክ ቤዛቸው እንደ ሆነ
አሰቡ፡፡
[36]ነገር ግን በአፋቸው ሸነገሉት፤
በአንደበታቸው ዋሹት፡፡
[37]ልባቸው በእርሱ የጸና አልነበረም፤
ለኪዳኑም ታማኞች አልነበሩም፡፡
[38]እርሱ ግን መሓሪ እንደ መሆኑ፣
በደላቸውን ይቅር አለ፤
አላጠፋቸውም፤
ቍጣውን ብዙ ጊዜ ገታ፤
መዓቱንም ሁሉ አላወረደም፡፡
[39]ወጥቶ የማይመለስ ነፋስ፣
ሥጋ ለባሾች መሆናቸውን አሰበ፡፡

[40]በምድረ በዳ ስንት ጊዜ ዐመፁበት!
በበረሓስ ምን ያህል አሳዘኑት!
[41]ደግመው ደጋግመው እግዚአብሔርን
ተፈታተኑት፤
የእስራኤልንም ቅዱስ አስቈጡት፡፡

78፥5 መዝ19፥7፤ 81፥5፤147፥19
78፥6 መዝ22፥31
78፥7 ዘዳ5፥29፤ 6፥12
78፥8 ዘፀ23፥21፤ 32፥9፤ዘዳ21፥18፤ 2ዜና30፥7፤ ኢሳ 30፥9፤65፥2
78፥9 ቍ57፤ መሳ 20፥39፤ 1ዜና12፥2፤ ሆሴ7፥16
78፥10 ዘፀ16፥28፤ ኢሱ7፥11፤2ነገ17፥15 ፤ኤር11፥8
78፥11 መዝ106፥13
78፥12 ዘፀ11፥9፤ ዘኍ13፥22፤ነህ9፥17፤ መዝ106፥22
78፥13 ዘፀ14፥21፡ 22፤15፥8፤መዝ66፥6፤ 136፥13
78፥14 ዘፀ13፥21፤ 105፥39
78፥15 ዘኍ20፥11፤ 1ቆሮ10፥4
78፥17 ቍ32፥40፤ ዘዳ9፥22፤ኢሳ30፥1፤ 63፥10፤ዕብ3፥16
78፥18 ዘፀ15፥24፤ 17፥2፤ዘኍ11፥4፤ 1ቆሮ10፥9
78፥19 ዘኍ21፥5
78፥20 ዘኍ11፥18፤ 20፥11፤ኢሳ35፥6
78፥21 ዘኍ11፥1
78፥22 ዘዳ1፥32፤ ዕብ3፥19
78፥23 ዘፍ7፥11፤ 2ነገ7፥2
78፥24 ዘፀ16፥4፤ ዮሐ6፥31
78፥26 ዘኍ11፥31
78፥27 ዘፀ16፥13፤ ዘኍ11፥31
78፥29 ዘኍ11፥20
78፥30 ዘኍ11፥33
78፥31 ኢሳ10፥16
78፥32 ቍ11፥17፡ 22
78፥33 ዘኍ14፥29፡ 35
78፥34 ዘዳ4፥29፤ ሆሴ5፥15
78፥35 ዘፍ49፥24፤ ዘዳ9፥26
78፥36 ሕዝ33፥31
78፥37 ቍ8፤ ሐሥ 8፥21
78፥38 ዘፀ34፥6፤ ኢዮ9፥13፤መዝ25፥11 ፤85፥2፤ኢሳ1፥25፤ 27፥9፥30፥18፤ 48፥10፤ ዳን11፥35
78፥39 ዘፍ6፥3፤ ኢዮ7፥7፤ኢሳ29፥5፤ ያዕ4፥14
78፥40 ዘፀ23፥21፤ መዝ95፥8፤106፥14፤ ኤፌ4፥30
78፥41 ዘፀ17፥2፤ 2ነገ19፥22፤መዝ71፥22፤89፥18

42እነርሱን በዚያን ቀን ከጠላት
የታደገበትን፣
ያን ኀይሉን አላስታወሱም፤
43በግብፅ ያደረገውን ታምራዊ ምልክት፣
በጣኔዎስም በረሓ ያሳየውን ድንቅ
ሥራ አላሰቡም።
44ወንዞቻቸውን ወደ ደም ለወጠ፤
ከጅረቶቻቸውም መጠጣት አልቻሉም።
45የዝንብ ሰራዊት ሰደደባቸው፤
ነደፏቸውም፤
ጓጉንቸርም ላከባቸው፤ ሰዎችንም
አጠፉ።
46አዝመራቸውን ለኩብኩባ፣
ሰብላቸውንም ለአንበጣ ሰጠባቸው።
47የወይን ተክላቸውን በበረዶ፣
የበለስ ዛፋቸውንም በውርጭ አጠፋ።
48ከብቶቻቸውን ለበረዶ፣
የከብት መንጋቸውን ለመብረቅ እሳት
ዳረገ።
49ጽኑ ቍጣውን በላያቸው ሰደደ፤
መዓቱን፣ የቅናቱን ቍጣና መቅ
ሠፍቱን ላከባቸው፤
አጥፊ የመላእክት ሰራዊትም
ሰደደባቸው።
50ለቍጣው መንገድ አዘጋጀ፤
ነፍሳቸውንም ከሞት አላተረፈም፤
ነገር ግን ሕይወታቸውን ለመቅሠፍት
አሳልፎ ሰጠ።
51የዐፍላ ጒልበታቸው መጀመሪያ
የሆኑትን በካም ድንኳን፣
በኵሮቻቸውንም ሁሉ በግብፅ ምድር
ፈጀ።
52ሕዝቡን ግን እንደ በግ አወጣቸው፤
በምድረ በዳም እንደ መንጋ መራቸው።
53በሰላም መራቸው፤ እነርሱም አልፈሩም፤
ጠላቶቻቸውን ግን ባሕር ዋጣቸው።
54ቀኝ እጁም ወዳስገኘችው ወደዚህ
ተራራ፣
ወደ ቅድስት ምድር አገባቸው።
55ሕዝቦችን ከፊታቸው አባረረ፤
ምድራቸውን ርስት አድርጎ
አከፋፈላቸው፤
የእስራኤልንም ነገዶች በጠላቶቻቸው
ቤት አኖረ።
56እነርሱ ግን ልዑል አምላክን ተፈታተኑት፤
በልዑልም ላይ ዐመፁ፤
ሥርዐቱንም አልጠበቁም።
57ተመልሰው እንደ አባቶቻቸው ከዳተኛ
ሆኑ፤
እንደማያስተማምን ጠማማ ቀስት
ተወላገዱ።
58በኰረብታ ማምለኪያዎቻቸው
አስቈጡት፤
ተቀርጸው በተሠሩ ጣዖቶቻቸው
አስቀኑት።
59እግዚአብሔር ይህን በሰማ ጊዜ እጅግ
ተቈጣ፤
እስራኤልንም ፈጽሞ ተወ።
60በሰዎች መካከል ያቆማትን ድንኳን፣
የሴሎን ማደሪያ ተዋት።
61የኀይሉን ምልክት አስማረካት፤
ክብሩንም ለጠላቶቹ እጅ አሳልፎ ሰጠ።
62ሕዝቡን ለሰይፍ ዳረገ፤
በርስቱም ላይ እጅግ ተቈጣ።
63ጐልማሶቻቸውን እሳት በላቸው፤
ልጃገረዶቻቸውም የሰርግ ዘፈን
አልተዘፈነላቸውም።
64ካህናታቸው በሰይፍ ተገደሉ፤
መበለቶቻቸውም ማልቀስ ተሳናቸው።
65ጌታም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፤
የወይን ጠጅ ስካር እንደ በረደለት
ጀግናም ብድግ አለ።
66ጠላቶቹን መትቶ ወደ ኋላ መለሳቸው፤
የዘላለም ውርደትም አከናነባቸው።
67የዮሴፍን ድንኳን ተዋት፤
የኤፍሬምንም ነገድ አልመረጠም።
68ነገር ግን የይሁዳን ነገድ፣
የወደዳትን የጽዮንን ተራራ መረጠ።
69መቅደሱን እንደ ታላቅ ከፍታ፣
ለዘላለም እንደ መሠረታት ምድር
ሠራት።
70ባሪያውን ዳዊትን መረጠ፤
ከበጎች ጒረኖ ውስጥ ወሰደው፤
71ለሕዝቡ ለያዕቆብ፣
ለርስቱም ለእስራኤል እረኛ ይሆን ዘንድ፣
የሚያጠቡ በጎችን ከመከተል
አመጣው።
72እርሱም በቅን ልቡ ጠበቃቸው፤
ብልኀት በተሞላ እጁም መራቸው።

## መዝሙር 79

### ብሔራዊ ሰቆቃ

የአሳፍ መዝሙር

1አምላክ ሆይ፤ ሕዝቦች ርስትህን ወረሩ፤
የተቀደሰውን ቤተ መቅደስህን አረከሱ፤
ኢየሩሳሌምንም አፈራርሰው ጣሏት።
2የባሪያዎችህን ሬሳ ለሰማይ ወፎች፣
የቅዱሳንህንም ሥጋ ለምድር አራዊት፣
ምግብ አድርገው ሰጡ።
3ደማቸውንም በኢየሩሳሌም ዙሪያ፣
እንደ ውሃ አፈሰሱ፤
የሚቀብራቸውም አልተገኘም።
4እኛም ለጎረቤቶቻችን መዘባበቻ፣
በዙሪያችንም ላሉት መሣቂያ

78፥42 መሳ3፥7፤ ነህ9፥17፤መዝ27፥11
78፥43 ዘፀ3፥20፤ 10፥1
78፥44 ዘፀ7፥20፡21 ፤መዝ105፥29
78፥45 ዘፀ8፥2፡6፡ 24፤መዝ105፥31
78፥46 ዘፀ10፥13፤ ናሆ3፥15
78፥47ዘፀ9፥23፤ መዝ 105፥32፤ 147፥17
78፥48 ዘፀ9፥25
78፥49 ዘፍ19፥13፤ ዘፀ15፥7፤1ቆሮ10፥10
78፥51 ዘፀ12፥12፤ መዝ105፥23፤ 106፥22፤135፥8
78፥52 ኢዮ21፥11፤ መዝ28፥9
78፥53 ዘፀ14፥28፤ 15፥7፤106፥10
78፥54 መዝ44፥3
78፥55 ዘዳ1፥38፤ ኢሱ13፥7፤መዝ44፥2፤ ሐሥ13፥19
78፥57 ቈ9፤ 2ዜና30፥7፤ ሕዝ20፥27
78፥58 ዘፀ20፥4፤ ዘሌ26፥30፤ዘዳ5፥8፤ 32፥21፤መሳ2፥12
78፥59 ዘሌ26፥28፤ ዘኍ32፥14፤ዘዳ32፥1 9፤መዝ55፥19
78፥60 ኢሱ18፥1፤ ሕዝ8፥6
78፥61 1ሳሙ4፥17 ፤መዝ132፥8
78፥62 ዘዳ28፥25፤ 1ሳሙ10፥1
78፥63 ዘኍ11፥1፤ 1ነገ4፥32፤ኤር7፥34፤ 16፥9፤25፥10
78፥64 1ሳሙ4፥17
78፥65 መዝ44፥23
78፥66 1ሳሙ5፥6
78፥67 ኤር7፥15፤ ሆሴ9፥13፤12፥1
78፥68 ዘፀ15፥17፤ ዘኍ1፥7፤መዝ68፥16፤ 108፥8
78፥69 መዝ15፥1
78፥70 1ሳሙ16፥1
78፥71 ዘፍ37፥2፤ መዝ28፥9
78፥72 ዘፍ17፥1
79፥1 ዘፀ34፥9፤ ዘሌ20፥3፤2ነገ25፥9፤ ነህ4፥2፤ኢሳ6፥11
79፥2 ዘዳ28፥26፤ ኤር 7፥33፤ ራእ19፥17-18
79፥3 ኤር16፥4፤ 25፥33፤ራእ11፥9
79፥4 መዝ39፥8፤ 44፥13፤80፥6፤ ሕዝ 5፥14

*መሣለቂያ ሆንን*።

5*እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ*
*ነው? የምትቈጣውስ ለዘላለም*
*ነውን?*
*ቅናትህስ እንደ እሳት ሲነድ ይኖራልን?*
6በማያውቁህ ሕዝቦች ላይ፣
ስምህን በማይጠሩ፣
*መንግሥታት* ላይ፣
*መዓትህን* አፍስስ፤
7*ያዕቆብን* በልተውታልና፤
*መኖሪያ ቦታውንም* ባድማ አድርገዋል።
8የአባቶቻችንን ኀጢአት በእኛ ላይ
አትቍጠርብን፤
ምሕረትህ ፈጥና ወደ እኛ ትምጣ፤
በጭንቅ ላይ እንገኛለንና።

9አዳኛችን የሆንህ ኤሎሂም ሆይ፤
ስለ ስምህ ክብር ብለህ እርዳን፤
ስለ ስምህ ስትል፣
ታደገን፤ ኀጢአታችንንም ይቅር በል።
10ሕዝቦች፣ "ኤሎሂማቸው የት አለ?"
ለምን ይበሉ?
የፈሰሰውን የአገልጋዮችህን ደም በቀል፣
ዐይናችን እያየ ሕዝቦች ይወቁት።
11የእስረኞች ሰቈቃ በፊትህ ይድረስ፤
በክንድህም ብርታት፣
ሞት የተፈረደባቸውን አድን።

12ጌታ ሆይ፤ ጎረቤቶቻችን በአንተ ላይ
የተዘባበቱትን መዘባበት፣
ሰባት ዕጥፍ አድርገህ አስታቅፋቸው።
13እኛ ሕዝብህ፣ የማሰማሪያህ በጎችህ፣
ለዘላለም ምስጋና እናቀርብልሃለን፤
ከትውልድ እስከ ትውልድም፣
ውለታህን እንናገራለን።

## *መዝሙር* 80

## ለእስራኤል ተሐድሶ የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ "የኪዳን ጽጌረዳ" በሚለው ቅኝት የሚዜም፤ የአሳፍ መዝሙር*

1ዮሴፍን እንደ በግ መንጋ የምትመራ፣
የእስራኤል እረኛ ሆይ፤ ስማን፤
በኪሩቤል ላይ በዙፋን የምትቀመጥ
ሆይ፤
በብርሃንህ ተገለጥ፤
2በኤፍሬም፣ በብንያምና በምናሴ ፊት
ደምቀህ ታይ።
ኀይልህን አንቀሳቅስ፤
*መጥተህም* አድነን።

3ኤሎሂም ሆይ፤ መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን።

4የሰራዊት ኤሎሂም *እግዚአብሔር* ሆይ፤
በሕዝብህ ጸሎት ላይ ቍጣህ የሚነደው፣
እስከ መቼ ድረስ ነው?
5የእንባ እንጀራ አበላሃቸው፤
ስፍር የሞላ እንባም አጠጣሃቸው።
6ለጎረቤቶቻችን የጠብ ምክንያት
አደረግኸን፤
ጠላቶቻችንም ተሣሣቁብን።

7የሰራዊት ኤሎሂም ሆይ፤ መልሰን፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን።

8ከግብፅ የወይን ግንድ አመጣህ፤
አሕዛብን አባርረህ እርሷን ተከልሃት።
9*መሬቱን* መነጠርህላት፤
እርሷም ሥር ሰዳ አገሩን ሞላች።
10ተራሮች በጥላዋ ተሸፈኑ፤
ግዙፍ ዝግቦችም በቅርንጫፎቿ
ተጠለሉ።
11ቅርንጫፎቿን እስከ ባሕሩ፣[ኘ]
ቍጥቋጦዋንም እስከ ወንዙ[ኦ] ዘረጋች።

12ታዲያ ዐላፊ አግዳሚው ፍሬዋን
እንዲለቅም፣
ለምን ቅጥሯን አፈረስህ?
13ዕርያ ከዱር ወጥቶ ያበለሻሻታል፤
በሜዳ የሚንጋጋ እንስሳ ሁሉ
ይበላታል።
14የሰራዊት ኤሎሂም ሆይ፤ እንግዲህ
ወደ እኛ ተመለስ፤
ከሰማይ ተመልከት፤ እይም፤
ይህችን የወይን ተክል ተንከባከባት፤
15ይህች ቀኝ እጅህ የተከላት ቡቃያ፣
ለራስህ ያጸደቅሃት ተክል[ከ] ናት።

16እርሷም በእሳት ተቃጥላለች፤
የግንባርህ ተግሣጽ ያጠፋቸዋል።
17ለራስህ ባበረታኸው የሰው ልጅ ላይ፣
በቀኝ እጅህ ሰው ላይ እጅህ ትሁን።
18ከእንግዲህ አንተን ትተን ወደ ኋላ
አንመለስም፤
ሕያዋን አድርገን፤ እኛም ስምህን
እንጠራለን።

19የሰራዊት ኤሎሂም *እግዚአብሔር* ሆይ፤
*መልሰን*፤
እንድንም ዘንድ፣
ፊትህን አብራልን።

## *መዝሙር* 81

## ለዳስ በዓል የሚዜም ቅኔ

*ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዜም፣ የአሳፍ መዝሙር*

1ብርታታችን ለሆነው ኤሎሂም በደስታ

79፥5 ዘዳ29፥20፤ መዝ74፥1፡10፤85፥5፤ 89፥46፤ሶፎ3፥8
79፥6 መዝ2፥5፤ 14፥4፤69፥24፤110፥5 ፤147፥20፤ኤር10፥25 ፤ራእ16፥1
79፥7 ኢሳ9፥12፤ ኤር10፥25
79፥8 ዘፍ9፥25፤ መዝ116፥6፤142፥6፤ ኤር44፥21
79፥9 2ዜና14፥11፤ መዝ25፥11፤31፥3፤ ኤር14፥7
79፥10 ቆላ3፤ መዝ 42፥3፤94፥1፤ ራእ6፥10
79፥12 ዘፍ4፥15፤ ኢሳ65፥6፤ኤር32፥18
79፥13 መዝ44፥8፤ 74፥1
80፥1 ዘፀ25፥22፤ መዝ77፥20
80፥2 ዘኍ2፥18-24 ፤መዝ35፥23፤54፥1፤ 69፥1፤71፥2፤109፥26 ፤116፥4፤119፥94
80፥3 ቆላ7፡19፤ ዘኍ6፥25፤መዝ71፥20፤ 85፥4፤ኤር31፥18፤ ሰቆ5፥21
80፥4 ዘዳ29፥20፤ መዝ74፥10
80፥5 ኢዮ3፥24፤ ኢሳ30፥20
80፥6 መዝ79፥4
80፥7 ቆላ3
80፥8 ዘፀ15፥17፤ 23፥28-30፤ኢሱ13፥6 ፤ኢሳ5፥1-2፤ኤር2፥21 ፤ማቴ21፥33-41፤ ሐሥ7፥45
80፥11 መዝ72፥8
80፥12 መዝ89፥40 ኢሳ5፥5፤30፥13፤ ኤር 39፥8
80፥13 ኤር5፥6
80፥14 ዘዳ26፥15
80፥16 ዘዳ28፥20፤ መዝ79፥1
80፥17 ኢዮ25፥6
80፥18 መዝ85፥6፤ ኢሳ57፥15፤ሆሴ6፥2
81፥1 መዝ66፥1

[ኘ]11 ሜድትራኒያን ሳይሆን አይቀርም።
[ኦ]11 የኤፍራጥስ ወንዝ ለማለት ነው።
[ከ]15 ወንድ ልጅ የሚሉ ትርጕሞች አሉ።

ዘምሩ፤
ለያዕቆብ አምላክ እልል በሉ።
2ዝማሬውን ጀምሩ፤ ከበሮውን ምቱ፤
በበገናና በመሰንቆ ጥዑም ዜማ አሰሙ።
3በሙሉ ጨረቃ፣ በክብረ በዓላችን ዕለት፣
በወሩ መግቢያ፣ ጨረቃ ስትወለድ
መለከት ንፉ፤
4ይህ ለእስራኤል የተሰጠ ሥርዐት፣
የያዕቆብም አምላክ ድንጋጌ ነውና።
5ሙሉ ለሙሉ ግብፅን ለቆ በወጣ ጊዜ፣
ይህን ለዮሴፍ ደነገገለት፤
በማላውቀውም[ኸ] ቋንቋ እንዲህ ሲል
ሰማሁ፦

6"ትከሻውን ከሸክም ገላገልሁት፤
እጁንም ቅርጫት ከመያዝ አሳረፍሁ።
7በመከራህ ጊዜ ጠራኸኝ፤ እኔም
ታደግሁህ፤
በነጐድጓድ መሰወሪያ ውስጥ መለስሁልህ፤
በመሪባ ውሃ ዘንድ ፈተንሁህ። ሴላ

8"ሕዝቤ ሆይ፤ ሳስጠነቅቅህ ስማኝ፤
እስራኤል ሆይ፤ ምነው ብታደምጠኝ!
9በአንተ ዘንድ ባዕድ አምላክ አይኑር፤
ለሌላም አምላክ አትስገድ።
10ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ፣
እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ፤
አፍህን በሰፊው ክፈተው፤ እኔም
እሞላዋለሁ።

11"ሕዝቤ ግን አላደመጠኝም፤
እስራኤልም እሺ አልሰጥ አለኝ።
12ስለዚህ በገዛ ዕቅዳቸው እንዲሄዱ፣
አሳልፌ ለደንዳናው ልባቸው
ሰጠኋቸው።

13"ምነው ሕዝቤ ቢያደምጠኝ ኖሮ፣
እስራኤል በመንገዴ በሄደ ኖሮ፣
14ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባንበረከክኋቸው
ነበር፤
እጄን በባላጋራዎቻቸው ላይ ባነሣሁ
ነበር።
15እግዚአብሔርን የሚጠሉ በፊቱ ይርዳሉ፤
ቅጣታቸውም እስከ ዘላለም የሚዘልቅ
ነው።
16እናንተን ግን ምርጡን ስንዴ አበላችኋለሁ፤
ከዐለቱም ማር አጠግባችኋለሁ።"

## መዝሙር 82

### ሙሴናን ዳኞች

የአሳፍ መዝሙር

1እግዚአብሔር በአማልክት ጉባኤ መካከል
ተሰየመ፤
በአማልክትም ላይ ይፈርዳል፤ እንዲህም
ይላል፦

81፥2 ዘፀ15፥20፤ ኢዮ21፥12፤መዝ92፥3
81፥3 ዘፀ19፥13፤ ነህ10፥33
81፥4 ቀኈ1
81፥5 ዘፀ11፥4፤ መዝ114፥1
81፥6 ዘፀ1፥14፤ ኢሳ 9፥4፤52፥2
81፥7 ዘፀ2፥23፤ 17፥7፤19፥19፤ ዘዳ 33፥8
81፥8 መዝ50፥7፤ 78፥1
81፥9 ዘፀ20፥3
81፥10 ዘፀ6፥6፤ 13፥3፤29፥46፤ መዝ107፥9፤ሕዝ2፥8
81፥11 ዘፀ32፥1-6
81፥12 ሕዝ20፥25፤ ሐሥ7፥42፤ሮሜ1፥24
81፥13 ዘዳ5፥29
81፥14 መዝ47፥3፤ አሞ1፥8
81፥15 2ሳሙ22፥45
81፥16 ዘዳ32፥14
82፥1 ኢዮ21፥22፤ መዝ7፥8፤58፥11፤ ኢሳ 3፥13፤66፥16፤ ኢል 3፥12
82፥2 ዘዳ1፥17፤ መዝ58፥1-2፤ምሳ18፥5
82፥3 ዘዳ24፥17፤ መዝ140፥12፤ ኤር5፥28፤22፥16
82፥5 መሳ5፥4፤ ኢዮ30፥26፤መዝ11፥3፤ 14፥4፤53፥2፤ ኢሳ5፥30፤8፥21-22፤ 9፥2፤ 59፥9፤60፥2፤ ኤር13፥16፤23፥12፤ ሰቆ3፥2
82፥6 ዮሐ10፥34
82፥7 መዝ49፥12 ፤ሕዝ31፥14
82፥8 መዝ2፥8፤ 12፥5፤76፥9
83፥1 መዝ28፥1፤ 35፥22፤ኢሳ42፥14፤ 57፥11፤62፥1፤64፥12
83፥2 መሳ8፥28፤ መዝ2፥1፤ኢሳ17፥12
83፥3 ዘፀ1፥10፤ መዝ 17፥14፤31፥13
83፥4 አስ3፥6፤ ኤር 11፥19፤33፥24
83፥5 መዝ2፥2
83፥6 ዘፍ25፥16፤ 2ዜና20፥1፤መዝ137፥7 ፤ ኢሳ34፥5፤ ኤር49፥7፤አሞ1፥11
83፥7 ዘፍ14፥7፤ 19፥38፤ዘፀ15፥14፤ 17፥14፤ኢሱ13፥5፤ ኢሳ23፥3፤ሕዝ27፥3
83፥8 ዘፍ10፥11፤ ዘዳ2፥9

2"ፍትሕን የምታጓድሉት እስከ መቼ
ነው?
ለክፉዎች የምታደሉትስ እስከ መቼ
ነው? ሴላ
3ለዐቅመ ቢሶችና ለድኻ አደጎች
ፍረዱላቸው፤
የችግረኛውንና የምስኪኑን መብት
አስከብሩ።
4ወገን የሌለውንና ችግረኛውን ታደጉ፤
ከግፈኛውም እጅ አስጥሏቸው።

5"ዕውቀትም ማስተዋልም የላቸውም፤
በጨለማ ውስጥ ወዲያ ወዲህ
ይመላለሳሉ፤
የምድርም መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ።

6"እኔም፤ 'እናንተ አማልክት ናችሁ፤
ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ'
አልሁ።
7ነገር ግን እንደ ማንኛውም ሰው
ትሞታላችሁ፤
እንደ ማንኛውም ገዥ
ትወድቃላችሁ።"

8አምላክ ሆይ፤ ተነሥ፤ በምድር ላይ
ፍረድ፤
ሕዝቦች ሁሉ ርስትህ ናቸውና።

## መዝሙር 83

### በእስራኤል ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት

የአሳፍ መዝሙር፤ ማሕሌት

1አምላክ ሆይ፤ ዝም አትበል፤
አምላክ ሆይ፤ ጸጥ አትበል፤ ጭጭ
አትበል።
2ጠላቶችህ እንዴት እንደ ተነሣሡ፣
ባላንጣዎችህም እንዴት ራሳቸውን ቀና
ቀና እንዳደረጉ ተመልከት።
3በሕዝብህ ላይ በተንኰል አሤሩ፤
በውድ ልጆችህ ላይ በአንድነት
ተመካከሩ።
4"የእስራኤል ስም ከእንግዲህ እንዳይታወስ፣
ኑና ሕዝብ እንዳይሆኑ እንደምስሳቸው"
አሉ።
5በአንድ ሐሳብ ተስማምተው ተማከሩ፤
በአንተም ላይ ተማማሉ፤
6የኤዶምና የእስማኤላውያን ድንኳኖች፣
የሞዓብና የአጋራውያን ድንኳኖች፣
7ጌባል፣[ወ] አሞንና አማሌቅ፣
ፍልስጥኤምም ከጢሮስ ሕዝብ ጋር
ሆነው ዶለቱ፤
8አሦርም ከእነርሱ ጋር ተባበረ፤
የሎጥ ልጆችም ረዳት ሆኑ። ሴላ

[ኸ]5 አንዳንዶች *የማናውቀውን ድምፅ ሰማን* ይላሉ።
[ወ]7 *ቢብሎስ* ለማለት ነው።

9በምድያም ላይ እንዳደረግኸው
አድርግባቸው፤
በቂሶንም ወንዝ በሲሣራና በኢያቢስ
ላይ ያደረስኸው ይድረስባቸው።
10እነርሱም በዐይንዶር ጠፉ፤
እንደ ምድርም ጕድፍ ሆኑ።
11*መኳንንታቸውን* እንደ ሔሬብና እንደ
ዜብ፣
*መሳፍንታቸውንም* ሁሉ እንደ ዛብሄልና
እንደ ስልማና አድርጋቸው፤
12እነዚህም፣ "የእግዚአብሔርን የግጦሽ ቦታ፣
ወስደን የግላችን እናድርግ" የሚሉ
ናቸው።

13አምላኬ ሆይ፤ በዐውሎ ነፋስ እንደሚነዳ
ትቢያ፣
በነፋስም ፊት እንዳለ ገለባ
አድርጋቸው።
14እሳት ደንን እንደሚያጋይ፣
ነበልባልም ተራራን እንደሚያቃጥል፣
15እንዲሁ በሞገድህ አሳዳቸው፤
በማዕበልህም አስደንግጣቸው።
16*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስምህን ይሹ ዘንድ፣
*ፊታቸውን* በዕፍረት *ሙላው*፤
17*ለዘላለም* ይፈሩ፤ ይታወኩም፤
በውርደትም ይጥፉ።
18ስምህ *እግዚአብሔር* የሆነው አንተ
ብቻ፣
በምድር ሁሉ ላይ ልዑል እንደ ሆንህ
ይወቁ።

## *መዝሙር* 84

### ወደ መቅደሱ ጕዞ መዝሙር

*ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት የሚዜም የቆሬ ልጆች መዝሙር*

1የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
*ማደሪያህ ምንኛ የተወደደ ነው!*
2ነፍሴ *የእግዚአብሔርን* አደባባዮች
ትናፍቃለች፤
እጅግም ትጓጓለታለች፤
ልቤና *ሥጋዬም*፣
ለሕያው አምላክ እልል በሉ።
3ንጉሤና አምላኬ የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
*መሠዊያህ* ባለበት ስፍራ፣
ድንቢጥ እንኳ *መኖሪያ* ቤት፣
ዋኖስም ጫጩቶቿን የምታኖርበት
ጐጆ አገኘች።
4በቤትህ የሚኖሩ የተባረኩ ናቸው፤
እነርሱም ለዘላለም ያመሰግኑሃል። ሴላ

5አንተን ብርታታቸው ያደረጉ፣
በልባቸው የጽዮንን መንገድ የሚያስቡ
ቡሩካን ናቸው።
6በልቅሶ ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ፣
የምንጭ መፍለቂያ ቦታ ያደርጉታል፤
የበልጉም ዝናብ ያረሰርሰዋል።[0]
7ከኀይል ወደ ኀይል ይሸጋገራሉ፤
እያንዳንዱም በጽዮን ባለው አምላክ ፊት
ይቀርባል።
8የሰራዊት አምላክ ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
የያዕቆብ አምላክ ሆይ አድምጠኝ።
ሴላ

9አምላክ ሆይ፤ ጋሻችንን″ እይልን፤
የቀባኸውንም ተመልከት።

10በሌላ ስፍራ ሺህ ቀን ከመኖር፣
በአደባባይህ አንዲት ቀን መዋል
ይሻላል፤
በክፉዎች ድንኳን ከመቀመጥ ይልቅ፣
በአምላኬ ቤት ደጅ መቆም
እመርጣለሁ።
11*እግዚአብሔር* አምላክ ፀሓይና ጋሻ
ነውና፤
*እግዚአብሔር* ሞገስንና ክብርን
ይሰጣል፤
እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን፣
መልካም ነገር አይነፍጋቸውም።

12የሰራዊት አምላክ ሆይ፤
በአንተ የታመነ ሰው ቡሩክ ነው።

## *መዝሙር* 85

### ለሰላም የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች፤ መዝሙር*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለምድርህ በጎ
ውለሃል፤
የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ።
2የሕዝብህን በደል ይቅር አልህ፤
ኀጢአታቸውንም ሁሉ ሸፈንህ።
3*መዓትህን* ሁሉ አራቅህ፤
ከብርቱ ቍጣህም ተመለስህ።
4*መድኀኒታችን* የሆንህ አምላክ ሆይ፤
*መልሰን*፤
በእኛ ላይ የተቃጣውን ቍጣህን
*መልሰው*።
5የምትቈጣን ለዘላለም ነውን?
ቍጣህስ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይቀጥላልን?
6ሕዝብህ በአንተ ሐሤት ያደርግ ዘንድ፣
*መልሰህ* ሕያዋን አታደርገንምን?
7*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህን አሳየን፤
ማዳንህን ለግሰን።
8*እግዚአብሔር* አምላክ የሚናገረውን
እሰማለሁ፤
ለሕዝቡ፣ ለቅዱሳኑ ሰላምን ይናገራልና፤
ዳሩ ግን ወደ ከንቱ ምግባራቸው
አይመለሱ።

83፥9 ዘፍ25፥2፤ ኢሱ11፥1፤መሳ4፥2: 23-24፤7፥1-23
83፥10 1ሳሙ28፥7 ፤2ነገ9፥37፤ኢሳ5፥25፤ ኤር8፥2፤9፥22፤16፥4 ፤25፥33፤ሶፎ1፥17
83፥11 መሳ7፥25፤ 8፥5
83፥12 2ዜና20፥11 ፤ሕዝ35፥10
83፥13 ኢዮ13፥25
83፥14 ዘዳ32፥22 ፤ኢሳ9፥18
83፥15 ኢዮ9፥17፤ መዝ50፥3
83፥16 መዝ34፥5፤ 109፥29፤132፥18
83፥17 2ነገ19፥26፤ መዝ35፥4
83፥18 ኢዮ34፥29፤ መዝ7፥8፤18፥13፤ 68፥4
84፥1 ዘዳ33፥27፤ መዝ27፥4፤43፥3፤ 90፥1፤132፥5
84፥2 ኢሱ3፥10፤ ኢዮ19፥27
84፥3 መዝ2፥6፤ 5፥2፤43፥4፤44፥11
84፥5 መዝ81፥1፤ ኤር31፥6
84፥6 ኢዮ38፥26፤ ኢል2፥23
84፥7 ዘዳ16፥16፤ 1ነገ8፥1፤ኢዮ17፥9
84፥8 መዝ4፥1
84፥9 1ሳሙ16፥6፤ መዝ2፥2፤18፥50፤ 59፥11፤132፥17
84፥10 1ዜና23፥5
84፥11 ዘፍ15፥1፤ መዝ34፥10፤ኢሳ 60፥19፤ኤር43፥13፤ ራእ21፥23
84፥12 መዝ2፥12
85፥1 ዘዳ30፥3፤ መዝ14፥7
85፥2 ዘፀ32፥30፤ ዘኍ14፥19፤ መዝ78፥38
85፥3 ዘፀ32፥12፤ ዘዳ 13፥17፤ መዝ78፥38፤106፥23፤ ዳን9፥16፤ዮና3፥9
85፥4 መዝ65፥5፤ 71፥20
85፥5 መዝ50፥21
85፥6 መዝ80፥18፤ ፊል3፥1
85፥7 መዝ6፥4፤ 27፥1
85፥8 ዘሌ26፥6፤ ምሳ26፥11፤27፥22፤ ኢሳ60፥17፤ ዮሐ14፥27፤2ተሰ3፥16

[0]6 ወይም *ይባርከዋል*
″9 ወይም *ልዑል*

[9]ክብሩ በምድራችን ይኖር ዘንድ፣
ማዳኑ ለሚፈሩት በእርግጥ ቅርብ ነው።
[10]ምሕረትና *ታማኝነት* ተገናኙ፤
ጽድቅና ሰላም ተቃቀፉ።
[11]*ታማኝነት* ከምድር በቀለች፤
ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች።
[12]*እግዚአብሔር* በጎ ነገር ይለግሳል፤
ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች።
[13]ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፤
ለአረማመዱም መንገድ *ያዘጋጃል*።

### *መዝሙር* 86

## የመከራ ጊዜ ጸሎት

የዳዊት ጸሎት

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጆሮህን ወደ እኔ ጣል፤ ስማኝም፤
እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና።
[2]ለአንተ የተለየሁ ሰው ነኝና ነፍሴን ጠብቃት፤
አንተ አምላኬ ሆይ፤
በአንተ የ*ታ*መነብህን ባሪያህን አድን።
[3]ጌታ ሆይ፤ ማረኝ፤
ቀኑን ሙሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና።
[4]የባሪያህን ነፍስ ደስ አሰኛት፤
ጌታ ሆይ፤ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁና።
[5]ጌታ ሆይ፤ አንተ ቸርና ይቅር ባይ ነህ፤
ለሚጠሩህ ሁሉ ምሕረትህ ወሰን የለውም።
[6]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጸሎቴን አድምጥ፤
የልመናዬን ጩኸት ስማ።
[7]አንተ ስለምትመልስልኝ፣
በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጣራለሁ።
[8]ጌታ ሆይ፤ ከአማልክት መካከል እንደ አንተ ያለ የለም፤
ከአንተም ሥራ ጋር የሚወዳደር ሥራ የለም።
[9]ጌታ ሆይ፤ አንተ የሠራሃቸው ሕዝቦች ሁሉ፣
መጥተው በፊትህ ይሰግዳሉ፤
ለስምህም ክብር ይሰጣሉ፤
[10]አንተ *ታ*ላቅ ነህና፤ *ታ*ምራትም ትሠራለህ፤
አንተ ብቻህን አምላክ ነህ።
[11]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መንገድህን አስተምረኝ፤
በእውነትህም እሄዳለሁ፤
ስምህን እፈራ ዘንድ፣
ያልተከፋፈለ ልብ ስጠኝ።
[12]ጌታ አምላኬ ሆይ፤ በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ፤
ስምህንም ለዘላለም አከብራለሁ፤
[13]ለእኔ ያሳየሃት ምሕረት *ታ*ላቅ ናትና፤

85፥9 ዘፀ29፥43፤ መዝ27፥1፤ኢሳ43፥3፤ 45፥8፤46፥13፤51፥5፤ 56፥1፤60፥19፤62፥11 ፤ሐጌ2፥9፤ዘካ2፥5
85፥10 መዝ72፥2-3፤89፥14፤115፥1፤ ምሳ3፥3፤ኢሳ32፥17
85፥11 ኢሳ45፥8
85፥12 ዘሌ26፥4፤ መዝ67፥6፤84፥11፤ ዘካ8፥12፤ያዕ1፥17
86፥1 መዝ17፥6
86፥2 መዝ25፥2፤ 31፥14
86፥3 መዝ4፥1፤ 9፥13፤57፥1፤88፥9
86፥4 መዝ46፥5፤ 143፥8
86፥5 ዘፀ34፥6፤ ነህ 9፥17፤ መዝ103፥8፤145፥8፤ ኢል2፥13፤ዮና4፥2
86፥6 መዝ5፥2፤17፥1
86፥7 ኢዮ22፥27፤ መዝ3፥4፤4፥3፤27፥5፤ 50፥15፤80፥18፤ 91፥15፤ 94፥13፤ኢሳ30፥19፤ 58፥9፤65፥24፤ ዕን3፥16፤ዘካ13፥19
86፥8 ዘፀ8፥10፤ ኢዮ21፥22፤መዝ18፥31
86፥9 መዝ65፥2፤ 66፥4፤ኢሳ19፥21፤ 27፥13፤43፥7፤44፥23 ፤49፥7፤ዘካ8፥20-22፤ 14፥16፤ራእ15፥4
86፥10 ዘፀ3፥20፤ ዘዳ6፥4፤2ሳሙ7፥22፤ መዝ48፥1፤71፥17፤ 72፥18፤ኢሳ43፥10፤ ማር12፥29፤1ቆሮ8፥4
86፥11ዘፀ33፥13፤ዘዳ 6፥24፤1ሳሙ12፥23፤ መዝ25፥5፤26፥3፤ ኤር 24፥7፤32፥39፤ ሕዝ11፥19፤1ቆሮ7፥35
86፥12 መዝ9፥1
86፥13 መዝ16፥10 ፤34፥4፤49፥15፤56፥1 3፤116፥8
86፥14 መዝ54፥3
86፥15 ቍ5፤ዘፀ 34፥6፤ዘኍ14፥18፤ነህ 9፥17፤መዝ51፥1፤103፥8 ፤111፥4፤116፥5፤ 145፥8፤ኢል2፥13
86፥16 መዝ6፥4፤ 9፥13፤18፥1፤116፥16
86፥17 ዘፀ3፥12፤ ማቴ24፥3፤ዮሐ2፥11
87፥1 መዝ48፥1
87፥2 መዝ2፥6
87፥3 መዝ46፥4
87፥4 2ሳሙ8፥1፤ ኢዮ9፥13፤ መዝ45፥12 ፤83፥7፤ ኢሳ19፥25፤ኢል3፥4
87፥6 ዘፀ32፥32፤ መዝ69፥28፤ኢሳ 4፥3፤ሚል3፥16
87፥7 መዝ36፥9፤ 149፥3
88፥1 መዝ3፥4፤22፥2፤51፥14፤ሉቃ18፥7

ነፍሴንም ከሲኦል[ሠ] ጥልቀት አውጥተሃል።
[14]አምላክ ሆይ፤ እብሪተኞች ተነሥተውብኛል፤
የዐመፀኞችም ጉባኤ ነፍሴን ይሿታል፤
አንተንም ከምንም አልቈጠሩም።
[15]ጌታ ሆይ፤ አንተ ግን መሓሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ፤
ለቍጣ የዘገየህ፣ ምሕረትህና *ታ*ማኝነትህ የበዛ።
[16]ወደ እኔ ተመልከት፤ ማረኝም፤
ለባሪያህ ኀይልህን ስጥ፤
የሴት ባሪያህንም[ረ] ልጅ አድን።
[17]የሚጠሉኝ አይተው ያፍሩ ዘንድ፣
የበጎነትህን ምልክት አሳየኝ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ረድተኸኛልና፤ አጽናንተኸኛልም።

### *መዝሙር* 87

## ጽዮን የሕዝቦች እናት

የቆሬ ልጆች *መዝሙር*፤ ማሕሌት

[1]*መሠረቱን በተቀደሱ ተራሮች አቆመ*፤
[2]*እግዚአብሔር* ከያዕቆብ ማደሪያዎች ሁሉ ይልቅ፣
የጽዮንን ደጆች ይወዳል።
[3]የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፤
ስለ አንቺ ክቡር የሆነ ነገር እንዲህ ተብሎ ይነገራል፤ ሴላ
[4]"ከሚያውቁኝ መካከል፣
ረዓብንና[ሰ] ባቢሎንን እጠቅሳለሁ፤
እነሆ፤ ፍልስጥኤምና ጢሮስ ከኢትዮጵያ ጋር፣
'ይህ[ሸ] ሰው በዚያ ነው የተወለደው'
ይላሉ።"
[5]በእርግጥም ስለ ጽዮን፣
"ይህም ያም ሰው በእርሷ ውስጥ ተወለዱ፤
ልዑልም ራሱ ያጸናታል" ይባላል።
[6]*እግዚአብሔር* ሕዝቡን ሲመዘግብ፣
"ይህ ሰው የተወለደው በዚያ ነው" ብሎ ይጽፋል። ሴላ
[7]የሚያዜሙም መሣሪያ የሚጫወቱም፣
"ምንጬ ሁሉ በአንቺ ውስጥ ይገኛል"
ይላሉ።

### *መዝሙር* 88

## ሰቆቃ

ማሕሌት፤ የቆሬ ልጆች *መዝሙር*፤ ለመዘምራን አለቃ፤ በማኸላት የሚዘመር፤ የይዝራኤላዊው የኤማን ትምህርት

[1]አዳኜ የሆንህ አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤

[ሠ]13 አንዳንዶች *መቃብር* ይላሉ።
[ረ]16 *ታማኝ ወንድ ልጅህን* የሚሉ አሉ።
[ሰ]4 የግብፅ ቅኔያዊ ስያሜ ነው።
[ሸ]4 ወይም *ረዓብ ባቢሎን፣ ፍልስጥኤምና ኢትዮጵያ*

በቀንና በሌሊት በፊትህ አጮኻለሁ።
[2]ጸሎቴ በፊትህ ትድረስ፤
ጆሮህንም ወደ ጩኸቴ አዘንብል፤

[3]ነፍሴ በመከራ ተሞልታለችና፤
ሕይወቴም ወደ ሲኦል[ኀ] ተቃርባለች።
[4]ወደ ጒድጓድ ከሚወርዱት ጋር
ተቈጠርሁ፤
ዐቅምም አጣሁ።
[5]በሙታን መካከል እንደ ተጣሉ፣
ተገድለው በመቃብር ውስጥ እንደ
ተጋደሙ፣
አንተ ከእንግዲህ እንደማታስባቸው፣
ከእጅህም ወጥተው እንደ ተወገዱ
ሆንሁ።

[6]በዐዘቅት ጥልቀት ውስጥ ጣልኸኝ፤
በጨለማ ጒድጓድ ውስጥ ከተትኸኝ።
[7]የቍጣህ ክብደት በላዬ ዐርፎአል፤
በማዕበልህም ሁሉ አጥለቅልቀኸኛል።
ሴላ
[8]የሚቀርቡኝ ባልንጀሮቼን ከእኔ አራቅህ፤
እንዲጸየፉኝም አደረግህ፤
ተከብቤአለሁ፤ ማምለጥም አልችል፤
[9]ዐይኖቼም በሐዘን ፈዘዙ።
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዘወትር ወደ አንተ
እጣራለሁ፤
እጆቼንም ወደ አንተ ዘረጋሁ።
[10]ድንቅ ሥራህን ለሙታን ታሳያለህን?
የሙታንስ መናፍስት ተነሥተው
ያመሰግኑሃልን?
ሴላ
[11]ምሕረትህ በመቃብር ውስጥ፣
ታማኝነትህስ እንጦርጦስ[ጠ]
ይነገራልን?
[12]ድንቅ ሥራህ በጨለማ ስፍራ፣
ጽድቅህስ በመረሳት ምድር
ትታወቃለችን?

[13]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔ ግን ትረዳኝ
ዘንድ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
በጧትም ጸሎቴን በፊትህ አደርሳለሁ።
[14]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለምን ታርቀኛለህ?
ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ?

[15]እኔ ከልጅነቴ ጀምሮ ችግረኛና ለሞት
የተቃረብሁ ነበርሁ፤
መዓትህ አሠቃየኝ፤ ግራም ተጋባሁ።
[16]ቍጣህ በላዬ ላይ ተከነበለ፤
መዓትህም አጠፉኝ።
[17]ቀኑን ሙሉ እንደ ጐርፍ ከበቡኝ፤
በአንድነትም ዙሪያዬን አጥረው
ያዙኝ።
[18]ወዳጄንና ባልንጀራዬን ከእኔ አራቅህ፤
ጓደኛዬ ጨለማ ብቻ ሆኖ ቀረ።

**88፥3** ኢዮ33፥22፤ መዝ6፥3፤25፥17
**88፥4** መዝ18፥1፤ 31፥12
**88፥5** መዝ31፥22
**88፥6** መዝ30፥1፤ 69፥15፤ሰቆ3፥55፤ ዮና2፥3
**88፥7** መዝ7፥11፤ 42፥7
**88፥8** ኢዮ3፥23፤ 19፥13፤መዝ31፥11፤ ኤር32፥2፤33፥1
**88፥9** ኢዮ11፥13፤ መዝ5፥2፤38፥10፤ 143፥6
**88፥10** መዝ6፥5
**88፥11** መዝ30፥9
**88፥13** መዝ5፥3፤ 30፥2፤55፥17፤ 119፥147
**88፥14** መዝ13፥1፤ 43፥2
**88፥15** ኢዮ6፥4፤ 18፥11፤መዝ9፥12፤ 129፥1፤ኤር22፥21፤ ሕዝ 16፥22፤ ሆሴ2፥15፤2ቆሮ4፥8
**88፥16** ኢዮ6፥4፤ መዝ7፥11
**88፥17** መዝ124፥4
**88፥18** ቀኍ8፤ መዝ 38፥11

**89፥1** መዝ36፥5፤ 40፥10፤59፥16
**89፥2** መዝ36፥5
**89፥4** 2ሳሙ7፥12-16፤1ነገ8፥16፤ መዝ132፥11-12፤ ኢሳ9፥7፤ ሕዝ37፥24-25፤ ማቴ1፥1፤ሉቃ1፥33
**89፥5** መዝ1፥5፤ 19፥1
**89፥6** ዘፍ1፥26፤ ዘፀ9፥14፤ መዝ18፥31፤113፥5
**89፥7** ኢዮ5፥1፤ መዝ 47፥2፤111፥1
**89፥8** መዝ71፥19፤ ኢሳ6፥3
**89፥9** መዝ65፥7
**89፥10** ኢዮ9፥13፤ መዝ59፥11፤68፥1፤ 92፥9
**89፥11** ዘፍ1፥1፤ ዘዳ 10፥14፤ 1ዜና29፥11፤ መዝ24፥1፤115፥16
**89፥12** ዘዳ3፥8፤ 4፥48፤ኢሱ19፥22፤ መዝ98፥8
**89፥13** ኢሱ4፥24
**89፥14** መዝ85፥10-11፤97፥2

## መዝሙር 89

### መዝሙርና ለእግዚአብሔር ታማኝነት የቀረበ ጸሎት

የይዝራኤላዊው የኤታን ትምህርት

[1]ስለ *እግዚአብሔር* ምሕረት ለዘለላለም
እዘምራለሁ፤
በአፌም ታማኝነትህን ከትውልድ እስከ
ትውልድ እገልጻለሁ።
[2]ምሕረትህን ለዘላለም እንደምትመሠርት፣
ታማኝነትህንም በሰማይ እንደምታጸና
እናገራለሁና።

[3]አንተም እንዲህ ብለሃል፤ “ከመረጥሁት
ጋር ኪዳን ገብቻለሁ፤
ለባሪያዬ ለዳዊት ምያለሁ፤
[4]‘ዘርህን ለዘላለም እተክላለሁ፤
ዙፋንህንም ከትውልድ እስከ ትውልድ
አጸናለሁ።’ ” ሴላ
[5]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሰማያት ድንቅ
ሥራህን፣
ታማኝነትህንም በቅዱሳን ጉባኤ
መካከል ያወድሳሉ፤
[6]በላይ በሰማያት *ከእግዚአብሔር* ጋር
ማን ሊስተካከል ይችላል?
ከሰማያውያን ፍጥረታትስ መካከል
ማን *እግዚአብሔርን* ይመስለዋል?
[7]እግዚአብሔር በቅዱሳን ጉባኤ መካከል
በጣም የሚፈራ፣
በዙሪያውም ካሉት ሁሉ በላይ እጅግ
የሚከበር ነው።
[8]የሰራዊት አምላክ *እግዚአብሔር* ሆይ፤
እንደ አንተ ያለ ማን ነው?
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ኀያል ነህ፤
ታማኝነትህም ከብቦሃል።

[9]የባሕርን ቍጣ ትቈጣጠራለህ፤
ሞገዱም ሲነሣ ጸጥ ታደርገዋለህ።
[10]አንተ ረዓብን የተሰየፈ ያህል
አደቀቅኸው፤
በብርቱ ክንድህም ጠላቶችህን
በተንሃቸው።
[11]ሰማያት የአንተ ናቸው፤ ምድርም
የአንተ ናት፤
ዓለምንና በውስጧ ያለውን ሁሉ አንተ
መሠረትህ።
[12]ሰሜንንና ደቡብን የፈጠርህ አንተ ነህ፤
ታቦርና አርሞንዔም በስምህ ሐሤት
ያደርጋሉ።
[13]አንተ ክንደ ብርቱ ነህ፤
እጅህ ኀያል ናት፤ ቀኝ እጅህም ከፍ
ከፍ ያለች ናት።

[14]ጽድቅና ፍትሕ የዙፋንህ መሠረቶች

[ኀ]3 *መቃብር* የሚሉ አሉ።
[ጠ]11 በዕብራይስጥ *አባዶን* ማለት ነው፤ *የመውደሚያ ስፍራ* ነው።

ናቸው፤
ምሕረትና ታማኝነት በፊትህ ይሄዳሉ።
15 እግዚአብሔር ሆይ፤ እልልታን
የሚያውቅ፣
በፊትህም ብርሃን የሚሄድ ሕዝብ
ምስጉን ነው።
16 ቀኑን ሙሉ በስምህ ደስ ይላቸዋል፤
በጽድቅህም ሐሤት ያደርጋሉ፤
17 አንተ የብርታታቸው ክብር ነህና፤
በሞገስህም ቀንዳችንን[ጨ] ከፍ ከፍ
አደረግህ።
18 ጋሻችን[ጳ] የእግዚአብሔር ነውና፤
ንጉሣችንም የራሱ የእስራኤል ቅዱስ
ነው።

19 በዚያን ጊዜ በራእይ ተናገርህ፤
ታማኝ ሕዝብህንም እንዲህ አልህ፤
"ኀያሉን ሰው ሥልጣን አጐናጸፍሁት፤
ከሕዝብ መካከል የተመረጠውንም ከፍ
ከፍ አደረግሁት።
20 ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፤
በተቀደሰው ዘይቴም ቀባሁት።
21 እጄ ይደግፈዋል፤
ክንዴም ያበረታዋል።
22 በጠላት አይበለጥም፤
ክፉ ሰውም አይበግረውም።
23 ባላንጣዎቹን በፊቱ አደቅቃቸዋለሁ፤
ጠላቶቹንም እቀጠቅጣለሁ።
24 ታማኝነቴና ምሕረቴ ከእርሱ ጋር
ይሆናል፤
በስሜም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል።
25 እጁን በባሕር ላይ፣
ቀኝ እጁንም በወንዞች ላይ አኖራለሁ።
26 እርሱም፣ 'አንተ አባቴ ነህ፤
አምላኬና መዳኛ ዐለቴም ነህ' ብሎ
ይጠራኛል።
27 እኔም ደግሞ በኵሬ አደርገዋለሁ፤
ከምድር ነገሥታትም በላይ ከፍ ይላል።
28 ምሕረቴንም ለዘላለም ለእርሱ
እጠብቃለሁ፤
ከእርሱ ጋር የገባሁት ኪዳንም ጸንቶ
ይኖራል።
29 የዘር ሐረጉን ለዘላለም፣
ዙፋኑንም በሰማያት ዕድሜ ልክ
አጸናለሁ።

30 "ልጆቹ ሕጌን ቢተዉ፣
ደንቤን ባይጠብቁ፣
31 ሥርዐቴን ቢጥሱ፣
ትእዛዜንም ባያከብሩ፣
32 ኀጢአታቸውን በበትር፣
በደላቸውን በጅራፍ እቀጣለሁ።
33 ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቅም፤
ታማኝነቴንም አላጓድልበትም።

89፥15 መዝ1፥1፤ 44፥3
89፥16 መዝ30፥4፤ 105፥3
89፥17 ቍ24፤ መዝ 18፥1፤75፥10፤ 92፥10፤112፥9፤ 148፥14
89፥18 መዝ18፥2፤ 47፥9፤ኢሳ16፥5፤ 33፥17፡22
89፥20 ዘፀ29፥7፤ 1ሳሙ2፥35፤ 2ሳሙ22፥51፤ 1ነገ1፥39፤ መዝ78፥70፤ ሐሥ13፥22
89፥21 ቍ13፤ መዝ 18፥35
89፥22 መሳ3፥15፤ 2ሳሙ7፥10
89፥23 2ሳሙ7፥9፤ መዝ18፥40
89፥24 2ሳሙ7፥15
89፥25 መዝ72፥8
89፥26 2ሳሙ7፥14 ፤22፥47፤መዝ62፥2፤ ኤር3፥4፤ዕብ1፥5
89፥27 ዘኍ24፥7፤ መዝ2፥6፤ቈላ1፥18፤ ራእ1፥5፤19፥16
89፥28 ቍ33-34፤ ኢሳ55፥3
89፥29 ቍ4፡36
89፥32 2ሳሙ7፥14
89፥33 2ሳሙ7፥15
89፥34 ዘኍ23፥19
89፥36 ቍ4
89፥37 ኤር33፥20-21
89፥38 1ዜና28፥9፤ መዝ44፥9፤78፥59
89፥39 ሰቆ5፥16
89፥40 መዝ80፥12 ፤ኢሳ22፥5፤ሰቆ2፥2
89፥41 መሳ2፥14፤ መዝ44፥13
89፥42 መዝ13፥2፤ 80፥6
89፥43 መዝ44፥10
89፥45 መዝ39፥5፤ 44፥15፤109፥29
89፥46 መዝ79፥5
89፥47 ዘፍ47፥9፤ ኢዮ7፥7፤መዝ39፥5፤ 1ጴጥ1፥24
89፥48 ዘፍ5፥24፤ መዝ22፥29
89፥50 መዝ69፥19
89፥51 መዝ74፥10

34 ኪዳኔን አላፈርስም፤
ከአፌ የወጣውንም አላጥፍም።
35 አንድ ጊዜ በቅድስናዬ ምያለሁና፣
ዳዊትን አልዋሽውም።
36 የዘር ሐረጉ ለዘላለም፣
ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሓይ ጸንቶ
ይኖራል፤
37 በሰማይ ታማኝ ምስክር ሆና
እንደምትኖረው፣
እንደ ጨረቃ እርሱ ለዘላለም
ይመሠረታል።" ሴላ

38 አሁን ግን ናቅኸው፤ ጣልኸውም፤
የቀባኸውንም እጅግ ተቈጣኸው።
39 ከባሪያህ ጋር የገባኸውን ኪዳን አፈረስህ፤
የክብር ዘውዱን ትቢያ ላይ ጥለህ
አቃለልኸው።
40 ቅጥሩን ሁሉ አፈራረስህ፤
ምሽጉንም ደመሰስህ።
41 ዐላፊ አግዳሚው ሁሉ ዘረፈው፤
ለጎረቤቶቹ መዘባበቻ ሆነ።
42 የጠላቶቹን ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ አደረግህ፤
ባላንጣዎቹም ሁሉ ደስ አላቸው።
43 የሰይፉን ስለት አጠፍህ፤
በጦርነትም ጊዜ አልረዳኸውም።
44 ግርማዊነቱን አጠፋህበት፤
ዙፋኑንም ከዐፈር ደባለቅኸው።
45 የወጣትነት ዘመኑን አሳጠርኸው፤
ዕፍረትንም አከናነብኸው። ሴላ

46 እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህ እስከ መቼ
ይሆናል? ራስህንስ ለዘላለም
ትሰውራለህን?
ቍጣህስ እንደ እሳት የሚነደው እስከ
መቼ ነው?
47 ዘመኔ ምን ያህል አጭር እንደ ሆነች
አስብ፤
የሰውን ልጆች እንዲያው ለከንቱ
ፈጠርሃቸው!
48 ሞትን ሳያይ ሕያው ሆኖ የሚቀር
ሰው አለን?
ራሱን ከሲኦል እጅ ማዳን የሚችል
ማን ነው? ሴላ።
49 ጌታ ሆይ፤ ለዳዊት በታማኝነትህ
የማልህለት፣
የቀድሞው ምሕረትህ የት አለ?
50 ጌታ ሆይ፤ ባሪያህ[ጳ] እንዴት እንደ
ተፌዘበት፣
የብዙ ሰዎችንም ነቀፋ እንደ ታቀፍሁ
አስብ።
51 እግዚአብሔር ሆይ፤ ጠላቶችህ
የተሣለቁበትን፣

[ጨ]17 የጥንካሬ ምልክት ነው።
[ጳ]18 ወይም *ልዑል* ማለት ነው።
[ጳ]50 *ባሮችህ* የሚሉ አሉ።

*የቀባኸውን ሰው እርምጃ የነቀፉበትን*
*ሁኔታ አስብ።*

52*እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ፤*
*አሜን፤ አሜን።*

**አራተኛ መጽሐፍ**
**ከመዝሙር 90-106**

**መዝሙር 90**

**የሰው ልጅ ሕይወት**

የእግዚአብሔር ሰው የሙሴ ጸሎት

1*እግዚአብሔር ሆይ፤*
*አንተ ከትውልድ እስከ ትውልድ*
*መጠጊያችን ሆንህልን።*

2ገና ተራሮች ሳይወለዱ፣
ምድርንና ዓለምን ከመፍጠርህ በፊት፣
አንተ ከዘላለም እስከ ዘላለም ሕያው
ነህ።

3ሰዎችን ወደ ዐፈር ትመልሳለህ፤
"የሰው ልጆች ሆይ፤ ወደ ቦታችሁ
ተመለሱ" ትላለህ፤
4ሺህ ዓመት በፊትህ፣
እንዳለፈችው እንደ ትናንት ቀን፣
እንደ ሌሊትም እርቦ ነውና።
5እንደ ጐርፍ ጠርገህ ስትወስዳቸው፣
እንደ ሕልም ይበናሉ፤
እንደ ማለዳ ሣር ታድሰው ይበቅላሉ፤
6ሣሩም ንጋት ላይ አቈጥቍጦ
ይለመልማል፤
ምሽት ላይ ጠውልጎ ይደርቃል።

7በቍጣህ አልቀናልና፤
በመዓትህም ደንግጠናል።
8በደላችንን በፊትህ፣
የተሰወረ ኀጢአታችንንም በገጽህ
ብርሃን ፊት አኖርህ።
9ዘመናችን ሁሉ በቍጣህ ዐልፎአልና፤
ዕድሜአችንንም በመቃተት እንጨርሳለን።
10የዕድሜአችን ዘመን ሰባ ዓመት፣
ቢበዛም ሰማንያ ነው፤
ከዚያ በላይ ከሆነም ድካምና መከራ
ብቻ ነው፤
ቶሎ ያልፋልና፤ እኛም ወዲያው
እንነጒዳለን።

11የቍጣህን ኀይል ማን ያውቃል?
መዓትህም የመፈራትህን ያህል
ታላቅ ነው።
12ጥበብን የተሞላ ልብ ይኖረን ዘንድ፣
ዕድሜያችንን መቍጠር አስተምረን።

13*እግዚአብሔር ሆይ፤ ተመለስ፤ ይህ*
*እስከ መቼ ይሆናል?*
*ለአገልጋዮችህም ራራላቸው።*
14በዘመናችን ሁሉ ደስ እንዲለን፣
ሐሤትም እንድናደርግ፣
ምሕረትህን በማለዳ አጥግበን።
15መከራ ባሳየኸን ዘመን መጠን፣
ክፉም ባየንባቸው ዓመታት ልክ
ደስ አሰኘን።
16ሥራህ ለአገልጋዮችህ፣
ክብርህም ለልጆቻቸው ይገለጥ።

17የጌታ የአምላካችን ሞገስ[θ] በላያችን ይሁን፤
የእጆቻችንን ሥራ ፍሬያማ
አድርግልን፤
አዎን፣ ፍሬያማ አድርግልን።

**መዝሙር 91**

**የእግዚአብሔር ጥበቃ**

1በልዑል መጠጊያ የሚኖር፣
ሁሉን በሚችል አምላክ[ፊ] ጥላ ሥር
ያድራል።
2*እግዚአብሔርን*፣ "መጠጊያዬ፣ ምሽጌ፣
የምታመንበት አምላኬ" እለዋለሁ።[T]

3እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ፣
ከአሰቃቂ ቸነፈር ያድንሃልና።
4በላባዎቹ ይጋርድሃል፤
በክንፎቹ ሥር መሸሸጊያ ታገኛለህ፤
ታማኝነቱ ጋሻና መከታ ይሆንሃል።
5የሌሊትን አስደንጋጭነት፣
በቀን የሚወረወረውንም ፍላጻ አትፈራም፤
6በጨለማ የሚያደባ ቸነፈር፣
በቀትር ረፍራፊውም አያሠጋህም።
7በአጠገብህ ሺህ፣
በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃል፤
ወደ አንተ ግን አይቀርብም።
8በዐይንህ ብቻ ትመለከታለህ፤
የክፉዎችንም መቀጣት ታያለህ።

9*እግዚአብሔርን መሸሸጊያ*፣
ልዑልንም መጠጊያህ አድርገኸዋልና።
10ክፉ ነገር አያገኝህም፤
መቅሠፍትም ወደ ድንኳንህ አይገባም፤
11በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ፣
መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና።
12እግርህ ከድንጋይ ጋር እንዳይጋጭ፣
በእጆቻቸው ወደ ላይ ያነሡሃል።
13በአንበሳና በእፉኝት ላይ ትጫማለህ፤
ደቦሉን አንበሳና ዘንዶውን ትረግጣለህ።

14"ወዶኛልና እታደገዋለሁ፤
ስሜን አውቆአልና እከልለዋለሁ።
15ይጠራኛል፤ እመልስለታለሁ፤
በመከራው ጊዜ ከእርሱ ጋር እሆናለሁ፤
አድነዋለሁ፤ አከብረዋለሁ።
16ረጅም ዕድሜን አጠግበዋለሁ፤

[θ]17 *ውበት* ለማለት ነው።
[ፊ]1 በዕብራይስጥ *ሻዳይ* ማለት ነው።
[T]2 አንዳንድ ትርጒሞች *ይላል* ይላሉ።

89፥52 መዝ41፥13፤72፥19
90፥1 ዘዳ33፥27፤ ኤፌ2፥22፤ራእ21፥3
90፥2 ዘፍ21፥33፤ ኢዮ10፥5፤15፥7፤ መዝ102፥24-27፤ ምሳ 8፥23-26፤ ኢሳ9፥6፤ 57፥15
90፥3 ዘፍ2፥7፤ ኢዮ 7፥21፤34፥15፤ 1ቆሮ15፥47
90፥4 ኢዮ10፥5፤ 2ጴጥ3፥8
90፥5 ዘፍ19፥15
90፥6 ኢሳ40፥6-8፤ ማቴ6፥30፤ያዕ1፥10
90፥8 መዝ19፥12፤ 2ቆሮ4፥2፤ኤፌ5፥12፤ ዕብ4፥13
90፥9 መዝ78፥33
90፥10 2ሳሙ19፥35፤ኢዮ5፥7፤20፥8፤ 34፥15፤ኢሳ23፥15፡ 17፤ኤር25፥11
90፥11 መዝ7፥11፤ 76፥7
90፥12 ዘዳ32፥29፤ መዝ39፥4፤139፥16፤ ምሳ16፥9፤20፥24
90፥13 ዘዳ32፥36፤ መዝ6፥3
90፥14 መዝ5፥11፤ 31፥7፤77፥8፤103፥5፤ 107፥9፤143፥8፤ 145፥16፡19
90፥16 መዝ44፥1፤ዕን3፥2
90፥17 ኢሳ26፥12
91፥1 ዘፀ33፥22፤ መዝ63፥7፤ ኢሳ49፥2፤ሰቆ4፥20
91፥2 ቈ9፤ 2ሳሙ 22፥2፡3፤ መዝ9፥9
91፥3 1ነገ8፥37፤ መዝ124፥7፤ምሳ6፥5
91፥4 ዘዳ32፥10፤ ሩት2፥12፤መዝ17፥8፤35፥2፤ኢሳ27፥3፤ 31፥5፤ዘካ12፥8
91፥5 ኢዮ5፥21
91፥8 መዝ37፥34፤ 58፥10
91፥10 ምሳ12፥21
91፥11 ዘፍ32፥1፤ መዝ34፥7፤ዕብ1፥14
91፥12 ማቴ4፥6፤ ሉቃ4፥10-11
91፥13 ዳን6፥22፤ ሉቃ10፥19
91፥15 1ሳሙ2፥30፤ዮሐ12፥26
91፥16 ዘዳ6፥2፤ መዝ21፥4፤50፥23

*ማዳኔንም አሳየዋለሁ።”*

## *መዝሙር* 92

### ጻድቅ ሰው ሲደሰት

*በሰንበት ቀን የሚዘመር መዝሙር፤ ማሕሌት*

1*እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፤*
*ልዑል ሆይ፤ ለስምህ መዘመር*
*ጥሩ ነው፤*
2*ምሕረትህን በማለዳ፣*
*ታማኝነትህንም በሌሊት ማወጅ*
*መልካም ነው፤*
3*ዐሥር አውታር ባለው በገና፣*
*በመሰንቆም ቅኝት ታጅቦ ማወጅ*
*ጥሩ ነው።*

4*እግዚአብሔር ሆይ፤ በሥራህ ስለ*
*ተደሰትሁ፣*
*ስለ እጅህ ሥራ በደስታ እዘምራለሁ።*
5*እግዚአብሔር ሆይ፤ ሥራህ እንዴት*
*ታላቅ ነው!*
*ሐሳብህስ ምን ያህል ጥልቅ ነው!*
6*ደነዝ ሰው ይህን አያውቅም፤*
*ነኁላላም አያስተውለውም።*
7*ክፉዎች እንደ ሣር ቢበቅሉ፣*
*ክፉ አድራጊዎች ቢለመልሙ፣*
*ለዘላለሙ ይጠፋሉ፤*

8*እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን*
*ለዘላለም ልዑል ነህ።*

9*ጠላቶችህ እግዚአብሔር ሆይ፤*
*ጠላቶችህ ይጠፋሉና፤*
*ክፉ አድራጊዎችም ሁሉ ይበተናሉ።*
10*የእኔን ቀንድ ግን እንደ አውራሪስ*
*ቀንድ*[ሀ] *ከፍ ከፍ አደረግኸው፤*
*በለጋ ዘይትም አረሰረስኸኝ።*
11*ዐይኖቼ የባላንጦቼን ውድቀት አዩ፤*
*ጆሮዎቼም የክፉ ጠላቶቼን ድቀት ሰሙ።*
12*ጻድቃን እንደ ዘንባባ ይንሰራፋሉ፤*
*እንደ ሊባኖስ ዝግባም ይንዠረገጋሉ።*
13*በእግዚአብሔር ቤት ተተክለዋል፤*
*በአምላካችንም አደባባይ ይንሰራፋሉ።*
14*ባረጁ ጊዜ እንኳ ያፈራሉ፤*
*እንደ ለመለሙና እንደ ጠነከሩም*
*ይኖራሉ።*
15*“እግዚአብሔር ትክክለኛ ነው፤*
*እርሱ ዐለቴ ነው፤ በእርሱ ዘንድ እንከን*
*የለም” ይላሉ።*

## *መዝሙር* 93

### የእግዚአብሔር ግርማ

1*እግዚአብሔር ነገሠ፤ ግርማንም*
*ተጐናጸፈ፤*
*እግዚአብሔር ግርማን ለበሰ፤*
*ብርታትንም ታጠቀ፤*
*ዓለም እንዳትናወጥ ጸንታለች፤*
*ማንም አይነቀንቃትም።*
2*ዙፋንህ ከጥንት ጀምሮ የጸና ነው፤*
*አንተም ከዘላለም እስከ ዘላለም አለህ።*

3*እግዚአብሔር ሆይ፤ ወንዞች ከፍ አደረጉ፤*
*ወንዞች ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ፤*
*ወንዞች የሚያስገመግም ማዕበላቸውን*
*ከፍ አደረጉ።*
4*ከብዙ ውሆች ድምፅ ይልቅ፣*
*ከባሕርም ሞገድ ይልቅ፣*
*ከፍ ብሎ ያለው እግዚአብሔር ኀያል*
*ነው።*

5*ሥርዐትህ የጸና ነው፤*
*እግዚአብሔር ሆይ፤ እስከ ዘላለሙ፣*
*ቤትህ በቅድስና ይዋባል።*

## *መዝሙር* 94

### የእግዚአብሔር ፍትሕ

1*የበቀል አምላክ፣ አንተ እግዚአብሔር ሆይ፤*
*የበቀል አምላክ ሆይ፤ ደምቀህ ተገለጥ።*
2*አንተ የምድር ዳኛ ሆይ፤ ተነሥ፤*
*ለትዕቢተኞች የእጃቸውን ስጣቸው።*
3*ክፉዎች እስከ መቼ እግዚአብሔር ሆይ፤*
*ክፉዎች እስከ መቼ ይፈነጫሉ?*

4*የእብሪት ቃላት ያዥጐደጕዳሉ፤*
*ክፉ አድራጊዎች ሁሉ ጕራ ይነዛሉ።*

5*እግዚአብሔር ሆይ፤ ሕዝብህን አደቀቁ፤*
*ርስትህንም አስጨነቁ።*
6*መበለቲቱንና መጻተኛውን ገደሉ፤*
*የድኻ አደጉንም ነፍስ አጠፉ።*
7*እነርሱም “እግዚአብሔር አያይም፤*
*የያዕቆብም አምላክ አያስተውልም” አሉ።*

8*እናንት በሕዝቡ መካከል ያላችሁ ደነዞች፤*
*ልብ በሉ፤*
*እናንት ቂሎች፤ ጥበበኞች የምትሆኑት*
*መቼ ነው?*
9*ጆሮን የተከለው እርሱ አይሰማምን?*
*ዐይንንስ የሠራ እርሱ አያይምን?*
10*ሕዝቦችን በተግሣጽ ወደ መንገድ*
*የሚመልስ፣*
*ዕውቀትንስ ለሰው ልጆች የሚያስተምር*
*አይቀጣምን?*
11*እግዚአብሔር የሰው ሐሳብ መና፣*
*ከንቱም እንደ ሆነ ያውቃል።*

12*እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ*
*የምትገሥጸው፣*
*ከሕግህም የምታስተምረው ሰው ምስጉን*
*ነው።*

92፥1 መዝ9፥2፤ 27፥6፤135፥3፤147፥1
92፥2 መዝ55፥17
92፥3 1ሳሙ10፥5፤ ነህ12፥27፤መዝ33፥2፤ 71፥22፤81፥2
92፥4 መዝ5፥11፤ 8፥6፤27፥6፤111፥7፤ 143፥5
92፥5 ኢዮ36፥24፤ መዝ40፥5፤139፥17፤ ኢሳ28፥29፤31፥2፤ ሮሜ11፥33፤ራእ15፥3
92፥6 መዝ73፥22
92፥7 መዝ37፥2
92፥9 መዝ45፥5፤ 68፥1፤89፥10
92፥10 መዝ23፥5፤ 29፥6፤89፥17
92፥11 መዝ54፥7፤ 91፥8
92፥12 መዝ1፥3፤ 52፥8፤72፥7፤ኤር 17፥8፤ሆሴ14፥6
92፥13 መዝ135፥2
92፥14 መዝ1፥3፤ ዮሐ15፥2
92፥15 ኢዮ34፥10
93፥1 1ዜና16፥30፡ 31፤ኢዮ40፥10፤መዝ 21፥5፤24፥2፤65፥6፤ 78፥69፤96፥10፤ 97፥1፤119፥90
93፥2 ዘፍ21፥33፤ 2ሳሙ7፥16
93፥3 ኢዮ9፥8፤መዝ 46፥3፤96፥11፤98፥7፤ 107፥25፡29፤ኢሳ5፥30 ፤17፥12-13፤51፥15፤ ኤር6፥23፤31፥35፤ ዕን3፥10
93፥4 ነህ9፥32፤ኢዮ 9፥4፤መዝ18፥4፤65፥7 ፤ኤር6፥23፤ዮና1፥15
93፥5 መዝ5፥7፤ 23፥6፤29፥2፤96፥9
94፥1 ዘፍ4፥24፤ ዘዳ33፥2፤መዝ80፥1፤ ሮሜ12፥19
94፥2 ዘፍ18፥25፤ ዘኍ10፥35፤ መዝ31፥23፤ ዕብ12፥23፤ያዕ5፥9
94፥3 መዝ13፥2
94፥4 መዝ52፥1፤ ኤር43፥2
94፥5 መዝ28፥9፤ 44፥2፤74፥8፤ ኢሳ3፥15፤ኤር8፥21
94፥6 ዘዳ10፥18፤ 24፥19፤ኢሳ1፥17
94፥7 ዘፍ24፥12፤ ኢዮ22፥14
94፥8 ዘዳ32፥6፤ መዝ73፥22
94፥9 ዘፀ4፥11፤ ምሳ20፥12
94፥10 ዘፀ35፥34፤ ኢዮ35፥11፤መዝ 39፥11፤ኢሳ28፥26
94፥11 መዝ139፥2 ፤ምሳ15፥26፤ማቴ9፥4፤1ቆሮ3፥20
94፥12 ዘዳ8፥3፤1ሳሙ12፥23፤ ኢዮ5፥17፤1ቆሮ11፥32፤ዕብ12፥5

[ሀ] 10 ጥንካሬን የሚያመለክት ነው።

[13]ለኀጢአተኞች ጒድጓድ እስኪማስላቸው
ድረስ፣
እርሱን ከመከራ ታሳርፈዋለህ።
[14]እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልምና፤
ርስቱንም አይተውም።
[15]ፍርድ ተመልሶ በጽድቅ አሠራር ላይ
ይመሠረታል፤
ልባቸውም ቀና የሆነ ሁሉ
ይከተሉታል።
[16]ክፉዎችን የሚቋቋምልኝ ማን ነው?
ከክፉ አድራጊዎችስ ጋር የሚሟገትልኝ
ማን ነው?
[17]እግዚአብሔር ረዳቴ ባይሆን ኖሮ፣
ነፍሴ ወደ ዝምታው ዓለም ፈጥና
በወረደች ነበር።
[18]እኔ፣ "እግሬ አዳለጠኝ" ባልሁ ጊዜ፣
እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ ደግፎ
ያዘኝ።
[19]የውስጤ ጭንቀት በበዛ መጠን፣
ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኛት።
[20]ዐመፃን ሕጋዊ የሚያደርግ፣
የጥፋት ዙፋን ከአንተ ጋር ሊያብር
ይችላልን?
[21]በጻድቁ ላይ ተሰልፈው ይወጣሉ፤
በንጹሑም ላይ ሞት ይፈርዳሉ።
[22]ለእኔ ግን እግዚአብሔር ምሽግ፣
አምላኬም መጠጊያ ዐለት ሆኖኛል።
[23]በደላቸውን ወደ ራሳቸው ይመልሳል፤
በክፋታቸውም ያጠፋቸዋል፤
እግዚአብሔር አምላካችን ይደመስሳቸዋል።

## መዝሙር 95

### የየዕለቱ መዝሙር

[1]ኑ፤ ደስ እያለን ለእግዚአብሔር
እንዘምር፤
በድነታችንም ዐለት እልል እንበል።
[2]ምስጋና ይዘን ፊቱ እንቅረብ፤
በዝማሬም እናወድሰው።
[3]እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ታላቅ
ንጉሥ ነው።
[4]የምድር ጥልቆች በእጁ ናቸው፤
የተራራ ጫፎችም የእርሱ ናቸው።
[5]እርሱ ፈጥሮአታልና፣ ባሕር የእርሱ ናት፤
እጁም የብስን አበጀ።
[6]ኑ፤ እናምልከው፤ እንስገድለትም፤
በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ፊት
እንንበርከክ፤
[7]እርሱ አምላካችን ነውና፤
እኛም በእጁ ጥበቃ ሥር ያለን በጎቹ፣
የመሰማሪያውም ሕዝብ ነን።
ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣
[8]በምድረ በዳ በነበራችሁበት ቀን
በማሳህ፣[^]
በመሪባም[ሐ] እንዳደረጋችሁት፣
ልባችሁን አታደንድኑ።
[9]ሥራዬን ቢያዩም፣
አባቶቻችሁ በዚያ ፈተኑኝ፤
ተፈታተኑኝም።
[10]ያን ትውልድ አርባ ዓመት ሙሉ
ተቈጣሁት፤
እኔም፣ "ልቡ የሸፈተ ሕዝብ ነው፤
መንገዴንም አላወቀም" አልሁ።
[11]ስለዚህ፣ "ፈጽሞ ወደ ዕረፍቴ
አይገቡም" ብዬ፣
በቍጣዬ ማልሁ።

## መዝሙር 96

### እግዚአብሔር፤ ንጉሥም ዳኛም

96፥1-13 ተጓ ምብ-1ዜና16፥23-33

[1]ለእግዚአብሔር አዲስ ዝማሬ ዘምሩ፤
ምድር ሁሉ፤ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።
[2]ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ ስሙንም ባርኩ፤
ማዳኑንም ነጋ ጠባ አውሩ።
[3]ክብሩን በሕዝቦች መካከል፣
ድንቅ ሥራውንም በሰዎች ሁሉ ፊት
ተናገሩ።
[4]እግዚአብሔር ታላቅ ነውና፤ ውዳሴም
የሚገባው ነው፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ ሊፈራ
ይገባዋል።
[5]የሕዝብ አማልክት ሁሉ ጣዖታት ናቸው፤
እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።
[6]ክብርና ግርማ በፊቱ ናቸው፤
ብርታትና ውበትም በመቅደሱ ውስጥ
አሉ።
[7]የሕዝቦች ወገኖች ሆይ፤ ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
ክብርንና ብርታትን ለእግዚአብሔር
ስጡ።
[8]ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር
ስጡ፤
ቍርባንን ይዛችሁ ወደ አደባባዩ ግቡ።
[9]በተቀደሰ ውበት ለእግዚአብሔር ስገዱ፤
ምድር ሁሉ፤ በፊቱ ተንቀጥቀጡ።
[10]በሕዝቦች መካከል፣ "እግዚአብሔር
ነገሠ" በሉ፤

**94፥13** መዝ7፥15፤55፥23፤86፥7 **94፥14** ዘዳ31፥6፤መዝ37፥28፤ሮሜ11፥2 **94፥15** መዝ7፥10፤11፥2፤36፥10፤97፥2 **94፥16** ዘኍ10፥35፤መዝ17፥13፤59፥2፤ኢሳ14፥22 **94፥17** መዝ31፥17፤124፥2 **94፥18** ዘዳ32፥35፤ኢዮ12፥5 **94፥19** ኢዮ6፥10፤መክ11፥10 **94፥20** መዝ58፥2፤ኤር22፥30፤36፥30 **94፥21** ዘፍ18፥23፤መዝ56፥6፤106፥38፤ምሳ17፥15፡26፤28፥21፤ኢሳ5፥20፡23፤ማቴ27፥4 **94፥22** 2ሳሙ22፥3፤መዝ18፥2፤61፥2 **94፥23** ዘፀ32፥34፤መዝ9፥5፤37፥35፤54፥5፤145፥20 **95፥1** 2ሳሙ22፥47፤መዝ5፥11፤34፥11፤80፥2፤81፥1፤ኢሳ44፥23፤ሶፎ3፥14 **95፥2** መዝ42፥4፤81፥2፤100፥2፤ሚክ6፥6፤ኤፌ5፥19 **95፥3** መዝ47፥2፤48፥1፤86፥10፤96፥4፤97፥9፤145፥3፤147፥5 **95፥4** መዝ63፥9 **95፥5** ዘፍ1፥9፤መዝ 146፥6 **95፥6** 2ሳሙ12፥16፤2ዜና6፥13፤መዝ22፥29፤100፥3፤149፥2፤ኢሳ17፥7፤54፥5፤ዳን6፥10-11፤ሆሴ8፥14፤ፊል2፥10 **95፥7** መዝ74፥1 **95፥8** ዘፀ17፥7፤ዘዳ33፥8፤መዝ78፥40፤ማር10፥5፤ዕብ3፥8፡15፤4፥7 **95፥9** ዘኍ14፥22፤1ቆሮ10፥9 **95፥10** ዘፀ16፥35፤ዘኍ14፥34፤ዘዳ8፥6፤መዝ58፥3፤119፥67፡176፤ምሳ12፥26፤16፥29፤ኢሳ53፥6፤ኤር31፥19፤50፥6፤ሕዝ34፥6፤ ሐሥ7፥36፤ዕብ3፥17 **95፥11** ዘኍ14፥23፤ዘዳ1፥35፤ዕብ3፥7-11፤4፥3 **96፥1** መዝ30፥4፤33፥3፤40፥3፤98፥1፤144፥9፤149፥1፤ኢሳ 42፥10፤ራእ5፥9 **96፥2** መዝ27፥1፤68፥4፤71፥15 **96፥3** መዝ8፥1፤71፥17፤ራእ15፥3

**96፥4** ዘዳ28፥58፤1ዜና16፥25፤መዝ48፥1፤89፥7፤95፥3 **96፥5** ዘፍ1፥1፤ ዘሌ19፥4፤2ዜና2፥12 **96፥6** መዝ21፥5፤29፥1፤89፥17 **96፥7** መዝ22፥27፤29፥1 **96፥8** መዝ45፥12፤51፥19፤65፥4፤72፥10፤84፥10፤92፥13፤100፥4 **96፥9** ዘፀ15፥14፤23፥25፤መዝ33፥8፤93፥5፤114፥7፤ዮና1፥9 **96፥10** መዝ24፥2፤58፥11፤67፥4፤78፥69፤93፥1፤97፥1፤98፥9፤119፥90

[^]8 ማሳህ *ፈተና* ማለት ነው።
[ሐ]8 መሪባ *ጠብ* ማለት ነው።

ዓለም በጽኑ ተመሥርታለች፤
አትናወጥም፤
እርሱ ለሕዝቦች በእኩልነት ይፈርዳል።
11 ሰማያት ደስ ይበላቸው፤ ምድርም
ሐሤት ታድርግ፤
ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ ያስተጋባ፤
12 መስኩና በላዩ ያለው ሁሉ ይፈንጥዝ፤
ያን ጊዜ የዱር ዛፎች ሁሉ በደስታ
ይዘምራሉ፤
13 እርሱ ይመጣልና *በእግዚአብሔር* ፊት
ይዘምራሉ፤
በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣል፤
በዓለም ላይ በጽድቅ፣
በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

### *መዝሙር* 97

## የእግዚአብሔር ድል አድራጊነት

1 *እግዚአብሔር ነገሠ*፤ ምድር ደስ ይበላት፤
በሩቅ ያሉ የባሕር ጠረፎች ሐሤት
ያድርጉ።
2 ደመናና ጥቅጥቅ ያለ ጭጋግ በዙሪያው
አለ፤
ጽድቅና ፍትሕ የዙፋኑ መሠረት
ናቸው።
3 እሳት በፊቱ ይሄዳል፤
በዙሪያው ያሉትንም ጠላቶቹን
ይፈጃል።
4 መብረቁ ዓለምን አበራ፤
ምድርም አይታ ተንቀጠቀጠች።
5 ተራሮች *በእግዚአብሔር* ፊት፣
በምድርም ሁሉ ጌታ ፊት እንደ ሰም
ቀለጡ።
6 ሰማያት ጽድቁን ያውጃሉ፤
ሕዝቦችም ሁሉ ክብሩን ያያሉ።
7 ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ፣
በጣዖታትም የሚመኩ ሁሉ ይፈሩ፤
እናንተ አማልክት ሁሉ፤ ለእርሱ ስገዱ።
8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስለ ፍርድህ፣
ጽዮን ሰምታ ደስ አላት፤
የይሁዳም ሴት ልጆች ሐሤት አደረጉ።
9 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ በምድር
ሁሉ ላይ ልዑል ነህና፤
ከአማልክትም ሁሉ በላይ እጅግ ከፍ
ያልህ ነህ።
10 *እግዚአብሔርን* የምትወዱ ክፋትን
ጥሉ፤
እርሱ የታማኞቹን ነፍስ ይጠብቃልና፤
ከዐመፀኞችም እጅ ይታደጋቸዋል።
11 ብርሃን ለጻድቃን፣
ሐሤትም ልባቸው ለቀና ወጣ።
12 እናንተ ጻድቃን *በእግዚአብሔር* ደስ
ይበላችሁ፤
ቅዱስ ስሙንም አመስግኑ።

### *መዝሙር* 98

## የዓለም ሁሉ ዳኛ

*መዝሙር*

1 *ለእግዚአብሔር* አዲስ ዝማሬ አቅርቡ፤
እርሱ ድንቅ ነገሮችን አድርጎአልና፤
ቀኝ እጁ፣ ቅዱስ ክንዱም፣
ማዳንን አድርገውለታል።
2 *እግዚአብሔር* ማዳኑን አሳወቀ፤
ጽድቁንም በሕዝቦች ፊት ገለጠ።
3 ለእስራኤል ቤት ምሕረቱን፣
ታማኝነቱንም አሰበ፤
የምድር ዳርቻዎችም ሁሉ፣
የአምላካችንን ማዳን አዩ።
4 ምድር ሁሉ *ለእግዚአብሔር* እልል በሉ፤
ውዳሴን አፍልቁ፤ በደስታና በዝማሬ
አመስግኑ፤
5 *ለእግዚአብሔር* በገና ደርድሩለት፤
በበገናና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩለት፤
6 በእንቢልታና በመለከት ድምፅ፣
በንጉሡ *በእግዚአብሔር* ፊት እልል
በሉ።
7 ባሕርና በውስጧ ያለው ሁሉ፣
ዓለምና የሚኖሩባትም ሁሉ ያስገምግሙ።
8 ወንዞች በእጃቸው ያጨብጭቡ፤
ተራሮችም በአንድነት ይዘምሩ፤
9 እነዚህ *በእግዚአብሔር* ፊት ይዘምሩ፤
እርሱ በምድር ላይ ሊፈርድ
ይመጣልና፤
በዓለም ላይ በጽድቅ፣
በሕዝቦችም ላይ በእውነት ይበይናል።

### *መዝሙር* 99

## ጻድቅና ቅዱስ አምላክ

1 *እግዚአብሔር ነገሠ*፤
ሕዝቦች ይንቀጥቀጡ፤
በኪሩቤል ላይ በዙፋን ተቀምጦአል፤
ምድር ትናወጥ።
2 *እግዚአብሔር* በጽዮን ታላቅ ነው፤
ከሕዝቦችም ሁሉ በላይ ከፍ ከፍ
ብሎአል።
3 ታላቁንና አስፈሪውን ስምህን ይወድሱ፤
እርሱ ቅዱስ ነው።
4 ፍትሕን የምትወድ፣ ኀያል ንጉሥ ሆይ፤
አንተ ትክክለኛነትን መሠረትህ፤
ፍትሕንና ቅንነትንም፣
ለያዕቆብ አደረግህ።

**96፥11** መዝ97፥1፤ ኢሳ49፥13፤ራእ12፥12 **96፥12** መዝ65፥13፤ኢሳ44፥23፤55፥12፤ሕዝ17፥24 **96፥13** መዝ7፥11፤86፥11፤ሐሥ17፥31፤ራእ19፥11 **97፥1** ዘፀ15፥18፤ አስ10፥1፤መዝ93፥1፤96፥10፡11፤99፥1፤ ኢሳ 24፥23፤52፥7 **97፥2** ዘፀ19፥9፤ ኢዮ22፥14፤መዝ89፥14 **97፥3** 2ሳሙ22፥9፤ ኢሳ9፥19፤ዳን7፥10፤ ኢል1፥19፤2፥3፤ዕን3፥5 **97፥4** 2ሳሙ22፥8፤ ኢዮ36፥30፤ መዝ18፥7፤104፥32፤ ራእ 6፥12 **97፥5** ኢሱ3፥11፤ መዝ22፥14፤46፥2፡6 **97፥6** መዝ19፥1፤ 50፥6፤98፥2 **97፥7** ዘፀ12፥12፤ ዘሌ 26፥1፤ዘዳ5፥8፤ መዝ16፥4፤ኢሳ42፥17፤ ኤር10፥14፤ዕብ1፥6 **97፥8** መዝ9፥2፤ 48፥11 **97፥9** ኢዮ34፥29፤ መዝ7፥8፤47፥9 **97፥10** ኢዮ28፥28፤ መዝ31፥23፤34፥7፤37፥28፡40፤145፥20፤ምሳ2፥8፤ኤር15፥21፤20፥13፤ዳን3፥28፤6፥16፤ አሞ5፥15፤ሮሜ12፥9 **97፥11** ኢዮ22፥28፤ መዝ7፥10፤11፥5 **97፥12** ኢዮ22፥19፤ ዘፀ3፥15፤መዝ99፥3፤ 104፥34፤ኢሳ41፥16፤ ፊል4፥4 **98፥1** ዘፀ15፥1፡6፤ ኢሱ4፥24፤ኢዮ40፥9፤ መዝ30፥4፤44፥3፤96፥1፡3፤ኢሳ12፥5፤51፥9፤52፥10፤53፥1፤59፥16፤63፥5፤ሉቃ1፥51 **98፥2** መዝ67፥2፤ 97፥6፤ኢሳ52፥10፤ ሉቃ3፥6 **98፥3** ዘፍ49፥10፤ 1ዜና16፥15፤መዝ 48፥10፤50፥23 **98፥4** መዝ20፥5፤ ኢሳ12፥6፤44፥23፤ 52፥9፤54፥1፤55፥12 **98፥5** መዝ33፥2፤ 92፥3፤147፥7፤ ኢሳ 51፥3 **98፥6** ዘፀ19፥13፤ዘኍ 10፥2፤2ሳሙ6፥15፤ መዝ2፥6፤20፥5፤47፥7፤100፥1፤ኢሳ12፥6 **98፥7** መዝ24፥1፤ 93፥3 **98፥8** 2ነገ11፥12፤ መዝ148፥9፤ ኢሳ44፥23፤55፥12

**98፥9** መዝ96፥10 **99፥1** ዘፀ15፥14፤25፥22፤2ሳሙ6፥2፤1ዜና16፥30፡31፤መዝ97፥1 **99፥2** ዘፀ15፥1፤መዝ2፥6፤46፥10፤48፥1፤97፥9፤113፥4፤148፥13 **99፥3** ዘፀ15፥11፤ዘሌ11፥44፤መዝ30፥4፤33፥21፤76፥1፤97፥12፤103፥1፤106፥47፤111፥10፤145፥21፤148፥5፤ራእ4፥8 **99፥4** ዘፍ18፥19፤1ነገ10፥9፤መዝ2፥6፤98፥9፤ራእ15፥3

5አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
በእግሩ መርገጫ ስገዱ፤
እርሱ ቅዱስ ነውና ።
6ሙሴና አሮን ካህናቱ ከሆኑት መካከል
ነበሩ፤
ሳሙኤልም ስሙን ከጠሩት መካከል
አንዱ ነበረ፤
እነርሱ ወደ እግዚአብሔር ተጣሩ፤
እርሱም መለሰላቸው።
7ከደመና ዐምድ ውስጥ ተናገራቸው፤
እነርሱም ሥርዐቱንና የሰጣቸውን
ድንጋጌ ጠበቁ።
8እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ፤
አንተ መለስህላቸው፤
ጥፋታቸውን[መ] ብትበቀልም እንኳ፣
አንተ ይቅር የምትላቸው አምላክ ነህ።
9አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
በቅዱስ ተራራውም ላይ ስገዱ፤
አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና።

## መዝሙር 100

### እግዚአብሔርን ለማመስገን የቀረበ ግብዣ

*የምስጋና መዝሙር*

1ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፤
2እግዚአብሔርን በደስታ አገልግሉት፤
በፍስሓ ዝማሬ ፊቱ ቅረቡ።
3እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ዕወቁ፤
እርሱ ፈጠረን፤ እኛም የእርሱ ነን፤
እኛ ሕዝቡ የማሰማሪያው በጎች ነን።
4በምስጋና ወደ ደጆቹ፣
በውዳሴም ወደ አደባባዮቹ ግቡ፤
አመስግኑት፤ ስሙንም ባርኩ፤
5እግዚአብሔር ቸር፣ ምሕረቱም ለዘላለም
ነውና፤
ታማኝነቱም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ነው።

## መዝሙር 101

### ትክክለኛ አስተዳደር

*የዳዊት መዝሙር*

1ስለ ምሕረትና ስለ ፍትሕ እዘምራለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ ለአንተ በምስጋና
እቀኛለሁ።
2እንከን የማይገኝባትን መንገድ አጥብቄ
እይዛለሁ፤
አንተ ወደ እኔ የምትመጣው መቼ ነው?
በቤቴ ውስጥ፣
በንጹሕ ልብ እመላለሳለሁ።
3በዐይኔ ፊት፣
ክፉ ነገር አላኖርም።
የከሓዲዎችን ሥራ እጠላለሁ፤
ከእኔም ጋር አይጣበቅም።
4ጠማማ ልብ ከእኔ ይርቃል፤
ለክፋትም ዕውቅና አልሰጥም።
5ባልንጀራውን በስውር የሚያማውን፣
አጠፋዋለሁ፤
ትዕቢተኛ ዐይንና ኵራተኛ ልብ ያለውን፣
እርሱን አልታገሠውም።
6ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ፣
ዐይኖቼ በምድሪቱ ታማኞች ላይ ናቸው፤
በንጽሕና መንገድ የሚሄድ፣
እርሱ ያገለግለኛል።
7አታላይ የሆነ ማንም ሰው፣
በቤቴ ውስጥ አይኖርም፤
ሐሰትን የሚናገር፣
በፊቴ ቀና ብሎ አይቆምም።
8በምድሪቱ ላይ ያሉትን ክፉዎች ሁሉ፣
በየማለዳው አጠፋቸዋለሁ፤
ክፉ አድራጊዎችንም ሁሉ፣
ከእግዚአብሔር ከተማ
እደመስሳቸዋለሁ።

## መዝሙር 102

### በክፉ ጊዜ የቀረበ ጸሎት

*ባዘነና ልመናውን በእግዚአብሔር ፊት ባፈሰሰ ጊዜ፣
የተጨነቀ ሰው ጸሎት*

1እግዚአብሔር ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ጩኸቴም ወደ አንተ ይድረስ።
2በመከራዬ ቀን፣
ፊትህን ከእኔ አትሰውር፤
ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፤
በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ መልስልኝ።
3ዘመኔ እንደ ጢስ ተኖ አልቆአልና፤
ዐጥንቶቼም እንደ ማንደጃ ግለዋል።
4ልቤ ዋግ እንደ መታው ሣር ደርቆአል፤
እህል መብላትም ዘንግቻለሁ።
5ከጩኸቴ ድምፅ የተነሣ፣
ዐጥንቴ ከቈዳዬ ጋር ተጣበቀ።
6የምድረ በዳ እርኩም መሰልሁ፤
በፍርስራሽ መካከል እንዳለ ጉጉት
ሆንሁ።
7ያለ እንቅልፍ አድራለሁ፤
በቤቱ ጉልላት ላይ እንዳለ ብቸኛ ወፍ
ሆንሁ።
8ጠላቶቼ ቀኑን ሙሉ ይዘልፉኛል፤
የሚያክፋፉኝም ስሜን እንደ ርግማን
ቈጥረውታል።
9ዐመድ እንደ እህል ቅሜአለሁና፤
መጠጤንም ከእንባ ጋር ቀላቅያለሁ።

[መ]8 ወይም *የተፈጸመባቸውን በደል* ማለት ነው።

99፥5 ዘፀ15፥2
99፥6 ዘፀ24፥6፡28፥1፤ 1ሳሙ7፥5፤መዝ4፥3፤ 91፥15
99፥7 ዘፀ13፥21፤ 19፥9፤ዘኍ11፥25
99፥8 ዘፀ22፥27፤ ዘሌ26፥18፤ዘኍ14፥20
100፥1 መዝ98፥6
100፥2 ዘዳ10፥12፤ መዝ95፥2
100፥3 2ሳሙ24፥17 ፤1ነገ18፥2፤ኢዮ10፥3 ፤መዝ46፥10፤74፥1፤ 79፥13፤ኢሳ19፥25፤ 63፥8፥17-19፥64፥9
100፥4 መዝ42፥4፤ 96፥8፤116፥17
100፥5 1ዜና16፥34 ፤ዕዝ3፥11፤ መዝ 106፥1፤ 108፥4፤119፥90
101፥1 መዝ33፥1፤ 51፥14፤89፥1፤145፥7
101፥2 ዘፍ17፥1፤ 1ነገ3፥14፤ፊል1፥10
101፥3 መዝ5፥5፤ ኤር16፥18፤ ሕዝ 11፥21፤ ሆሴ9፥10
101፥4 ምሳ3፥32፤ 6፥16-19፤11፥20
101፥5 ዘፀ20፥16፤ ዘሌ19፥16፤መዝ10፥5
101፥6 ቍ2፤ መዝ 119፥1
101፥8 2ሳሙ3፥39 ፤መዝ5፥3፤46፥4፤ 75፥10፤118፥10-12፤ ኤር21፥12
102፥1 ዘፀ2፥23፤ መዝ4፥1
102፥2 2ነገ19፥16፤ መዝ22፥24፤31፥2፤ 88፥2
102፥3 መዝ37፥20 ፤ሰቆ1፥13፤ያዕ4፥14
102፥4 1ሳሙ1፥7፤ ዕዝ10፥6፤ኢዮ33፥20 ፤መዝ37፥2፤90፥5-6
102፥5 መዝ6፥6
102፥6 ዘዳ14፥15-17፤ኢዮ30፥29፤ ኢሳ34፥11፤ሶፎ2፥14
102፥7 መዝ38፥11 ፤77፥4
102፥8 ዘፀ22፥28፤ መዝ31፥11፤42፥10፤ ኢሳ65፥15፤ኤር24፥9 ፤25፥18፤42፥18፤ 44፥12፤ሕዝ14፥8፤ዘካ 8፥13፤ሉቃ22፥63-65 ፤23፥35-37
102፥9 መዝ6፥6፤ 42፥3፤80፥5፤ ኢሳ 44፥20

[10]ከቍጣህና ከመዓትህ የተነሣ፣
ወደ ላይ አንሥተኸኝ የነበርሁትን
መልሰህ ጣልኸኝ።
[11]ዘመኖቼ እንደ ምሽት ጥላ ናቸው፤
እኔም እንደ ሣር ደርቄአለሁ።
[12]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተ ግን ለዘላለም
በዙፋንህ ተቀምጠሃል፤
ስምህም ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራል።
[13]ትነሣለህ፤ ጽዮንንም በርኅራኄ ዐይን
ታያለህ፤
ለእርሷ በጎነትህን የምታሳይበት ዘመን
ነውና፤
የተወሰነውም ጊዜ ደርሶአል።
[14]አገልጋዮችህ በድንጋዮቿ ደስ ይሰኛሉ፤
ለዐፈሯም ይሳሳሉ።
[15]ሕዝቦች *የእግዚአብሔርን* ስም፣
የምድርም ነገሥታት ሁሉ ክብርህን
ይፈራሉ።
[16]*እግዚአብሔር* ጽዮንን መልሶ ይሠራታልና፤
በክብሩም ይገለጣል።
[17]እርሱ ወደ ችግረኞች ጸሎት
ይመለከታል፤
ልመናቸውንም አይንቅም።
[18]ወደ ፊት የሚፈጠር ሕዝብ *እግዚ
አብሔርን* ያወድስ ዘንድ፣
ይህ ለመጪው ትውልድ እንዲህ
ተብሎ ይጻፍ፤
[19]"*እግዚአብሔር* በከፍታ ላይ ካለው
መቅደሱ ወደ ታች
ተመልክቶአልና፤
ከሰማይም ሆኖ ምድርን አይቶአል፤
[20]ይኸውም የእስረኞችን ጩኸት ይሰማ
ዘንድ፣
ሞት የተፈረደባቸውንም ያድን ዘንድ
ነው።"
[21]ስለዚህ *የእግዚአብሔር* ስም በጽዮን፣
ምስጋናውም በኢየሩሳሌም ይታወጃል፤
[22]ይህም፣ ሕዝቦችና መንግሥታት፣
*እግዚአብሔርን* ለማምለክ በአንድነት
ሲሰበሰቡ ይሆናል።
[23]ብርታቴን መንገድ ላይ ቀጨው፤[ሠ]
ዕድሜዬንም ባጭሩ አስቀረው።
[24]እኔም እንዲህ አልሁ፤
"አምላኬ ሆይ፤ በዘመኔ እኩሌታ
አትውሰደኝ፤
ዘመናትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ይኖራሉ።
[25]አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፤
ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው።
[26]እነርሱ ይጠፋሉ፤ አንተ ግን ጸንተህ
ትኖራለህ፤

102፥10 መዝ7፥11፤ 38፥3
102፥11 1ዜና29፥15፤ኢዮ8፥12፤14፥2፤ መዝ39፥6፤ያዕ1፥10
102፥12 ዘፀ3፥15፤ 15፥18፤መዝ135፥13፤ ኢሳ55፥13፤63፥12
102፥13 ዘፀ13፥10፤ ዘዳ32፥36፤1ነገ3፥26፤ መዝ44፥26፤77፥7፤ 119፥126፤ኢሳ54፥8 ፤60፥10፤ዳን8፥19፤ ዘካ10፥6፤ሐሥ1፥7
102፥15 1ነገ8፥43፤ መዝ67፥7፤76፥12፤ 138፥4፤148፥11፤ ኢሳ 2፥2
102፥16 መዝ8፥1፤ 51፥18፤ኢሳ60፥1-2
102፥17 1ነገ8፥29፤ መዝ4፥1፤6፥9
102፥18 መዝ22፥31 ፤ሮሜ4፥24
102፥19 መዝ53፥2
102፥20 መዝ68፥6 ፤ሉቃ4፥19
102፥21 መዝ9፥14 ፤22፥22
102፥22 መዝ22፥27 ፤ኢሳ49፥22-23፤ ዘካ8፥20-23
102፥23 መዝ39፥5
102፥24 ዘፍ21፥33፤ ኢዮ36፥26፤ መዝ90፥2
102፥25 ዘፍ1፥1፤ 2ዜና2፥12፤መዝ8፥3፤ ዕብ1፥10-12
102፥26 ኢሳ13፥10 ፡13፤34፥4፤51፥6፤ ሕዝ32፥8፤ኢል2፥10፤ ማቴ24፥35፤2ጴጥ 3፥7-10፤ራእ20፥11
102፥27 ዘኍ23፥19 ፤መዝ9፥7፤ዕብ13፥8፤ ያዕ1፥17
102፥28 መዝ25፥13 ፤69፥36፤89፥4
103፥1 መዝ28፥6፤ 30፥4፤104፥1
103፥2 ዘዳ6፥12፤ መዝ77፥11፤106፥1፤ 117፥1
103፥3 ዘፀ15፥26፤ 34፥7፤ቈላ3፥13፤ 1ጴጥ2፥24፤1ዮሐ1፥9
103፥4 መዝ8፥5፤ 23፥6፤34፥22፤56፥13 ፤ኢሳ43፥1
103፥5 ዘፀ19፥4፤ ኢዮ33፥25፤መዝ90፥ 14፤104፥28፤119፥25 ፡93፤2ቆሮ4፥16
103፥6 መዝ9፥8፤ 65፥5፤74፥21፤ ኢሳ 9፥7፤ሉቃ4፥19
103፥7 ዘፀ33፥13፤ መዝ99፥7፤106፥22፤ 147፥19
103፥8 ዘፀ22፥27፤ መዝ86፥15፤ሚክ7፥

ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፤
እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፤
እነርሱም ወዲያ ይጣላሉ።
[27]አንተ ግን ያው አንተ ነህ፤
ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።
[28]የአገልጋዮችህ ልጆች ተደላድለው
ይኖራሉ፤
ዘራቸውም በፊትህ ጸንቶ ይኖራል።

## *መዝሙር* 103

### እግዚአብሔር ፍቅር ነው

*የዳዊት መዝሙር*

[1]ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ
የውስጥ ሰውነቴም ሁሉ ቅዱስ ስሙን
ባርኪ።
[2]ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
ውለታውንም ሁሉ አትርሺ፤
[3]ኀጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፣
ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፣
[4]ሕይወትሽን ከጥፋት ጕድጓድ የሚያድን፣
ምሕረትንና ርኅራኄን የሚያቀዳጅሽ፣
[5]ጕልማሳነትሽም እንደ ንስር ይታደስ
ዘንድ፣
ምኞትሽን በበጎ ነገር የሚያረካ እርሱ
ነው።
[6]*እግዚአብሔር* ለተጨቈኑ ሁሉ፣
ቅን ፍርድንና ፍትሕን ይሰጣቸዋል።
[7]*መንገዱን ለሙሴ*፣
*ሥራውንም ለእስራኤል ሕዝብ
አሳወቀ።*
[8]*እግዚአብሔር* መሓሪና ይቅር ባይ፣
ለቍጣ የዘገየ፣ ፍቅሩም የበዛ ነው።
[9]እርሱ ሁልጊዜ በደልን አይከታተልም፤
ለዘላለምም አይቈጣም።
[10]እንደ ኀጢአታችን አልመለሰልንም፤
እንደ በደላችንም አልከፈለንም።
[11]ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣
እንዲሁ ለሚፈሩት ምሕረቱ ታላቅ ናት።
[12]ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፣
መተላለፋችንን በዚያው መጠን ከእኛ
አስወገደ።
[13]አባት ለልጆቹ እንደሚራራ፣
*እግዚአብሔር* ለሚፈሩት እንዲሁ ይራራል።
[14]እርሱ አፈጣጠራችንን ያውቃልና፤
ትቢያ መሆናችንንም ያስባል።

18-19፤ያዕ5፥11 103፥9 መዝ30፥5፤79፥5፤ኢሳ57፥16፤ኤር3፥5፡ 12፤ሚክ7፥18 103፥10 ዕዝ9፥13፤ሮሜ6፥23 103፥11 2ዜና 6፥31፤መዝ13፥5፤57፥10፤100፥5፤106፥45፤117፥2፤ሰቆ3፥22፤ኤፌ 3፥18 103፥12 2ሳሙ12፥13፤ሮሜ4፥7፤ኤፌ2፥5 103፥13 ሚል 3፥17፤1ዮሐ3፥1 103፥14 ዘፍ2፥7፤መዝ119፥73፤139፥13-15፤ 146፥4፤ኢሳ29፥16

[ሠ]23 *ወይም በኀይሉ ብርታቴን ቀጨው*

15ሰው እኮ ዘመኑ እንደ ሣር ነው፤
እንደ ዱር አበባ ያቈጠቍጣል፤
16ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ግን ድራሹ ይጠፋል፤
ምልክቱም በቦታው አይገኝም።
17*የእግዚአብሔር* ምሕረት ግን፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ
ነው፤
ጽድቁም እስከ ልጅ ልጅ ድረስ
በላያቸው ይሆናል፤
18ኪዳኑን በሚጠብቁት ላይ፣
ትእዛዙንም ለመፈጸም በሚተጉት ላይ
ይሆናል።
19*እግዚአብሔር* ዙፋኑን በሰማይ አጽንቶአል፤
መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።
20እናንተ ለቃሉ የምትታዘዙ መላእክቱ፤
ትእዛዙንም የምትፈጽሙ እናንተ
ኀያላን፤
*እግዚአብሔርን* ባርኩ።
21እናንተ ፈቃዱን የምትፈጽሙ አገልጋዮቹ፤
ሰራዊቱ ሁሉ፣ *እግዚአብሔርን* ባርኩ።
22እናንተ በግዛቱ ሁሉ የምትኖሩ፣
ፍጥረቱ ሁሉ፣ *እግዚአብሔርን* ባርኩ፤
ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ።

## መዝሙር 104

### የፍጥረት መብት

1ነፍሴ ሆይ፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ፤
*እግዚአብሔር* አምላኬ ሆይ፤ አንተ እጅግ
ታላቅ ነህ፤
ክብርንና ግርማን ለብሰሃል።
2ብርሃንን እንደ ሸማ ተጐናጽፈሃል፤
ሰማያትንም እንደ ድንኳን መጋረጃ
ዘረጋህ፤
3የእልፍኝህን አግዳሚ በውሆች ላይ
አኖርህ፤
ደመናትን ሠረገላህ አደረግህ፤
በነፋስ ክንፍ ትሄዳለህ።
4መላእክትህን´ መንፈስ፣
አገልጋዮችህንም የእሳት ነበልባል
ታደርጋለህ።
5ለዘላለም እንዳትናወጥ፣
ምድርን በመሠረቷ ላይ አጸናሃት።
6በጥልቁ እንደ ልብስ ሸፈንሃት፤
ውሆችም ከተራሮች በላይ ቆሙ።
7በገሠጽሃቸው ጊዜ ግን ፈጥነው ሄዱ፤
የነጐድጓድህንም ድምፅ በሰሙ
ጊዜ ሸሹ።
8በተራሮች ላይ ፈሰሱ፤
ወዳዘጋጀህላቸው ስፍራ፣
ወደ ሸለቆዎች ወረዱ።
9ተመልሰው ምድርን እንዳይሸፍኑ፣
አልፈውም እንዳይመጡ ድንበር
አበጀህላቸው።
10 ምንጮችን በሸለቆ ውስጥ እንዲሄዱ
አደረግህ፤
በተራሮችም መካከል ይፈሳሉ፤
11የዱር እንስሳትም ከዚያ ይጠጣሉ፤
የሜዳ አህዮችም ጥማቸውን
ይቈርጣሉ።
12የሰማይ ወፎች ጎጆቻቸውን በወንዞቹ ዳር
ይሠራሉ፤
በቅርንጫፎችም መካከል ይዘምራሉ።
13ከላይ ከእልፍኝህ ተራሮችህን ታጠጣለህ፤
ምድርም በሥራህ ፍሬ ትረካለች።
14ከምድር ምግብን ታወጣ ዘንድ፣
ለእንስሳት ሣርን፣
ለሰው ልጆች ሥራ ዕፀዋትን
ታበቅላለህ፤
15የሰውን ልብ ደስ የሚያሰኝ ወይን፣
ፊቱን የሚያወዛ ዘይት፣
ልቡን የሚያበረታ እህል በዚህ
ይገኛል።
16ደግሞም *የእግዚአብሔር* ዛፎች፣
እርሱ የተከላቸውም የሊባኖስ ዝግባዎች
ጠጥተው ይረካሉ፤
17ወፎች ጎጆአቸውን በዚያ ይሠራሉ፤
ሽመላ በጥዶቹ ውስጥ ማደሪያ ታገኛለች።
18ረጃጅሙ ተራራ የዋልያ መኖሪያ፣
የዐለቱም ዋሻዎች የሽኮኮ መሸሸጊያ
ናቸው።
19ጨረቃን የወቅቶች መለያ አደረግሃት፤
ፀሓይም የምትጠልቅበትን ጊዜ
ታውቃለች።
20ጨለማን ታመጣለህ፤ ሌሊትም ይሆናል፤
የዱር አራዊትም ሁሉ በዚህ ጊዜ
ወጥተው ይራወጣሉ።
21የአንበሳ ግልገሎች ምግብ ፍለጋ ይጮኻሉ፤
የሚበሉትንም ከእግዚአብሔር ይሻሉ።
22ፀሓይ በወጣች ጊዜም ይመለሳሉ፤
በየጐሬአቸውም ገብተው ይተኛሉ።
23ሰውም ወደ ሥራው ይሄዳል፤
እስኪመሽም በተግባሩ ላይ ይሰማራል።
24*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ሥራህ እንዴት
ብዙ ነው!
ሁሉን በጥበብ ሠራህ፤
ምድርም በፍጥረትህ ተሞላች።
25ይህች ባሕር ሰፊና የተንጣለለች ናት፤

103፥15 ኢዮ14፥2፤ መዝ37፥2፤90፥5፤ 102፥11፤ኢሳ40፥6፤ ያዕ1፥10
103፥16 ኢዮ7፥8፤ ኢሳ40፥7፤ሐጌ1፥9
103፥17 ዘፍ48፥11፤ ዕዝ9፥12
103፥18 ዘኍ15፥40 ፤ዘዳ29፥9፤መዝ119፥52፤ ዮሐ14፥15
103፥19 መዝ22፥28 ፤47፥8፤66፥7፤80፥1፤ 113፥5፤ዳን4፥17
103፥20 ነህ9፥6፤ መዝ28፥6፤29፥1፤ 107፥25፤135፥7፤ 148፥8፤ሉቃ2፥13፤ ዕብ1፥14
103፥21 1ነገ22፥19 ፤ነህ7፥73
103፥22 ቍ1፤መዝ 19፥1፤67፥3፤104፥1፤ 145፥10፤150፥6
104፥1 ኢዮ40፥10 ፤መዝ103፥22
104፥2 ኢዮ9፥8፤ 37፥18፤መዝ18፥12፤ 19፥4፤ኢሳ40፥22፤ 42፥5፤44፥24፤49፥18 ፤ኤር43፥12፤51፥15፤ ዘካ12፥1፤1ጢሞ6፥16
104፥3 ዘዳ33፥26፤ 2ነገ2፥11፤መዝ18፥10 ፤24፥2፤ኢሳ19፥1፤ አሞ 9፥6፤ናሆ1፥3
104፥4 ዘፍ3፥24፤ 2ነገ2፥11፤መዝ148፥8 ፤ዕብ1፥7
104፥5 ዘፀ31፥17፤ 1ሳሙ2፥8፤ኢዮ26፥7፤ መዝ24፥1-2፤102፥25 ፤121፥2
104፥6 ዘፍ1፥2፤ 7፥19፤2ጴጥ3፥6
104፥7 ዘፀ9፥23፤ መዝ18፥15፤29፥3
104፥8 መዝ33፥7
104፥9 ዘፍ1፥9፤ መዝ16፥6
104፥10 መዝ107፥33 ፤ኢሳ41፥18
104፥11 ቍ13፤ ዘፍ16፥12፤ኢሳ 32፥14፤ኤር14፥6
104፥13 ቍ17፤ ማቴ8፥20፤13፥32
104፥13 ዘሌ26፥4፤ መዝ135፥7፤147፥8፤ ኤር10፥13፤አሞ9፥6፤ ዘካ10፥1
104፥14 ዘፍ1፥30፤ ኢዮ28፥5፤38፥27፤ መዝ147፥8
104፥15 ዘፍ14፥18 ፤ዘዳ8፥3፤መሳ9፥13፤ መዝ23፥5፤92፥10፤ ማቴ6፥11፤ሉቃ7፥46
104፥16 ዘፍ1፥11፤ መዝ72፥16
104፥17 ቍ12
104፥18 ዘዳ14፥5፤ ምሳ30፥26 104፥19 ዘፍ1፥14፤መዝ19፥6 104፥20 መዝ50፥10 ፤74፥16፤ኢሳ45፥7፤አሞ5፥8 104፥21 መዝ145፥15፤ኢል1፥20፤ አሞ3፥4፤ማቴ6፥26 104፥22 ኢዮ37፥8 104፥23 ዘፍ3፥19፤ መሳ19፥16 104፥24 ዘፍ1፥31፤መዝ24፥1፤40፥5፤50፥10-11 104፥25 መዝ69፥34፤ሕዝ47፥10

´4 *መልእክተኞቹን ወይም አገልጋዮቹን*

ታላላቅና ታናናሽ እንስሳት፣
ስፍር ቍጥር የሌላቸውም ነፍሳት
በውስጧ አሉ።
26መርከቦች በላይዋ ይመላለሳሉ፤
አንተ የፈጠርኸውም ሌዋታን በውስጧ
ይፈነጫል።
27ምግባቸውን በወቅቱ ትሰጣቸው ዘንድ፣
እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ።
28በሰጠሃቸውም ጊዜ፣
አንድ ላይ ያከማቻሉ፤
እጅህንም ስትዘረጋ፣
በመልካም ነገር ይጠግባሉ።
29ፊትህን ስትሰውር፣
በድንጋጤ ይሞላሉ፤
እስትንፋሳቸውንም ስትወስድባቸው
ይሞታሉ፤
ወደ ዐፈራቸውም ይመለሳሉ።
30መንፈስህን ስትልክ፣
እነርሱ ይፈጠራሉ፤
የምድርንም ገጽ ታድሳለህ።
31የእግዚአብሔር ክብር ለዘላለም ጸንቶ
ይኑር፤
እግዚአብሔር በሥራው ደስ ይበለው፤
32እርሱ ምድርን ሲመለከት፣ ትንቀጠቀጣለች፤
ተራሮችም እርሱ ሲዳስሳቸው ይጤሳሉ።
33በሕይወት ሳለሁ ለእግዚአብሔር
እዘምራለሁ፤
ቆሜ እስከ ሄድሁ ድረስም ለአምላኬን
እወድሳለሁ።
34እኔ በእግዚአብሔር ደስ እንደሚለኝ፣
የልቤ ሐሳብ እርሱን
ደስ ያሰኘው።
35ኀጥአን ከምድር ገጽ ይጥፉ፤
ዐመፀኞች ከእንግዲህ አይገኙ።

ነፍሴ ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኪ፤
ሃሌ ሉያ።[ሰ]

## መዝሙር 105

### የእስራኤል ድንቅ ታሪክ

105፥1-15 ተጓ ምብ-1ዜና 16፥8-22

1እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ስሙንም ጥሩ፤
ሥራውንም በሕዝቦች መካከል ግለጡ።
2ተቀኙለት፤ ዘምሩለት፤
ድንቅ ሥራዎቹንም ሁሉ ተናገሩ።
3በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ፤
እግዚአብሔርን የሚሹት ልባቸው ደስ
ይበለው።
4እግዚአብሔርንና ብርታቱን ፈልጉ፤
ፊቱንም ዘወትር ፈልጉ።
5ያደረጋቸውን ድንቅ ሥራዎች፣
ታምራቱንና ከአፉ የወጣውን ፍርድ
አስቡ፤
6እናንተ የአገልጋዩ የአብርሃም ዘሮች፣
ለራሱም የመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች
ሆይ፤ አስታውሱ።
7እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው፤
ፍርዱም በምድር ሁሉ ላይ ነው።
8ኪዳኑን ለዘላለም፣
ያዘዘውንም ቃል እስከ ሺህ ትውልድ
ያስታውሳል።
9ከአብርሃም ጋር ያደረገውን ኪዳን፣
ለይስሐቅም በመሐላ የተሰጠውን ተስፋ
አይረሳም።
10ይህንም ለያዕቆብ ሥርዐት አድርጎ፣
ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን አድርጎ
አጸናለት፤
11እንዲህም አለ፤ "የርስትህ ድርሻ
አድርጌ፣
የከነዓንን ምድር እሰጥሃለሁ።"
12በቍጥር አነስተኞች ሆነው ሳሉ፣
እጅግ ጥቂትና ባይተዋሮች ሳሉ፣
13ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ሲንከራተቱ፣
ከአንዱ መንግሥት ወደ ሌላው
ሲቀበበዙ፣
14ማንም ግፍ እንዲፈጽምባቸው አልፈቀደም፤
ስለ እነርሱም ነገሥታትን እንዲህ ሲል
ገሥጸ፤
15"የቀባኋቸውን አትንኩ፤
በነቢያቴም ላይ ክፉ አታድርጉ።"
16በምድሪቱ ላይ ራብን ጠራ፤
የምግብንም አቅርቦት ሁሉ አቋረጠ፤
17በባርነት የተሸጠውን ሰው፣
ዮሴፍን ከእነርሱ አስቀድሞ ላከ።
18እግሮቹ በእግር ብረት ተላላጡ፤
በዐንገቱም የብረት ማነቆ ገባ።
19የተናገረው ቃል እስኪፈጸምለት፣
የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው።
20ንጉሥ ልኮ አስፈታው፤
የሕዝቦችም ገዥ ነጻ አወጣው።
21የቤቱ ጌታ፣
የንብረቱም ሁሉ አስተዳዳሪ አደረገው፤
22ይኸውም ሹማምቱን በራሱ መንገድ
ይመራ ዘንድ፣
ታላላቆቹንም ጥበብ ያስተምር ዘንድ
ነበር።
23እስራኤል ወደ ግብፅ ገባ፤
ያዕቆብ በካም ምድር መጻተኛ ሆነ።
24እግዚአብሔር ሕዝቡን እጅግ አበዛ፤
ከጠላቶቻቸውም ይልቅ አበረታቸው፤

104፥26 ዘፍ1፥21፤ ኢዮ3፥8፤40፥20፤41፥1፤መዝ107፥23፤ ሕዝ 27፥9፤ዮና1፥3
104፥27 ኢዮ36፥31፤መዝ145፥15፤147፥9
104፥28 መዝ103፥5፤145፥16፤ኢሳ58፥11
104፥29 ዘዳ31፥17፤ኢዮ7፥21
104፥30 ዘፍ1፥2
104፥31 ዘፍ1፥4፤ ዘፀ40፥35፤መዝ8፥1፤ ሮሜ11፥36
104፥32 ዘፀ19፥18፤ መዝ97፥4፤144፥5
104፥33 ዘፀ15፥1፤ መዝ108፥1
104፥34 መዝ2፥11፤ 9፥2፤32፥11
104፥35 ኢዮ7፥10፤ መዝ28፥6፤37፥38፤ 105፥45፤106፥48
105፥1 1ዜና16፥34፤መዝ80፥18፤99፥6፤ 116፥13፤ኢል2፥32፤ ሐሥ2፥21
105፥2 መዝ7፥17፤ 18፥49፤27፥6፤30፥4፤ 33፥3፤59፥17፤71፥22፤75፥1፤96፥1፤146፥2
105፥3 መዝ89፥16
105፥4 መዝ24፥6
105፥5 ዘዳ7፥18፤ መዝ40፥5
105፥6 ቍ42፤ዘዳ 10፥15፤መዝ106፥5
105፥8 ዘፍ9፥15፤ መዝ106፥45፤ 111፥5፤ሕዝ16፥60፤ ሉቃ1፥72
105፥9 ዘፍ12፥7፤ 15፥18፤22፥16-18፤ ሉቃ1፥73፤ገላ3፥15-18
105፥10 ዘፍ28፥ 13-15፤ኢሳ55፥3
105፥11 ዘፍ12፥7፤ ዘኍ34፥2
105፥12 ዘፍ23፥4፤ ዘዳ7፥7፤ዕብ11፥19
105፥13 ዘፍ15፥13-16፤ዘኍ32፥13፤ 33፥3-49
105፥14 ዘፍ12፥17-20፤20፥3፤35፥5፤ መዝ 9፥5
105፥15 ዘፍ20፥7፤ 26፥11፤1ሳሙ12፥3
105፥16 ዘፍ12፥10፤ዘሌ26፥26፤ ኢሳ3፥1፤ሕዝ4፥16
105፥17 ዘፍ37፥28፤ሐሥ7፥9
105፥18 ዘፍ40፥15
105፥19 ዘፍ12፥10፤40፥20-22፤41፥40
105፥20 ዘፍ41፥14
105፥22 ዘፍ41፥40፥43-44
105፥23 ዘፍ46፥6፤ 47፥28፤መዝ78፥51፤ ሐሥ7፥15፤13፥17
105፥24 ዘፀ1፥7፡9፤ሐሥ7፥17

[ሰ]35 እግዚአብሔር ይመስገን የሚሉ ትርጕሞች አሉ፤ በሰብዓ ሊቃናት ትርጕም ይህ መሥመር በመዝ105 መጀመሪያ ላይ ይገኛል።

25 ሕዝቡን እንዲጠሉ፣
በባሪያዎቹም ላይ እንዲያሤሩ
ልባቸውን ለወጠ።
26 ባሪያውን ሙሴን፣
የመረጠውንም አሮንን ላከ።
27 እነርሱም ታምራታዊ ምልክቶችን
በመካከላቸው፣
ድንቅ ነገሮቹንም በካም ምድር
አደረጉ።
28 ጨለማን ልኮ ምድሪቱን ጽልመት
አለበሰ፤
እነርሱም በቃሉ ላይ ማመፅን ተዉ።
29 ውሃቸውን ወደ ደም ለወጠ፤
ዓሦቻቸውንም ፈጀ።
30 ምድራቸውም፣ የነገሥታታቸው
እልፍኝ ሳይቀር፣
ጓጉንቸር ተርመሰመሰባቸው።
31 እርሱ በተናገረ ጊዜ የዝንብ መንጋ
መጣ፤
ትንኞችም ምድራቸውን ወረሩ።
32 ዝናባቸውን በረዶ አደረገው፤
ምድራቸውም ሁሉ መብረቅ አወረደ።
33 ወይናቸውንና በለሳቸውን መታ፤
የአገራቸውንም ዛፍ ከተከተ።
34 እርሱ በተናገረ ጊዜ አንበጣ መጣ፤
ስፍር ቍጥር የሌለውም ኵብኵባ
ከተፍ አለ፤
35 የምድሪቱንም ዕፀዋት ሁሉ በላ፤
የመሬታቸውንም ፍሬ ሙጥጥ አደረገ፤
36 ደግሞም በአገራቸው ያለውን በኵር
ሁሉ፣
የኀይላቸውንም ሁሉ በኵራት መታ።

37 የእስራኤልንም ሕዝብ ብርና ወርቅ
ጭኖ እንዲወጣ አደረገ፤
ከነገዶቻቸውም አንድም አልተደናቀፈም።
38 እጅግ ፈርተዋቸው ነበርና፣
ወጥተው ሲሄዱ ግብፅ ደስ አላት።
39 ደመናን እንደ መጋረጃ ዘረጋላቸው፤
እሳትም በሌሊት አበራላቸው።
40 በለመኑትም ጊዜ፣ ድርጭት አመጣላቸው፤
የሰማይንም እንጀራ አጠገባቸው።
41 ዐለቱን ሰነጠቀ፤ ውሃም ተንዶለደለ፤
እንደ ወንዝም በበረሓ ፈሰሰ።

42 ለባሪያው ለአብርሃም የሰጠውን፣
ቅዱስ የተስፋ ቃሉን አስቦአልና።
43 ሕዝቡን በደስታ፣
ምርጦቹንም በእልልታ አወጣቸው።
44 የሌሎችን ሕዝቦች ምድር ሰጣቸው፤
የእነዚህንም የድካም ፍሬ ወረሱ፤
45 ይህም ሥርዐቱን ይጠብቁ ዘንድ፣
ሕጉንም ይፈጽሙ ዘንድ ነው።
ሃሌ ሉያ።[ሸ]

105፥25 ዘፀ1፥6-10፤4፥21፤ሐሥ7፥19
105፥26 ዘፀ3፥10፤4፥16፤ዘኍ16፥5፤17፥5-8፤33፥1
105፥27 ቍ28-37፤ዘፀ3፥20፤4፥17፤7፥8-12፡51፤10፥1፤ዳን4፥3
105፥28 ዘፍ1፥4፤ዘፀ7፥22፤10፥22
105፥29 ዘፀ7፥21፤78፥44
105፥30 ዘፀ8፥2፡6
105፥31 ዘፀ8፥16-18፡21-24፤መዝ78፥45፤107፥25፤148፥8
105፥32 ዘፀ9፥22-25፤ኢዮ38፥22፤መዝ 78፥47
105፥33 ዘፀ10፥5፡12፤መዝ78፥47
105፥34 ዘፀ10፥4፡12-15፤1ነገ8፥37፤መዝ107፥25፤ኢል 1፥6
105፥36 ዘፀ4፥23፤12፥12
105፥37 ዘፀ3፥21፡22
105፥38 ዘፀ15፥16
105፥39 ዘፀ13፥21፤መዝ78፥14፤1ቆሮ10፥1
105፥40 ዘፀ16፥4፡13፤መዝ78፥18፤ዮሐ6፥31
105፥41ዘኍ20፥11፤1ቆሮ10፥4
105፥42 ዘፍ12፥1-3፤13፥14-17፤15፥13-16
105፥43 ዘፀ15፥1-18፤መዝ106፥12
105፥44 ዘፀ32፥13፤ዘዳ6፥10-11፤ኢሱ11፥16-23፤12፥8፤13፥6-7፤መዝ78፥55፤111፥6
105፥45 ዘዳ4፥40፤6፥21-24፤መዝ78፥5-7፤104፥35
106፥1 ዕዝ3፥11፤መዝ22፥23፤ 103፥2፤119፥68፤136፥1-26፤ኤር33፥11
106፥2 መዝ71፥16
106፥3 መዝ15፥2፤112፥5፤ሆሴ12፥6
106፥4 ዘፍ50፥24፤መዝ25፥6፡7፤77፥7
106፥5 ዘፀ34፥9፤ዘዳ30፥15፤መዝ1፥3፤20፥5፤27፥6፤47፥5፤105፥6፤118፥15
106፥6 1ነገ8፥47፤2ዜና30፥7፤ነህ1፥7፤ሮሜ3፥9
106፥7 ዘፀ14፥11-12፤መሳ3፥7፤መዝ78፥42
106፥8 ዘፀ9፥16፤14፥30፡31፤መዝ23፥3

## መዝሙር 106

### ብሔራዊ ኑዛዜ

106፥1፡47-48 ተጓ ምብ-1ዜና 16፥34-36

1 ሃሌ ሉያ[ቀ]
ቸር ነውና፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ነውና።
2 ስለ እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ማን
ሊናገር ይችላል?
ምስጋናውንስ ሁሉ ማን ተናግሮ
ይጨርሳል?
3 ፍትሕ እንዳይዛነፍ የሚጠብቁ፣
ጽድቅን ሁልጊዜ የሚያደርጉ የተባረኩ
ናቸው።
4 እግዚአብሔር ሆይ፤ ለሕዝብህ ሞገስ
ስታድል አስበኝ፤
በምታድናቸውም ጊዜ ርዳኝ፤
5 ይኸውም የምርጦችህን ብልጽግና አይ
ዘንድ፣
በሕዝብህ ደስታ ደስ ይለኝ ዘንድ፣
ከርስትህም ክብር የተነሣ እጓደድ
ዘንድ ነው።

6 እኛም እንደ አባቶቻችን ኀጢአት
ሠራን፤
በደልን፤ ክፉም አደረግን።
7 አባቶቻችን በግብፅ ሳሉ፣
ታምራትህን አላስተዋሉም፤
የምሕረትህን ብዛት አላሰቡም፤
በባሕሩ አጠገብ፣ ገና ቀይ ባሕር[በ]
አጠገብ ዐመፁብህ።
8 እርሱ ግን የኀይሉን ታላቅነት ለማሳወቅ፣
ስለ ስሙ አዳናቸው።
9 ቀይ ባሕርን ገሠጸ፤ እርሱም ደረቀ፤
በምድረ በዳ እንደሚታለፍ በጥልቅ
ውሃ መካከል መራቸው።

10 ከባለጋራቸው እጅ አዳናቸው፤
ከጠላትም እጅ ታደጋቸው።
11 ባላንጦቻቸውን ውሃ ዋጣቸው፤
ከእነርሱም አንድ አልተረፈም።
12 ከዚህ በኋላ የተስፋ ቃሉን አመኑ፤
በዝማሬም አመሰገኑት።

13 ነገር ግን ያደረገውን ወዲያውኑ ረሱ፤
በምክሩም ለመሄድ አልታገሡም።
14 በምድረ በዳ እጅግ መመኘት አበዙ፤

፤80፥3፤107፥13፤ኢሳ25፥9፤ኢል2፥32 106፥9 ዘፀ14፥21፤መዝ18፥15፤78፥13፤ኢሳ50፥2፤63፥11-14፤ናሆ1፥4 106፥10 ዘፀ14፥30፤መዝ78፥42፡53፤107፥2፡13፤ኢሳ35፥9፤62፥12 106፥11 ዘፀ14፥28 106፥12 ዘፀ15፥1-21፤105፥43 106፥13 ዘፀ15፥24፤16፥28፤ዘኍ27፥21 106፥14 ዘፀ17፥2፤መዝ68፥7፤78፥40፤10፥9

[ሸ]45 እግዚአብሔር ይመስገን የሚሉ ትርጒሞች አሉ።
[ቀ]1 እግዚአብሔር ይመስገን ማለት ሲሆን በቍ48 ላይም በድጋሚ ተጠቅሶአል።
[በ]7 በዕብራይስጥ ያም ሱፍ የሚባል ሲሆን የደንገል ባሕር ማለት ነው፤ በቍ9 እና 22 ላይም ይገኛል።

በበረሓም እግዚአብሔርን ተፈታተኑት።
15 እርሱም የለመኑትን ሰጣቸው፤
ዳሩ ግን የሚያኰስምን ሕመም
ሰደደባቸው።

16 በሰፈር በሙሴ ላይ፣
ለእግዚአብሔር በተቀደሰውም በአሮን
ላይ ቀኑ።
17 ምድር ተከፍታ ዳታንን ዋጠች፤
የአቤሮንን ወገን ሰለቀጠች።
18 እሳት በጉባኤያቸው መካከል ነደደ፤
ነበልባሉም ክፉዎችን ፈጅቶ አስወገደ።

19 በኮሬብ ጥጃ ሠሩ፤
ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ።
20 ክብራቸው የሆነውንም ሣር በሚበላ፣
በበሬ ምስል ለወጡ።
21 በግብፅ ታላቅ ነገር ያደረገውን፣
ያዳናቸውን አምላክ ረሱ፤
22 እርሱ ግን በካም ምድር ድንቅ ሥራ፣
በቀይ ባሕርም አስደናቂ ነገር አደረገ።
23 ስለዚህ በመቅሠፍቱ እንዳያጠፋቸው
ይመለስ ዘንድ፣
እርሱ የመረጠው ሙሴ በመካከል ገብቶ፣
በፊቱ ባይቆም ኖሮ፣
እንደሚያጠፋቸው ተናግሮ ነበር።

24 ከዚያም በኋላ መልካሚቱን ምድር ናቁ፤
የተስፋ ቃሉንም አላመኑም።
25 በድንኳኖቻቸው ውስጥ አጕረመረሙ፤
የእግዚአብሔርንም ድምፅ አላዳመጡም።
26 በምድረ በዳ ሊጥላቸው፣
እጁን አንሥቶ ማለ፤
27 ዘራቸውንም በሕዝቦች መካከል ሊጥል፣
ወደ ተለያየ ምድርም እንደሚበትናቸው
ማለ።

28 ራሳቸውን ከብዔል ፌጎር ጋር አቈራኙ፤
ለሙታን የተሠዋውን መሥዋዕት በሉ፤
29 በሥራቸውም እግዚአብሔርን አስቈጡት፤
ቸነፈርም በላያቸው መጣ።
30 ፊንሐስም ተነሥቶ ጣልቃ ገባ፤
ቸነፈሩም ተገታ፤
31 ይህም ከትውልድ እስከ ትውልድ፣
ለዘላለም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።

32 ደግሞም በመሪባ ውሃ አጠገብ እግዚ
አብሔርን አስቈጡት፤
ሙሴም ከእነርሱ የተነሣ ተቸገረ፤
33 የእግዚአብሔርንም መንፈስ ስላስመረሩት፣
ሙሴ የማይገባ ቃል ከአንደበቱ
አወጣ።[†]

34 እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት፣
ሕዝቦችን ከማጥፋት ወደ ኋላ አሉ፤
35 እንዲያውም ከሕዝቦቹ ጋር ተደባለቁ፤
ልማዳቸውንም ቀሠሙ፤
36 ጣዖቶቻቸውንም አመለኩ፤
ይህም ወጥመድ ሆነባቸው።
37 ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን
ለአጋንንት ሠዉ።
38 የወንዶችና የሴቶች ልጆቻቸውን ደም፣
ለከነዓን ጣዖታት የሠዉአቸውን፣
ንጹሕ ደም አፈሰሱ፤
ምድሪቱም በደም ተበከለች።
39 በተግባራቸው ረከሱ፤
በድርጊታቸውም አመንዝሮች ሆኑ።

40 ስለዚህ የእግዚአብሔር ቍጣ በሕዝቡ
ላይ ነደደ፤
ርስቱንም ተጸየፈ።
41 ለአሕዛብ አሳልፎ ሰጣቸው፤
ጠላቶቻቸውም በላያቸው ሠለጠኑ።
42 ጠላቶቻቸው ጨቈኗቸው፤
በሥልጣናቸውም ሥር አዋሏቸው።
43 እርሱ ብዙ ጊዜ ታደጋቸው፤
እነርሱ ግን ዐመፃን የሙጥኝ አሉ፤
በኀጢአታቸውም ተዋረዱ።

44 ሆኖም ጩኸታቸውን በሰማ ጊዜ፣
ጭንቀታቸውን ተመለከተ፤
45 ለእነርሱም ሲል ቃል ኪዳኑን አሰበ፤
እንደ ምሕረቱም ብዛት ከቍጣው
ተመለሰ።
46 የማረኳቸው ሁሉ፣
እንዲራሩላቸው አደረገ።

47 አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፤ አድነን፤
ለቅዱስ ስምህ ምስጋና እናቀርብ
ዘንድ፣
አንተን በመወደስ እንኳደድ ዘንድ፣
ከሕዝቦች መካከል ሰብስበህ አምጣን።

48 የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣
ከዘላለም እስከ ዘላለም ይባረክ፤
ሕዝብም ሁሉ፣ “አሜን!” ይበል።
ሃሌ ሉያ።

## አምስተኛ መጽሐፍ
## መዝሙር 107-150

### መዝሙር 107
### ከመከራ ሁሉ የሚታደግ አምላክ

1 ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ነውና።
2 እግዚአብሔር የተቤዣቸው፣
ከጠላት እጅ የታደጋቸው ይህን ይበሉ፤

106፥15 ዘፀ16፥13፤ ዘኍ11፥33፤መዝ78፥29
106፥16 ዘኍ16፥1-3
106፥17 ዘፀ15፥12፤ ዘኍ16፥1፤ዘዳ11፥6
106፥18 ዘሌ10፥2
106፥19 ዘፀ32፥4፤ ሐሥ7፥41
106፥20 ኤር2፥11፤ ሮሜ1፥23
106፥21 ዘዳ10፥21 ፤መዝ75፥1፤78፥11
106፥22 ዘፀ3፥20፤ ዘዳ4፥34፤መዝ78፥51
106፥23 ዘፀ32፥10፡ 11-14፤ዘኍ11፥2፤ ዘዳ9፥19
106፥24 ዘኍ14፥11 ፡30-31፤ዘዳ8፥7፤ኤር 3፥19፤ዕብ3፥18-19
106፥25 ዘፀ15፥24፤ ዘዳ1፥27፤1ቆሮ10፥10
106፥26 ዘኍ14፥23፤ ዘዳ2፥14፤ዕብ3፥17፤ 4፥3
106፥27 ዘሌ26፥33
106፥28 ዘኍ23፥28
106፥29 ዘኍ16፥46፤ 25፥3፡8፤መዝ64፥2፤ 141፥4
106፥30 ዘፀ6፥25፤ ዘኍ25፥8
106፥31 ዘፍ15፥6፤ ዘኍ25፥11-13፤ መዝ 49፥11
106፥32 ዘፀ17፥7፤ ዘኍ20፥2-13
106፥33 ዘፀ17፥4-7፤ 23፥21፤ዘኍ20፥8-12፤ መዝ51፥11፤ 107፥11፤ኢሳ63፥10
106፥34 ዘፀ23፥24፤ ዘዳ2፥34፤7፥16፤ 20፥17፤ኢሱ9፥15፤ መሳ1፥27-36
106፥35 መሳ3፥5-6፤ ዕዝ9፥1-2
106፥26 ዘፀ10፥7፤ ዘዳ7፥16
106፥37 ዘፀ22፥20፤ ዘሌ18፥21፤ዘዳ12፥31 ፤32፥17፤ሕዝ16፥20- 21፤1ቆሮ10፥20
106፥38 ዘሌ18፥21 ፤ዘዳ18፥10፤2ነገ3፥27
106፥39 ዘፍ3፥17፤ ዘሌ18፥24፤ዘኍ 15፥39፤ሕዝ20፥18
106፥40 ዘፀ34፥9፤ ዘሌ26፥28፤ዘዳ9፥29
106፥41 መሳ2፥14
106፥42 መሳ4፥3
106፥43 ኢሱ10፥14 ፤መሳ2፥16-19፤ 6፥1-7፤7፥1-25፤ ነህ9፥28፤ መዝ81፥13-14
106፥44 መሳ3፥9
106፥45 ዘፍ9፥15፤ ዘፀ32፥14፤መዝ17፥7 ፤103፥11፤105፥8፤ ሉቃ1፥72 106፥46 ዘፀ3፥21፤1ነገ8፥50 106፥47 መዝ28፥9፤ 30፥4፤99፥3፤105፥1፤107፥3፤147፥2፤ኢሳ11፥12፤27፥13፤56፥8፤ 66፥20፤ኤር31፥8፤ሕዝ20፥34፤ሚክ4፥6 106፥48 መዝ41፥13፤ 72፥19 107፥1 1ዜና16፥8፤2ዜና5፥13፤7፥3 107፥2 መዝ106፥10፤ ኢሳ35፥9

[†]33 አንዳንዶች ራሱን ባለመቈጣጠርና በችኰላ ተናገረ

3 ከምሥራቅና ከምዕራብ፣ ከሰሜንና
ከደቡብ፣[ቸ]
ከየአገሩ የሰበሰባቸው እንዲህ ይናገሩ፡፡
4 አንዳንዶቹ ጭው ባለ በረሓ ተቅበዘበዙ፤
ወደሚኖሩባት ከተማ የሚያደርስ
መንገድ አጡ፡፡
5 ተራቡ፤ ተጠሙ፤
ነፍሳቸውም በውስጣቸው ዛለች፡፡
6 በተጨነቁ ጊዜ ወደ *እግዚአብሔር*
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
7 ወደሚኖሩባትም ከተማ፣
በቀና መንገድ መራቸው፡፡
8 *እግዚአብሔርን* ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ
ሥራ ያመስግኑት፤
9 እርሱ የተጠማችውን ነፍስ አርክቶአልና፤
የተራበችውንም ነፍስ በበጎ ነገር
አጥግቦአል፡፡
10 አንዳንዶቹ በብረት ሰንሰለት ታስረው
የተጨነቁ፣
በጨለማ፣ በጥልማሞት ውስጥ
የተቀመጡ ነበሩ፤
11 በእግዚአብሔር ቃል ላይ በማመፅ፣
የልዑልን ምክር አቃለዋልና፡፡
12 ስለዚህ በጒልበት ሥራ ልባቸውን አዛለ፤
ተዝለፈለፉ፤ የሚደግፋቸውም
አልነበረም፡፡
13 በተጨነቁ ጊዜ ወደ *እግዚአብሔር*
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
14 ከጨለማና ከጥልማሞት አወጣቸው፤
እስራታቸውንም በጠሰላቸው፡፡
15 *እግዚአብሔርን* ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ
ያመስግኑት፤
16 እርሱ የናሱን በሮች ሰብሮአልና፤
የብረቱንም መወርወሪያ ቈርጦአል፡፡
17 አንዳንዶቹ ከዐመፃቸው የተነሣ ቂሎች
ሆኑ፤
ከበደላቸው የተነሣ ችግር ውስጥ ገቡ፡፡
18 ሰውነታቸው የምግብ ዐይነት ሁሉ
ተጸየፈች፤
ወደ ሞትም ደጆች ቀረቡ፡፡
19 በተጨነቁ ጊዜ ወደ *እግዚአብሔር*
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
20 ቃሉን ልኮ ፈወሳቸው፤
ከመቃብርም አፋፍ መለሳቸው፡፡
21 *እግዚአብሔርን* ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ ሥራ
ያመስግኑት፤

22 የምስጋናም መሥዋዕት ያቅርቡለት፤
ሥራውንም ደስ በሚል ዝማሬ
ይግለጹ፡፡
23 አንዳንዶቹ በመርከብ ወደ ባሕር ወረዱ፤
በታላቅም ውሃ ላይ ሥራቸውን
አከናወኑ፤
24 *የእግዚአብሔርን ሥራ* በዚያ አዩ፤
ድንቅ አድራጎቱንም በጥልቁ ውስጥ
ተመለከቱ፡፡
25 እርሱ ተናግሮ ዐውሎ ነፋስን አስነሣ፤
ነፋሱም ማዕበሉን ከፍ ከፍ አደረገ፡፡
26 ወደ ሰማይ ወጡ፤ ወደ ጥልቅም ወረዱ፤
ከመከራቸውም የተነሣ ሐሞታቸው
ፈሰሰ፡፡
27 እንደ ሰከረ ሰው ዞሮባቸው ወዲያ ወዲህ
ተንገዳገዱ፤
መላው ጠፍቶባቸው የሚያደርጉትን
አጡ፡፡
28 በተጨነቁ ጊዜ ወደ *እግዚአብሔር*
ጮኹ፤
እርሱም ከመከራቸው አዳናቸው፡፡
29 ዐውሎ ነፋሱን ጸጥ አደረገ፤
የባሕሩም ሞገድ ረጭ አለ፡፡
30 ጸጥ በማለቱም ደስ አላቸው፤
ወዳሰቡትም ወደብ አደረሳቸው፡፡
31 *እግዚአብሔርን* ስለ ምሕረቱ፣
ለሰው ልጆችም ስላደረገው ድንቅ
ሥራ ያመስግኑት፤
32 በሕዝብ ጉባኤ መካከል ከፍ ከፍ
ያድርጉት፤
በሽማግሌዎችም ሸንጎ ይወድሱት፡፡
33 ወንዞችን ወደ ምድረ በዳ፣
የውሃ ምንጮችንም ወደ ደረቅ ምድር
ለወጠ፡፡
34 ከነዋሪዎቿ ክፋት የተነሣ፣
ፍሬያማዋን ምድር በጨው የተበከለች
አደረጋት፡፡
35 ምድረ በዳውን ወደ ውሃ መከማቻ፣
ደረቁንም ምድር ወደ ውሃ ምንጭ
ቀየረ፡፡
36 የተራቡትን በዚያ አስቀመጠ፤
የሚኖሩባትንም ከተማ ሠሩ፡፡
37 በዕርሻውም ዘሩበት፤ ወይንም ተከሉ፤
ብዙ ፍሬም አመረቱ፡፡
38 ይባርካቸዋል፤ እነርሱም እጅግ ይበዛሉ፤
የከብቶቻቸውም ብዛት እንዲያንስ
አያደርግም፡፡

107፥3 ነህ1፥9
107፥4 ቍ36፤ ኢሱ 5፥6
107፥5 ዘፀ15፥22፤ 16፥3፤17፥2
107፥6 ዘፀ14፥10
107፥7 ቍ36፤ ዕዝ 8፥21
107፥8 መዝ6፥4፤ 75፥1፤105፥1
107፥9 መዝ22፥26 ፤23፥1፤63፥5፤ኢሳ 58፥11፤ኤር31፥25፤ ማቴ5፥6፤ሉቃ1፥53
107፥10 ቍ14፤ ኢዮ36፥8፤መዝ88፥6 ፤102፥20፤143፥3፤ ኢሳ 9፥2፤42፥7፡16፤ 49፥9፤61፥1፤ሚክ7፥9
107፥11 ዘኍ14፥11 ፤1ነገ22፥5፤2ዜና 36፥16፤መዝ5፥10
107፥12 2ነገ14፥26 ፤መዝ72፥12
107፥13 መዝ106፥8
107፥14 ቍ10፤ ኢዮ36፥8፤መዝ86፥13፤ 116፥16፤ኢሳ9፥2 ፤29፥18፤42፥7፤50፥10፤ 59፥9፤60፥2፤ሉቃ1፥79 ፤ ሐሥ12፥7
107፥15 ቍ8፡21፡ 31፤መዝ6፥4፤75፥1፤ 105፥1
107፥17 ዘሌ26፥16፤ መዝ25፥7፤53፥1፤ ኢሳ65፥6-7፤ኤር 30፥14-15፤ገላ6፥7-8
107፥18 ኢዮ3፥24፤ 6፥6፤17፥16፤33፥22
107፥19 ቍ13፡28፤ መዝ5፥2፤34፥4
107፥20 ዘፀ15፥26፤ ዘዳ32፥2፤ኢዮ33፥28፤ መዝ16፥10፤30፥3፤ 56፥13፤147፥15፤ ማቴ 8፥8፤ሉቃ7፥7
107፥21 ቍ15፤ መዝ 6፥4፤75፥1
107፥22 ዘሌ7፥12፤ ኢዮ8፥21፤መዝ9፥11 ፤65፥8፤73፥28፤ 118፥17
107፥23 መዝ104፥ 26፤ኢሳ42፥10
107፥24 መዝ64፥9 ፤111፥2፤143፥5
107፥25 መዝ50፥3 ፤93፥3፤105፥31
107፥26 ኢሱ2፥11 ፤ሉቃ8፥23
107፥27 ኢሳ19፥14 ፤24፥2፤28፥7
107፥28 ቍ19፤ መዝ 4፥1፤ዮና1፥6
107፥29 መዝ65፥7 ፤93፥3፤ዮና1፥15፤ ሉቃ8፥24
107፥30 ቍ7
107፥31 ቍ15፤ መዝ6፥4፤75፥1፤106፥2

107፥32 መዝ1፥5፤22፥22፤26፥12፤30፥1፤34፥3፤35፥18፤99፥5 107፥33 1ነገ17፥1፤መዝ74፥15፤104፥10፤ኢሳ41፥15፤42፥15 ፤50፥2 107፥34 ዘፍ13፥10 107፥35 2ነገ3፥17፤ኢዮ38፥26፤ መዝ105፥41፤126፥4፤ኢሳ35፥7፤43፥19፤51፥3 107፥37 2ነገ 19፥29፤ኢሳ37፥30 107፥38 ዘፍ12፥2፤49፥25፤ዘዳ7፥13

[ቸ]3 ዕብራይስጡ *ሰሜንና ባሕሩ* ይለዋል፡፡

39 በጭንቅ፣ በመከራና በሐዘን፣
ቊጥራቸው አንሶ፣ ተዋርደው ነበር፤
40 በመኳንንቱም ላይ መናቅን አዘነበባቸው፤
*መውጫ መግቢያው በማይታወቅ በረሓ*
ውስጥም አንከራተታቸው።
41 ችግረኞችን ግን ከጭንቀታቸው መዝዞ
አወጣቸው፤
ቤተ ሰባቸውንም እንደ በግ መንጋ
አበዛ።
42 ልበ ቅኖች ይህን አይተው ሐሤት
ያደርጋሉ፤
ጥመትም ሁሉ አፏን ትዘጋለች።
43 እንግዲህ ማንም ብልህ ቢሆን፣ ይህን
ነገር ልብ ይበል፤
እርሱም *የእግዚአብሔርን* ምሕረት
ያስተውላል።

## *መዝሙር* 108

### የጧት ውዳሴና ብሔራዊ ጸሎት

108፥1-5 ተጓ ምብ-መዝ57፥7-11
108፥6-13 ተጓ ምብ-መዝ60፥5-12

*የዳዊት መዝሙር፤ ማኅሌት*

1 ሰ᎐ᎈ ሆይ፤ ልቤ ጽኑ ነው፤
እዘምራለሁ፤ በፍጹም ነፍሴም
እዘምራለሁ።
2 በገናም መሰንቆም ተነሡ፤
እኔም ማልጄ እነሣለሁ።
3 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ በሕዝብ መካከል
አመሰግንሃለሁ፤
በሕዝቦችም መካከል እዘምርልሃለሁ።
4 ምሕረትህ ከሰማያት በላይ ታላቅ ናትና፤
ታማኝነትህም እስከ ጠፈር ትደርሳለች።
5 ሰ᎐ᎈ ሆይ፤ ከሰማያት በላይ ከፍ ከፍ
በል፤
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትንሰራፋ።

6 ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ፣
በቀኝ እጅህ ታደግ፤ መልስልኝም።
7 እግዚአብሔር ከመቅደሱ እንዲህ አለ፤
ደስ እያለኝ ሴኬምን እሸነሽናለሁ፤
“የሱኮትንም ሸለቆ እለካለሁ።
8 ገለዓድ የእኔ ነው፤ ምናሴም የእኔ ነው፤
ኤፍሬም የራስ ቊሬ ነው፤
ይሁዳም በትረ መንግሥቴ።
9 ሞዓብ መታጠቢያ ገንዳዬ ነው፤
በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን
እወረውራለሁ፤
በፍልስጥኤም ላይ በድል አድራጊነት
እፎክራለሁ።”

10 ወደ ተመሸገችው ከተማ ማን
ይወስደኛል?
ወደ ኤዶምያስስ ማን ያደርሰኛል?
11 እግዚአብሔር ሆይ፤ የጣልኸን አንተ
አይደለህምን?
ሰ᎐ᎈ ሆይ፤ ከሰራዊታችንም ጋር
አልወጣ አልህ!
12 አሁንም የሰው ማዳን ከንቱ ነውና፣
በጠላታችን ላይ ድልን አቀዳጀን።
13 እግዚአብሔር ሲረዳን ብርቱ እንሆናለን፤
ጠላቶቻችንንም ከእግሩ በታች
የሚረግጥ እርሱ ነው።

## *መዝሙር* 109

### በጠላት ላይ የቀረበ ጸሎት

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1 የምስጋናዬ ምንጭ የሆንህ ሰ᎐ᎈ ሆይ፤
ዝም አትበል፤
2 ክፉዎችና አታላዮች፣
አፋቸውን ከፍተውብኛልና፤
በውሸተኛ አንደበት ተናግረውብኛል።
3 በጥላቻ ቃል ከበውኛል፤
ያለ ምክንያትም ጥቃት አድርሰውብኛል።
4 ስወዳቸው ይወነጅሉኛል፤
እኔ ግን እጸልያለሁ።
5 በበጎ ፈንታ ክፋትን፣
በወደድኋቸው ፈንታ ጥላቻን
ይመልሱልኛል።

6 ክፉ ሰው[ጎ] በላዩ ሹም፤
ከሳሽም[ነ] በቀኙ ይቁም።
7 ፍርድ ፊት ሲቆም በደለኛ ሆኖ ይገኝ፤
ጸሎቱም ለፍርድ ትሁንበት።
8 ዕድሜው ይጠር፤
ሹመቱንም ሌላ ይወሰደው።
9 ልጆቹ ድኻ አደጎች ይሁኑ፤
ሚስቱም መበለት ትሁን።
10 ልጆቹ ይንከራተቱ፤ ለማኞችም ይሁኑ፤
ከፈረሰው ቤታቸውም ይሰደዱ።
11 ያለውን ሁሉ ዕዳ ጠያቂ ይውረሰው፤
የድካሙንም ዋጋ ባዕዳን ይቀሙት።
12 ማንም ሰው ምሕረት አያድርግለት፤
ለድኻ አደግ ልጆቹም የሚራራ
አይኑር።
13 ዘሩ ተለይቶ ይጥፋ፤
ስማቸውም በሚቀጥለው ትውልድ
ይደምሰስ።
14 የአባቶቹ በደል *በእግዚአብሔር* ፊት
ይታሰብ፤
የእናቱም ኀጢአት አይደምሰስ።
15 መታሰቢያቸውን ከምድር ያጠፋ ዘንድ፣
ኀጢአታቸው ሁልጊዜ *በእግዚአብሔር*
ፊት ይኑር፤
16 ችግረኛውንና ምስኪኑን፣ ልቡም
የቈሰለውን፣

107፥39 2ነገ10፥32፤ መዝ44፥9፤ሕዝ5፥12
107፥40 ዘዳ32፥10፤ ኢዮ12፥18
107፥41 1ሳሙ2፥8፤ ኢዮ21፥11፤ መዝ 113፥7-9
107፥42 ኢዮ5፥16፤ 22፥19፤መዝ97፥10-12፤ ሮሜ3፥19
107፥43 መዝ103፥ 11፤ኤር9፥12፤ ሆሴ14፥9
108፥1 መዝ18፥49፤ 112፥7፤119፥30፡112
108፥2 ኢዮ21፥12
108፥4 ዘፀ34፥6፤ ዘኍ14፥18፤ መዝ36፥5፤106፥45
108፥5 መዝ8፥1፤ 57፥5
108፥6 ኢዮ40፥14
108፥7 ዘፍ12፥6፤ 33፥17፤መዝ68፥35፤ 89፥35፤102፥19
108፥8 መዝ78፥68
108፥9 ዘፍ19፥37፤ 2ሳሙ8፥1፡13-14
108፥11 መዝ44፥9
108፥12 መዝ118፥8 ፤146፥3፤ኢሳ10፥3፤ 30፥5፤31፥3፤ ኤር2፥36፤17፥5
108፥13 መዝ44፥5 ፤ኢሳ22፥5፤63፥3፡6
109፥1 ዘፀ15፥2፤ ኢዮ 34፥29፤ ኤር17፥14
109፥2 መዝ43፥1፤ 52፥4
109፥3 መዝ35፥7፤ 69፥4፤ዮሐ15፥25
109፥4 መዝ69፥13 ፤141፥5
109፥5 ዘፍ44፥4
109፥6 1ዜና21፥1፤ ኢዮ1፥6፤ዘካ3፥1
109፥7 መዝ1፥5፤ ምሳ28፥9፤ኢሳ41፥24
109፥8 ኢዮ15፥32፤ ሐሥ1፥20
109፥9 ዘፀ22፥24፤ ኤር18፥21
109፥10 ዘፍ4፥12
109፥11 ዘኍ14፥3፤ ነህ5፥3፤ኢዮ20፥18፤ ኢሳ1፥7፤6፥11፤ 36፥1፤ ሰቆ5፥2
109፥12 ኢዮ5፥4
109፥13 ዘኍ14፥12 ፤ኢዮ18፥19፤መዝ9፥5፤ 21፥10፤ምሳ10፥7
109፥14 ዘፀ20፥5፤ ዘኍ14፥18፤ኢሳ 65፥6-7፤ኤር32፥18
109፥15 ዘፀ17፥14፤ ዘዳ32፥26፤መዝ90፥8
109፥16 ኢዮ20፥19 ፤መዝ34፥18፤35፥10

[ጎ]6 ወይም *ክፉው*
[ነ]6 ወይም *ሰይጣንን*

እስከ ሞት አሳደደ እንጂ፣
ምሕረት ያደርግ ዘንድ አላሰበምና::
17መራገምን ወደደ፤
ወደ እርሱም መጣች፤
በመባረክ ደስ አልተሰኘም፤
በረከትም ከእርሱ ራቀች::
18መርገምን እንደ ልብስ ለበሳት፤
እርሷም እንደ ውሃ ወደ ውስጥ
ሰውነቱ፤
እንደ ዘይትም ወደ ዐጥንቱ ዘለቀች::
19ገላውን እንደሚሸፍንበት ልብስ፣
ዘወትር እንደሚታጠቀውም መቀነት
ትሁነው::
20እግዚአብሔር ለሚወነጅሉኝ ሰዎች፣
በነፍሴም ላይ ክፉ ለሚናገሩ
የሚከፍላቸው ይኸው ይሁን::

21አንተ ግን ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፤
ስለ ስምህ በበጎ ተመልከተኝ፤
ምሕረትህም መልካም ናትና አድነኝ::
22እኔ ድኻና ችግረኛ ነኝና፤
ልቤም በውስጤ ቈስሎአልና::
23እንደ ምሽት ጥላ ከእይታ ተሰውሬአለሁ፤
እንደ አንበጣም ረግፌአለሁ::
24ከጾም የተነሣ ጕልበቴ ዛለ፤
ሰውነቴም ከስቶ ዐመድ ለበሰ::
25ለመሣለቂያ ሆንሁላቸው፤
ሲያዩኝም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ::

26እግዚአብሔር አምላኬ ሆይ፤ ርዳኝ፤
እንደ ምሕረትህም አድነኝ::
27እግዚአብሔር ሆይ፤ እጅህ ይህን
እንዳደረገች፣
አንተም ይህን እንደ ፈጸምህ ይወቁ::
28እነርሱ ይራገማሉ፤ አንተ ግን
ትባርካለህ፤
በሚነሡበት ጊዜ ይዋረዳሉ፤
ባሪያህ ግን ሐሤት ያደርጋል::
29የሚወነጅሉኝ ውርደትን ይከናነቡ፤
ዕፍረትንም እንደ ሸማ ይልበሱ::

30እግዚአብሔርን በአንደበቴ እጅግ
አመሰግናለሁ፤
በታላቅ ሕዝብም መካከል አወድሰዋለሁ::
31በነፍሱ ላይ ከሚፈርዱት ያድነው
ዘንድ፣
እርሱ በችግረኛው ቀኝ በኩል
ይቆማልና::

## መዝሙር 110

### መሲሑ ንጉሥና ካህን

የዳዊት መዝሙር

1እግዚአብሔር ጌታዬን፣
"ጠላቶችህን ለእግርህ መርገጫ፣
እስከማደርግልህ ድረስ፣
በቀኜ ተቀመጥ" አለው::

2እግዚአብሔር ብርቱ በትርህን ከጽዮን
ወደ ውጭ ይሰዳል፤
አንተም በጠላቶችህ መካከል ሆነህ
ትገዛለህ::
3ለጦርነት በምትወጣበት ቀን፣
ሰራዊትህ በገዛ ፈቃዱ በጐንህ
ይቆማል፤
ከንጋት ማሕፀን፣
በቅዱስ ግርማ ደምቀህ፣
የጕልማሳነትህን ልምላሜ[ኘ] እንደ ጠል
ትቀበላለህ::

4"እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዐት፤
አንተ ለዘላለም ካህን ነህ" ብሎ፣
እግዚአብሔር ምሎአል፤
እርሱ ሐሳቡን አይለውጥም::

5ጌታ በቀኝህ ነው፤
በቍጣውም ቀን ነገሥታትን
ያደቃቸዋል::
6በሕዝቦች መካከል ይፈርዳል፤
በየአገሩ ያሉትንም ራሶች ከስክሶ
ሬሳ በሬሳ ያደርጋቸዋል::
7መንገድ[አ] ዳር ካለች ፈሳሽ ውሃ
ይጠጣል፤
ስለዚህ ራሱን ቀና ያደርጋል::

## መዝሙር 111[ከ]

### ለመለኮቱ ባሕርያት የቀረበ ጸሎት

1ሃሌ ሉያ::

በቅኖች ሸንጎ፣ በጉባኤም መካከል፣
ለእግዚአብሔር በፍጹም ልቤ ምስጋና
አቀርባለሁ::

2የእግዚአሔር ሥራ ታላቅ ናት፤
ደስ የሚሰኙባትም ሁሉ ያውጠነጥኗታል::
3ሥራው ባለ ክብርና ባለ ግርማ ነው፤
ጽድቁም ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል::
4ድንቅ ሥራው ሲታወስ እንዲኖር
አደረገ፤
እግዚአብሔር ቸር፣ ርኅሩኅም ነው::
5ለሚፈሩት ምግብን ይሰጣል፤
ኪዳኑንም ለዘላለም ያስባል::
6ለሕዝቡ የአሕዛብን ርስት በመስጠት፣
የአሠራሩን ብርታት አሳይቶአል::
7የእጆቹ ሥራ እውነተኛና ቅን ነው፤
ሥርዐቱም ሁሉ የታመነ ነው፤

109፥17 ምሳ28፥27፤ማቴ7፥2
109፥18 ዘኍ5፥22፤መዝ10፥7
109፥19 ቀኍ29፤መዝ73፥6፤ሕዝ7፥27
109፥20 ዘፀ32፥34፤መዝ54፥5፤71፥10፤94፥23፤ኢሳ3፥11፤2ጢሞ4፥14
109፥21 ዘፀ9፥16፤መዝ3፥7፤23፥3፤69፥16
109፥23 ኢዮ14፥2
109፥24 ኢዮ16፥8፤መዝ35፥13፤ዕብ12፥12
109፥25 ኢዮ16፥4፤መዝ22፥6፤ማቴ27፥39፤ማር15፥29
109፥26 መዝ12፥1፤119፥86
109፥27 ኢዮ37፥7
109፥28 2ሳሙ16፥12፤መዝ66፥4፤ኢሳ35፥10፤51፥11፤54፥1፤65፥14
109፥29 መዝ35፥26
109፥30 መዝ35፥18
109፥31 መዝ16፥8፤108፥6
110፥1 ኢሱ10፥24፤1ነገ5፥3፤ማቴ22፥44፤ማር12፥36፤16፥19፤ሉቃ20፥42፤ሐሥ2፥34፤1ቆሮ15፥25፤ዕብ1፥13፤12፥2
110፥2 ዘፍ49፥10፤መዝ2፥6፤45፥6፤72፥8፤ኢሳ14፥5፤ኤር48፥17
110፥3 ዘፀ15፥11፤ሚክ5፥7
110፥4 ዘፍ14፥18፤ዘኍ23፥19፤ዘካ6፥13፤ዕብ5፥6፡10፤7፥15-17፡21
110፥5 ዘዳ7፥24፤መዝ2፥5፡12፤16፥8፤68፥21፤76፥12፤ኢሳ60፥12፤ዳን2፥44፤ሮሜ2፥5፤ራእ6፥17፤11፥18
110፥6 መዝ9፥19፤18፥38፤ኢሳ5፥25፤34፥3፤66፥24
110፥7 መዝ3፥3፤27፥6
111፥1 መዝ1፥5፤9፥1፤34፥1፤89፥7፤109፥30፤115፥18፤145፥10
111፥2 ኢዮ36፥24፤መዝ64፥9፤143፥5፤ራእ15፥3
111፥3 መዝ112፥3፡9፤119፥142
111፥4 ዘዳ4፥31፤መዝ86፥15
111፥5 ዘፍ1፥30፤1ዜና16፥15፤መዝ37፥25፤103፥11፤105፥8፤ማቴ6፥31-33
111፥6 መዝ64፥9፤66፥3፡5፤105፥44
111፥7 መዝ19፥7፤ 92፥4፤119፥128

[ኘ]3 ወይም *ጐልማሶችህ እንደ ንጋት ወዳንተ ይመጣሉ* ማለት ነው::
[አ]7 ወይም *ሥልጣን ለመስጠት ኀይል ያለው ሥልጣን ላይ ያስቀምጠዋል*
[ከ]መዝሙር 111 የግጥሙ መሥመሮች እያንዳንዳቸው ከላይ እስከታች በተከታታይ በዕብራይስጥ ፊደሎች ቅደም ተከተል የተቀመጡ ናቸው::

8 ከዘላለም እስከ ለዘላለም የጸና ነው፤
በእውነትና በቅንነትም የተሠራ ነው።
9 ለሕዝቡ መዳንን ሰደደ፤
ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ፤
ስሙም የተቀደሰና የተፈራ ነው።
10 እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ
መጀምሪያ ነው፤
ትእዛዙንም የሚፈጽሙ ጥሩ ማስተዋል
አላቸው፤
ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል።

## መዝሙር 112

### የጻድቅ ሰው ባሕርይ

1 ሃሌ ሉያ።[ኸ]

እግዚአብሔርን የሚፈራ፣
በትእዛዙም እጅግ ደስ የሚሰኝ
የተባረከ ነው።

2 ዘሩ በምድር ላይ ኀያል ይሆናል፤
የቅኖች ትውልድ ትባረካለች።
3 ሀብትና ብልጽግና በቤቱ ይሞላል፤
ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል።
4 ቸር፣ ርኅሩኅና ጻድቅ እንደ መሆኑ፣
ለቅን ሰው በጨለማ ውስጥ ብርሃን
ይወጣለታል።
5 ለጋስና ያለ ማንገራገር የሚያበድር፣
ሥራውንም በትክክል የሚያከናውን
ሰው መልካም ይሆንለታል፤
6 ለዘላለም ከስፍራው አይናወጥምና፤
ጻድቅ ሰው[ወ] ሲታወስ ይኖራል።
7 ክፉ ወሬ አያሸብረውም፤
ልቡ እግዚአብሔርን በመተማመን የጸና
ነው።
8 ልቡ የጸና ነው፤ አይፈራምም፤
በመጨረሻም የጠላቶቹን ውድቀት ያያል።
9 በልግስና ለድኾች ሰጠ፤
ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል፤
ቀንዱም[ዐ] በክብር ከፍ ከፍ ይላል።

10 ክፉ ሰው ይህን በማየት ይበሳጫል፤
ጥርሱን ያፋጫል፤ እየመነመነም
ይጠፋል፤
የክፉዎችም ምኞት ትጠፋለች።

## መዝሙር 113

### ለታላቁና ለመሓሪው ጌታ ምስጋና

1 ሃሌ ሉያ።[ዘ]

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆይ፤
አመስግኑት፤
የእግዚአብሔርን ስም አወድሱ።
2 ከአሁን እስከ ዘላለም፣
የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።
3 ከፀሓይ መውጫ እስከ መግቢያው
ድረስ፣
የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን።
4 እግዚአብሔር ከሕዝቦች ሁሉ በላይ ከፍ
ያለ ነው፤
ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው።
5 እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር፣
በላይ በዙፋኑ የተቀመጠ ማን ነው?
6 በሰማይና በምድር ያሉትንስ ለማየት፣
ራሱን ወደ ታች ዝቅ የሚያደርግ ማን
ነው?
7 ድኻውን ከትቢያ ያነሣል፤
ችግረኛውን ከዐመድ ከፍ ከፍ ያደርጋል፤
8 ከመኳንንትም እኩል ስፍራ ይሰጠዋል፤
ከሕዝቡም ሹማምት ጋር
ያስቀምጠዋል።
9 መካኒቱን ሴት በቤት ያኖራታል፤
ደስተኛም የልጆች እናት ያደርጋታል።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 114

### ለፋሲካ የቀረበ ውዳሴ

1 እስራኤል ከግብፅ ወጥቶ ሲሄድ፣
የያዕቆብም ቤት ቋንቋው ልዩ ከሆነ
ሕዝብ ተለይቶ ሲወጣ፣
2 ይሁዳ የእግዚአብሔር መቅደስ፣
እስራኤልም ግዛቱ ሆነ።

3 ባሕር አየች፤ ሸሸችም፤
ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ።
4 ተራሮች እንደ አውራ በግ፣
ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ዘለሉ።

5 አንቺ ባሕር፤ የሸሸሽው
አንቺም ዮርዳኖስ ያፈገፈግሽው
ለምንድን ነው?
6 እናንተ ተራሮች እንደ አውራ በግ፣
ኰረብቶችም እንደ ጠቦት ለምን
ዘለላችሁ?

7 ምድር ሆይ፤ በጌታ ፊት፣
በያዕቆብ አምላክ ፊት ተንቀጥቀጪ፤
8 እርሱ ዐለቱን ወደ ኩሬ፤
ቋጥኙንም ወደ ውሃ ምንጭ ለወጠ።

## መዝሙር 115

### አንዱ እውነተኛው አምላክ

115፥4-11 ተጓ ምብ-መዝ135፥15-20

1 ለእኛ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ሆይ፤
ለእኛ ሳይሆን፣
ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ፣

111፥8 መዝ119፥89፡152፡160፤ኢሳ40፥8፤ማቴ5፥18
111፥9 መዝ30፥4፤34፥22፤99፥3፤103፥4፤130፥7፤ሉቃ1፥49፡68
111፥10 ዘዳ4፥6፤ኢዮ23፥12፤መዝ19፥9፤28፥6፤89፥52፤119፥98፡104፡130
112፥1 ኢዮ1፥8፤መዝ1፥1-2፤33፥2፤103፥1፡11፤115፥13፤119፥14፡16፡47፡92፤128፥1
112፥2 መዝ25፥13፤37፥26፤128፥2-4
112፥3 ዘዳ8፥18፤መዝ 37፥6፤111፥3
112፥4 መዝ5፥12፤18፥28
112፥5 መዝ37፥21፡26፤ሉቃ6፥35
112፥6 መዝ15፥5፤55፥22፤ምሳ10፥7፤መክ2፥16
112፥7 መዝ28፥7፤56፥3-4፤57፥7፤108፥1፤ኢሳ12፥2
112፥8 መዝ3፥6፤27፥1፤54፥7፤56፥11፤ምሳ1፥33፤ኢሳ12፥2
112፥9 መዝ75፥10፤111፥3፤ሉቃ19፥8፤ሐሥ9፥36፤2ቆሮ9፥9
112፥10 ኢዮ8፥13፤መዝ34፥21፤37፥12፤86፥17፤ማቴ8፥12
113፥1 መዝ22፥23፤34፥22፤103፥21፤134፥1
113፥2 መዝ30፥4፤48፥10፤115፥18፤131፥3፤145፥21፤148፥13፤149፥3፤ኢሳ12፥4፤ዳን2፥20
113፥3 ኢሳ24፥15፤45፥6፤59፥19፤ሚል1፥11
113፥4 መዝ8፥1፤57፥11፤99፥2
113፥5 ዘፀ8፥10፤ኢዮ16፥19፤መዝ35፥10፤103፥19
113፥6 መዝ11፥4፤138፥6፤ኢሳ57፥15
113፥7 1ሳሙ2፥8፤መዝ35፥10፤68፥10፤107፥41፤140፥12
113፥8 2ሳሙ9፥11
113፥9 1ሳሙ2፥5
114፥1 ዘፀ13፥3፤29፥46
114፥2 ዘፀ15፥17፤መዝ76፥1፤78፥68-69
114፥3፤ ዘፀ14፥21፤15፥8፤ኢሱ3፥16፤መዝ77፥16
114፥4 መሳ5፥5
114፥5 ዘፀ14፥21
114፥7 ዘፀ15፥14፤1ዜና16፥30
114፥8 ዘፀ17፥6፤ ዘኍ20፥11
115፥1 ዘፀ34፥6፤መዝ29፥2፤66፥2፤96፥8

ኸ1 እግዚአብሔር ይመስገን ማለት ነው።
ወ6 ወይም እግዚአብሔር ቸር ርኅሩኅና ጻድቅ ስለ ሆነ
ዐ9 በዚህ ስፍራ ክብርን ያመለክታል።
ዘ1 እግዚአብሔር ይመስገን ማለት ሲሆን፣ በቍ9 ላይም ይገኛል።

ለስምህ ክብርን ስጥ፡፡
2አሕዛብ፣ “አምላካቸው የት አለ?”
ለምን ይበሉ?
3አምላካችንስ በሰማይ ነው፤
እርሱ ደስ የሚለውን ያደርጋል፡፡
4የእነርሱ ጣዖታት ግን የሰው እጅ የሠራቸው፣
ብርና ወርቅ ናቸው፡፡
5አፍ አላቸው፤ አይናገሩም፤
ዐይን አላቸው፤ አያዩም፣
6ጆሮ አላቸው፤ አይሰሙም፤
አፍንጫ አላቸው፤ አያሸቱትም፤
7እጅ አላቸው፤ አይዳስሱም፤
እግር አላቸው፤ አይሄዱም፤
በጒሮሮአቸውም ድምፅ አይፈጥሩም፡፡
8እነዚህን የሚያበጁ፣
የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ
ይሁኑ፡፡

9የእስራኤል ቤት ሆይ፤ *በእግዚአብሔር*
*ታመኑ፤*
ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው፡፡
10የአሮን ቤት ሆይ፤ *በእግዚአብሔር ታመኑ፤*
ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው፡፡
11እናንተ *እግዚአብሔርን* የምትፈሩ ሆይ፤
*በእግዚአብሔር ታመኑ፤*
ረዳታቸውና ጋሻቸው እርሱ ነው፡፡

12*እግዚአብሔር* ያስበናል፤ ይባርከናልም፤
እርሱ የእስራኤልን ቤት ይባርካል፤
የአሮንንም ቤት ይባርካል፡፡
13*እግዚአብሔርን* የሚፈሩትን ሁሉ፣
ትልቁንም ትንሹንም ይባርካል፡፡

14*እግዚአብሔር* እናንተንና ልጆቻችሁን፣
በባርኮቱ ያብዛችሁ፡፡
15ሰማይንና ምድርን በፈጠረ፣
*በእግዚአብሔር* የተባረካችሁ ሁኑ፡፡

16ሰማየ ሰማያት *የእግዚአብሔር* ናቸው፤
ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት፡፡
17*እግዚአብሔርን* የሚያመሰግኑት
የሞቱት አይደሉም፤
ወደ ዝምታው ዓለም የሚወርዱም
አይደሉም፡፡
18ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
*እግዚአብሔርን* የምንባርክ እኛ ነን፡፡
*እግዚአብሔር* ይመስገን፡፡[ቸ]

## መዝሙር 116

### ምስጋና

1የልመናዬን ድምፅ ሰምቶአልና፣
*እግዚአብሔርን* ወደድሁት፡፡
2ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና፣
በሕይወት ዘመኔ ሁሉ ወደ እርሱ
እጣራለሁ፡፡

3የሞት ወጥመድ ያዘኝ፤
የሲኦልም[የ] ጣር አገኘኝ፤
ጭንቅና ሐዘን አሸነፈኝ፡፡
4እኔም *የእግዚአብሔርን* ስም ጠራሁ፤
“*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ነፍሴን ታድናት
ዘንድ እለምንሃለሁ” አልሁ፡፡

5*እግዚአብሔር* ቸርና ጻድቅ ነው፤
አምላካችን መሓሪ ነው፡፡
6*እግዚአብሔር* ገሮችን ይጠብቃል፤
እጅግ ተቸግሬ ሳለሁ አዳነኝ፡፡

7ነፍሴ ሆይ፤ ወደ ዕረፍትሽ ተመለሺ፤
*እግዚአብሔር* መልካም አድርጎልሻልና፤

8አንተ ነፍሴን ከሞት፣
ዐይኔን ከእንባ፣
እግሮቼን ከመሰናከል አድነሃልና፡፡
9እኔም በሕያዋን ምድር፣
*በእግዚአብሔር* ፊት እመላለሳለሁ፡፡

10“እጅግ ተጨንቄአለሁ” ባልሁበት ጊዜ
እንኳ፣[ደ]
እምነቴን ጠብቄአለሁ፡፡
11ግራ በተጋባሁ ጊዜ፣
“ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው” አልሁ፡፡

12ስለ ዋለልኝ ውለታ ሁሉ፣
*ለእግዚአብሔር* ምን ልክፈለው?
13የመዳንን ጽዋ አነሣለሁ፤
*የእግዚአብሔርንም* ስም እጠራለሁ፡፡
14በሕዝቡ ሁሉ ፊት፣
ስእለቴን *ለእግዚአብሔር* እፈጽማለሁ፡፡
15የቅዱሳኑ ሞት፣
*በእግዚአብሔር* ፊት የተከበረ ነው፡፡
16*እግዚአብሔር* ሆይ፤ እኔ በእውነት
ባሪያህ ነኝ፤
እኔ የሴት ባሪያህ[ጀ] ልጅ፣ ባሪያህ ነኝ፣
ከእስራቴም ፈታኸኝ፡፡

17ለአንተ የምስጋና መሥዋዕት አቀርባለሁ፤
*የእግዚአብሔርንም* ስም እጠራለሁ፡፡
18በሕዝቡ ሁሉ ፊት፣
ስእለቴን *ለእግዚአብሔር* እፈጽማለሁ፤
19ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ይህን በመካከልሽ፣
*በእግዚአብሔር* ቤት አደባባይ አደርጋለሁ፡፡

ሃሌ ሉያ፡፡[ገ]

## መዝሙር 117

### የምስጋና ጥሪ

1አሕዛብ ሁላችሁ፤ *እግዚአብሔርን*

115፥2 መዝ42፥3
115፥3 ዕዝ5፥11፤ ነህ1፥4፤መዝ103፥19፤ 135፥6፤136፥26፤ ማቴ6፥9
115፥4 2ነገ19፥18 ፤2ዜና32፥19፤ ኤር10፥3-5፤ ሐሥ19፥26፤ራእ9፥20
115፥5 ኤር10፥5
115፥9 መዝ37፥3፤ 62፥8
115፥10 ዘፀ30፥30፤ መዝ118፥3
115፥11መዝ22፥23 ፤103፥11፤118፥4
115፥12 ዘፍ12፥2፤ 1ዜና16፥15
115፥13መዝ112፥1
115፥14 ዘዳ1፥11
115፥15 ዘፍ1፥1፤ ሐሥ14፥15፤ ራእ10፥6
115፥16 ዘፍ1፥28፤ መዝ8፥6-8፤89፥11
115፥17 መዝ88፥ 10-12
115፥18 መዝ28፥6 ፤33፥2፤103፥1፤ 111፥1፤113፥2
116፥1 መዝ6፥9፤ 18፥1፤28፥2፤ 31፥22፤40፥1
116፥2 መዝ5፥1
116፥3 2ሳሙ22፥6 ፤መዝ18፥4-5
116፥4 መዝ80፥2፡ 18፤118፥5
116፥5 ዘፀ9፥27፤ 22፥27፤2ዜና12፥6፤ ዕዝ9፥15፤መዝ86፥15
116፥6 መዝ18፥3፤ 22፥5፤79፥8፤107፥13
116፥7 መዝ13፥6፤ 46፥10፤62፥1፤106፥1 ፤131፥2፤142፥7፤ ማቴ11፥29
116፥8 መዝ86፥13
116፥9 ዘፍ5፥22፤ ኢዮ28፥13፤መዝ27፥13፤ 56፥13፤89፥15፤ ኢሳ38፥11፤ኤር11፥19
116፥10 መዝ9፥18 ፤72፥2፤107፥17፤119 ፥67፡71፡75፤2ቆሮ4፥13
116፥11 ኤር9፥3-5 ፤ሆሴ7፥13፤ሚክ6፥12 ፤ሮሜ3፥4
116፥12መዝ103፥2 ፤106፥1
116፥13መዝ105፥1
116፥14 ዘኍ30፥2፤ መዝ66፥13
116፥15ዘኍ23፥10 ፤መዝ72፥14
116፥16 ኢዮ12፥18 ፤መዝ86፥16፤ 119፥125፤143፥12
116፥17 ዘሌ7፥12 ፤ዕዝ1፥4
116፥18 ቆኍ14፤ ዘሌ22፥18 116፥19 መዝ92፥13፤96፥8፤100፥4፤102፥21፤ 135፥2 117፥1 መዝ22፥23፤103፥2፤ሮሜ15፥11

[ቸ]18 ዕብራይስጡ *ሃሌ ሉያ* ይላል፡፡
[የ]3 ዕብራይስጡ *ሲኦል* ይላል፡፡
[ደ]10 ወይም *ያኔ እንኳን*
[ጀ]16 *ታማኝ አገልጋይህ* ወይም *ታማኝ ልጅህ*
[ገ]19 አንዳንዶች *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ፡፡

አመስግኑት፤
ሕዝቦችም ሁሉ፤ በምስጋና ከፍ ከፍ
አድርጉት፤
[2]እርሱ ለእኛ ያሳየው ምሕረት ታላቅ
ነውና፤
የእግዚአብሔርም ታማኝነት ጸንቶ
ይኖራል።

ሃሌ ሉያ።[ጣ]

## መዝሙር 118

### ለዳስ በዓል የቀረበ የጉዞ መዝሙር

[1]እግዚአብሔር ቸር ነውና አመስግኑት፤
ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

[2]የእስራኤል ሕዝብ፣
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” ይበል።
[3]የአሮን ቤት፣
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” ይበል።
[4]እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ፣
“ምሕረቱ ለዘላለም ነው” ይበሉ።

[5]በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፤
እግዚአብሔርም መለሰልኝ፤ ከመጠ
በብም አወጣኝ።
[6]እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው፤ አልፈራም፤
ሰው ምን ሊያደርገኝ ይችላል?
[7]ይረዳኝ ዘንድ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር
ነው፤
የጠላቶቼንም ውድቀት አያለሁ።

[8]ሰውን መከታ ከማድረግ ይልቅ፣
በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።
[9]በገዦች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ፣
በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።

[10]ሕዝቦች ሁሉ ከበቡኝ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም
አስወግዳቸዋለሁ።
[11]መክበቡንስ በየአቅጣጫው ከበቡኝ፤
ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም
አስወገዳቸዋለሁ።
[12]እንደ ንብ መንጋ ከበቡኝ፤
ነገር ግን እንደሚነድ እሾኽ ከሰሙ፤
በርግጥም በእግዚአብሔር ስም
አስወግዳቸዋለሁ።

[13]ተገፍትሬ ልወድቅ ተንገደገድሁ፤
እግዚአብሔር ግን ረዳኝ።
[14]እግዚአብሔር ብርታቴና ዝማሬዬ ነው፤
አዳኝ ሆነልኝ።

[15]በጻድቃን ድንኳን የእልልታና የሆታ
ድምፅ፣
እንዲህ እያለ ያስተጋባል፤
“የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ብርቱ ሥራ
ሠራች፤
[16]የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ከፍ ከፍ

117፥2 መዝ17፥7፤ 103፥11፤119፥90፤ 146፥6
118፥1 1ዜና16፥8፤ 2ዜና5፥13፤7፥3፤ ዕዝ 3፥11
118፥2 መዝ106፥1 ፤115፥9፤136፥1-26
118፥3 ዘፀ30፥30፤ መዝ115፥10
118፥4መዝ115፥11
118፥5 ቍ21፤ መዝ 18፥6፤31፥7፤ 34፥4፤77፥2፤86፥7፤ 116፥1፤120፥1፤138፥3
118፥6 ዘዳ31፥6፤ መዝ56፥4፤ዕብ13፥5
118፥7 ዘዳ33፥29፤ መዝ54፥7፤ዕብ13፥6
118፥8 2ዜና32፥7-8፤መዝ2፥12፤5፥11፤ 9፥9፤37፥3፤40፥4፤ 108፥12፤ኢሳ2፥22፤ 25፥4፤57፥13
118፥9 መዝ146፥3
118፥10 መዝ37፥9
118፥11 መዝ3፥6፤ 88፥17
118፥12 ዘዳ1፥44፤ መዝ37፥9፤58፥9
118፥13 ቍ7፤ 2ዜና 18፥31፤ መዝ86፥17
118፥14 ዘፀ15፥2፤ መዝ62፥2
118፥15 ዘፀ15፥6፤ ኢዮ8፥21፤ መዝ89፥13፤106፥5፤ 108፥6፤ሉቃ1፥51
118፥17 ዘዳ32፥3፤ መዝ64፥9፤71፥16፤ 73፥28፤ዕን1፥12
118፥18መዝ86፥13 ፤ኤር31፥18፤ 1ቆሮ11፥32፤ዕብ12፥5
118፥19 መዝ24፥7፤ 100፥4
118፥20 መዝ15፥1-2፤ 24፥3-4፤122፥1-2፤ ራእ22፥14
118፥21 ቍ5፤ መዝ 27፥1
118፥22 ኢሳ8፥14፤ 17፥10፤19፥13፤28፥16 ፤ ዘካ4፥7፤10፥4፤ ማቴ21፥42፤ማር 12፥10፤ሉቃ20፥17፤ ሐሥ4፥11፤1ጴጥ2፥7
118፥23 ማቴ21፥42 ፤ማር12፥11
118፥24 መዝ70፥4
118፥25 መዝ28፥9 ፤116፥4
118፥26መዝ129፥8 ፤ማቴ11፥3፤21፥9፤ 23፥39፤ማር11፥9፤ ሉቃ13፥35፤19፥38፤ ዮሐ12፥13
118፥27 ዘፀ27፥2፤ ዘሌ23፥40፤1ነገ18፥21 ፤መዝ27፥1፤ኢሳ58፥10፤ 60፥1፡19፡20

አለች፤
የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ብርቱ ሥራ
ሠራች።

[17]ተርፌ በሕይወት እኖራለሁ እንጂ
አልሞትም፤
የእግዚአብሔርንም ሥራ ገና እናገራለሁ።
[18]መገሠጹን እግዚአብሔር እጅግ
ገሥጾኛል፤
ነገር ግን ለሞት አሳልፎ አልሰጠኝም።

[19]የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ፤
በዚያ ገብቼ እግዚአብሔርን
አመሰግናለሁ።
[20]ይህች የእግዚአብሔር ደጅ ናት፤
ጻድቃን በእርሷ በኩል ይገባሉ።
[21]ሰምተህ መልሰህልኛልና፣
አዳኝም ሆነህልኛልና አመሰግንሃለሁ።

[22]ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፣
እርሱ የማእዘን ራስ ሆነ።
[23]እግዚአብሔር ይህን አደረገ፤
ለዐይናችንም ድንቅ ናት።
[24]እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት፤
በእርሷ ሐሤት እናድርግ፤ ደስም
ይበለን።
[25]እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ አድነን፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እባክህ አሳካልን።
[26]በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ
ነው።
ከእግዚአብሔር ቤት ባረክናችሁ።
[27]እግዚአብሔር አምላክ ነው፤
ብርሃኑንም በላያችን አበራ፤
እስከ መሠዊያው[ጨ] ቀንዶች ድረስ
በመውጣት፣
ዝንጣፊ ይዛችሁ በዓሉን ከሚያከብሩት
ጋር ተቀላቀሉ።

[28]አንተ አምላኬ ነህ፤ አመሰግንሃለሁ፤
አንተ አምላኬ ነህ፤ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።

[29]ቸር ነውና፣ እግዚአብሔርን አመስግኑ፤
ምሕረቱም ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች።

## መዝሙር 119[ጸ]

### ውዳሴ ለሕገ እግዚአብሔር

ℵ አሌፍ

[1]መንገዳቸው ነቀፋ የሌለበት፣

ሚል4፥2፤1ጴጥ2፥9
118፥28 ዘፍ28፥21 ፤ዘፀ15፥2፤መዝ16፥2 ፤63፥1፤ኢሳ25፥1
119፥1 ዘፍ17፥1፤ ዘዳ18፥13፤መዝ1፥2፤128፥1፤ምሳ11፥20

[ጣ]2 አንዳንዶች እግዚአብሔር ይመስገን ይላሉ።
[ጨ]27 ወይም የክብረ በዓልን መሥዋዕት በገመድ ማሰር ወይም መውሰድ
[ጸ]119 የዚህ መዝሙር የግጥም ስንኞች መነሻ ወይም መነሻና መድረሻ ሆህያት ቀ[ጉ]ልቀ[ጉ]ል ሲነበቡ ትርጉም አዘል ናቸው። እያንዳንዱ ስንኝ ተመሳሳይ በሆነ በዕብራይስጥ ፊደል ይጀምራል።

በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ የተባረኩ
ናቸው።
2ምስክርነቱን የሚጠብቁ፣
በፍጹምም ልብ የሚሹት የተባረኩ
ናቸው፤
3ዐመፅን አያደርጉም፤
ነገር ግን በመንገዱ ይሄዳሉ።
4ጠንቅቀን እንጠብቃት ዘንድ፣
አንተ ሥርዐትን አዘሃል።
5ሥርዐትህን እጠብቅ ዘንድ፣
ምነው መንገዴ ጽኑ በሆነልኝ ኖሮ!
6ወደ ትእዛዛትህ ስመለከት፣
በዚያን ጊዜ አላፍርም።
7የጽድቅ ፍርድህን ስማር፣
በቅን ልብ ምስጋና አቀርብልሃለሁ።
8ሥርዐትህን እጠብቃለሁ፤
ፈጽመህ አትተወኝ።

ב ቤት

9ጕልማሳ መንገዱን እንዴት ያነጻል?
በቃልህ መሠረት በመኖር ነው።
10በሙሉ ልቤ ፈለግሁህ፤
ከትእዛዛትህ ፈቀቅ እንዳልል አድርገኝ።
11አንተን እንዳልበድል፣
ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።
12እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ቡሩክ ነህ፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ።
13ከአንደበትህ የሚወጣውን ደንብ ሁሉ፣
በከንፈሬ እናገራለሁ።
14ሰው በሀብቱ ብዛት ደስ እንደሚለው፣
ምስክርነትህን በመከተል ደስ ይለኛል።
15ድንጋጌህን አሰላስላለሁ፤
ልቤን በመንገድህ ላይ ጥያለሁ።
16በሥርዐትህ ደስ ይለኛል፤
ቃልህንም አልዘነጋም።

ג ጋሜል

17ሕያው እንድሆን፣ ቃልህንም
እንድጠብቅ፣
ለአገልጋይህ መልካም አድርግ።
18ከሕግህ ድንቅ ነገርን እንዳይ፣
ዐይኖቼን ክፈት።
19እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝ፤
ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።
20ዘወትር ደንብህን በመናፈቅ፣
ነፍሴ እጅግ ዛለች።
21ከትእዛዛትህ የሳቱትን፣
እብሪተኞችንና ርጉሞችን ትገሥጻለህ።
22ምስክርነትህን ጠብቄአለሁና፣
ስድብንና ንቀትን ከእኔ አርቅ።
23ገዦች ተቀምጠው ቢዶልቱብኝ እንኳ፣
አገልጋይህ ሥርዐትህን ያሰላስላል።
24ምስክርነትህ ለእኔ ደስታዬ ነው፤
መካሪዬም ነው።

119፥2 ቍ146፤
ዘዳ 10፥12፤
መዝ40፥16፤ 99፥7፤
112፥1፤1ዜና16፥11፤
መዝ40፥16፤99፥7፤
112፥1፤ኢሳ56፥2
119፥3 መዝ59፥4፤
128፥1፤ኤር6፥16፤
7፥23፤1ዮሐ3፥9፤5፥18
119፥4 ቍ56፤
ዘዳ6፥17፤መዝ103፥18
119፥5 ዘሌ19፥37
119፥6 ቍ46፡80፡
117
119፥7 ዘዳ4፥8
119፥8 መዝ38፥21
119፥9 ቍ65፡169
፤መዝ39፥1
119፥10 ቍ21፡118
፤መዝ9፥1
119፥11 ቍ133፡
165፤ዘዳ6፥6፤
ኢዮ 22፥22፤
መዝ18፥22-23፤19፥13፤
ምሳ3፥23፤ኢሳ63፥13
119፥12 ዘፀ18፥20፤
መዝ28፥6፤143፥8፡10
119፥13 ቍ72
119፥14 ቍ111
119፥15 ቍ97፡
148፤መዝ1፥2
119፥16 መዝ112፥1
119፥17 ቍ67፤መዝ
13፥6፤103፥20፤116፥7
119፥19 ዘፍ23፥4፤
ዕብ11፥13
119፥20 ቍ131፤
መዝ42፥2፤63፥1፤
84፥2፤ኢሳ26፥9
119፥21 ቍ10፡51
፤ዘዳ27፥26፤ኢዮ30፥1
፤መዝ5፥5፤ኤር20፥7
፤50፥32፤ዳን4፥37፤
ሚል3፥15
119፥22 ቍ2፤
መዝ 39፥8
119፥25 ቍ9፡50፡
107፤መዝ44፥25፤
143፥11
119፥26 መዝ25፥4
፤27፥11፤86፥11
119፥27 መዝ105፥2
፤145፥5
119፥28 ቍ9፤
መዝ6፥7፤18፥1፤116፥3፤
ኢሳ40፥29፤41፥10፤
51፥11፤ኤር45፥3
119፥29 ዘኍ6፥25፤
መዝ26፥4
119፥30 ኢሱ24፥22
፤መዝ26፥3፤108፥1
119፥31 ዘዳ10፥20
119፥33 ቍ12
119፥34 ቍ27፡69፡
73፡144፡169፤ዘዳ6፥25
፤ኢዮ32፥8፤ምሳ2፥6፤
ዳን2፥21፤ያዕ1፥5
119፥35 ቍ32፤
መዝ 1፥2፤25፥4-5
119፥36 ኢሱ24፥23
፤ሕዝ33፥31

ד ዳሌጥ

25ነፍሴ ከዐፈር ተጣበቀች፤
እንደ ቃልህ መልሰህ ሕያው አድርገኝ።
26ስለ መንገዴ ገልጬ ነገርሁህ፤ አንተም
መለስህልኝ፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ።
27የድንጋጌህን መንገድ እንዳስተውል
አድርገኝ፤
እኔም ድንቅ ሥራህን አሰላስላለሁ።
28ነፍሴ በሐዘን ተዝለፈለፈች፤
እንደ ቃልህ አበርታኝ።
29የሸንገላን መንገድ ከእኔ አርቅ፤
ሕግህን በጸጋህ ስጠኝ።
30የእውነትን መንገድ መርጫለሁ፤
ሕግህንም ፊት ለፊቴ አድርጌአለሁ።
31እግዚአብሔር ሆይ፤ ከምስክርነትህ ጋር
ተጣብቄአለሁ፤
አሳልፈህ ለውርደት አትስጠኝ።
32ልቤን አስፍተህልኛልና፣
በትእዛዛትህ መንገድ እሮጣለሁ።

ה ሄ

33እግዚአብሔር ሆይ፤ የሥርዐትህን
መንገድ አስተምረኝ፤
እኔም እስከ መጨረሻው እጠብቀዋለሁ።
34ሕግህን እንድጠብቅ፣ በፍጹም ልቤም
እንድታዘዘው፣
ማስተዋልን ስጠኝ።
35በእርሷ ደስ ይለኛልና፣
በትእዛዝህ መንገድ ምራኝ።
36ከራስ ጥቅም ይልቅ፣
ልቤን ወደ ምስክርነትህ አዘንብል።
37ከንቱ ነገር ከማየት ዐይኖቼን መልስ፤
በራስህ መንገድ[a] እንደ ገና ሕያው
አድርገኝ።
38ትፈራ ዘንድ፣
ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል ፈጽም።
39የምፈራውን መዋረድ ከእኔ አርቅ፤
ደንብህ መልካም ነውና።
40እነሆ፤ ድንጋጌህን ናፈቅሁ፤
በጽድቅህ ሕያው አድርገኝ።

ו ዋው

41እግዚአብሔር ሆይ፤ ምሕረትህ ወደ እኔ
ይምጣ፤
ማዳንህም እንደ ቃልህ ይላክልኝ።
42በቃልህ ታምኛለሁና፣
ለሚሰድቡኝ መልስ እሰጣለሁ።
43ሕግህን ተስፋ አድርጌአለሁና፣

119፥37 ቍ9፡25፤መዝ71፥20 119፥38 ዘኍ23፥19 119፥39 ቍ22
መዝ69፥9፤89፥51፤ኢሳ25፥8፤51፥7፤54፥4 119፥40 ቍ20፡25፡
149፡154 119፥41 ቍ76፡116፡154፡170፤መዝ6፥4 119፥42 መዝ
42፥10፤ምሳ27፥11 119፥43 ቍ74፡81፡114፡147፤1ነገ17፥24

[a]37 አንዳንድ ትርጒሞች እንደ ቃልህ ይላሉ።

የእውነትን ቃል ከአፌ ፈጽመህ አታርቅ።
44ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ሕግህን ዘወትር እጠብቃለሁ።
45ሥርዐትህን እሻለሁና፣
እንደ ልቤ ወዲያ ወዲህ እመላለሳለሁ።
46ምስክርነትህን በነገሥታት ፊት እናገራለሁ፤
ይህን በማድረግም ዕፍረት አይሰማኝም።
47እኔ እወደዋለሁና፣
በትእዛዝህ ደስ ይለኛል።
48እጆቼን ወደምወዳቸው[θ] ትእዛዛትህ
አነሣለሁ፤
ሥርዐትህንም አሰላስላለሁ።

፣ ዛይ

49ለአገልጋይህ የገባኸውን ቃል ዐስብ፤
በዚያ ተስፋ ሰጥተኸኛልና።
50ቃልህ ሕያው ያደርገኛልና፣
ይህች በመከራዬ መጽናኛዬ ናት።
51እብሪተኞች እጅግ ተሣለቁብኝ፤
እኔ ግን ከሕግህ ንቅንቅ አላልሁም።
52እግዚአብሔር ሆይ፤ ከጥንት የነበረውን
ድንጋጌህን ዐሰብሁ፤
በዚህም ተጽናናሁ።
53ሕግህን ከተዉ ክፉዎች የተነሣ፣
ቍጣ ወረረኝ።
54በእንግድነቴ አገር፣
ሥርዐትህ መዝሙሬ ናት።
55እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህን በሌሊት
ዐስባለሁ፤
ሕግህንም እጠብቃለሁ።
56ሥርዐትህን እከተላለሁ፤
ይህችም ተግባሬ ሆነች።

ሸ ሔት

57እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው፤
ቃልህን ለመታዘዝ ቈርጫለሁ።
58በፍጹም ልቤ ፊትህን ፈለግሁ፤
እንደ ቃልህ ቸርነትህን አሳየኝ።
59መንገዴን ቃኘሁ፤
አካሄዴንም ወደ ምስክርህ አቀናሁ።
60ትእዛዝህን ለመጠበቅ፣
ቸኰልሁ፤ አልዘገየሁምም።
61የክፉዎች ገመድ ተተበተበብኝ፤
እኔ ግን ሕግህን አልረሳሁም።
62ስለ ጻድቅ ሥርዐትህ፣
በእኩለ ሌሊት ላመሰግንህ እነሣለሁ።
63እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ፣
ሥርዐትህንም ለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ።
64እግዚአብሔር ሆይ፤ ምድር በምሕረትህ
ተሞላች፤
ሥርዐትህን አስተምረኝ።

ፀ ጤት

65እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቃልህ፣
ለአገልጋይህ በጎ ውለሃል።
66በትእዛዛትህ አምናለሁና፣
በጎ ማስተዋልንና ዕውቀትን
አስተምረኝ።
67እንዲያው ሳይቸግረኝ መንገድ ስቼ
ሄድሁ፤
አሁን ግን ቃልህን እጠብቃለሁ።
68አንተ መልካም ነህ፤ የምታደርገው
መልካም ነው፤
እንግዲህ ሥርዐትህን አስተምረኝ።
69እብሪተኞች ስሜን በሐሰት አጠፉ፤
እኔ ግን ትእዛዝህን በፍጹም ልብ
እጠብቃለሁ።
70ልባቸው የሠባና የደነደነ ነው፤
እኔ ግን በሕግህ ደስ ይለኛል።
71ሥርዐትህን እማር ዘንድ፣
በመከራ ውስጥ ማለፌ መልካም ሆነልኝ።
72ከአእላፋት ብርና ወርቅ ይልቅ፣
ከአፍህ የሚወጣው ሕግ ይሻለኛል።

፣ ዮድ

73እጆችህ ሠሩኝ፤ አበጃጁኝም፤
ትእዛዛትህን እንድማር ማስተዋልን
ስጠኝ።
74ቃልህን ተስፋ አድርጌአለሁና፣
የሚፈሩህ እኔን አይተው ደስ
ይበላቸው።
75እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍርድህ የጽድቅ
ፍርድ፣
ያስጨነቅኸኝም በታማኝነት እንደ ሆነ
ዐወቅሁ።
76ለአገልጋይህ በገባኸው ቃል መሠረት፣
ምሕረትህ ለመጽናናት ትሁነኝ።
77ሕግህ ደስታዬ ነውና፣
በሕይወት እኖር ዘንድ ቸርነትህ
ትምጣልኝ።
78እብሪተኞች ያለ ምክንያት በደል
አድርሰውብኛልና ይፈሩ፤
እኔ ግን ትእዛዛትህን አሰላስላለሁ።
79አንተን የሚፈሩህ፣
ምስክርነትህንም የሚያውቁ ወደ
እኔ ይመለሱ።
80እኔ እንዳላፍር፤
ልቤ በሥርዐትህ ፍጹም ይሁን።

ፘ ካፍ

81ነፍሴ ማዳንህን እጅግ ናፈቀች፤
ቃልህንም ተስፋ አድርጋለሁ።

119፥44 ቍ33፡34፡55፤ዘጸ6፥25
115፥45ቍ94፡155
119፥46 ቍ6፤ማቴ 10፥18፤ሐሥ26፥1-2
119፥47 ቍ77፡97፡127፡143፡159፡163፡165፤መዝ112፥1
119፥48 ዘፍ24፥63
119፥49 ቍ9፡43
119፥50 ቍ25
119፥51 ቍ21፤ ኢዮ 16፥10፤17፥2፤23፥11
119፥52 መዝ103፥18
119፥53 ዘፀ32፥19፤33፥4፤መዝ89፥30
119፥54 ቍ172፤ መዝ101፥1፤138፥5
119፥55 ቍ44፡62፡72፤መዝ1፥2፤42፥8፤63፥6፤77፥2፤ኢሳ 26፥9፤ሐሥ16፥25
119፥56 ቍ4፡100፡134፡168፤ዘኍ15፥40
119፥57 ቍ17፡67፡101፤ዘዳ32፥9፤ ኤር51፥19፤ሰቆ3፥24
119፥58 ቍ41፤ ዘፍ43፥29፤ዘዳ4፥29፤1ዜና16፥11፤ዕዝ9፥8፤ መዝ 34፥4
119፥59ኢሱ24፥14-15፤መዝ39፥1
119፥60 ቍ115
119፥61 ቍ83፡109፡153፡176
119፥62 ቍ7፡55፤ሐሥ16፥25
119፥63 ቍ56፤ መዝ15፥4፤101፥6-7፤103፥11፤111፥10
119፥64 ቍ12፡108፤መዝ33፥5
119፥65 ቍ9፡17፤ መዝ125፥4፤50፥2፤59፥1፤ሚክ2፥7
119፥66 መዝ51፥6
119፥67 ቍ17፤ መዝ95፥10፤116፥10፤ ኤር8፥4
119፥68 ዘፀ18፥20፤ መዝ100፥5፤106፥1፤107፥1፤135፥3
119፥69 ኢዮ13፥4፤ መዝ109፥2
119፥70መዝ17፥10 ኢሳ29፥13፤ሐሥ28፥27
119፥71 ቍ67፡75
119፥72 ኢዮ28፥17፤መዝ19፥10
119፥73 ዘፍ1፥27፤ ኢዮ4፥17፤10፥8፤ መዝ 138፥8፤139፥13-16
119፥74 ቍ9፤ መዝ 34፥2፤130፥5
119፥75 ቍ7፡138፡172፤ዕብ12፥5-11
119፥76 ቍ41፤ መዝ6፥4 119፥77 ቍ47፤መዝ90፥13፤103፥13
119፥78 ቍ51፡ 86፡161፤መዝ35፥19፤ኤር50፥32
119፥79 ቍ27፡125 119፥80 ቍ1፡6፤ዘፍ26፥5፤1ነገ8፥61 119፥81 ቍ20፡43፡ 123፤መዝ84፥2

θ48 ወይም ለምወዳቸው

82“መቼ ታጽናናኛለህ?” እያልሁ፣
ዐይኖቼ ቃልህን በመጠባበቅ ደከሙ።
83ጢስ የጠጣ የወይን አቍማዳ
ብመስልም፣
ሥርዐትህን አልረሳሁም።
84የባሪያህ ዕድሜ ስንት ቢሆን ነው?
ታዲያ፣ በሚያሳድዱኝ ላይ
የምትፈርደው መቼ ይሆን?
85በሕግህ መሠረት የማይሄዱ፣
እብሪተኞች ማጥመጃ ጕድጓድ ቈፈሩልኝ።
86ትእዛዛትህ ሁሉ አስተማማኝ ናቸው፤
ሰዎች ያለ ምክንያት አሳደውኛልና
ርዳኝ።
87ከምድር ላይ ሊያስወግዱኝ ጥቂት
ቀራቸው፤
እኔ ግን ትእዛዛትህን አልተውሁም።
88እንደ ምሕረትህ መልሰህ ሕያው
አድርገኝ፤
እኔም የአፍህን ምስክርነት
እጠብቃለሁ።

ל ላሜድ

89እግዚአብሔር ሆይ፤ ቃልህ በሰማይ፣
ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።
90ታማኝነትህ ከትውልድ እስከ ትውልድ
ሁሉ ይኖራል፤
ምድርን መሠረትሃት፤ እርሷም ጸንታ
ትኖራለች።
91ሁሉም አገልጋይህ ነውና፣
በሕግህ መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ
ጸንተው ይኖራሉ።
92ሕግህ ደስታዬ ባይሆን ኖሮ፣
በመከራዬ ወቅት በጠፋሁ ነበር።
93በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና፣
ትእዛዝህን ከቶ አልረሳም።
94እኔ የአንተ ነኝ፤ እባክህ አድነኝ፤
ሕግህንም ፈልጌአለሁና።
95ክፉዎች ሊያጠፉኝ አድብተዋል፤
እኔ ግን ምስክርነትህን አሰላስላለሁ።
96ለፍጹምነት ሁሉ ዳርቻ እንዳለው አየሁ፤
ትእዛዝህ ግን እጅግ ሰፊ ነው።

מ ሜም

97አቤቱ፤ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ!
ቀኑን ሙሉ አሰላስለዋለሁ።
98ትእዛዛትህ ምን ጊዜም ስለማይለዩኝ፣
ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረጉኝ።
99ምስክርነትህን አሰላስላለሁና፣
ከአስተማሪዎቼ ሁሉ የላቀ አስተዋይ
ልብ አገኘሁ።
100መመሪያህን ተከትዬ እሄዳለሁና፣
ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋይ ሆንሁ።
101ቃልህን እጠብቅ ዘንድ፣
እግሬን ከክፉ መንገድ ሁሉ ከለከልሁ።
102አንተው ራስህ አስተምረኸኛልና፣
ከድንጋጌህ ዘወር አላልሁም።
103ቃልህ ለምላሴ ምንኛ ጣፋጭ ነው!
ለአፌም ከማር ወለላ ይልቅ ጣዕም አለው።
104ከመመሪያህ ማስተዋልን አገኘሁ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

נ ኖን

105ሕግህ ለእግሬ መብራት፣
ለመንገዴም ብርሃን ነው።
106የጽድቅ ሕግህን ለመጠበቅ፤
ምያለሁ፤ ይህንኑ አጸናለሁ።
107እጅግ ተቸግሬአለሁ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ቃልህ
መልሰህ ሕያው አድርገኝ።
108እግዚአብሔር ሆይ፤ ፈቅጄ
ያቀረብሁትን የአፌን የምስጋና
መሥዋዕት ተቀበል፤
ሕግህንም አስተምረኝ።
109ነፍሴ ዘወትር አደጋ ላይ ናት፤
ሕግህን ግን አልረሳሁም።
110ክፉዎች ወጥመድ ዘረጉብኝ፤
እኔ ግን መመሪያህን አልተላለፍሁም።
111ምስክርነትህ የዘላለም ውርሴ ናት፤
ልቤ በዚህ ሐሤት ያደርጋልና።
112ትእዛዝህን ለዘላለም፣ እስከ ወዲያኛው
ለመፈጸም፣
ልቤን ወደዚያው አዘነበልሁ።

ס ሳምኬት

113መንታ ልብ ያላቸውን ጠላሁ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ።
114አንተ መጠጊያዬና ጋሻዬ ነህ፤
ቃልህን በተስፋ እጠብቃለሁ።
115የአምላኬን ትእዛዝ እጠብቅ ዘንድ፣
እናንት ክፉ አድራጊዎች፣ ከእኔ ራቁ።
116እንደ ቃልህ ደግፈኝ፤ እኔም ሕያው
እሆናለሁ፤
ተስፋዬም መና ቀርቶ አልፈር።
117ያለ ሥጋት እቀመጥ ዘንድ ደግፈህ
ያዘኝ፤
ሥርዐትህንም ዘወትር እመለከታለሁ።
118መሰሪነታቸው በከንቱ ነውና፣
ከሥርዐትህ ውጭ የሚሄዱትን ሁሉ
ወዲያ አስወገድሃቸው።
119የምድርን ክፉዎች ሁሉ እንደ ጥራጊ
አስወገድሃቸው፤
ስለዚህ ምስክርህን ወደድሁ።

119፥82 ቍ41፡123፤ መዝ6፥7፤69፥3፤ ሰቆ2፥11
119፥83 ቍ61
119፥84 ቍ51፤መዝ 6፥3፤ኤር12፥3፤15፥15፤ 20፥11፤ራእ6፥10
119፥85 ቍ51፤ መዝ35፥7፤57፥6፤ ኤር18፥20፡22
119፥86 ቍ78፡138 ፤መዝ7፥1፤109፥26
119፥87 ቍ150፤ ኢሳ1፥4፡28፤58፥2፤ 59፥13
119፥88 ቍ2፡100፡ 124፡129፡134፡168፤ መዝ41፥2፤51፥1፤ 109፥26
119፥89 ቍ111፡ 144፤መዝ111፥8፤ ኢሳ51፥6፤ማቴ5፥18፤ 1ጴጥ1፥25
119፥90 ኢዮ8፥19፤ መዝ36፥5፤45፥17፤ 148፥6
119፥91 መዝ104፥ 2-4፤ኤር31፥35፤ 33፥25
119፥92 ቍ50፡67፤ መዝ37፥4፤112፥1
119፥93 ቍ83፤ መዝ103፥5
119፥94 ቍ45፡ 146፤መዝ54፥1፤ 116፥4፤ኤር17፥14፤ 31፥18፤42፥11
119፥95 ቍ99፤ መዝ69፥4
119፥96 መዝ19፥7
119፥97 ቍ15፡47
119፥98 ቍ130፤ ዘዳ4፥6፤መዝ19፥7፤ 2ጢሞ3፥15
119፥99 ቍ15
119፥100 ቍ56፤ ዘዳ6፥17
119፥101 ቍ57፤ ምሳ1፥15
119፥102 ዘዳ4፥5፤ 17፥20
119፥103 መዝ19፥ 10፤ምሳ24፥13-14
119፥104 ቍ128፤ መዝ111፥10
119፥105 ቍ130፤ ምሳ6፥23፤20፥27፤ 2ጴጥ1፥19
119፥106 ቍ7፤ ነህ10፥29
119፥107 ቍ25
119፥108 ቍ64፤ መዝ51፥15፤63፥5፤ 71፥8፤109፥30
119፥109 ቍ61፤ መሳ12፥3
119፥110 ቍ10፤ መዝ25፥15፤64፥5፤ ኢሳ8፥14፤አሞ3፥5
119፥111 ቍ14፡162
119፥112 ቍ33፤ መዝ108፥1 119፥113 ቍ47፤1ነገ18፥21፤ያዕ1፥8፤4፥8
119፥114 ቍ43፤ዘፍ15፥1፤መዝ18፥2 119፥115 መዝ6፥8
119፥116 ቍ41፤መዝ18፥35፤41፥3፤55፥22፤ኢሳ46፥4፤ሮሜ5፥5
119፥117 ቍ6፤መዝ34፥4፤ኢሳ41፥10፤46፥4 119፥118 ቍ10
119፥119 ቍ47፤ኢሳ1፥22፡25፤ሕዝ2፥18፡19

120 ሥጋዬ አንተን በመፍራት
ይንቀጠቀጣል፤
ፍርድህንም እፈራለሁ።

ፃ ጼ

121 ፍትሕና ጽድቅ ያለበትን ሠርቻለሁ፤
ለሚጨቍኑኝ አሳልፈህ አትስጠኝ።
122 ለባሪያህ በጎነት ዋስትና ሁን፤
እብሪተኛ እንዲጨቍነኝ
አትፍቀድላቸው።
123 ዐይኖቼ ማዳንህን፣
የጽድቅ ቃልህን በመጠባበቅ ደከሙ።
124 ለባሪያህ እንደ ምሕረትህ መጠን
አድርግ፤
ሥርዐትህንም አስተምረኝ።
125 እኔ ባሪያህ ነኝ፤
ምስክርነትህን ዐውቅ ዘንድ ማስተዋልን
ስጠኝ።
126 እግዚአብሔር ሆይ፤
ሕግህ እየተጣሰ ነውና፣
ጊዜው አንተ የምትሠራበት ነው።
127 ስለዚህ ከወርቅ፣ ከንጹሕ ወርቅ ይልቅ፣
ትእዛዛትህን ወደድሁ።
128 መመሪያህ ሙሉ በሙሉ ልክ ነው
አልሁ፤
ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠላሁ።

ፇ ፌ

129 ምስክርነትህ ሁሉ ድንቅ ነው፤
ስለዚህ ነፍሴ ትጠብቀዋለች።
130 የቃልህ ትርጓሜ ያበራል፤
አላዋቂዎችንም አስተዋዮች ያደርጋል።
131 ትእዛዝህን ናፍቄአለሁና፣
አፌን ከፈትሁ፤ አለከለክሁም።
132 ስምህን ለሚወዱ ማድረግ ልማድህ
እንደ ሆነ ሁሉ፣
ወደ እኔ ተመልሰህ፣ ምሕረት
አድርግልኝ።
133 አካሄዴን እንደ ቃልህ ቀና አድርግልኝ፤
ኀጢአትም በላዬ እንዲሠለጥን
አትፍቀድ።
134 ትእዛዝህን መጠበቅ እንድችል፣
ከሰዎች ጥቃት ታደገኝ።
135 በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ፤
ሥርዐትህንም አስተምረኝ።
136 ሕግህ ባለመከበሩ፤
እንባዬ እንደ ውሃ ይፈሳል።

ጿ ጻዴ

137 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ጻድቅ ነህ፤
ፍርድህም ትክክል ነው።
138 ምስክርነትህን በጽድቅ አዘዝህ፤
እጅግ አስተማማኝም ነው።
139 ጠላቶቼ ቃልህን ዘንግተዋልና፣
ቅናት አሳረረኝ።
140 ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው፤
ባሪያህም ወደደው።
141 እኔ ታናሽና የተናቅሁ ነኝ፤
ነገር ግን መመሪያህን አልዘነጋሁም።
142 ጽድቅህ ዘላለማዊ ጽድቅ ነው፤
ሕግህም እውነት ነው።
143 መከራና ሥቃይ ደርሶብኛል፤
ነገር ግን ትእዛዝህ ደስታዬ ነው።
144 ምስክርነትህ ለዘላለም የጽድቅ
ምስክርነት ነው፤
በሕይወት እኖር ዘንድ ማስተዋልን
ስጠኝ።

ꡈ ቆፍ

145 እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
እጮኻለሁና መልስልኝ፤
ሥርዐትህንም እጠብቃለሁ።
146 ወደ አንተ እጣራለሁና አድነኝ፤
ምስክርነትህንም እጠብቃለሁ።
147 ትረዳኝ ዘንድ ጎሕ ሳይቀድ ተነሥቼ
እጮኻለሁ፤
ቃልህንም ተስፋ አደርጋለሁ።
148 ቃልህን አሰላስል ዘንድ፣
ዐይኔ ሌሊቱን ሙሉ ሳይከደን
ያድራል።
149 እንደ ቸርነትህ መጠን ድምፄን ስማ፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ሕግህ
መልሰህ ሕያው አድርገኝ።
150 ደባ የሚያውጠነጥኑ ወደ እኔ ቀርበዋል፤
ከሕግህ ግን የራቁ ናቸው።
151 እግዚአብሔር ሆይ፤ አንተ ግን ቅርብ
ነህ፤
ትእዛዛትህም ሁሉ እውነት ናቸው።
152 ለዘላለም እንደ መሠረትሃቸው፣
ከጥንት ምስክርነትህ ተረድቻለሁ።

ᒥ ሬስ

153 ሕግህን አልረሳሁምና፣
ሥቃዬን ተመልከት፤ ታደገኝም።
154 ተሟገትልኝ፤ አድነኝም፤
እንደ ቃልህም ሕያው አድርገኝ።
155 ሥርዐትህን ስለማይሹ፣
ድነት ከክፉዎች የራቀ ነው።
156 እግዚአብሔር ሆይ፤ ርኅራኄህ ታላቅ
ነው፤
እንደ ሕግህ ሕያው አድርገኝ።
157 የሚያሳድዱኝ ጠላቶቼ ብዙዎች ናቸው፤
እኔ ግን ከምስክርህ ዘወር አላልሁም።

119፥120 ኢሱ 24፥14፤ኢዮ4፥14፤ ኢሳ64፥2፤ኤር10፥7 ፤ዕን3፥2
119፥121 2ሳሙ 8፥15፤ኢዮ27፥6
119፥122 ቍ21፡ 121፡134፤ኢዮ17፥3፤ መዝ106፥42
119፥123 ቍ81፡82 ፤ኢሳ38፥14
119፥124 ቍ12፡88 ፤መዝ25፥7
119፥125 ቍ79፤ መዝ116፥16
119፥126 ዘኍ15፥ 31
119፥127 ቍ47፤ ኢዮ3፥21፤መዝ19፥10
119፥128 ቍ104፡ 163፤መዝ19፥8፤ 31፥6፤ምሳ13፥5
119፥129 ቍ18፡ 22፡88
119፥130 ቍ105፤ መዝ19፥7
119፥131 ቍ20፤ መዝ42፥1
119፥132 2ሳሙ 24፥14፤መዝ5፥11፤ 6፥4፤9፥13፤ 2ሳሙ24፥14
119፥133 ቍ9፡11፤ ሮሜ6፥16
119፥134 ቍ56፡ 88፡122
119፥135 ቍ12፤ ዘኍ6፥25፤መዝ4፥6፤ 67፥1፤80፥3
119፥136 ቍ158፤ መዝ6፥6፤106፥25፤ ኤሳ22፥4፤42፥24፤ ኤር9፥1፡18፤13፥17፤ 14፥17፤ሰቆ1፥16፤ 34፥8፤ሕዝ9፥4
119፥137 ዘፀ9፥27 ፤ዕዝ9፥15፤ነህ9፥13
119፥138 ቍ75፡86 ፤መዝ19፥7
119፥139 መዝ69፥9 ፤ዮሐ2፥17
119፥140 ቍ47፤ ኢሱ23፥14፤ መዝ12፥6
119፥141 ቍ61፡ 134፤መዝ22፥6
119፥142 ቍ151፡ 160፤መዝ19፥7
119፥143 ቍ24፡47
119፥144 ቍ34
119፥145 ቍ10፡ 22፡55
119፥146 ቍ94
119፥147 መዝ5፥3 ፤57፥8፤108፥2
119፥148 መዝ63፥6
119፥149 ቍ40፡ 124፤መዝ27፥7
119፥150 መዝ37፥7
119፥151 ቍ142፤ መዝ34፥18፤ፊል4፥5

119፥152 ቍ7፡73፡89፤መዝ111፥8፤ሉቃ21፥33
119፥153 መዝ3፥7፤13፥3፤44፥17 119፥154 ቍ25፡41፤ 1ሳሙ24፥15፤መዝ35፥1፤ኤር50፥34፤ሚክ7፥9 119፥155 ቍ94 ፡118 119፥156 ቍ25፡149፤ነህ9፥27፤ያዕ5፥11
119፥157 መዝ7፥1፤44፥18

158ቃልህን አይጠብቁምና፣
ከዳተኞችን አይቼ አርቃቸዋለሁ።
159*መመሪያህን እንዴት እንደምወድ ተመልከት፤*
*እግዚአብሔር ሆይ፤ እንደ ምሕረትህ ሕያው አድርገኝ።*
160ቃልህ በሙሉ እውነት ነው፤
ጻድቅ የሆነው ሕግህም ዘላለማዊ ነው።

*ሠ ሳን*

161ገዦች ያለ ምክንያት አሳደዱኝ፤
ልቤ ግን ከቃልህ የተነሣ እጅግ ፈራ።
162ትልቅ ምርኮ እንዳገኘ ሰው፤
በቃልህ ደስ አለኝ።
163ሐሰትን እጠላለሁ፤ እጸየፋለሁ፤
ሕግህን ግን ወደድሁ።
164ጻድቅ ስለ ሆነው ሕግህ፤
በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሃለሁ።
165ሕግህን የሚወዱ ብዙ ሰላም አላቸው፤
ዕንቅፋትም የለባቸውም።
166*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ማዳንህን ተስፋ አደርጋለሁ፤
ትእዛዝህንም እፈጽማለሁ።
167ነፍሴ ምስክርነትህን ትጠብቃለች፤
እጅግ እወደዋለሁና።
168*መንገዴ* ሁሉ በፊትህ ግልጽ ነውና፣
ሕግህንና ምስክርነትህን እጠብቃለሁ።

*ተ ታው*

169*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጩኸቴ ከፊትህ ይድረስ፤
እንደ ቃልህም ማስተዋልን ስጠኝ።
170ልመናዬ ከፊትህ ይድረስ፤
እንደ ቃልህም ታደገኝ።
171ሥርዐትህን አስተምረኸኛልና፣
ከንፈሮቼ ምስጋናን አፈለቁ።
172ትእዛዛትህ ሁሉ የጽድቅ ትእዛዛት ናቸውና፣
አንደበቴ ስለ ቃልህ ይዘምር።
173ትእዛዝህን መርጫለሁና፣
እጅህ እኔን ለመርዳት ዝግጁ ይሁን።
174*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ማዳንህን ናፈቅሁ፤
ሕግህም ደስታዬ ነው።
175አመሰግንህ ዘንድ በሕይወት ልኑር፤
ሕግህም ይርዳኝ።
176እንደ ጠፋ በግ ተቅበዘበዝሁ፤
ትእዛዛትህን አልረሳሁምና፣
ባሪያህን ፈልገው።

### *መዝሙር* 120

**የሰላም ፀሮች**

*መዝሙረ መዓርግ*

1በተጨነቅሁ ጊዜ ወደ *እግዚአብሔር* ተጣራሁ፤

119፥158 ቍ104፡136፤ዘፀ32፥19
119፥159 ቍ25፤መዝ41፥2
119፥160 ቍ89፤መዝ111፥8
119፥161 ቍ23፡120፡122፡157፤1ሳሙ24፥14-15
119፥162 ቍ111፤1ሳሙ30፥16፤ኢሳ 9፥3፤53፥12
119፥163 ቍ47፡128
119፥164ቍ7፡160
119፥165ቍ11፤መዝ37፥11፡24፤ኢሳ26፥3፡12፤27፥5፤32፥17፤57፥19፤66፥12፤1ዮሐ2፥10
119፥166 ቍ81
119፥167 ቍ47
119፥168 ቍ2፡22፡56፡88፤ኢዮ10፥4፤23፥10፤መዝ139፥3፤ምሳ5፥21
119፥169 ቍ9፡34፤ኢዮ16፥18
119፥170 ቍ41፤1ነገ8፥30፤2ዜና6፥24፤መዝ3፥7፤22፥20፤28፥2፤59፥1፤140፥6፤143፥1
119፥171 መዝ51፥15፤63፥3፤94፥12፤ኢሳ 2፥3፤ሚክ4፥2
119፥172 ቍ7፡75፤መዝ51፥14
119፥173 ኢሱ24፥22፤መዝ37፥24፤73፥23፤ኢሳ41፥10
119፥174 ቍ16፡24፡166
119፥175 ቍ116፡159፤ኢሳ55፥3
119፥176 ቍ10፤መዝ44፥17፤95፥10፤ኤር50፥17፤ሕዝ34፥11፤ሉቃ15፥4
120፥1 2ሳሙ22፥7፤መዝ18፥6፤118፥5
120፥2 መዝ31፥18፤52፥4
120፥4 ዘዳ32፥23
120፥5 ዘፍ25፥13፤ኤር2፥10
121፥2 ዘፍ1፥1፤መዝ104፥5
121፥4 መዝ127፥1
121፥5 መዝ1፥6
121፥6 ኢሳ49፥10
121፥7 መዝ9፥9
121፥8 ዘዳ28፥6

እርሱም መለሰልኝ።
2*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከሐሰተኛ ከንፈር፣
ከአታላይ ምላስም አድነኝ።
3ሐሰተኛ አንደበት ሆይ፤ ምን ይከፈልህ?
ከዚህስ የባሰ ምን ይደረግብህ?
4በተሳለ የጦረኛ ቀስት፣
በግራር ከሰል ፍም ይቀጣሃል።
5በሜሼክ እኖራለሁና፣
በቄዳር ድንኳኖች መካከል
እቀመጣለሁና ወዮልኝ!
6ሰላምን በሚጠሉ መካከል፣
ነፍሴ እጅግ ብዙ ጊዜ ኖረች።
7እኔ ሰላም ፈላጊ ነኝ፤
እነርሱ ግን በተናገርሁ ጊዜ ጠብ ይሻሉ።

### *መዝሙር* 121

**የእስራኤል ጠባቂ**

*መዝሙረ መዓርግ*

1ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ፤
ረድኤቴ ከወዴት ይመጣል?
2ረድኤቴ ሰማይንና ምድርን ከፈጠረ፣
*ከእግዚአብሔር* ዘንድ ይመጣል።
3እግርህ እንዲሸራተት አይፈቅድም፤
የሚጠብቅህም አይተኛም።
4እነሆ፤ እስራኤልን የሚጠብቅ፣
አይተኛም፤ አያንቀላፋምም።
5*እግዚአብሔር* ይጠብቅሃል፤
*እግዚአብሔር* በቀኝህ በኩል
ይከልልሃል።
6ፀሓይ በቀን አያቃጥልህም፤
ጨረቃም በሌሊት ጕዳት አታመጣብህም።
7*እግዚአብሔር* ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፤
ነፍስህንም ይንከባከባታል።
8*እግዚአብሔር* ከአሁን ጀምሮ እስከ ዘላለም፣
መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል።

### *መዝሙር* 122

**ኢየሩሳሌም እልል በዪ!**

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1“ወደ *እግዚአብሔር* ቤት እንሂድ”
ባሉኝ ጊዜ፣
ደስ አለኝ።
2ኢየሩሳሌም ሆይ፤
እግሮቻችን ከደጆችሽ ውስጥ ቆመዋል።
3ኢየሩሳሌም እጅግ እንደ ተጠጋጋች፣
ከተማ ሆና ተሠርታለች።
4ለእስራኤል በተሰጠው ሥርዐት
መሠረት፣
*የእግዚአብሔርን* ስም ለማመስገን፣
*የእግዚአብሔር* ነገዶች፣
ወደዚያ ይመጣሉ።

5በዚያም የፍርድ ዙፋኖች የሆኑት፣
የዳዊት ቤት ዙፋኖች ተዘርግተዋል።
6እንዲህ ብላችሁ ለኢየሩሳሌም ሰላም ጸልዩ፤
"የሚወዱሽ ይለምልሙ፤
7በቅጥርሽ ውስጥ ሰላም ይሁን፤
በምሽግሽም ውስጥ መረጋጋት ይስፈን"።
8ስለ ወንድሞቼና ስለ ባልንጀሮቼ፣
"በውስጥሽ ሰላም ይስፈን" እላለሁ።
9ስለ አምላካችን ስለ *እግዚአብሔር* ቤት፣
በጎነትሽን እሻለሁ።

**መዝሙር** 123

## የተጨነቀ ሰው ጸሎት

*መዝሙረ መዓርግ*

1በሰማይ ዙፋን ላይ የተቀመጥህ ሆይ፤
ዐይኖቼን ወደ አንተ አነሣለሁ።
2የባሪያዎች ዐይን ወደ ጌታቸው እጅ፣
የባሪያዪቱም ዐይን ወደ እመቤቷ እጅ እንደሚመለከት፣
ምሕረት እስከሚያደርግልን ድረስ፣
የእኛም ዐይኖች ወደ አምላካችን ወደ *እግዚአብሔር* ይመለከታሉ።
3*እግዚአብሔር ሆይ*፤ ንቀት በዝቶብናልና፣
ማረን፣ እባክህ ማረን።
4ነፍሳችን የቅንጡዎች ስድብ፣
የትዕቢተኞችም ንቀት እጅግ በዝቶባታል።

**መዝሙር** 124

## የእስራኤል አዳኝ

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1እስራኤል እንዲህ ይበል፦
"*እግዚአብሔር* ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፣
2ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፣
*እግዚአብሔር* ከእኛ ጋር ባይሆን ኖሮ፣
3ቍጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፣
በቁመናችን በዋጡን ነበር፤
4ጐርፍ ባጥለቀለቀን፣
ፈረሰኛው ውሃ ባሰጠመን፣
5ደራሽ ውሃም
ጠራርጎ በወሰደን ነበር።
6በጥርሳቸው ከመዘንጠል የጠበቀን፣
*እግዚአብሔር* ይባረክ።
7ነፍሳችን እንደ ወፍ፣
ከዐዳኝ ወጥመድ አመለጠች፤
ወጥመዱ ተሰበረ፤
እኛም አመለጥን።
8የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣
የ*እግዚአብሔር* ስም ረዳታችን ነው።

**መዝሙር** 125

## እግዚአብሔር የሚታመኑበትን ይጠብቃል

*መዝሙረ መዓርግ*

1*በእግዚአብሔር የሚታመኑ*፣
ሳትናወጥ ለዘላለም እንደምትኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው።
2ተራሮች ኢየሩሳሌምን እንደ ከበቧት፣
ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም፣
*እግዚአብሔር* በሕዝቡ ዙሪያ ነው።
3ጻድቃን እጃቸውን፣
ለክፋት እንዳያነሡ፣
የክፉዎች በትረ መንግሥት፣
ለጻድቃን በተመደበች ምድር ላይ አያርፍም።
4*እግዚአብሔር ሆይ*፤ መልካም ለሆኑ፣
ልባቸውም ለቀና መልካም አድርግ።
5ወደ ጠማማ መንገዳቸው የሚመለሱትን ግን፣
*እግዚአብሔር* ከክፉ አድራጊዎች ጋር ያስወግዳቸዋል።
በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ።

**መዝሙር** 126

## የስደት ተመላሾች መዝሙር

*መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔር* የጽዮንን ምርኮ[ፊ] በመለሰ[ፐ] ጊዜ፣
ሕልም እንጂ እውን አልመሰለንም።
2በዚያን ጊዜ አፋችን በሣቅ፣
እንደበታችንም በእልልታ ተሞላ፤
በዚያን ጊዜም በሕዝቦች መካከል፣
"*እግዚአብሔር* ታላቅ ነገር አደረገላቸው" ተባለ።
3*እግዚአብሔር* ታላቅ ነገር አደረገልን፤
እኛም ደስ አለን።
4*እግዚአብሔር ሆይ*፤ በነጌብ እንዳሉ ጅረቶች፣
ምርኳችንን መልስ።[ሀ]
5በእንባ የሚዘሩ፣
በእልልታ ያጭዳሉ።
6ዘር ቋጥረው፣
እያለቀሱ የተሰማሩ፣
ነዶአቸውን ተሸክመው፣
እልል እያሉ ይመለሳሉ።

**መዝሙር** 127

## በእግዚአብሔር መታመን

*የሰሎሞን መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔር* ቤትን ካልሠራ፣

[ፊ]1 ወይም *እግዚአብሔር ሀብቷን ይመልሳል።*
[ፐ]1 ወይም *የሰዎቿ ጤንነት ይታደሳል።*
[ሀ]4 ወይም *ሀብታችንን መልስ*

122፥6 መዝ26፥8
122፥7 1ሳሙ25፥6፤መዝ48፥3
122፥9 መዝ128፥5
123፥1 መዝ68፥5፤ኢሳ6፥1፤63፥15
123፥2 መዝ25፥15
124፥1 መዝ129፥1
124፥4 መዝ81፥4፤88፥17
124፥7 መዝ25፥15፤91፥3
124፥8 ዘፍ1፥1፤1ሳሙ17፥45፤መዝ115፥15፤121፥2፤134፥3
125፥1 መዝ46፥5፤48፥2-5፡12፤ኢሳ 33፥20
125፥2 1ዜና21፥15፤መዝ32፥10፤ዘካ2፥4-5
125፥3 1ሳሙ24፥10፤አስ4፥11፤መዝ89፥22፤ምሳ22፥8፤ኢሳ 13፥11፤14፥5
125፥4 መዝ36፥10፤119፥65
125፥5 ኢዮ23፥11፤መዝ92፥7፤128፥6፤ምሳ2፥15፤17፥6፤ኢሳ59፥8፤ገላ6፥16
126፥1 ዕዝ1፥1-3፤መዝ85፥1፤ሆሴ6፥11
126፥2 ዘፍ21፥6፤ዘዳ10፥21፤ኢዮ8፥21፤መዝ65፥8፤71፥19፤ሉቃ1፥49
126፥3 መዝ9፥2፤16፥11፤106፥21፤ኢል 2፥21፡26
126፥4 ዘዳ30፥3፤መዝ107፥35፤ኢሳ 43፥19፤51፥3
126፥5 መዝ6፥6፤16፥11፤20፥5፤23፥6፤80፥5፤ኢሳ35፥10፤51፥11፤60፥15፤61፥7፤ኤር31፥6-7፡12፤50፥4፤ገላ6፥9
126፥6 ዘኍ25፥6፤መዝ30፥5
127፥1 መዝ78፥69፤121፥4

*ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤*
*እግዚአብሔር* ከተማን ካልጠበቀ፣
ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።
2የዕለት ጉርስ ለማግኘት በመጣር፣
ማልዳችሁ መነሣታችሁ፣
አምሽታችሁም መተኛታችሁ ከንቱ ነው፤
እርሱ ለሚወዳቸው እንቅልፍን ያድላልና።^
3እነሆ፤ ልጆች *የእግዚአብሔር* ስጦታ
ናቸው፤
የማሕፀንም ፍሬ ከቸርነቱ የሚገኝ ነው።
4በወጣትነት የተገኙ ወንዶች ልጆች፣
በጦረኛ እጅ እንዳሉ ፍላጾች ናቸው።
5ኮረጆዎቹ በእነዚህ የተሞሉ፣
የተባረከ ሰው ነው፤
ከጠላቶቻቸው ጋር በአደባባይ በሚሟ
ገቱበት ጊዜ፣
አይዋረዱም።

## *መዝሙር* 128

### የጻድቃን በረከት

*መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔርን* የሚፈሩ ሁሉ፣
በመንገዱም የሚሄዱ የተባረኩ ናቸው።
2የድካምህን ፍሬ ትበላለህ፤
ትባረካለህ፤ ይሳካልሃልም።
3ሚስትህ በቤትህ፣
እንደሚያፈራ ወይን ናት፤
ወንዶች ልጆችህ በማእድህ ዙሪያ፣
እንደ ወይራ ተክል ናቸው።
4እነሆ፤ *እግዚአብሔርን* የሚፈራ ሰው፣
እንዲህ ይባረካል።

5*እግዚአብሔር* ከጽዮን ይባርክህ፤
በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣
የኢየሩሳሌምን ብልጽግና ያሳይህ፤
6የልጅ ልጅ ለማየትም ያብቃህ።

በእስራኤል ላይ ሰላም ይውረድ።

## *መዝሙር* 129

### በጽዮን ጠላቶች ላይ የቀረበ ጸሎት

*መዝሙረ መዓርግ*

1እስራኤል እንዲህ ይበል፦
"ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ
አስጨነቁኝ፤
2በርግጥ ከልጅነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ
አስጨነቁኝ፤
ዳሩ ግን ድል አላደረጉኝም።
3ዐራሾች ጀርባዬን ዐረሱት፤
ትልማቸውንም አስረዘሙት።"
4*እግዚአብሔር* ግን ጻድቅ ነው፤
የክፉዎችን ገመድ በጣጥሶ ጣለው።

5ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ፣
ዐፍረው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።

127፥2 ዘፍ3፥17፤ ዘኍ6፥26፤ዘዳ33፥12፤ ኢዮ11፥18፤መክ2፥25
127፥3 ዘፍ1፥28
127፥4 መዝ112፥2 ፤127፥5ዘፍ23፥10፤ 24፥60፤መዝ128፥2-3
127፥5 ዘፍ23፥10፤ 24፥60፤መዝ128፥2-3
128፥1 መዝ103፥11 ፤112፥1፤119፥1-3
128፥2 ዘፍ39፥3፤ መዝ58፥11፤109፥11፤ ምሳ10፥22፤ኢሳ3፥10
128፥3 ዘፍ49፥22 ፤ኢዮ29፥5፤ መዝ52፥8፤144፥12
128፥4 መዝ1፥1፤ 112፥1
128፥5 መዝ20፥2፤ 122፥9
128፥6 ዘፍ48፥11፤ መዝ125፥5
129፥1 ዘፀ1፥13፤ መዝ88፥15፤124፥1
129፥2 ኤር1፥19፤ 15፥20፤20፥11፤ ማቴ 16፥18
129፥4 ዘፀ9፥27፤ መዝ37፥9፤140፥5
129፥5 መዝ70፥2፤ ሚክ4፥11
129፥6 2ነገ19፥26፤ መዝ102፥11፤ ኢሳ 37፥27
129፥7 ዘዳ28፥38፤ መዝ79፥12
129፥8 መዝ118፥26
130፥1 ኢዮ30፥19፤ መዝ22፥2፤42፥7፤55፥ 17፤142፥5፤ሰቆ3፥55
130፥2 2ዜና6፥40 ፤መዝ27፥7፤28፥2፡6፤ 31፥22፤86፥6፤140፥6
130፥3 1ሳሙ6፥20 ፤ዕዝ9፥15፤መዝ143፥2 ፤ናሆ1፥6፤ራእ6፥17
130፥4 ዘፀ34፥7፤ 2ሳሙ24፥14፤1ነገ 8፥40፤ኤር31፥34
130፥5 መዝ5፥3፤ 27፥14፤119፥74፤ ኢሳ 8፥17፤26፥8፤ 30፥18፤49፥23
130፥6 2ሳሙ23፥4 ፤መዝ63፥6
130፥7 1ዜና21፥13 ፤መዝ25፥5፤71፥14፤ 111፥9፤ሮሜ3፥24
130፥8 ዘፀ34፥7፤ ሉቃ1፥68፤ማቴ1፥21
131፥1 2ሳሙ22፥ 28፤ኢዮ5፥9፤41፥34፤ መዝ101፥5፤139፥6፤ ኢሳ2፥12፤ኤር45፥5፤ ሮሜ12፥16
131፥2 መዝ116፥7 ፤ማቴ18፥3፤ 1ቆሮ13፥11፤14፥20
131፥3 መዝ25፥5፤ 113፥2፤119፥43፤ 130፥7

6ገና ከመብቀሉ እንደሚደርቅ፣
በጣራ ላይ እንደ በቀለ ሣር ይሁኑ፤
7ደግሞም ለዐጫጅ እጁን፣
ለነዶ ሰብሳቢ ዕቅፉን እንደማይሞላ
ይሁኑ።
8መንገድ ዐላፊዎችም፣
"*የእግዚአብሔር* በረከት በእናንተ ላይ
ይሁን፤
*በእግዚአብሔር* ስም እንባርካችኋለን"
አይበሉ።

## *መዝሙር* 130

### ለርዳታ የቀረበ ጥሪ

*መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤
ከጥልቅ ወደ አንተ እጮኻለሁ።
2ጌታ ሆይ፤ ድምፄን ስማ፤
ጆሮዎችህ የልመናዬን ቃል፣
የሚያዳምጡ ይሁኑ።
3*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ኀጢአትን
ብትቈጣጠር፣
ጌታ ሆይ፤ ማን ሊቆም ይችላል?
4ነገር ግን በአንተ ዘንድ ይቅርታ አለ፤
ስለዚህም ልትፈራ ይገባሃል።

5*እግዚአብሔርን* ደጅ እጠናለሁ፤ ነፍሴም
በትዕግሥት ትጠብቀዋለች፤
በቃሉም ተስፋ አደርጋለሁ።
6ዘብ ዐዳሪ ንጋትን ከሚጠባበቅ ይልቅ፣
አዎን፤ ዘብ ዐዳሪ ንጋትን ከሚጠባበቅ
ይልቅ፣
ነፍሴ ጌታን ትጠባበቃለች።
7*በእግዚአብሔር* ዘንድ ምሕረት፣
በእርሱም ዘንድ ማዳን አለና፣
እስራኤል ሆይ፤ *በእግዚአብሔር*
ተስፋ አድርግ።
8እርሱም እስራኤልን፣
ከኀጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።

## *መዝሙር* 131

### በእግዚአብሔር መታመን

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ልቤ አልታበየም፤
ዐይኔ ከፍ ከፍ አላለም፤
ሐሳቤ ለዐጕል ትልቅነት አልተነሣሣም፤
ከዐቅሜም በላይ አልተንጠራራሁም።
2ነገር ግን ነፍሴን ጸጥ፣ ዝም አሰኘኋት፤
ጡት የጣለ ልጅ ዐርፎ እናቱ ላይ
እንደሚቀመጥ፣
ነፍሴ ጡት እንዳስተዉት ሕፃን
በውስጤ ጸጥ አለች።
3እስራኤል ሆይ፤ ከአሁን ጀምሮ
ለዘላለም፣

*^2 ወይም ተኝተው ሳሉ ምግብ ያዘጋጅላቸዋል።*

*በእግዚአብሔር ተስፋ አድርግ።*

## መዝሙር 132

### የክብረ በዓል መዝሙር

132፥8-10 ተጓ ምብ-2ዜና 6፥41-42

*መዝሙረ መዓርግ*

1 *እግዚአብሔር ሆይ፤ ዳዊትን፣*
*የታገሠውንም መከራ ሁሉ ዐስብ፤*
2 እርሱ *ለእግዚአብሔር* ማለ፤
ለያዕቆብም ኀያል አምላክ እንዲህ ሲል
ተሳለ፤
3 "ወደ ቤቴ አልገባም፤
ዐልጋዬም ላይ አልወጣም፤
4 ለዐይኖቼ እንቅልፍን፣
ለሽፋሽፍቶቼም ሽለብታ አልሰጥም፤
5 *ለእግዚአብሔር* ስፍራን፣
ለያዕቆብም ኀያል አምላክ ማደሪያን
እስካገኝ ድረስ።"

6 እነሆ፤ በኤፍራታ ሰማነው፤
በቂርያት ይዓሪም[ሐ] አገኘነው።
7 "ወደ ማደሪያው እንግባ፤
እግሮቹ በሚቆሙበት ቦታ እንስገድ።
8 *እግዚአብሔር ሆይ፤ ተነሥ፤*
አንተና የኀይልህ ታቦት ወደ ማረፊያህ
ስፍራ ሂዱ።
9 ካህናትህ ጽድቅን ይልበሱ፤
ቅዱሳንህም እልል ይበሉ።"

10 ስለ አገልጋይህ ስለ ዳዊት ስትል፣
የቀባኸውን ሰው አትተወው።

11 *እግዚአብሔር* ለዳዊት በእውነት ማለ፤
በማይታጠፍም ቃሉ እንዲህ አለ፤
"ከገዛ ራስህ ፍሬ፣
በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።
12 ወንዶች ልጆችህ ኪዳኔን፣
የማስተምራቸውንም ምስክርነቴን
ቢጠብቁ፣
ልጆቻቸው በዙፋንህ ላይ፣
ለዘላለም ይቀመጣሉ።

13 *እግዚአብሔር* ጽዮንን መርጦአታልና፣
ማደሪያውም ትሆን ዘንድ ወዶአልና
እንዲህ አለ፤
14 "ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት፤
ፈልጌአታለሁና በእርሷ እኖራለሁ።
15 እጅግ አትረፍርፌ እባርካታለሁ፤
ድኾቿን እንጀራ አጠግባለሁ።
16 ለካህናቷ ድነትን አለብሳለሁ፤
ቅዱሳኗም በደስታ ይዘምራሉ።

17 "በዚህም ለዳዊት ቀንድ[መ] አበቅላለሁ፤
ለቀባሁትም ሰው መብራት አዘጋጃለሁ።
18 ጠላቶቹን ኀፍረት አከናንባቸዋለሁ፤
እርሱ ግን በራሱ ላይ የደፋው ዘውድ
ያበራል።

132፥1 1ሳሙ18፥11፤2ሳሙ15፥14
132፥2 ዘፍ49፥24፤ ኢሳ49፥26፤60፥16
132፥3 2ሳሙ7፥2፡27
132፥5 1ነገ8፥17፤ሐሥ7፥46
132፥6 ኢሱ9፥17፤ 1ሳሙ7፥2፤17፥12
132፥7 2ሳሙ15፥25፤1ዜና28፥2፤ መዝ5፥7፤122፥1
132፥8 ዘኍ10፥35
132፥9 ኢዮ27፥6፤ መዝ16፥3፤30፥4፤149፥5፤ኢሳ61፥3፡10፤ዘካ3፥4፤ሚል3፥3፤ኤፌ6፥14
132፥11 1ዜና17፥11-14፤መዝ89፥3-4፡35፤ ማቴ1፥1፤ሉቃ3፥31
132፥12 2ዜና6፥16፤መዝ25፥10፤ ሉቃ1፥32፤ሐሥ2፥30
132፥13 ዘፀ15፥17፤ 1ነገ8፥13፤መዝ48፥1-2፤68፥16
132፥14 ቍ8፤ 2ሳሙ 6፥2፤ መዝ68፥6፤80፥1
132፥15 መዝ107፥9፤147፥14
132፥16 2ዜና6፥41፤ኢዮ8፥21፤መዝ149፥5
132፥17 1ሳሙ2፥10፤1ነገ11፥36፤2ነገ8፥19፤2ዜና21፥7፤መዝ18፥28፤84፥9፤92፥10፤ ሕዝ29፥21፤ሉቃ1፥69
132፥18 2ሳሙ12፥30፤ኢዮ8፥22
133፥1 ዘፍ13፥8፤ ዮሐ17፥11፤ ሮሜ12፥10
133፥2 ዘፀ29፥7
133፥3 ዘፀ15፥17፤ ዘሌ25፥21፤ዘዳ3፥8፤ 4፥48፤ኢዮ29፥19፤ መዝ2፥6፤21፥4፤74፥2፤ምሳ19፥12፤ኢሳ18፥4፤ 26፥19፤45፥8፤ ሆሴ14፥5፤ሚክ5፥7
134፥1 ዘኍ16፥9፤ 1ዜና15፥2፤23፥30፤ መዝ113፥1፤ 135፥1-2፤ራእ19፥5
134፥2 መዝ15፥1፤ 28፥2፤33፥2፤103፥1፤ 1ጢሞ2፥8
134፥3 ዘሌ25፥21፤ መዝ20፥2፤ መዝ124፥8
135፥1 ነህ7፥73
135፥2 1ዜና15፥2፤ መዝ116፥19፤ ሉቃ2፥37
135፥3 1ዜና16፥34፤መዝ68፥4፤92፥1፤ 119፥68፤147፥1
135፥4 ዘፀ19፥5፤ ዘዳ 7፥6፤10፥15፤ ሚል3፥17፤ቲቶ2፥14
135፥5 ዘፀ12፥12፤

## መዝሙር 133

### የወንድማማች ፍቅር

*የዳዊት መዝሙረ መዓርግ*

1 ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት
ሲኖሩ፣
እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ ደስ
ያሰኛል!
2 በራስ ላይ ፈሶ፣
እስከ ጢም እንደሚዘልቅ፣
እስከ አሮን ጢም እንደሚወርድ፣
እስከ ልብሱም ዐንገትጌ እንደሚደርስ
ውድ ሽቱ ነው።
3 ደግሞም በጽዮን ተራራ ላይ
እንደሚወርድ፣
እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፤
በዚያ *እግዚአብሔር* በረከቱን፣
ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዞአልና።

## መዝሙር 134

### የሠርክ መዝሙር

*መዝሙረ መዓርግ*

1 እናንት በሌሊት ቆማችሁ *በእግዚአብሔር*
ቤት የምታገለግሉ፣
*የእግዚአብሔር* ባሪያዎች ሁላችሁ፤
*እግዚአብሔርን* ባርኩ።
2 በመቅደሱ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ፤
*እግዚአብሔርንም* ባርኩ።
3 ሰማይንና ምድርን የሠራ *እግዚአብሔር*፣
ከጽዮን ይባርክህ።

## መዝሙር 135

### የምስጋና መዝሙር

135፥15-20 ተጓ ምብ-መዝ 115፥4-11

1 *ሃሌ ሉያ።*[ሠ]

*የእግዚአብሔርን* ስም ወድሱ፤
እናንት *የእግዚአብሔር* አገልጋዮች
ሆይ፤ አመስግኑት፤
2 *በእግዚአብሔር* ቤት፣
በአምላካችን ቤት አደባባይ የምትቆሙ
አመስግኑት።
3 *እግዚአብሔር* ቸር ነውና *እግዚአብሔርን*
አመስግኑ፤
መልካም ነውና፣ ለስሙ ዘምሩ፤
4 *እግዚአብሔር* ያዕቆብን ለራሱ፣
እስራኤልንም ውድ ንብረቱ አድርጎ
መርጦአልና።

5 *እግዚአብሔር* ታላቅ እንደ ሆነ፣

[ሐ]6 አንዳንዶቹ *ያዒር* ይላሉ።
[መ]17 እዚህ ላይ ቀንድ የጥንካሬ ትእምርት ሲሆን ንጉሥን ያመለክታል።
[ሠ]1 ቍ3 እና 21 ጭምር በአንዳንድ ትርጒሞች *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

ጌታችንም ከአማልክት ሁሉ እንደሚበልጥ
ዐውቃለሁና።

6በሰማይና በምድር፣
በባሕርና በጥልቅ ሁሉ ውስጥ፣
እግዚአብሔር ደስ ያሰኘውን ሁሉ
ያደርጋል።
7እርሱ ደመናትን ከምድር ዳርቻ
ያስነሣል፤
መብረቅ ከዝናብ ጋር እንዲወርድ
ያደርጋል፤
ነፋሳትንም ከማከማቻው ያወጣል።

8በኵር ሆኖ በግብፅ የተወለደውን፣
ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ቀሠፈ።
9ግብፅ ሆይ፤ በፈርዖንና በአገልጋዮቹ ሁሉ
ላይ፣
በመካከልሽ ታምራትንና ድንቅን
ሰደደ።
10ብዙ ሕዝቦችን መታ፤
ኀያላን ነገሥታትንም ገደለ።
11የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፣
የባሳንን ንጉሥ ዐግን፣
የከነዓንን ነገሥታት ሁሉ ገደለ፤
12ምድራቸውንም ርስት አድርጎ፣
ለሕዝቡ ርስት እንዲሆን ለእስራኤል
ሰጠ።

13እግዚአብሔር ሆይ፤ ስምህ ዘላለማዊ
ነው፤
እግዚአብሔር ሆይ፤ መታሰቢያህም
ከትውልድ እስከ ትውልድ ይኖራል።
14እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳልና፣
ለአገልጋዮቹም ይራራላቸዋል።

15የአሕዛብ ጣዖታት ከብርና ከወርቅ
የተሠሩ፣
የሰው እጅ ያበጃቸው ናቸው።
16አፍ አላቸው፤ አይናገሩም፤
ዐይን አላቸው፤ አያዩም፤
17ጆሮ አላቸው፤ አይሰሙም፤
በአፋቸውም እስትንፋስ የለም።
18እነዚህን የሚያበጁ፣
የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ
ይሁኑ።

19የእስራኤል ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን
ባርኩ፤
የአሮን ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን
ባርኩ፤
20የሌዊ ቤት ሆይ፤ እግዚአብሔርን ባርኩ፤
እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፤ እግዚ
አብሔርን ባርኩ።
21በኢየሩሳሌም የሚኖር እግዚአብሔር፣
ከጽዮን ይባረክ።

ሃሌ ሉያ።

1ዜና16፥25፤
ኢዮ 21፥22፤
መዝ48፥1፤145፥3
135፥6 መዝ115፥3
፤ዳን4፥35፤ማቴ6፥10
135፥7 ዘጸ28፥12፤
ኢዮ5፥10፤መዝ68፥9፤
ኢሳ30፥23፤ኤር10፥13፤
51፥16፤ኢል2፥23
፤አሞ4፥13፤ዘካ10፥1
135፥8 ዘፀ4፥23፤
12፥12
135፥9 ዘፀ7፥9፤
መዝ136፥10-15
135፥10ዘኍ21፥21-
25፤ኢሱ24፥8-11፤
መዝ44፥2፤78፥55፤
136፥17-21
135፥11ዘኍ21፥21
፥26፥33፤ኢሱ12፥7-24
፤24፥12
135፥12 ዘዳ29፥8
135፥13 ዘፀ3፥15፤
መዝ102፥12
135፥14 ዘዳ32፥36
፤1ሳሙ24፥15፤
ዕብ 10፥30
135፥15 መዝ96፥5
፤ኢሳ2፥8፤31፥7፤37፥19፤
40፥19፤ኤር1፥16፤
10፥5፤ራእ9፥20
135፥16 1ነገ18፥26
135፥17 ኤር10፥14
፤ዕን2፥19
135፥19መዝ22፥23
135፥21 1ነገ8፥13፤
2ዜና6፥2፤መዝ128፥5
፤134፥3
136፥1 ቈላ2-26፤
2ዜና5፥13፤ዕዝ3፥11፤
መዝ100፥5፤105፥1፤
106፥1፤118፥1-4፤145፥9፤
ኤር33፥11፤ናሆ1፥7
136፥2 ዘዳ10፥17፤
መዝ105፥1
136፥3 ዘዳ10፥17፤
መዝ105፥1፤
1ጢሞ6፥15
136፥4 ዘፀ3፥20፤
ኢዮ9፥10
136፥5 ዘፍ1፥1፤
ምሳ3፥19፤ኤር51፥15
136፥6 ዘፍ1፥1፥6፤
ኢሳ42፥5፤
ኤር10፥12፥33፥2
136፥7 ዘፍ1፥14፥16፤
መዝ74፥16፤ያዕ1፥17
136፥8 ዘፍ1፥16
136፥10 ዘፀ4፥23፤
12፥12
136፥11 ዘፀ6፥6፤
13፥3፤105፥43
136፥12 ዘፀ3፥20፤
ዘዳ5፥15፥9፥29
136፥13መዝ78፥13
136፥14 ዘፀ14፥22፤
መዝ106፥9
136፥15 ዘፀ14፥27
136፥16 ዘፀ13፥18፤
መዝ78፥52
136፥17 ዘኍ21፥23

## መዝሙር 136
### ምስጋና በቅብብሎሽ መዝሙር

1እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ ቸር ነውና፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
2የአማልክትን አምላክ አመስግኑ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
3የጌቶችን ጌታ አመስግኑ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
4እርሱ ብቻውን ታላላቅ ታምራትን
የሚያደርግ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
5ሰማያትን በብልኀት የሠራ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
6ምድርን በውሃ ላይ የዘረጋ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
7ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
8ፀሓይ በቀን እንዲሠለጥን ያደረገ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
9ጨረቃና ከዋክብት በሌሊት
እንዲሠለጥኑ ያደረገ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

10የግብፅን በኵር የመታ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
11እስራኤልን ከመካከላቸው ያወጣ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
12በኀያል እጅና በተዘረጋች ክንድ
ይህን ያደረገ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
13የኤርትራን ባሕር[a] ለሁለት የከፈለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
14እስራኤልን በመካከሉ ያሳለፈ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
15ፈርዖንንና ሰራዊቱን በኤርትራ ባሕር
ያሰጠመ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
16ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
17ታላላቅ ነገሥታትን የመታ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
18ኀያላን ነገሥታትን የገደለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
19የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን የገደለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
20የባሳንን ንጉሥ ዐግን የገደለ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
21ምድራቸውን ርስት አድርጎ የሰጠ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤

-25፤ኢሱ24፥8-11፤መዝ78፥55፤135፥9-12 136፥18 ዘዳ29፥7፤
ኢሱ12፥7-24 136፥19 ዘኍ21፥21-25 136፥20 ዘኍ21፥33-35
136፥21 ዘዳ1፥38፤ኢሱ12፥1፤14፥1

[22]ለባሪያው ለእስራኤል ርስት አድርጎ የሰጠ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
[23]በውርደታችን ጊዜ ያሰበን፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
[24]ከጠላቶቻችን እጅ ያዳነን፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
[25]ለፍጡር ሁሉ ምግብን የሚሰጥ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤
[26]የሰማይን አምላክ አመስግኑ፤
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

## መዝሙር 137

### የግዞተኞች ቅኔ

[1]በባቢሎን ወንዞች አጠገብ፣ በዚያ
ተቀምጠን ሳለን፣
ጽዮን ትዝ ባለችን ጊዜ አለቀስን።
[2]እዚያም በአኻያ ዛፎች ላይ፣
በገናዎቻችንን ሰቀልን።
[3]የማረኩን በዚያ እንድንዘምርላቸው ጠየቁን፤
የሚያሠቃዩን የደስታ ዜማ ፈለጉብን፤
ደግሞም፣ “ከጽዮን መዝሙሮች አንዱን
ዘምሩልን” አሉን።
[4]*የእግዚአብሔርን* ዝማሬ፣
እንዴት በባዕድ ምድር እንዘምር!
[5]ኢየሩሳሌም ሆይ፤ ብረሳሽ፣
ቀኝ እጄ ትክዳኝ።
[6]ሳላስታውስሽ ብቀር፣
ኢየሩሳሌምን የደስታዬ ቍንጮ ባላደርግ፣
ምላሴ ከትናጋዬ ጋር ትጣበቅ።
[7]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ኢየሩሳሌም
በወደቀችበት ቀን፣
ኤዶማውያን እንዴት እንደ ዛቱ ዐስብ፤
ደግሞም፣ “አፍርሷት፤
ፈጽማችሁ አፈራርሷት!” አሉ።
[8]አንቺ አጥፊ የሆንሽ የባቢሎን ልጅ ሆይ፤
በእኛ ላይ ስለ ፈጸምሺው ድርጊት፣
የእጅሽን የሚሰጥሽ የተመሰገነ ነው፤
[9]ሕፃናትሽንም ይዞ፣
በዐለት ላይ የሚፈጠፍጥ የተመሰገነ
ነው።

## መዝሙር 138

### የምስጋና መዝሙር

የዳዊት መዝሙር

[1]እግዚአብሔር ሆይ፤ በፍጹም ልቤ
አመሰግንሃለሁ፤
በአማልክት ፊት በመዝሙር
እወድስሃለሁ።
[2]ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ፤
ስለ ምሕረትህና ስለ ታማኝነትህ፣
ለስምህ ምስጋና አቀርባለሁ፤
ስምህንና ቃልህን፣
ከሁሉ በላይ ከፍ ከፍ አድርገሃልና።
[3]በጠራሁህ ቀን መልስ ሰጠኸኝ፤
ነፍሴን በማደፋፈርም ብርቱ
አደረግኸኝ።
[4]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የአፍህን ቃል
በሰሙ ጊዜ፣
የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመስግኑህ።
[5]*የእግዚአብሔር* ክብር ታላቅ ነውና፣
ስለ *እግዚአብሔር* መንገድ ይዘምሩ።
[6]*እግዚአብሔር* በከፍታ ስፍራ ቢሆንም፣
ዝቅ ያለውን ይመለከተዋል፤
ትዕቢተኛውን ከሩቅ ያውቀዋል።
[7]በመከራ መካከል ብሄድም፣
አንተ ሕይወቴን ትጠብቃታለህ፤
በጠላቶቼ ቍጣ ላይ እጅህን ትዘረጋለህ፤
በቀኝ እጅህም ታድነኛለህ።
[8]*እግዚአብሔር* በእኔ ላይ ያለውን ዐላማ
ይፈጽማል፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ምሕረትህ
ለዘላለም ነው።
የእጅህንም ሥራ ቸል አትበል።

## መዝሙር 139

### ሁሉን ዐዋቂ አምላክ

ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ መረመርኸኝ፤
ደግሞም ዐወቅኸኝ።
[2]አንተ መቀመጤንና መነሣቴን ታውቃለህ፤
የልቤንም ሐሳብ ገና ከሩቁ
ታስተውላለህ።
[3]መሄድ መተኛቴን አጥርተህ ታውቃለህ፤
መንገዶቼንም ሁሉ ተረድተሃቸዋል።
[4]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ገና ቃል ከአንደበቴ
ሳይወጣ፣
እነሆ፤ አንተ ሁሉንም ታውቃለህ።
[5]አንተ ከኋላም ከፊትም ዙሪያዬን
ከለልኸኝ፤
እጅህንም በላዬ አደረግህ።
[6]እንዲህ ያለው ዕውቀት ለኔ ድንቅ ነው፤
ልደርስበትም የማልችል ከፍ ያለ ነው።
[7]ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?
ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?
[8]ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ አለህ፤
መኝታዬንም በሲኦል[ሰ] ባደርግ በዚያ
ትገኛለህ።

136፥22 ዘዳ29፥8፤ መዝ78፥55፤ኢሳ 20፥3፤41፥8፤42፥19፤ 43፥10፤44፥1፡21፤ 45፥4፤49፥5-7
136፥23 መዝ78፥39 ፤103፥14፤115፥12
136፥24 ዘዳ6፥19፤ ኢሱ10፥14፤ነህ9፥28
136፥25 ዘፍ1፥30፤ ማቴ6፥26
136፥26 ዕዝ3፥11፤ መዝ105፥1፤115፥3
137፥1 ነህ1፥4፤ ኢሳ3፥26፤ሰቆ1፥4፤ ሕዝ 1፥1፡3፤ 3፥15፤10፥15
137፥2 ዘሌ23፥40፤ ኢዮ30፥31፤ኢሳ24፥8፤ ሕዝ26፥13፤አሞ6፥5
137፥3 ኢዮ30፥9፤ መዝ79፥1-4፤80፥6፤ ሰቆ1፥5፤ሕዝ16፥57፤ 22፥4፤34፥29
137፥4 ነህ12፥46
137፥5 ኢሳ2፥3፤ 56፥7፤65፥11፤66፥20
137፥6 ዘዳ4፥29፤ ነህ2፥3፤መዝ22፥15፤ ኤር51፥50፤ሕዝ6፥9
137፥7 ዘፍ25፥30፤ 2ነገ25፥1-10፤ 2ዜና 28፥17፤ መዝ74፥8፤83፥6፤ ሰቆ4፥21-22፤አብ1፥11
137፥8 ኢሳ13፥1፡ 19፤47፥1-15፤ ኤር25፥12፡26፤ 50፥1፡2-51፡58
137፥9 2ነገ8፥12፤ ኢሳ13፥16፤ ሉቃ 19፥44
138፥1 መዝ27፥6፤ 95፥3፤96፥4፤108፥1
138፥2 1ነገ8፥29፤ መዝ5፥7፤74፥21፤ 97፥12፤108፥4፤115፥1 ፤119፥9፤140፥13
138፥3 መዝ18፥6፤ 28፥7፤30፥2፤99፥6፤ 116፥4፤118፥5፤ ምሳ28፥1፤ሐሥ4፥29
138፥4 መዝ72፥11 ፤102፥15
138፥5 መዝ21፥5፤ 51፥14፤71፥16፤ 145፥7
138፥6 መዝ40፥4፤ 113፥6፤ማቴ23፥12
138፥7 ዘፀ7፥5፤ መዝ7፥6፤17፥7፡14፤ 20፥6፤23፥4፤41፥2፤ 60፥5፤108፥6
138፥8 ዕዝ3፥11፤ ኢዮ10፥3፡8፤መዝ51፥11 ፤100፥5፤ፊል1፥6
139፥1 መዝ17፥3፤ 44፥21፤ሮሜ8፥27
139፥2 2ነገ19፥27፤ መዝ94፥11፤ ምሳ24፥12፤ኤር12፥3
139፥3 2ነገ19፥27፤ ኢዮ31፥4 139፥4 ዕብ4፥13 139፥5 1ሳሙ25፥16፤መዝ32፥10፤ 34፥7፤125፥2 139፥6 መዝ131፥1፤ሮሜ11፥33 139፥7 ኤር 23፥24፤ዮና1፥3 139፥8 ዘዳ30፥12-15፤ኢዮ17፥13፤አሞ9፥2-3

[ሪ]13 ዕብራይስጡ *ያመሱፍ* የሚለው በቍ 15 ከሚገኘው ጭምር የሸምበቆ ባሕር ይለዋል።
[ሰ]8 አንዳንድ ትርጉሞች *በጥልቁ ውስጥ* ይላሉ።

9 በንጋት ክንፍ ተነሥቼ ብበር፣
እስከ ባሕሩ ዳርቻ መጨረሻ ብሄድ፣
10 በዚያም ቢሆን እጅህ ትመራኛለች፤
ቀኝ እጅህም አጥብቃ ትይዘኛለች።

11 እኔም፣ “ጨለማው በርግጥ ይሰውረኛል፤
በዙሪያዬ ያለውም ብርሃን ሌሊት
ይሆናል” ብል፣
12 ጨለማ የአንተን ዐይን አይዝም፤
ሌሊቱም እንደ ቀን ያበራል፤
ጨለማም ብርሃንም ለአንተ አንድ
ናቸውና።

13 አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፤
በእናቴም ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ
ሠራኸኝ።
14 ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና
አመሰግንሃለሁ፤
ሥራህ ድንቅ ነው፤
ነፍሴም ይህን በውል ተረድታለች።
15 እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፣
ዐጥንቶቼ ከአንተ አልተደበቁም፤
በምድር ጥልቀት ውስጥ በጥበብ
በተሠራሁ ጊዜ፣
16 ዐይኖችህ ገና ያልተበጀውን አካሌን
አዩ፤
ለእኔ የተወሰኑልኝም ዘመናት፣
ገና አንዳቸው ወደ መኖር ሳይመጡ፣
በመጽሐፍህ ተመዘገቡ።

17 አምላክ ሆይ፤ ለእኔ ያለህ ሐሳብ እንዴት
ክቡር ነው!
ቍጥሩስ ምንኛ ብዙ ነው!
18 ልቍጠራቸው ብል፣
ከአሸዋ ይልቅ ይበዙ ነበር።
ተኛሁም ነቃሁም፣
ገና ከአንተው ጋር ነኝ።

19 አምላክ ሆይ፣ ክፉዎችን ብትገድላቸው
ምናለበት!
ደም የተጠማችሁ ሰዎች ሆይ፤ ከእኔ ራቁ!
20 ስለ አንተ በክፋት ይናገራሉና፤
ጠላቶችህም ስምህን በከንቱ ያነሣሉ።
21 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ የሚጠሉህን
አልጠላምን?
በአንተ ላይ የሚነሡትንስ
አልጸየፍምን?
22 በፍጹም ጥላቻ ጠልቻቸዋለሁ፤
ባላጋራዎቼም ሆነዋል።

23 እግዚአብሔር ሆይ፤ መርምረኝ፤ ልቤንም
ዕወቅ፤
ፈትነኝ፤ ሐሳቤንም ዕወቅ፤
24 የክፋት መንገድ በውስጤ ቢኖር እይ፤
በዘላለምም መንገድ ምራኝ።

## *መዝሙር* 140

**በክፉዎች ላይ የቀረበ ጸሎት**

*ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት መዝሙር*

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከክፉ ሰዎች
አድነኝ፤
ከዐመፀኞችም ሰዎች ጠብቀኝ፤
2 እነርሱ በልባቸው ክፉ ነገር
ያውጠነጥናሉ፤
በየዕለቱም ጦርነት ይጭራሉ።
3 ምላሳቸውን እንደ እባብ ያሾላሉ፤
ከከንፈራቸውም በታች የእፉኝት
መርዝ አለ። ሴላ

4 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ከክፉዎች እጅ
ጠብቀኝ፤
እግሮቼንም ለመጥለፍ ከሚያደቡ
ዐመፀኞች ሰውረኝ።
5 ትዕቢተኞች ወጥመድ በስውር አስቀመጡብኝ፤
የመረባቸውን ገመድ ዘረጉብኝ፤
በመንገዴም ላይ አሽክላ አኖሩ። ሴላ

6 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ “አንተ አምላኬ ነህ”
እልሃለሁ፤
*እግዚአብሔር* ሆይ፤ የልመና ጩኸቴን
ስማ።
7 ብርቱ አዳኝ የሆንህ፣ ጌታ *እግዚአብሔር*
ሆይ፤
በጦርነት ዕለት የራስ ቍር ሆንኸኝ።
8 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ የክፉዎች ምኞት
አይፈጸም፤
በትዕቢትም እንዳይኰራሩ፣
ዕቅዳቸው አይሳካ። ሴላ

9 ዙሪያዬን የከበቡኝ ሰዎች ራስ፣
የከንፈራቸው መዘዝ ይጠምጠምበት።
10 የእሳት ፍም በላያቸው ይውረድ፤
ዳግመኛም እንዳይነሡ ወደ እሳት ይጣሉ፤
ማጥ ወዳለበት ጕድጓድ ይውደቁ።
11 ምላሰኛ በምድሪቱ ጸንቶ አይኑር፤
ዐመፀኛውን ሰው ክፋት አሳዶ
ያጥፋው።

12 *እግዚአብሔር* ለድኻ ፍትሕን
እንደሚያስከብር፣
ለችግረኛውም ትክክለኛ ፍርድን
እንደሚሰጥ ዐውቃለሁ።
13 ጻድቃን በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ፤
ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ።

## *መዝሙር* 141

**የክፉዎችን ድሎት ላለመመኘት የቀረበ ጸሎት**

1 *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወደ አንተ እጣራ
ለሁ፤ ፈጥነህ ድረስልኝ፤
ወደ አንተ ስጣራም ድምፄን ስማ።
2 ጸሎቴ በፊትህ እንደ ዕጣን ትቈጠርልኝ፤

139፥10 መዝ23፥3፤108፥6፤ኢሳ41፥10
139፥12 ኢዮ34፥22፤ዳን2፥22
139፥13 ኢዮ10፥11፤መዝ119፥73፤ኢሳ44፥2፡24፤46፥3፤49፥5፤ኤር1፥5
139፥14 ኢዮ40፥19፤መዝ119፥164፤145፥10
139፥15 ኢዮ10፥11፤መዝ63፥9፤መክ11፥5
139፥16 ኢዮ33፥29፤መዝ90፥12
139፥17 ኢዮ5፥9፤መዝ92፥5
139፥18 ኢዮ29፥18፤መዝ3፥5፤40፥5
139፥19 መዝ5፥6፤6፥8፤59፥2፤ኢሳ11፥4
139፥20 ዘጸ5፥11፤መዝ65፥7
139፥21 2ዜና19፥2፤መዝ26፥5፤31፥6፤119፥113
139፥22 ማቴ5፥43
139፥23 1ሳሙ16፥7፤1ዜና29፥17፤ኢዮ 31፥6፤መዝ7፥9፤ምሳ17፥3፤ኤር11፥20፤ራእ2፥23
139፥24 መዝ5፥8፤23፥2፤143፥10፤ኤር25፥5፤36፥3
140፥1 ቍ11፤መዝ17፥13፤25፥20፤59፥2፤71፥4፤86፥14፤142፥6፤143፥9
140፥2 መዝ36፥4፤52፥2፤68፥30፤ምሳ6፥14፤16፥27፤ኢሳ59፥4፤ሆሴ7፥15
140፥3 መዝ57፥4፤58፥4፤ሮሜ3፥13፤ያዕ3፥8
140፥4 መዝ36፥11፤141፥9
140፥5 ኢዮ18፥8፡9፤34፥30፤መዝ31፥4፤38፥12፤119፥110
140፥6 መዝ16፥2፤28፥2፡6
140፥7 መዝ68፥20
140፥8 መዝ10፥2-3፤66፥7
140፥9 ምሳ18፥7
140፥10 መዝ11፥6፤21፥9፤ማቴ3፥10፤ሉቃ12፥49፤ራእ 20፥15
140፥11 መዝ34፥21
140፥12 1ነገ8፥45፤መዝ35፥10፤82፥3
140፥13 መዝ11፥7፤16፥11፤138፥2
141፥1 መዝ4፥1፤5፥1-2፤22፥19፤27፥7፤143፥1
141፥2 ዘፀ29፥39፡41፤30፥8፤መዝ28፥2፤

እጄን ማንሣቴም እንደ ሠርክ
መሥዋዕት ትሁን።
[3]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ለአፌ ጠባቂ
አድርግ፤
የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።
[4]ከዐመፀኞች ጋር፣
በክፉ ሥራ እንዳልተባበር፣
ልቤን ወደ ክፉ አታዘንብል፤
ከድግሳቸውም አልቋደስ።
[5]ጻድቅ[ሽ] ሰው ይቀጣኝ፤ ይህ በጎነት ነው፤
ይገሥጸኝም፤ በራሴ ላይ እንደሚፈስ
ዘይት ነው፤
ራሴም ይህን እንቢ አይልም።
ጸሎቴ ግን በክፉዎች ተግባር ላይ ነው፤
[6]ሹማምታቸው ከገደል አፋፍ ቍልቍል
ይወረወራሉ፣
ቃሌ የምታረካ ናትና፣ ይሰሟታል።
[7]ደግሞም፣ "ሰው ምድርን እንደሚያርስና
ዐፈሩን እንደሚፈረካክስ፣
እንዲሁ ዐጥንታችን በሲኦል[ቀ] አፋፍ
ላይ ተበታተነ" ይላሉ።
[8]ጌታ *እግዚአብሔር* ሆይ፤ ዐይኖቼ ግን
ወደ አንተ ይመለከታሉ፤
መጠጊያዬም አንተ ነህ፤ እንግዲህ
ነፍሴን አትተዋት።
[9]ከዘረጉብኝ ወጥመድ፣
ከክፉ አድራጊዎችም አሽክላ ጠብቀኝ።
[10]እኔ ብቻ በደኅና ሳመልጥ፣
ክፉዎቹ በገዛ ወጥመዳቸው ይውደቁ።

## *መዝሙር* 142
## የሚታደን ሰው ጸሎት

ዋሻ ውስጥ በነበረ ጊዜ፤ የዳዊት ትምህርት፤[በ] ጸሎት

[1]ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ *እግዚአብሔር*
እጮኻለሁ፤
ድምፄን ከፍ አድርጌ ወደ *እግዚ
አብሔር* ልመና አቀርባለሁ።
[2]ብሶቴን በፊቱ አፈስሳለሁ፤
ችግሬንም በፊቱ እናገራለሁ።
[3]መንፈሴ በውስጤ ሲዝል፣
መንገዴን የምታውቅ አንተ ነህ፤
በመተላለፊያ መንገዴ ላይ፤
ወጥመድ በስውር ዘርግተውብኛል።
[4]ወደ ቀኜ ተመልከት፤ እይም፤
ስለ እኔ የሚገደው የለም፤
ማምለጫም የለኝም፤
ስለ ነፍሴም ደንታ ያለው የለም።
[5]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ወደ አንተ እጮኻለሁ፤
ደግሞም፣ "አንተ መጠጊያዬ ነህ፤
በሕያዋንም ምድር ዕድል ፈንታዬ ነህ"

63፥4፤ሉቃ1፥9፤
1ጢሞ 2፥8፤
ራእ5፥8፤8፥3
141፥3 መዝ12፥2፤
34፥13፤ያዕ1፥26፤3፥8
141፥4 ኢሱ24፥23፤
መዝ106፥29፤
ምሳ23፥1-3
141፥5 ዘፀ29፥7፤
መዝ23፥5፤ምሳ9፥8፤
19፥25፤ 25፥12፤
መክ7፥5
141፥6 2ዜና25፥12
141፥7 ዘኍ16፥30፡
32-33፤መዝ129፥3
141፥8 መዝ2፥12
፤11፥1፤123፥2
141፥9 መዝ38፥12
፤64፥5፤140፥4
141፥10 መዝ7፥15
፤35፥8፤57፥6፤124፥7
142 ርዕስ 1ሳሙ
22፥1፤24፥3፤
መዝ57ርዕስ
142፥1 1ነገ8፥52፤
መዝ3፥4፤30፥8
142፥2 መዝ50፥15
፤64፥1
142፥3 መዝ6፥2፤
77፥3፤84፥2፤88፥4፤
143፥4፡7፤ኤር8፥18፤
ሰቆ1፥22
142፥4 ኤር25፥35፤
30፥17
142፥5 ዘዳ32፥9፤
ኢዮ28፥13፤
መዝ16፥5፤
27፥13፤46፥1
142፥6 መዝ17፥1፤
25፥20፤79፥8፤
ኤር31፥11
142፥7 2ዜና6፥41፤
መዝ7፥17፤9፥2፤
66፥11
143፥1 ዘፀ34፥6፤
መዝ28፥2፤71፥2፤
89፥1-2፤130፥2፤
141፥1
143፥2 መዝ14፥3፤
ሮሜ3፥10
143፥3 መዝ107፥
10፤ሰቆ3፥6
143፥4 መዝ30፥7
143፥5 ዘፍ24፥63፤
መዝ77፥6
143፥6 ዘፀ9፥29፤
ኢዮ11፥13
143፥7 መዝ22፥24
፤27፥9፤30፥7፤69፥17፤
142፥3
143፥8 ዘፀ33፥13፤
ኢዮ34፥32፤መዝ6፥4
፤25፥1-2፤27፥11፤
32፥8፤86፥4፤90፥14
143፥9 መዝ18፥17
፤31፥15፤140፥1
143፥10 ነህ9፥20፤
መዝ25፥4-5፤26፥12፤
31፥14፤119፥12
143፥11 መዝ25፥11
፤31፥1፤41፥2፤71፥2

እላለሁ።
[6]እጅግ ተስፋ ቈርጫለሁና፣
ጩኸቴን ስማ፤
ከዐቅም በላይ ሆነውብኛልና፣
ከሚያሳድዱኝ አድነኝ።
[7]ስምህን አመሰግን ዘንድ፣
ነፍሴን ከወህኒ አውጣት፤
ከምታደርግልኝም በጎ ነገር የተነሣ፣
ጻድቃን በዙሪያዬ ይሰበሰባሉ።

## *መዝሙር* 143
## ትሑት ልመና

የዳዊት መዝሙር

[1]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ጸሎቴን ስማ፤
ልመናዬን አድምጥ፤
በታማኝነትህና በጽድቅህም፣
ስምተህ መልስልኝ።
[2]ሰው ሆኖ በፊትህ ጻድቅ የለምና፣
ባሪያህን ወደ ፍርድ አታቅርበው።
[3]ጠላት እስከ ሞት አሳዶኛል፤
ሕይወቴንም አድቅቆ ከዐፈር
ቀላቅሎአል፤
ቀደም ብለው እንደ ሞቱትም፣
በጨለማ ውስጥ አኑሮኛል።
[4]ስለዚህ መንፈሴ በውስጤ ዝላለች፤
ልቤም በውስጤ ደንግጦአል።
[5]የቀድሞውን ዘመን አስታወስሁ፤
ሥራህንም ሁሉ አሰላሰልሁ፤
የእጅህንም ሥራ አውጠነጠንሁ።
[6]እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ፤
ነፍሴም እንደ ምድረ በዳ አንተን
ተጠማች። ሴላ
[7]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ፈጥነህ መልስልኝ፤
መንፈሴ ደከመች፤
ወደ ጕድጓድ እንደሚወርዱት
እንዳልሆን፣
ፊትህን ከእኔ አትሰውር።
[8]በአንተ ታምኛለሁና፣
በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ፤
ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና፣
የምሄድበትን መንገድ አሳየኝ።
[9]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ አንተን መሰወሪያ
አድርጌአለሁና፣
ከጠላቶቼ አድነኝ።
[10]አንተ አምላኬ ነህና፣
ፈቃድህን እንድፈጽም አስተምረኝ፤
መልካሙ መንፈስህም፣
በቀናችው መንገድ ይምራኝ።
[11]*እግዚአብሔር* ሆይ፤ ስለ ስምህ ሕያው

[ሽ]5 ወይም *ጻድቁ*
[ቀ]7 አንዳንድ ትርጕሞች *መቃብር* ይላሉ።
[በ]ርእሱ ላይ ሥነ ጽሑፋዊ ወይም የዜማ ቃል ሊሆን ይችላል።

አድርገኝ፤
በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራ አውጣት፡፡
12 ጠላቶቼንም ለእኔ ስላለህ ምሕረት
ደምስሳቸው፤
እኔ ባሪያህ ነኝና፣
ነፍሴን የሚያስጨንቋትን ሁሉ
አጥፋቸው፡፡

## መዝሙር 144

### የጦርነት መዝሙር

የዳዊት መዝሙር

1 እጆቼን ለጦርነት፣
ጣቶቼን ለውጊያ የሚያሠለጥን፣
እግዚአብሔር ዐለቴ ይባረክ፡፡
2 እርሱ አፍቃሪ አምላኬና ጽኑ ዐምባዬ
ነው፤
ምሽጌና ታዳጊዬ፣
የምከለልበትም ጋሻዬ ነው፤
ሕዝቤን የሚያስገዛልኝም† እርሱ ነው፡፡
3 እግዚአብሔር ሆይ፤ ይህን ያህል በልብህ
ስፍራ ትሰጠው ዘንድ ሰው ምንድን
ነው?
ታስበውስ ዘንድ የሰው ልጅ እስከዚህ
ምንድን ነው?
4 ሰው እንደ እስትንፋስ ነው፤
ዘመኑም ፈጥኖ እንደሚያልፍ ጥላ
ነው፡፡
5 እግዚአብሔር ሆይ፤ ሰማያትህን
ሰንጥቀህ ውረድ፤
ይጤሱም ዘንድ ተራሮችን ዳስስ፡፡
6 የመብረቅ ብልጭታ ልከህ በትናቸው፤
ፍላጻህን ሰደህ ግራ አጋባቸው፡፡
7 እጅህን ከላይ ዘርጋ፤
ከኀይለኛ ውሃ፣
ከባዕዳንም እጅ፣
ታደገኝ፤ አድነኝም፤
8 አንደበታቸው ሐሰትን ይናገራል፤
ቀኝ እጃቸውም የቅጥፈት ቀኝ እጅ
ናት፡፡
9 አምላክ ሆይ፤ አዲስ ቅኔ እቀኝልሃለሁ፤
ዐሥር አውታር ባለው በገና
እዘምርልሃለሁ፡፡
10 ነገሥታትን ድል የሚያጐናጽፍ፣
ባሪያውን ዳዊትን ከሚጐዳ ሰይፍ
የሚያድነው እርሱ ነው፡፡
11 አንደበታቸው ሐሰትን ከሚናገር፣
ቀኝ እጃቸው የቅጥፈት ቀኝ እጅ
ከሆነችው፣
ከባዕዳን እጅ፣
ታደገኝ፤ አድነኝም፡፡
12 ወንዶች ልጆቻችን በወጣትነታቸው፣
የተሟላ ዕድገት እንዳገኘ ተክል፣
ሴቶች ልጆቻችንም ቤተ መንግሥት
ለማስጌጥ፣
እንደ ተቀረጹ የማእዘን ዐምዶች
ይሁኑ፡፡
13 ጐተራዎቻችን በተለያየ የእህል ዐይነት፣
የተሞሉ ይሁኑ፤
በጎቻችን እስከ ሺህ ይውለዱ፤
በመስኮቻችንም እስከ ዐሥር ሺህ
ይባዙ፡፡
14 ከብቶቻችን ይክበዱ፤‡
አይጨንግፉ፤ አይጥፉም፡፡
እኛም በምርኮ አንወሰድ፤
በአደባባዮቻችንም ዋይታ አይሰማ፡፡
15 ይህ ባርኮት ገንዘቡ የሆነ ሕዝብ ምስጉን
ነው፤
እግዚአብሔር አምላኩ የሆነ ሕዝብ
ምስጉን ነው፡፡

## መዝሙር 145ኀ

### ምስጋና ለንጉሡ ለእግዚአብሔር

የዳዊት የምስጋና መዝሙር

1 አምላኬና ንጉሤ ሆይ፤ ከፍ ከፍ
አደርግሃለሁ፤
ስምህን ከዘላለም እስከ ዘላለም
እባርካለሁ፡፡
2 በየቀኑ እባርክሃለሁ፤
ስምህንም ከዘላለም እስከ ዘላለም
አመሰግናለሁ፡፡
3 እግዚአብሔር ታላቅ ነው፤
እጅግ ሊመሰገንም ይገባዋል፤
ታላቅነቱም አይመረመርም፡፡
4 ሥራህን አንዱ ትውልድ ለሌላው
ትውልድ ያስተጋባል፤
ብርቱ ሥራህን ያውጃል፡፡
5 ስለ ግርማህ ውበትና ስለ ክብርህ ይናገራሉ፤
እኔም ስለ ድንቅ ሥራህ አሰላስላለሁ፡፡
6 ስለ ድንቅ ሥራህ ብርታት ይነጋገራሉ፤
እኔም ስለ ታላቅነትህ ዐውጃለሁ፡፡
7 የበጎነትህን ብዛት በደስታ ያወሳሉ፤
ስለ ጽድቅህም በእልልታ ይዘምራሉ፡፡
8 እግዚአብሔር ቸር ነው፤ ርኅሩኅም ነው፤
ለቍጣ የዘገየ፣ ምሕረቱ የበዛ፡፡
9 እግዚአብሔር ለሁሉ ቸር ነው፤
ምሕረቱም በፍጥረቱ ሁሉ ላይ ነው፡፡
10 እግዚአብሔር ሆይ፤ ፍጥረትህ ሁሉ
ያመሰግንሃል፤

†2 አንዳንዶች ሕዝቦችን የሚያስገዛልኝ ይላሉ፡፡
‡14 ወይም *መሪዎቻችን ይጠነክራሉ*፡፡
ኀም145 ይህ መዝሙር ተከታታይ በሆኑ የዕብራይስጥ ፊደ ላት የሚጀምር ሲሆን (ከቍ13 ጭምር) መነሻዎቹ ወይም መነሻዎቹና መድረሻዎቹ ሆህያት ቍልቍል ሲነበቡ ትርጒም ያላቸውን ቃላት የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

143፥12 መዝ8፥2፤54፥5፤116፥16
144፥1 ዘፍ49፥24
144፥2 ዘፍ15፥1፤መሳ4፥23፤መዝ18፥2፡39፤27፥1፤37፥39፤43፥2፤59፥9፤91፥2
144፥3 ዕብ2፥6
144፥4 1ዜና29፥15፤ኢዮ7፥7፤14፥2፤27፥3፤ኢሳ2፥22፤ያዕ4፥14
144፥5 ዘፍ11፥5፤መዝ18፥9፤57፥3፤104፥32፤ኢሳ64፥1
144፥6 መዝ7፥12-13፤18፥14፤59፥11፤68፥1፤ዕን3፥11፤ዘካ9፥14
144፥7 2ሳሙ22፥17፤መዝ3፥7፤18፥44፤57፥3፤69፥2
144፥8 ዘፍ14፥22፤ዘጸ32፥40፤መዝ12፥2፤36፥3፤41፥6
144፥9 መዝ28፥7፤33፥2-3፤71፥22፤96፥1
144፥10 2ሳሙ8፥14፤ኢዮ5፥20፤መዝ 18፥50
144፥11 መዝ3፥7፤12፥2፤18፥44፤25፥20፤36፥3፤41፥6-7፤106፥26፤ኢሳ44፥20
144፥12 መዝ92፥12-14፤128፥3፤መሐ4፥4፤7፥4
144፥13 ምሳ3፥10
144፥14 2ነገ25፥11፤ምሳ14፥4፤ኢሳ24፥11፤ ኤር14፥2-3
144፥15 ዘዳ28፥3
145፥1 መዝ2፥6፤5፥2፤30፥1፤34፥1፤54፥6
145፥2 መዝ34፥1፤71፥6፤ኢሳ25፥1፤26፥8
145፥3 2ሳሙ22፥4፤ኢዮ5፥9፤መዝ95፥3፤96፥41
145፥4 ዘዳ11፥19፤መዝ22፥30፤71፥16
145፥5 መዝ75፥1፤96፥6፤148፥13
145፥6 ዘዳ32፥3፤መዝ66፥3፤75፥1፤78፥4፤106፥22
145፥7 ዘፀ18፥9፤መዝ5፥11፤27፥13፤101፥1፤138፥5
145፥8 መዝ86፥5፡15፤103፥8
145፥9 1ዜና16፥34፤መዝ103፥13-14፤136፥1፤ማቴ19፥17፤ማር10፥18
145፥10 መዝ8፥6፤30፥4፤103፥22፤115፥17-18፤139፥14፤

ቅዱሳንህም ይባርኩሃል።
11ስለ *መንግሥትህ* ክብር ይናገራሉ፤
ስለ ኀይልህም ይነጋገራሉ፤
12በዚህም ብርቱ *ሥራህን*፣
*የመንግሥትህንም ግርማ* ክብር
*ያስታውቃሉ*።
13*መንግሥትህ* የዘላለም *መንግሥት* ናት፤
*ግዛትህም ለትውልድ ሁሉ ጸንቶ*
*ይኖራል*።

*እግዚአብሔር ቃሉን* ሁሉ ይጠብቃል፤
በ*ሥራውም*[ኘ] ሁሉ ቸር *ነው*።
14*እግዚአብሔር የሚንገዳገዱትን* ሁሉ
*ይደግፋል*፤
የወደቁትንም ሁሉ *ያነሣል*።
15የሁሉ ዐይን *አንተን* በተስፋ ይጠብቃል፤
*አንተም* ምግባቸውን በወቅቱ
ትሰጣቸዋለህ።
16*አንተ* እጅህን ትዘረጋለህ፤
የሕያዋን ፍጥረታትንም ሁሉ ፍላጎት
ታረካለህ።

17*እግዚአብሔር* በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ፣
በ*ሥራውም* ሁሉ ቸር *ነው*።
18*እግዚአብሔር* ለሚጠሩት ሁሉ፣
በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ *ነው*።
19ለሚፈሩት ፍላጎታቸውን ይፈጽማል፤
ጩኸታቸውን ይሰማል፤ *ያድናቸዋልም*።
20*እግዚአብሔር* የሚወዱትን ሁሉ
ይጠብቃል፤
ክፉዎችን ሁሉ ግን *ያጠፋል*።

21አፌ *የእግዚአብሔርን* ምስጋና ይናገራል፤
ፍጡር ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም፣
ቅዱስ ስሙን ይባርክ።

## *መዝሙር* 146
## ለረድኤት አምላክ ምስጋና

1*ሃሌ ሉያ*።[አ]
ነፍሴ *ሆይ*፤ *እግዚአብሔርን* ባርኪ።
2በምኖርበት ዘመን ሁሉ *እግዚአብሔርን*
አመሰግናለሁ፤
በሕይወትም እስካለሁ ለአምላኬ
እዘምራለሁ።
3በገዥች አትታመኑ፤
*ማዳን* በማይችሉ *ሥጋ* ለባሾችም
አትመኩ።
4*መንፈሳቸው* ትወጣለች፤ ወደ
*መሬታቸውም ይመለሳሉ*፤
*ያን* ጊዜም ዕቅዳቸው እንዳልነበር
ይሆናል።

5*ረዳቱ* የያዕቆብ አምላክ የሆነ፣
ተስፋውንም በአምላኩ *በእግዚአብሔር*
ላይ የጣለ ሰው ምስጉን *ነው*፤
6እርሱ ሰማይንና ምድርን፣ ባሕርንም፣

148፥14፤149፥9
**145፥11** ቊ12-13፤ ዘፀ15፥2፤መዝ21፥13፤ ማቴ6፥33
**145፥12** ቊ11፤ መዝ75፥1፤103፥19፤ 105፥1፤ኢሳ2፥10፥19፥21
**145፥13** ዘፀ15፥18፤ ዘዳ7፥9፤ኢሱ23፥14፤ 1ቆሮ1፥9፤ 1ጢሞ 1፥17፤ 2ጴጥ1፥11፤ራእ11፥15
**145፥14** 1ሳሙ2፥8፤መዝ37፥17፤38፥6፤ 146፥8
**145፥15** ዘፍ1፥30፤ ኢዮ28፥5፤ መዝ37፥25፤ማቴ6፥26
**145፥16** መዝ90፥14፤104፥28
**145፥17** ቊ13፤ ዘፀ9፥27፤ዕዝ9፥15
**145፥18** ዘኍ23፥21፤መዝ18፥6፤46፥1፤ 80፥18፤ፊል4፥5
**145፥19** 1ሳሙ10፥ 19፤ኢዮ22፥28፤ መዝ 7፥10፤20፥4፤ 31፥22፤34፥18፤40፥1
**145፥20** መዝ1፥6፤ 31፥23፤91፥14፤94፥2 3፤97፥10
**145፥21** ዘፀ3፥15፤ መዝ30፥4፤65፥2፤ 71፥8፤99፥3፤150፥6
**146፥1** መዝ103፥1፤ 104፥1
**146፥2** መዝ63፥4፤ 104፥33፤105፥2
**146፥3** መዝ60፥11፤ 108፥12፤118፥9፤ ኢሳ 2፥22
**146፥4** ዘፍ3፥19፤ ኢዮ7፥21፤መዝ33፥10፤ 103፥14፤መክ12፥7፤ 1ቆሮ2፥6
**146፥5** መዝ33፥18፤ 37፥9፤70፥5፤71፥5፤ 119፥43፤121፥2፤ 144፥15፤ኤር17፥7
**146፥6** ዘዳ7፥9፤ 2ዜና2፥12፤መዝ18፥25፤ 108፥4፤115፥15፤117፥2፤ሐሥ14፥15፤ራእ10፥6
**146፥7** መዝ37፥17፤ 66፥11፤68፥6፤103፥6፤107፥9፤145፥15
**146፥8** ዘፀ4፥11፤ ዘዳ7፥13፤ኢዮ23፥10፤ መዝ38፥6፤ምሳ20፥12፤ ኢሳ29፥18፤32፥3፤ 35፥5፤42፥7፤18-19፤ 43፥8፤ማቴ11፥5
**146፥9** ዘፀ22፥22፤ ዘሌ19፥34፤መዝ10፥18፤ያዕ1፥27
**146፥10** ዘፍ21፥33፤ 1ዜና16፥31፤መዝ93፥1፤99፥1፤ራእ11፥15
**147፥1** መዝ33፥1፤ 135፥3
**147፥2** መዝ51፥18

በእነዚህም ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረ፣
*ታማኝነቱንም* ለዘላለም የሚጠብቅ *ነው*፤
7ለተበደሉት የሚፈርድ፣
ለተራቡት ምግብን የሚሰጥ እርሱ *ነው*፤
*እግዚአብሔር* እስረኞችን ከእስራት
ያወጣል፤
8*እግዚአብሔር* የዕውራንን ዐይን *ያበራል*፤
*እግዚአብሔር* የተዋረዱትን ከፍ
*ያደርጋል*፤
*እግዚአብሔር* ጻድቃንን ይወዳል፤
9*እግዚአብሔር* ስደተኞችን ይጠብቃል፤
ድኻ ዐደጎችንና መበለቶችን ይደግፋል፤
የክፉዎችን መንገድ ግን *ያጠፋል*።

10*እግዚአብሔር* ለዘላለም ይነግሣል፤
ጽዮን *ሆይ*፤ አምላክሽ ለትውልድ ሁሉ
*ንጉሥ ነው*።

*ሃሌ ሉያ*።

## *መዝሙር* 147
## *መዝሙር* ለሁሉን ቻይ አምላክ

1*ሃሌ ሉያ*።[ከ]
አምላካችንን በ*መዝሙር* ማወደስ እንዴት
*መልካም ነው*፤
እርሱን ማመስገን ደስ *ያሰኛል*፤ ይህ
ተገቢም *ነው*።

2*እግዚአብሔር* ኢየሩሳሌምን *መልሶ*
*ይሠራታል*፤
ከእስራኤል የተበተኑትን ይሰበስባል።
3ልባቸው የተሰበረውን ይፈውሳል፤
ቍስላቸውንም ይጠግናል።
4የከዋክብትን ብዛት *ያውቃል*፤
እያንዳንዱንም በስሙ ይጠራዋል።
5ጌታችን *ታላቅ ነው*፤ እጅግ ኀያልም *ነው*፤
ለጥበቡም ወሰን የለውም።
6*እግዚአብሔር* ትሑታንን ከፍ *ያደርጋል*፤
ክፉዎችን ግን ወደ ምድር ይጥላል።

7*ለእግዚአብሔር* በምስጋና ዘምሩ፤
ለአምላካችንም በመሰንቆ ምስጋና
አቅርቡ።
8ሰማይን በደመናት የሚሸፍን እርሱ *ነው*፤

፤106፥47 **147፥3** ዘኍ12፥13፤ኢዮ5፥18፤መዝ34፥18፤ኢሳ1፥6፤ ሕዝ34፥16 **147፥4** ዘፍ15፥5 **147፥5** ዘፀ14፥31፤መዝ48፥1፤ 145፥3፤ኢሳ40፥28 **147፥6** 2ዜና33፥23፤መዝ37፥9-10፤ 145፥20፤146፥8-9 **147፥7** መዝ27፥6፤30፥4፤33፥3፤42፥4፤ 98፥5 **147፥8** ዘዳ11፥14፤32፥2፤2ሳሙ1፥21፤ኢዮ5፥10፤ 26፥8፤28፥26፤መዝ104፥14

[ነ]5 የሙት ባሕር ጥቅልሎች እና ሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ) *ስለግርማህ ታላቅነትና ክብር፣ ዕፁብ ድንቅ ሥራህን አሰላስላለሁ* ይላሉ።
[ኘ]13 አንድ የማስሬቲክ ቅጅ፣ የሙት ባሕር ጥቅልሎች እና ሱርስት (የሰብዓ ሊቃናትን ትርጒም ይመ) እንዲሁም አብዛኛው የማስሬቲክ ቅጆች የቊ13 ሁለት ስንኞች የሏቸውም።
[አ]1 አንዳንዶች ከ10 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።
[ከ]1 አንዳንዶች ከቊ20 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

ለምድርም ዝናብን ይሰጣል፤
በተራሮችም ላይ ሣር ያበቅላል።
9ለእንስሳት ምግባቸውን፣
የቍራ ጫጩቶችም ሲንጫጩ
የሚበሉትን ይሰጣቸዋል።

10እርሱ በፈረስ ኀይል አይደሰትም፤
በሯጭም ብርታት ላይ ደስታውን
አያደርግም።
11ነገር ግን *እግዚአብሔር* በሚፈሩት፣
በምሕረቱ በሚታመኑትም ይደሰታል።

12ኢየሩሳሌም ሆይ፤ *እግዚአብሔርን*
አመስግኚ፤
ጽዮን ሆይ፤ አምላክሽን አወድሺ፤
13እርሱ የደጆችሽን መወርወሪያ
አጽንቶአልና፤
ልጆችሽንም በውስጥሽ ባርኮአል።
14በድንበርሽ ውስጥ ሰላም ያሰፍናል፤
ማለፊያ ስንዴም ያጠግብሻል።

15ትእዛዙን ወደ ምድር ይልካል፤
ቃሉም እጅግ በፍጥነት ይሮጣል።
16ዐመዳዩን እንደ በርኖስ ይዘረጋል፤
ውርጩን እንደ ዐመድ ይነሰንሳል።
17የበረዶውን ድንጋይ ቍልቍል
ይወረውረዋል፤
በውሽንፍሩስ ቅዝቃዜ ፊት ማን ሊቆም
ይችላል?
18ቃሉን ልኮ ያቀልጣቸዋል፤
ነፋሱን ያነፍሳል፤ ውሆችንም ያፈሳል።

19ቃሉን ለያዕቆብ፣
ሥርዐቱንና ፍርዱን ለእስራኤል
ይገልጣል።
20ይህን ለማንኛውም ሌላ ሕዝብ
አላደረገም፤
እነርሱም ፍርዱን አላወቁም።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 148

### ፍጥረተ ዓለም ሁሉ ያመስግን

1ሃሌ ሉያ።[ኸ]

*እግዚአብሔርን* ከሰማያት አመስግኑት፤
በላይ በአርያም አመስግኑት።
2መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት፤
ሰራዊቱ ሁሉ አመስግኑት፤
3ፀሓይና ጨረቃ አመስግኑት፤
የምታበሩ ከዋክብት ሁሉ አመስግኑት።
4ሰማየ ሰማያት አመስግኑት፤
ከሰማያትም በላይ ያላችሁ ውሆች
አወድሱት።
5እርሱ ስላዘዘ ተፈጥረዋልና፣
*የእግዚአብሔርን* ስም ያመስግኑት።
6ከዘላለም እስከ ዘላለም አጸናቸው፤
የማይሻርም ሕግ ደነገገላቸው።

7የባሕር ውስጥ ግዙፍ ፍጥረትና ጥልቅ
ውሆች ሁሉ፣
*እግዚአብሔርን* ከምድር አመስግኑት።
8እሳትና በረዶ፣ ዐመዳይና ጭጋግ፣
ትእዛዙንም የሚፈጽም ዐውሎ ነፋስ፣
9ተራሮችና ኰረብቶች ሁሉ፣
የፍሬ ዛፎችና ዝግቦች ሁሉ፣
10የዱር አራዊትና የቤት እንስሳት ሁሉ፣
በምድር የሚሳቡ ፍጥረታትና የሚበሩ
ወፎችም፣
11የምድር ነገሥታትና ሕዝቦች ሁሉ፣
መሳፍንትና የምድር ገዦች ሁሉ፣
12ወጣት ወንዶችና ደናግል፣
አረጋውያንና ልጆች ያመስግኑት።

13ስሙ ብቻውን ከፍ ያለ ነውና፣
ክብሩም ከምድርና ከሰማይ በላይ ነውና፣
እነዚህ ሁሉ *የእግዚአብሔርን* ስም
ያመስግኑ።
14እርሱ ለሕዝቡ ቀንድን[ሠ] አስነሥቶአል፤
ለቅዱሳኑ ሁሉ ምስጋና፣
እጅግ ቅርቡ ለሆነው ሕዝቡ፣ ለእስራኤል
ልጆች።

ሃሌ ሉያ።

## መዝሙር 149

### የድል መዝሙር

1ሃሌ ሉያ።[ዐ]

*ለእግዚአብሔር* አዲስ ቅኔ ተቀኙ፤
ምስጋናውንም በቅዱሳን ጉባኤ ዘምሩ።

2እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው፤
የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤት
ያድርጉ።
3ስሙን በሽብሸባ ያመስግኑ፤
በከበሮና በመሰንቆ ይዘምሩለት።
4*እግዚአብሔር* በሕዝቡ ደስ ይለዋልና፤
የዋሃንንም በማዳኑ ውበት ያጐናጽፋል።
5ቅዱሳን በዚህ ክብር ይጓደዱ፤
በመኝታቸውም ላይ እልል እያሉ ይዘምሩ።

6የአምላክ ውዳሴ በአንደበታቸው፣
ባለ ሁለት ልሳን ሰይፍም በእጃቸው
ይሁን፤
7በዚህ ሕዝቦችን ይበቀላሉ፤
ሰዎችንም ይቀጣሉ፤

147፥9 ዘፍ1፥30፤ 8፥7፤መዝ104፥27-28 ፤ማቴ6፥26
147፥10 1ሳሙ16፥7 ፤ኢዮ39፥11፤ መዝ33፥ 16-17
147፥11 መዝ6፥4፤ 33፥18፤35፥27፤ 103፥11፤119፥43
147፥12 መዝ48፥1
147፥13 ዘዳ33፥25 ፤ዘሌ25፥21፤ መዝ128፥5፤134፥3
147፥14 ዘሌ26፥6፤ ዘዳ32፥14፤2ሳሙ7፥10 ፤መዝ132፥15፤ ኢሳ 48፥18
147፥15 ኢዮ37፥12 ፤መዝ33፥9፤148፥5፤ ኢሳ55፥1
147፥16 መዝ148፥8 ፤ኢዮ37፥12፤38፥29
147፥17 ዘፀ9፥22-23፤ ኢዮ38፥22፤መዝ78፥47
147፥18 ቍ15፤መዝ 33፥9፤50፥3፤107፥20
147፥19 ዘፀ20፥1፤ ዘዳ33፥4፤ኢሱ1፥8፤ 2ነገ22፥8፤መዝ78፥5፤ ሚል4፥4፤ሮሜ3፥2፤ 9፥4
147፥20 ዘዳ4፥7-8 ፡32-34፤መዝ33፥2፤ 79፥6፤103፥1
148፥1 መዝ19፥1፤ 33፥2፤69፥34፤ 103፥1፤150፥1
148፥2 1ነገ22፥19፤ መዝ103፥20
148፥3 መዝ19፥1
148፥4 ዘፍ1፥7፤ ዘዳ10፥14
148፥5 መዝ145፥21 ፤147፥15
148፥6 ኤር31፥35-36፤33፥25
148፥7 ዘፍ1፥21፤ ዘዳ33፥13፤መዝ33፥2 ፤74፥13-14
148፥8 ዘፀ9፥18፤ ኢሱ10፥11፤ ኢዮ37፥11-12፤ መዝ103፥20፤ 147፥15-18
148፥9 ኢሳ44፥23፤ 49፥13፤55፥12
148፥10 ኢሳ43፥20 ፤ሆሴ2፥18
148፥11 መዝ102፥15
148፥13 መዝ8፥1፤ 113፥2፤138፥4፤145፥5
148፥14 ዘፀ15፥2፤ ዘዳ26፥19፤1ሳሙ2፥1 ፤መዝ22፥3፤145፥10
149፥1 መዝ1፥5፤ 28፥7፤33፥2፤96፥1፤ 103፥1፤ራእ5፥9
149፥2 ኢዮ10፥3፤ መዝ10፥16፤47፥6፤ 95፥6፤ኢሳ13፥3፤32፥1፤ 44፥2፤45፥11፤54፥5፤ ኤር51፥48፤ዘካ9፥9

149፥3 ዘፀ15፥20፤57፥8 149፥4 መዝ35፥27 ፤132፥16፤ 147፥11 149፥5 ኢዮ35፥10፤ 42፥8፤132፥16
149፥6 ነህ4፥17፤መዝ66፥17፤ዕብ4፥12፤ራእ1፥16
149፥7 ዘኍ31፥3፤ ዘዳ32፥41፤መዝ81፥15

[ኸ]1 አንዳንዶች ከቍ14 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።
[ሠ]14 ቀንድ የጥንካሬ ትእምርት ሲሆን *ንጉሥን* ያመለክታል።
[ዐ]1 አንዳንዶች ከቍ9 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ።

8 ነገሥታታቸውን በሰንሰለት፣
መኳንንታቸውንም በእግር ብረት
ያስራሉ፤
9 ይህም በእነርሱ ላይ የተጻፈውን ፍርድ
ለመፈጸም ነው፡፡
ለቅዱሳኑም ሁሉ ይህች ክብር ናት፡፡
ሃሌ ሉያ፡፡

## **መዝሙር** 150

**የምስጋና መዝሙር**

1 ሃሌ ሉያ፡፡ʺ

*እግዚአብሔርን* በመቅደሱ አመስግኑት፤
በታላቅ ጠፈሩ አወድሱት፡፡
2 ስለ ብርቱ ሥራው አመስግኑት፤
እጅግ ታላቅ ነውና ወድሱት፡፡
3 በመለከት ድምፅ አመስግኑት፤
በበገናና በመሰንቆ ወድሱት፡፡
4 በከበሮና በሽብሸባ አመስግኑት፤
በባለ አውታር መሣሪያና በእምቢልታ
አወድሱት፡፡
5 ተርገብጋቢ ድምፅ ባለው ጸናጽል
አመስግኑት፤
ድምፀ መልካም በሆነ ጸናጽል
ወድሱት፡፡
6 እስትንፋስ ያለው ሁሉ *እግዚእብሐርን*
ያመስግን፡፡
ሃሌ ሉያ፡፡

149፥8 2ሳሙ3፥34፤2ዜና33፥11፤ ኢሳ 14፥1-2
149፥9 ዘዳ7፥1፤ መዝ145፥10፤ ሕዝ 28፥26
150፥1 መዝ68፥24-26፤73፥17፤102፥19፤112፥1፤148፥1
150፥2 ዘፀ15፥7፤ ዘዳ3፥24
150፥3 ዘኍ10፥2፤ መዝ57፥8
150፥4 ዘፍ4፥21፤ ዘፀ15፥20፤መዝ45፥8
150፥5 2ሳሙ6፥5
150፥6 መዝ103፥22

ʺ1 አንዳንዶች ከቍ6 ጭምር *እግዚአብሔር ይመስገን* ይላሉ፡፡